# ማውጫ




“የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት”
*ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ለሚከበረው ለ120ኛ ልደታቸው መታሰቢያ*
ገፅ 6

አማርኛ ካሳ እንዲከፍል አይገደድም
ገፅ 14

ይድረስ ለሕወሓት ድርጅት
ገፅ 17

የእነእስክንድር ነጋ ንብረት ሊወረስ ነው
ገፅ 35

ቃሊቲን በጨረፍታ
ገፅ 36

ከመለስ በኋላስ? ፪
ገፅ 3

የሃይማኖት ነፃነትና መቻቻል
ገፅ 4

የአገሩን ተቃውሞ በአገሩ ቅኔ
ገፅ 5

ስለመለስ ውርሶች ጥቂት ነጥቦች
ገፅ 8

“ታዲያስ፣ ሰላም ነው!?”
ገፅ 9

ፐ/ር መስፍን ቄሣራውያንና የቀንዱ አገዛዝ ...
ገፅ 10

አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንዳንድ ከያኒ ስመስለው...
ገፅ 16

ሀይማኖትና ፖለቲካ
ገፅ 18


*ቀጣዩ ዕትማችን ቁጥር 6*
*ጥቅምት 10/2005 ዓ.ም*
*ቅዳሜ ይጠብቁን*

## ርዕሰ አንቀፅ

# ተመልሰናል

ከሁለት ወራት በፊት የፌደራሉ ዐቃቤ ሕግ ‹‹ለሀገር ደህንነት የሚያሰጋ ዘገባ›› በሚል ምክንያት የ2004 ዓ.ም. ሐምሌ አስራ ሶስቱን የፍትህ ጋዜጣ እትም አገደ፡፡ በቀጣዮቹ ሳምንታት ደግሞ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ቀጥተኛ ባልሆነ ትዕዛዝ በተላለፈለት ውሳኔ ፍትህ ጋዜጣን ማተም እንደማይችል ነገረን፡፡ እናም ፍትህ ጋዜጣ በስርዓቱ መሪዎች ፖለቲካዊ ውሳኔ ወደ ገበያ እንዳትመለስ ከታገደች ሁለት ወራቶች አለፉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ላለፉት ሁለት ወራት እንድንቆይ ብንገደድም ምርጫችን ሁለት ነበር፡፡ በአቶ መለስ ከመሪነት መራቅ ወዲህ ወደ መንበሩ የመጡት ገዢዎች እንደተመኙት ከአደባባዩ ርቀን መቆየት አልያም ሌላ አማራጭን ተጠቅሞ ወደ አንቢባዎቻችን መድረስ፡፡ እነሆ እኛም በተደጋጋሚ እንዳልነው ‹‹ዝም ማለት አይቻለንምና›› በዚህ መልኩ ወደ አደባባዩ ተመልሰናል፡፡

ከመጽሔት ስያሜነት እና ከቅርፅ ውጪ አንባቢዎች በዚህች መጽሔት እና በተወዳጇ ፍትህ ጋዜጣ መሀከል አንዳችም ልዩነት እንደሌለ እንደሚገነዘቡ እናምናለን፡፡ በፍትህ ጋዜጣ የምትከታተሏቸው ፀሐፊዎችም ሆኑ የየፀሐፊዎቹ ሙግቶች ከዚህ ዕትም በኋላ በአዲስ ታይምስ መጽሔት በኩል ታገኛችኋላችሁ፡፡ እናም በዚህች መጽሔት ላይ እንደሁልጊዜውም ለሀገራችን እና ለህዝባችን ይጠቀማሉ ብለን በምናምናቸው ጉዳዮች ላይ ካለአንዳች ፍርሃትና ማንገራገር መፃፋችንን እንቀጥላለን፡፡ ካለአንዳች ፍርሃትና ማንገራገር መረጃዎችን እናስተላልፋለን፡፡

‹‹ፍትህ ጋዜጣ›› መስዕዋት የሆነችውም ያለፍራቻ በዘገበችው ዜና መሆኑም ይታወቃል፡፡ ምንአልባትም ዜናን አማርጦ የመስራት ወይም የሚደፈርና የማይደፈር ጉዳይን ለይትን መስራት ብንመርጥ ኖሮ ‹‹ፍትህ››ን የሚያህል ዋጋ አንከፍልም ነበር፡፡ ፍትህንም በዚህ መልኩ አናጣትም ነበር፡፡ ሆኖም ደጋግመን እንፅፍ እንደነበረው ምንግዜም የምንቆመው ከእውነት እና ከህዝብ ጋር ነውና በዛን አስቸጋሪ ወቅት፣ ሚዲያው በተፈተነበት ወቅት ያለአንዳች መወላወል ቃላችንንአክብረን አቋማችንን አሳይተናል፡፡ እናም ምንም እንካ የተነጠቅነው ህልማችንን ቢሆንም፣ ምንም እንኳ የከፈልነው ዋጋ የመረረ ቢሆንም ለቃላችን እና ለእውነት መገዛታችን ዛሬ አንገታችንን እንዳንሰብር አድርጎናል፡፡

በወቅቱ ለፍትህ መታገድ ምክንያት የነበረው ዜና ከአንድ ወር በኋላ በራሱ ፍትህን በአፈነው ኃይል ይፋ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በእነዛ ወሳኝ ቀናት፣ በእነዛ የፈተና ቀናት፣ በእነዛ የቁርጥ ቀን ህዝብን የሚያሳስት መረጃ ሲያስተላልፉ የነበሩ ጋዜጦች ዛሬ አንገታቸውን ሰብረው ይቅርታ እየጠየቁ ነው፤ ይቅራታ ያልጠየቁት ደግም ይቅርታ ይጠይቁ ዘንድ ግዴታቸው ነውና እንጠብቃለን፡፡ ይቅርታ የጠየቁትንም ከዚህ በኋላ ይህን ስህተት አይደግሙ በሚል ቀናነት የይቅርታ ቃላቸው ዋጋ ያገኝ ዘንድ ምኞታችን ነው፡፡ የፍትህን የእውነት መንገድ ይከተሉ ዘንድ፣ የፍትህን አርዕያ ይከተሉም ዘንድ እንምኛለን፡፡

ሌላው የአዲስ ታየምስ ርዕስ አንቀፅ ትኩረት በአቶ ኃይለማርያም መሪነት ሀገሪቱን ለመምራት ለተዘጋጀው ገዢ ቡድንም ሁለት መልእክቶች ማስተላለፉ ላይ ነው፡፡ የመጀመሪያው እና ቀዳሚው ካለአንዳች ፍትሃዊም (ዐቃቤ ሕግ ጋዜጣችን እንድትታገድ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል) እና ርትዕዊ እርምጃ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በኩል ጋዜጣችንን እንዳናሳትም የተቀመጠብን ኢ-ህግ መንግስታዊ ዕግድ እንዲነሳ እንጠይቃለን፡፡ በስልሳ ሺህ ወጣቶች ደም ቆሟል የሚባለው ሕገ-መንግሥት ለዜጎች ከሰጠው መብቶች መሀከል አንደኛው የመናገርና የመፃፍ ነፃነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ከሟቹ መለስ በባሰ መልኩ አዲሶቹ መሪዎች ሕገ-መንግሥቱን እየናዱ መቀጠል የለባቸውም፡፡ አዲሱ አመራር የመለስን ‹‹ራዕይ›› መከተል ብቸኛው ምርጫው አድርጎ ሲወስድ፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር በምሬት ከሚተቹባቸው ርዕሰ ጉዳዮች መሀከል አንደኛው የፐሬስ ነፃነትን አለማክበር በመሆኑ፣ ተከታዮቻቸው ይህን የመሪያቸው ክፉ ውርስ እንዳይቀጥል መስራት እንዳለባቸው አጥብቀን እናስገነዝባለን፡፡

ሁለተኛው መልዕክታችን ኢህአዴግ ቅጥ ባጣ አምባገነናዊ መንገድ ሀገሪቱን ለሁለት አስርታት ገዝቷል፡፡ በአገዛዙ ውስጥ የተደረጉ ሀገራዊ ምርጫዎች ካለፍትሃዊነት የስርዓቱን አሸናፊነት ብቻ እንዲያስረግጡ ተደርገዋል፡፡ የገዢውን ቡድን ፖለቲካዊ የበላይነት ለመገዳደር የሞከሩ ድምፆች በግድያ፣ በእስርና በስደት ከአደባባዩ ተገልለዋል፡፡ በዚህ መንገድ ለመግዛት መሞከር ምን ዓይነት ሀገራዊ ክስረት ውስጥ እንደጣለን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ስለሆነም አዲሱ አመራር ኢህአዴግ እስከዛሬ ከመጣበት መንገድ በተሻለ ፖለቲካዊ ምህዳሩን እንዲያሰፋ፣ አፋኝ ህግጋቶቹን እንዲያነሳ እና በህገ-መንግሥቱ የተፈቀዱ የዜጐችን ሁለንተናዊ መብቶች ካለምንም መሸራረፍ አክብሮ እንዲያስከብር እንጠይቃለን፡፡ ከዚሁ ጋር በተዛመደ፤ እየተንቀለጳጰሱ የሚቀርቡልን የ‹‹ባለ ራዕዩ›› የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውርሶች እንደገና እንዲፈተሹ እንጠይቃለን፡፡ ተገኝቷል የሚባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ዜጐችን ካለውዴታቸው በማፈናቀል የሀገር መጪ ጊዜያትን በሚያጨልም መንገድ ለሌሎች መንግሥታትና ተቋማት ለም መሬቶችን በመስጠት፤ የብዙሃኑን ዜጋ የኑሮ ውድነት መግራት ያልቻለ ዕድገት አልፎም በግዳጅ እና ርትዐዊ ባልሆነ አካሄድ በሚሰበሰብ ግብር ላይ የተመሰረተ ነውና፤ ይህ የፖሊሲ አካሄድ እንደገና በቅጡ እንዲፈተሽ ማስታወስ ዜግነታዊ ግዴታችን ነው ብለን እናምናለን፡፡ ይህ ስርዓት በቀድሞው መሪው ባህል እቀጥላለሁ የሚል ከሆነ ራሱንም ሆነ ሀገሪቱን ወደ አዘቅጥ ሊከታት እንደሚችል ማስታወስ ያሻል፡፡


## አዲስ ታይምስ

*ሃገራዊ፣ ማኅበራ፣ ኢኮኖሚ ያዊና*
*ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሔት*

**አሳታሚ:-**
አዱ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር:-**
ተመስገን ደሳለኝ

**ስራአስኪያጅ**
ኃይለመስቀል በሸዋየለም

**ዋና አዘጋጅ:-**
ዳዊት ታደሰ
አድራሻ አቃ/ቃ/ክ/ከተማ
ወረዳ 8
የቤት ቁጥር 003
E-mail nigusdawit@yahoo.com

**ግራፊክ ዲዛይን**
በአዲስ ታይምስ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ:-**
አቃ/ቃ/ክ/ከተማ
ወረዳ 8
የቤት ቁጥር አዲስ
ስልክ ቁጥር
+251 922 87 19 37
+251 911 55 49 01
E-mail addistimes@yahoo.com

**አታሚ**
ሐርቴጅ ሕትመትና ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር
አድራሻ:- ቂርቆስ ክ/ከተማ
ቀበሌ 10፣ ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 006

፩ በሉ



ተመስገን ደሳለኝ

# ከመለስ በኋላስ? ፪

መስከረም ጠባ። መስቀል ተተኮሰ። ...ድንገትም ፓርላማው ከእረፍት ወደስብሰባ ለመመለስ ተገደደ። ህይወታቸው ባለፈው የቀድሞ ጠቅላይ ሚንስትር ምትክም ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ‹‹ጠቅላይ ሚንስትር›› ሆነው ቃለ-መሀላ ፈፀሙ። ይህንንም ተከትሎ ‹‹ተተኪውን›› በተመለከተ ውስጥ ውስጡን ‹‹ሲጎሽም›› የነበረው እና ‹‹ሊሆን ይችላል›› በሚል የተናፈሱ በርካታ መላ-ምቶች ከሸፉ። ጥቂት የማይባሉ መላ-ምቶች ደግሞ ግባቸውን መቱ። ...እነሆም መለስ ጥለውት የሄዱት ኢህአዴግ እና የአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር የፖለቲካ ቁመናን በተመለከተ በርካታ መላ ምቶች መመታታቸውን ቀጠሉ። እኔም በጉዳዩ ላይ ምልከታዬን ለማቅረብ ወደድኩ። ...ከዋናው አጀንዳችን በፊት ግን ጥቂት ስለ‹‹ህዝባዊ ትዝብት›› እንነጋገር።

## መግቢያ-1- ‹‹ህዝባዊ ትዝብት›› ስንል...

ኢትዮጵያ በምትባለው ሀገር ከጀግንነት እና በውርስ ከሚገኝ ሹመት ባሻገር ‹‹ፖለቲካ›› የሚባል ፍልስፍና መሬት ከወረደበት ዘመን ጀምሮ የህዝባችንን ፍላጎት (አቋም) በጥናትም ሆነ በትንተና እርግጠኛ መሆን እንደማይቻል በርከት ባሉ ጊዜያት፣ በርከት ባሉ ክስተቶች የተመለከትነው የአደባባይ እውነት ነው። የአቶ መለስ መሞትን ተከትሎ አንዳንድ ያልጠበቅናቸው ነገሮችን ለመታዘብ የቻልንበት አጋጣሚም ከእነዚህ ጋር የሚመደብ ነው። እንደማሳያም ‹‹መለስ አልሞተም››፣ ‹‹ጀግና አይሞትም›› ከሚሉት አንስቶ፡-

‹‹አለ ገና አለ ገና አለ ገና
‹‹የእከሌም አለ ገና››

(የሁለት ባለስልጣናትን ስም እየጠሩ) እያሉ እስከሚጨፍሩ ሰልፈኞች ድረስ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች የሰማናቸውን ድምፆችን ማስታወስ ይቻላል።

ለዚህም ሳይሆን አይቀርም የሀገሬን ስነ-ልቦናችንን መረዳት እንኳን ለእኔ ለጉምቱ የማህበራዊ ስነ-ልቦና ተመራማሪዎችም የዳገት ያህል አድካሚ የሆነው። መቼም ከሰልፍ ጋር እንደሀበሻ በፍቅር የወደቀ ህዝብ ያለ አይመስለኝም። በጃንሆይ ላይ የተቃጣው የ1953 ዓ.ም መፈንቅለ መንግሥት ሲከሽፍ ሰለፍ መውጣ። ራሳቸው ጃንሆይ በ1966ቱ አብዮት ከቤተ መንግሥቱ ሲባረሩ ‹‹ሌባ፣ ሌባ፣ ሌባ...›› ብሎ ለመስደብ መሰለፍ። ...ለአብዮት በዓል በአዲስ አመት የመጀመሪያው ቀን ማግስት መሰለፍ፤ መንግሥቱ ኃይለማርያም በ1969 ዓ.ም ህዳር 13 ቀን በኢህአፓ የተደረገባቸው የግድያ ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ቆራጡ መንጌ በኢቲቪ ቀርበው ሁለት እጃቸውን ወደላይ ቀስረው ‹‹የበረደች ጥይት ሞኚይቴን ከመምታቷ ውጭ ሙሉ ጤነኛ ነኝ›› እያሉ መንፏለላቸውን ተከትሎ በማግስቱ በዛው አደባባይ ለድጋፍ ሰልፍ ስንወጣም ወፍ እንኳ ‹‹ጭጭ...›› አላለም።

በእንዲህ አይነት ሁኔታ ከተደረጉ ከየትኞቹም ሰልፎች እጅግ ምፀታዊ በሆነ መንገድ የሚታወሰኝ በወራት ልዩነት የተደረገው የአስራ ዘጠኝ ስልሳ ዘጠኙ ሆሆታ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው፡- በ1969 ዓ.ም ሚያዚያ 23 የሰራተኞች ቀንን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር በ‹‹ኢማሌድህ›› ስም መኢሶን ባስተባበረው ሰልፍ (እነመንግስቱ ኃ/ማሪያምም ባሉበት) ድፍን የአዲስ አበባ ህዝብ ‹‹መኢሶን ፓርቲያችን››ን እየዘመረ አብዮት አደባባይን በሰልፍ አጥለቀለቀው። ይህ በሆነ በ3ኛው ወር ያ ሁሉ ውዳሴ የጎረፈለት መኢሶን ከደርግ ጋር በፈጠረው ፀብ የአመራር አባሉ ተደናግጦ ዋነኛ ምሽጉ የነበረውን የህዝብ ድርጅት ጽ/ቤትን ለቆ ከሀገር ለመውጣት ሲሞክር ሱሉልታ አካባቢ ተያዘ፤ ይህን ጊዜም በአብዮት አደባባይ ‹‹መኢሶን ፓርቲያችን›› እያለ ‹‹ለውዳሴ›› የተሰለፈው ህዝብ


‹‹ተይዞ መጣ፤
ጠላ ሲጠጣ።››

በማለት እያላገጠ ጨፈረበት። በ1981 ዓ.ም ግንቦት 8 ቀን በመንግሥቱ ኃይለማርያም ወታደራዊ ጁንታ አገዛዝ ላይ የተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት በመክሸፉም ቅዳሜ ግንቦት 12 ቀን 1981 ዓ.ም. በአብዮት አደባባይ የተጥለቀለቀ የድጋፍ ሰልፍ ያደረገው ህዝብ፣ ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም. መንግሥቱ ኃይለማርያም ሀገር ጥሎ መጥፋቱ በሬዲዮ ሲነገር ‹‹ሌባ፣ ሌባ...›› እያለ አደባባይ ከመውጣትም አልፎ ግዙፉን የሌኒን ሀውልትን አፍርሶ ነው የተመለሰው። ...ባለፉት ሃያ አንድ የአቶ መለስ እና የኢህአዴግ የጉልበተኝነት ዘመናትም እንዲሁ በርካታ ‹‹ጉራማይሌ ሰልፎች››ን ታዝበናል። በ1997 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም. የተደረጉትን ሁለት ሰልፎች ብናነፃፅር በኢህአዴግ ዘመን ከተደረጉት መሀከል እጅግ ጉራማይሌ የሆነውን ሰልፍ እናገኛለን። በ97 ቅንጅትን ደግፎ የወጣው ህዝብ ነው ከአምስት ዓመት በኋላ የኢህአዴግን ጠቅላይ አሸናፊነት ለማብሰርም የወጣው (ከትንሽ ማስተካከያ ጋር። ማለትም፡- በመሀከል ባሉት ዓመታት ለአቅመ-ፖለቲካ ወይም ምርጫ የደረሰውን የማህበረሰብ ክፍል ሳናካትት ማለቴ ነው) ብለን ብንከራከር ቢያንስ የስነ-ህዝብ ፖለቲካ (Political Demography) ያጠናን ዘዬ ይደግፈናል ብዬ አስባለሁ።

ከወርሃ ነሀሴ ጀምሮ ለ‹‹ጉሮአችን›› እና ለበርካታ ወሳኝ የፖለቲካ ጥያቄዎቻችን ግርዶሽ



ወደ ገፅ 20 ዞሯል



# የሃይማኖት ነፃነትና መቻቻል

## የሃይማኖት ነፃነት በሕገ መንግሥቱ የተከበረ ነው፤ አንቀጽ 27/1

ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም

‹‹ማንኛውም ሰው የማሰብ፤ የሕሊናና የሃይማኖት ነጻነት አለው፤ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ፣ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር፣ ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡››

ብዙ ሰዎች ይህ አንቀጽ እንደገባቸው አድርገው ይናገራሉ፤ አንቀጹ ከሃይማኖት ነጻነት በተጨማሪ ብዙ ሌሎች መብቶችንም የያዘ ነው፤ የሕሊና ነጻነትና የሃይማኖት ነጻነት አንድ አይደለም፤ የሃይማኖት ነጻነትና እምነት አንድ አይደለም፤ እነዚህ የተጠቀሱት ሀሳቦች አንድ አይደሉም ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ይጋጫሉ ወይም ይቃረናሉ፤ ኅሊናና እምነት፣ ወይም ኅሊናና ሃይማኖት፣ ወይም እምነትና ሃይማኖት አንዳንድ ጊዜ አይስማሙም፡፡

እነዚህን በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተጠቀሱትን፤ ቃላት በትክክል ከተረዳን ሕጋዊ ሥርዓት ባለበት ሁሉ ችግሮች አይኖሩም ወይም በጣም ይቀነሳሉ፤ ለምሳሌ ሴቶች በሃይማኖት የተደገፈ ጥቃት ወይም በደል ይደርስባቸዋል፤ በዚህ ምክንያት ኅሊና ከሃይማኖት ጋር ያቃረናል፤ ሃይማኖትም ኅሊናም ያለው ሰው ይጨነቃል፤ የሃይማኖትን ትእዛዝ ማክበር ወይም የኅሊናን ድምጽ መቀበል ለብዙ ሰዎች አስቸጋሪ ምርጫ ነው፤ በዚህ ላይ የማኅበረሰቡም ድምጽ አለ፤ መሠልጠን ማለት፣ መብሰል ማለት፣ ማደግ ማለት እነዚህን ውስጣዊና አፍአዊ ግጭቶች ከራስ ጋር ሳይጣሉ በሰላም ማስተናገድ ነው፤ አማራጩ ምንድን ነው? አማራጩ ልጅ ሆኖ መኖር ነው፤ አማራጩ የፈለጉት ካልሆነ ሲያለቅሱ መኖር ነው፤ አማራጩ የፈለጉት ካልሆነ እየተበሳጩና እየተጣሉ ሲደባደቡ መኖር ነው፡፡

ለብዙ ሰዎች መቻቻል ማለት አትንካኝ-አልነካህም ብቻ ይመስላቸዋል፤ አይደለም፤ ከአትንካኝ-አልነካህም በጣም ያልፋል፤ ለምሳሌ የሀሳብ ነጻነት ማለት የሚቃወሙትን እምነትም ሆነ ሃይማኖት፣ ሀሳብም ሆነ ድርጊት መተቸትና መንቀፍን ይጨምራል፤ በቅርቡ አንድ ቀደም ብሎ የተጻፈ መጽሐፍ አየሁ፤ ጥቂት ገጾች ካነበብሁ በኋላ በቃኝ፤ አንድ ካቶሊክ ስለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጽፎ ኖሮአል፤ አንድ ኦርቶዶክስ ይህንን የካቶሊኩን ጽሑፍ አልወደደውም፤ አለመውደድ መብቱ ነው፤ ነገር ግን ኦርቶዶክሱ ሲመልስ አትኩሮቱ በፍሬ ነገሩ ላይ ሳይሆን በካቶሊኩ ሰውዬ ላይ ነው፤ ይህን ሲያደርግ መብቱን አለፈ፤ የሰው መብት ነካ፤ በአጭሩ ኦርቶዶክሱ ካቶሊኩ ሰውዬ ላይ ማተኮሩ ለእኔ ምንም ምክንያት አይታየኝም፡፡

አንድ ሰው ከፈለገ <u>የሃይማኖቱን ተከታዮች</u> ሳይነካ የትኛውንም ሃይማኖት ሊተችና ሊነቅፍ ይችላል፤ መብቱ ነው፤ የመቻቻል ሙሉ ትርጉሙ ካልገባቸው የተነቀፈው ሃይማኖት ተከታዮች ሊቀየሙ ወይም ሊከፉ ይችላሉ፤ ግን ሰውዬው የራሱን ሀሳብ ወይም እምነት በመግለጽ የማንንም መብት አልጣሰም፤ በሌላ አነጋገር መቻቻል መታፈንን አይጨምርም፤ ሀሳብን ወይም እምነትን የመግለጽ መብትም ጨዋነትን አይደመስስም፤ መቻቻል ማለት የአንድን ሰው የመናገር መብት መገደብ ማለት አይደለም፤ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 27/1 ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡

አንዳንድ ሃይማኖት-ነክ ነገሮች ማኅበረሰብ-ነክም ሊሆኑ ይችላሉ፤ ስለዚህም በሃይማኖትና በማኅበረሰቡ ድንበር ላይ የሚገኙትን ነገሮች ካልሆነ በቀር በእምነትም ሆነ በጣዕም ላይ ክርክር መክፈት የዋህነት ነው፤ ማንም ሊያሸንፍ የሚችልበት ሚዛን የለም፤ ለምሳሌ በመጀመሪያ የተጠቀሰው በሴቶች ላይ የሚፈጸም አድልዎ፣ ወይም በልጆች አስተዳደግ ላይ የሚታይ ጉድለት፣ ወይም ማኅበረሰቡን ለአደጋ የሚያጋልጥ ጉዳይ ሆኖ ሲታይ በሃይማኖት ወይም በእምነት ላይ ትችት ማቅረብ አስፈላጊ የሚመስልበት ጊዜ ይኖራል፤ ማኅበረሰቡ ከነሃይማኖቶቹና ከነእምነቶቹ የተሳሰረበት የመንፈሳዊና የሕግ ቃል ኪዳን ተጠብቆ እንዲቆይ የሚነቀፈውን ሁሉ እያወጣ ማበጠር ያስፈልገዋል፤ ማናቸውም የተሸፈነና የተሸሸገ ነገር ጊዜውን ጠብቆ ባሕርዩን ይለውጣል፤ በዚያን ጊዜ የእርምት እርምጃን ለመውሰድ አይቻልም፤ ቢቻልም በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፤ ላይ ላዩን መቻቻል ውስጥ ውስጡን መቆሳሰል ውሎ አድሮ ለማኅበረሰቡ በአጠቃላይ ጉዳትን እንጂ ጥቅምን አያመጣም፡፡

በተጠቀሰው የሕገ መንግሥት አንቀጽ ውስጥ ቁልፉ ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት መብት ነው፤ አንድ ግለሰብ፣ ወይም አንድ ቡድን፣ ወይም አንድ አገዛዝ ለእኔ የማይበጅ ወይም የማልወደውን ሀሳብ መግለጽ አትችልም ወደማለት ደረጃ ላይ ከደረሰ የእኔን ሀሳብና እምነት አትንቀፍ ለማለት ምን ያግደዋል? የእኔን ሃይማኖት አትንቀፍ የሚል ትክክለኛው ሃይማኖት የእኔ ብቻ ነው ለማለት ምን ያቅተዋል? አንዱ መሠረታዊ ችግራችን የነጻነት ግንዛቤያችን እኛ በምንፈልገውና በምንወደው ላይ ብቻ የቆመ ነው፤ ማንንም ሰው ሳልነካ እኔ የምወደውን ለማድረግ ነጻነት አለኝ ብሎ የሚያምን ሰው ሌላውም ሰው እንዲሁ ማንንም ሰው ሳይነካ የወደደውን ለማድረግ ነጻነት እንዳለው ማመን አለበት፤ አለዚያ የራሱም ነጻነት አደጋ ላይ ነው፤ ከአሥር ዓመታት በፊት ከገንዘብ በላይ ምንም ነገር አለ ብለው በማያምኑ ሰዎች አንዳንድ የብልግና ጋዜጦችና መጽሔቶች መውጣት ጀምረው ነበረ፤ እነዚህን መጽሔቶችና ጋዜጦች ለማገድ ሙከራ ሲደረግ በኢሰመጉ ውስጥ ጉዳዩ ሲታይ አንዳንድ ሰዎች መታገድ አለባቸው የሚል እምነት ነበራቸውና ኃይለኛ ክርክር ነበር፤ እነዚህን የብልግና ማሰራጫ ጽሑፎች መከላከልና ማጥፋት የሚቻለው ነጻነትን በመገደብ ሳይሆን ጽሑፎቹን ባለመግዛት ባለው ነጻነት በመጠቀም ነው፤ አለዚያ የአንዱን ነጻነት በሌላው ነጻነት እየመነዘረና እያጋጨ የሁሉንም ነፃነት የሚገፍ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ሀሳብን የሚፈራ ማኅበረሰብ እንደረጋ ውሀ ባለበት ይቀራል፤ የሚያድሰውን መንገድ ሁሉ ስለዘጋ አይታደስም፤ ከራሱ የሚተርፈውም አይኖረውምና ለማንም አይበጅም፡፡

አብሮ መኖር አብሮ ማደግንም መጨመር አለበት፤ ይህንን ከአመንን መቻቻልን ከእምነትና ከሃይማኖት፣ ከሙሉ ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት ጋር መቀበል አለብን፤ ሀሳብን የመግለጽ ነጻነትን ችላ ብሎ የሃይማኖትን መብት ለማስከበር በጣም ያስቸግራል፡፡

> **…አንድ ካቶሊክ ስለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጽፎ ኖሮአል፤ አንድ ኦርቶዶክስ ይህንን የካቶሊኩን ጽሑፍ አልወደደውም፤ አለመውደድ መብቱ ነው፤ ነገር ግን ኦርቶዶክሱ ሲመልስ አትኩሮቱ በፍሬ ነገሩ ላይ ሳይሆን በካቶሊኩ ሰውዬ ላይ ነው፤ ይህን ሲያደርግ መብቱን አለፈ፤ የሰው መብት ነካ፤ በአጭሩ ኦርቶዶክሱ ካቶሊኩ ሰውዬ ላይ ማተኮሩ ለእኔ ምንም ምክንያት አይታየኝም…**



# የአገሩን ተቃውሞ በአገሩ ቅኔ

ዓለማየሁ ገላጋይ

የዚህ ዘመን ተቃውሞ መላ-ሰውነቱን ያሳረፈው ሥነ ቀልድ ላይ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የነበሩት ዘመናት ተቃውሟቸውን ያስተናግዱ የነበረው በአመዛኙ በቅኔ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ቅኔ፤ ምርጊቱ እንደተከፈተ የጋን ጠላ በጊዜ ሂደት ኃይሉን እያጣ የመምጣቱ ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ የቀድሞቹ ምሁራን መሰረታቸው የቤተክህነት ትምህርት ስለነበር ፖለቲካዊ ቅሬታቸውን የቅኔ ግብአት ለማድረግ አይቸገሩም ነበር፡፡ ቀደም ያሉትን ነጋድራስ ተሰማ እሸቴንና ዮፍታሔ ንጉሴን አልፈን የለውጡ ዘመን ወጣቶች ላይ እንረፍ፤

ከ1966 አብዮት አስቀድሞ ተማሪዎች ከአፄ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ጋር ቁርሾ መፍጠር ሲጀምሩ ዳርዳርታቸውን ያሳዩት በግጥም ነበር፡፡ የኮሌጅ ቀንን ምክንያት በማድረግ የሚቀርቡት የተማሪ ግጥሞች የህዝቡን ጭቆናና በደል የሚያንፀባርቁ ሲሆን አልፎ-አልፎ ደግሞ የቅኔን ልዩ ባህርይ በመንተራስ ሁለት መልክ ያለው መልእክት ይዘው ብቅ ይሉ ነበር፡፡ ‹‹አላልንም››፣ ‹‹ብለናል›› በሚል አካፋይ ሰርጥ ውስጥ የተደበቁት ቅኔዎች ዛሬ ወቅታቸው አልፎ ሲነበቡ አንዳንዶቹ ከተልዕኳቸው፣ ከቀስቃሽነት ይልቅ አዝናኝነታቸው ይጐላል፡፡ ለምሳሌ ይሄን እንመልከት፡፡

የኃይልዬን ሱሪ ሠፊ አሳጥሮበት፣
ከማይጨው ሲመለስ ጉልበቱ ታየበት፡፡

ቅኔው የፀገየወይን ገብረመድህን ነው፡፡ በጥር 1958 ዓ.ም. ‹‹ታጠቅ›› የተሰኘ መጽሔት ላይ ይውጣ እንጂ ቅኔው የተፃፈው ከዚያ በፊት ተማሪዎቹ ከንጉሱ ጋር መደፋፈር እንደጀመሩ ሰሞን ይመስላል፡፡ ‹‹ኃይልዬ›› የሚላቸው አፄ ኃይለሥላሴን እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ አፄው በማይጨው ጦርነት ሽንፈት የመቅመሳቸውን ታሪካዊ ዳራ ይዞ የተቀኘ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ከሱሪ ጋር ተያይዞ ይቀርቡ የነበሩ ብዙ የሽሙጥ ቅኔዎች በወቅቱ ነበሩ፡፡ ‹‹ተፈሪ›› የተሰኘ የሱሪ ሞድ ስለነበር ይሆናል ቅኔዎቹ ሁሉ ወደዚያው ሲያመሩ የሚስተዋሉት፡፡ ዋለልኝ መኮንን የተቀኘውን ደግሞ እንይ፡-

ከለበሱ አይቀር ሱሪ
የጥንቱን ነበር የተፈሪ
ግን አይመችም ለሥራ
አጥብቆ ይዞ ከቀኝ ከግራ፡፡

እንግዲህ ቅኔዎቹ በአመዛኙ ተመዝግበው የሚገኙት በተማሪዎቹ ነው፡፡ ወደ አስተዳደሩ የሚወነጨፉት ቅኔዎች ከወደ ቤተ-መንግሥቱ አካባቢ ምን አይነት አፀፋ እንደሚሰጥ ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡ አንዳንድ ብቅ ብለው የሚስተዋሉ ቅኔዎች ግን አልጠፋም፡፡ ለምሳሌ በነጭ መምህራን ትምህርት የሚያገኙት እነዚህ ወጣቶች ለአመፅ መነሳታቸውን በማየት እንዲህ ተብሎ ቅኔ ተዘርፎ ነበር፡-

የነጯ ላም ጥጃ
ማደጓንም እንጃ

የተማሪዎቹ ቅኔዎች ግን እንደውርጅብኝ የሚቆጠሩ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ ንጉሱን አስመልክቶ ልምዶችንና ወጐችን ጭምር የሚተቹ ቅኔዎች በብዛት ፈልቀዋል፡፡ አሁንም ፀገየወይን ገብረመድህን ይቺን ቅኔ ጀባ ይለናል፡-

ዕድሜያችን ሰባ ነው
ቢበዛ ሰማኒያ
ብሎ ነግሮን ነበር
ዳዊት በበገና
ዳሩ ምን ይሆናል ትንቢቱ ቀረና
ዘላለም ይኑሩ ብሎ ያንጋጥጣል
የሰነፍ ልቦና፡፡

ተማሪዎች በአፄ ኃይለሥላሴ ላይ የተቃጣውን የታህሣሥ መፈንቅለ-መንግሥት በግልፅ ደግፈው ሠላማዊ ሰልፍ ወጥተው ነበር፡፡ ነገሩ እንደተታሰበው ሳይሆን ቀርቶ መፈንቅለ መንግሥቱ ሲከሽፍ ተማሪዎቹ አፄውን ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎቹ ይቅርታ ውስጡ ማድፈጥ ኖሮበት በተገኘው አጋጣሚ የመፈንቅለ-መንግሥቱን መክሸፍ በቁጭት ያሱታል፡፡ ለምሳሌ ያህል ይሄን ቅኔ መመልከት ይቻላል፡፡

ቁማር ጨዋታ ተጫውቼ
ገንዘቤን ተበልቼ
ቀረሁ እጄን አጨብጭቤ
ምንኛ ዕድሌ በሰመረ
ዘውዴን ገልብጬ በነበረ፡፡

በዚሁ ጭብጥ ላይ ሌላም ተማሪ አንድ ቅኔ ጣል አድርጓል፡፡ የተማሪው ሥም በምህፃረ ቃል ‹‹ኃ.ገ›› ይሰኛል፡፡

የቁልቢውን ገብርኤል
አያሌ ሰዎች ወደውታል
ይሄን አይተው ካህናቱ
እንዲደረጅ በስዕሉ
እንደታህሳሱ ይሁን ሳይሉ
ሌላም ለማገነስ ያስባሉ፡፡

እዚች ቅኔ ላይ ‹‹እንደታህሣሱ›› የምትለው ቃል መንታ ሃሳብ አርግዛ ነው ግጥሙን ወደ ቅኔነት ያሻገረችው፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ኃብተወልድ ጥገናዊ ለውጥ ላይ ተማሪዎቹ ቅሬታ እንደተሰማቸው ለመግለጽ የተቀኘ ሳይሆን አይቀርም ብለን እንጠረጥራለን፡፡ ተማሪዎቹ በዚህ ቅኔ ሥርነቀል ለውጥ የመጠየቅ ደረጃ መድረሳቸውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የተማሪዎቹ ንቅናቄ ያላረገዘውን ወልዶ የመታቀፍ ዕዳ ከመጣበት በኋላ በቀጣዩ ሥርዓት የአፄውን ያህል እንኳን በአደባባይ የቅሬታ ቅኔ ማሰማት ሳይቻል ቀረ፡፡ ዳፋው እስከመላው ሕዝብ ወርዶ መደገፍ እንጂ መንቀፍ ከፍተኛው የአገሪቱ ወንጀል ሆነ፡፡ ሌላው ቀርቶ በስማ በለው ፍቺ አንዳንድ ፀሐፊዎችና ድምፃውያን ዘብጥያ ወረዱ፡፡ ጥላሁን ገሠሠ፣ ፀጋዬ ደቦጭ፣ ተስፋዬ ለማና የመሳሰሉትን ማንሳት ይቻላል፡፡ ይሁንና ‹‹ስርዓት-ጐናጭ›› የሆኑ አንዳንድ ቅኔዎች በሽፍንፍን ብቅ-ብቅ ማለታቸው አልቀረም፡፡ ለምሳሌ ያህል የብሔራዊ ቴአትሩ ጌታቸው ደባልቄ ፅፈውት አስናቀች ወርቁ ያቀነቀነችውን ቅኔ እንመልከት፡፡

እግዚአብሔር ይመስገን
አልጋው ሥራ አልፈታም
አልተገኘም እንጂ
እንዳንት ያለ መልካም፡፡

የዚህ ቅኔ የሰምና ወርቅ ማደሪያ ቃል ‹‹አልጋው›› የሚለው ነው፡፡ ሰሙ ከፆታ ፍቅር ጋር ተያይዞ የሚፈታበት አግባብ ላይ ያርፋል፡፡ ወርቁ ደግሞ ከንጉሠ-ነገሥቱ ‹‹አልጋ›› አንፃር ሲታይ ፍንትው ብሎ ይገለፅልናል፡፡ አፄ ኃይለሥላሴንና ሊቀመንበር መንግሥቱን አነፃፅሮ በመልካምነትና በመጥፎነት ይፈርጃቸዋል፡፡

ሌላው ሥርዓት የሚጐንጥ ቅኔ የይልማ ገብረአብ ነው፡፡ ለድምፃዊ ኤፍሬም ታምሩ ሰጥቶት ተጫውቶታል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

በይ ስፊልኝ ገሳ
የእኔ እንቦሳ፤

የዚህ ቅኔ ወርቅ ምንጭ የመጀመሪያው ሐረግ አላልቶ ከማንበብ ይመነጫል፡፡ ‹‹በይ ስፊልኝ ገሳ›› የሚለው ሲላላና ‹‹ፊ›› በ ‹‹ቪ›› ስትቀየር ‹‹በይ ሲቪል ይንገሥ›› የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይሄ ለወታደራዊው መንግሥት የሚያስቆጣ አዝማሚያ ነው፡፡ ከማስቆጣትም አልፎ የመጨረሻውን እርምጃ እንዲወስድ የሚገፋፋ ነው፡፡ እንዳልነው ነው! ቅኔ ምርጊቱ እንደተከፈተ ጠላ በጊዜ ሂደት ኃይሉን ሲያጣ ባለቅኔን ብቻ ሳይሆን ቅኔን በአግባቡ የመፍታት አቅምን ይነሳል፡፡ ስለዚህ ደርግ እነዚህን ጐናጭ ቅኔዎች ሳይረዳቸው በገዛ ሬዲዮኑ በየዕለቱ ሲያዘፍናቸው ቆይቷል፡፡

ወደዚህ ዘመን እንምጣ…

…ይሄን ዘመን በንባብም፣ በእግርም የቻልኩትን ያህል አሰስኩ፡፡ ዘመኑ የወለዳቸውን ቅኔዎች ማግኘት አልቻልኩም፡፡ የቤተክህነት ትምህርት ወዳላቸው አንድ አዛውንት ሄጄ ነበር፡፡ ቅኔ በተላበሰ አኳኋን አተኰሩብኝ፡፡ አይንም ይቀኛል እንዴ? ግራ ተጋባሁ፡፡

‹‹እንኛ ልጅ›› አሉኝ፡፡ አፋቸው እንጂ አይናቸው ተስፋ አስቆራጭ አልነበረም፡፡ እንዳሰብኩትም ‹‹ብቻ›› አሉ ‹‹ብቻ የጐንደር ቀሳውስት ለባለስልጣኖቹ የመወድስ ቅኔ አቅርበው ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ››

እኔም ሰምቻለሁ፤ ጥር 11 2003ዓ.ም ጎንደር ከተማ ጥምቀት ሲከበር ፒያሳ አደባባይ ላይ ለአዲሱ ለገሠ፣ ለበረከት ስምዖንና ለአያሌው ጎበዜ ቅኔው ፈሰሶላቸው ነበር፡፡

‹‹ተገቢ ነው፣ ይላሉ?›› ስል ጠየኳቸው፡፡

‹‹እሱስ ነባር ወግ ነው፡፡ እበላ ባይ ቄስ በየባላባቱ ደጃፍ ለውዳሴ ከንቱ ይቀኛል፡፡ ቅኔውም ያለው እዚህ ላይ ነው፡፡ ያሁኖቹን ባለስልጣናት እንደተላላ ባላባት ቆጥረዋቸዋል ማለት ነው፡፡›› በዚያው በቅኔ አኳኋናቸው ጥርሳቸውን ሳያሳዩ ሳቁ፡፡

የአዛውንቱ ንግግር ወደነዚያ ተማሪዎች መልሶ ወሰደኝ፡፡ ቅኔያቸውን በእዝነ ልቦናዬ ደገምኩት፡፡


ቤተክርስቲያን እናት
ታላቅ መልእክት አላት
ምን ይሆናል የጐደላት
አንዳንድ ቅን-ቅን ካህናት፡፡

ቅኔው የደምረው ሱራፌል ነው፡፡ በወቅቱ ሚሥ መንግሥት የነበራት ቤተክርስቲያን ለአገዛዙ ያላትን ጥብቅና በመመልከት አንጀታቸው ከሚያረው ተማሪዎች ብዙ ቅኔ ወደካህናቱ ይወነጨፍ ነበር፡፡ አንዱን እንድገምና መለስ እንበል፡፡ ቅኔው የአክሊሉ ወልደአማኑኤል ነው፡፡

አባቶቻችን ካህናት
ሲጠመጥሙ ከጥንት
ለሥልጣናቸው ለክህነት
መለያ ነበር ምልክት
አሁንማ ጠምጣሞቹ
ሹሞቹና ጠበቆቹ፡፡

ለዚህ ዘመን የቅኔ ድርቅ ወደ አጕራባች ዘመን ቃርሚያ መማተር ይመስላል፡፡ ደግሞም ነው፡፡ ይሄንን ዘዴ ተጠቅሞ አንድ ጥሩ አልበም ያቀረበ ድምፃዊ አውቃለሁ፡፡ አንጋፋው አርቲስት ተሾመ ምትኩ፡፡ ተሾመ የጥንቶቹን ቅኔዎች ለዚህ ዘመንና ብጤት እንዲስማማ አድርጐ ቀድዶ በመስፋት ‹‹ሺራ›› በሚል ርዕስ አቅርቦልን ነበር፡፡ አጠቃላይ ሥራውን ወደፊት እመለስበታለሁ፡፡ አሁን እጅግ ያስደነቀችኝን አንድ የዚህ ዘመን ቅኔውን ጀባ ልበላችሁ፡፡

እባቡን የእባብ ዘር እባብ በላውና፣
መዳህኒቱ ጠፋ እርስ በእርስ ሆነና፡፡



# “የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት”

## ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ለሚከበረው ለ120ኛ ልደታቸው መታሰቢያ

*ያሬድ ጥበቡ*

ገጽ፡ 809
ደራሲ - አምባሳደር ዘውዴ ረታ
ዘመን - ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓም

---

ከወራት በፊት “የሁለት አምባዎች ወግ” የ ሚል የሁለት መጽሃፎች ግምገማ ጀምሬ፣ ወግ አንድን በአቶ በረከት ስሞኦን “የሁለት ምርጫዎ ች ወግ” ላይ ተችቼ፣ ሁለተኛው ወግ ስለ ሌ/ኮሎ ኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም መጽሃፍ ይሆናል ብዬ ቃል ገብቼ ነበር ። ሆኖም የኮሎኔሉን መጽ ሃፍ ለመተቸት ምሬቴ ያልበረደ ሆኖ ስለተሰማ ኝ ዝምታን መረጥኩ ። ክፍል ሁለትን ስትጠባበ ቁ ለነበራችሁ የ”ፍትሕ” ታዳሚዎቼ ማካካሻ እን ዲሆንልኝ እነሆ የአምባሳደር ዘውዴን ታላቅ ሥ ራ አንብቤ፣ ለመገምገም እንኳ ስልጠናውም ሆነ አቅሙ ባይኖረኝም፣ ከመጽሃፉ የተማርኩትን ባ ካፍላችሁ ይጠቅማል ብዬ 809 ገጾች በማንበብ የ ደከምኩበትን መጣጥፍ እነሆ!

ክፍል አንድ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የንግስ በ አል ተጀምሮ ለ100 ገጾች እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ አምስቱን አመታት እያላጋን ይዞን ይዘልቃ ል ። በዚህ ክፍል እጅግ ቀልቤን የሳበው፣ ንጉሠ ነገስቱ “በመልካም ፈቃዳቸው” በሕገ መንግስት የ ምትተዳደር ሃገር ለመገንባት ቆርጠው መነሳታ ቸው ነው ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተራማጅነት ጎልቶ የሚወጣበት ዘመን ነው ። ቀኃሥ የ39 አ መት ጎልማሳ ቢሆኑም በልጅነታቸው የቆነጠጣ ቸው የካቶሊክ ቄስ ምን ያህል አስተምህሮው ሰር ጾ እንደገባባቸው መረዳት ይቻላል ። አባ እንድር ያስ ዣሮሶ አንጎል የሚያዞሩ ምሁር መሆናቸው የሚገባን 300 ገጾችን ጠብቀን፣ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ሲሟገቱ ስናገኛቸው ነው ። በአውሮ ፓ አስተሳሰብ ተፈሪ መኮንንን አንፀዋቸዋል›› ባ ይ ነኝ። ያለበለዚያማ ገና ዘውድ በጫኑ በዘጠኝ ወራቸው፣ ህዝቡ ሳይጠይቅ ሕገ መንግሥት ማ ስረቀቅን ምን አመጣው?

የአውሮፓን የዘመናዊነት ጭራ ለመያዝ ሩጫ ውን የጀመሩት ንጉሠ ነገስቱ ራሳቸው እንደነበሩ ስንገነዘብና፣ ለዚህም ግፊቱን የሚያደርገው የኢት ዮጵያ አፈር (የሕዝቡ ጥያቄ) ሳይሆን፣ በዘመናዊ ነት ስም የመጣው የአውሮፓ ትምህርት መሆኑን ስንረዳ፣ ሃገሪቷ ወደፊት ከመራመድ ይልቅ ለም ን ባለችበት እንደምትረግጥ ፍንጭ ይሰጠናል ። የ120ኛ የልደት በአላቸውን የምናስብላቸው፣ የቀ ዳማዊ ኃይለሥላሴ ሕይወት የሚያስተምረን ነገር

ቢኖር ሃገርን ያህል ነገር በጥቂቶች ሃገር ለማዘ መን በቆረጡ ጀግኖችና ምሁራን፣ አንዴ ከምዕራ ብ አንዴ ከምስራቅ ርዕዮተ ዓለምና የፈጣን ልማ ት ስትራቴጂዎች እየተበደሩ፣ ከመፈክር መፈክር እየተንከባለሉ፣ ሕዝቡን ከዳር ተመልካች አድር ጎ፣ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ነው። ይህ ዛ ሬም ምላሽ ያላገኘ ጥያቄ መሆኑን ነው ከአምባሳ ደር ዘውዴ ታላቅ ሥራ የተማርኩት ።

ይህንኑ የ1923 ሕገ መንግስት እንዲያረቅ የ ተቋቋመው ኮሚቴ አባል በነበሩት በኮሚቴው ሰ ብሳቢ በልዑል ራስ ካሣ ሀይሉ ና በበጅሮንድ ተ ክለ ሃዋርያት መካከል የሚጦፈውን ክርክር ለማ ዳመጥ፣ አምባሳደር ዘውዴ አዳራሹ ድረስ ይዘው ን በመግባት መከዳዎቹ ላይ አስቀምጠው ያስኮም ኩሙናል ። ያውም በእረፍት ጊዜ ከቤተ መንግ ስት ከተላከው ብርዝና ጠጅ እያስጎነጩን ። ራስ ካሣ “ከኢትዮጵያዊ ልማዳችን ወጥተን በሕገ መ ንግስት መተዳደር ለምን አስፈለገ?” ለሚለው ጥ ያቄያችው የሚሰጣችው መልስ “የፈረንጆቹን ሥ ልጣኔ ካልተከተልን ይወሩናል” የሚል ስለነበር፣ “ፈረንጆች የሚወሩን የነርሱን ልማድ ስላልተከተ ልን ሳይሆን፣ ሀብታችንን በመፈለግ ነው” የሚ ለው ድምጻቸው ሲያስገመግም በመገረም አዳመ ጥኳችው ።

ስለኘህ መስፍን ሌላው የገረመኝ ጉዳይ፣ በ ጅሮንድ ተክለሃዋርያት ከተማሪው ንቅናቄ መሪ ዎች ባልተናነሰ ቋንቋ “ዛሬ ባለንበት አለም ላይ ፣ ክቡራን መሳፍንት የምታምኑበት የአገዛዝ ደን ብ በሙሉ ተለውጧል ። የአገር አስተዳደር ሥ ልጣን እንደግል ንብረት ለዘር የሚተላለፍ መሆ ኑ ጭራሽ ከተወገደ ዘመን የለውም” እያሉ ሲሞ ግቷቸው፣ ራስ ካሣ ሲመልሱ “በእኛና በምናስተ ዳድረው ሕዝብ መካከል ያለውን ፍቅርና መተማ መን አናውቅም ብላችሁ እኛን ለሕዝብ የማናስብ ክፉ ገዢዎች አድርጋችሁ የምትቆጥሩን ከሆነ፣ በአንድ ገበታ ላይ ተሰብስበን ለትልቁ የአገር ጉዳ ይ አብረን መሥራት የለብንም “ ብለው ሲመል ሱ፣ ይሄ እስከዛሬም ሰቅዞ የያዘንን ደዌ - በአንዲ ት ኢትዮጵያ ልጆች መሃል እንደ ወዳጅና ጠላት የጎሪጥ የምንተያይበት ክፉ በሽታ - የሚያስከትለ ው ጦስ፣ በጥራት ይታያችው እንደነበር ስገነዘብ ባግራሞት ተዋጥኩ ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ገና መጽሃፉ ሲጀ

> **በተፈሪ መኮንን ተማሪነቴ ወቅት ስኔም ሆነ ስሃገሬ ጠቀሜታ ከሌስው ስስ እንግሊዝና ፈረንሳይ የ30 አመታት ጦርነት ታሪክ ከምማር፣ ምነው ትምህርት ቤቴን ስማቋቋም ስስተደረገው አበሳና ትግል በተማርኩ ኖሮ በሚል ቁጭት ነው ምዕራፉን ያጣጣምኩት**

መር ገጽ 28 ላይ፣ ገና በማለዳ በ1923 ዓም የሰ ማነው ሆኖ ሳለ፣ ከ25 አመታት በሁዋላም፣ ጸሃ ፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስን ከስልጣን ለማውረድ በእቴጌ ቪላ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴና አቶ መኮንን ሀብተወልድ ጋር የህቡዕ/ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ በተገኙበት ወቅትም ራስ ካሣ ይህንኑ ፍራቻችው ን ከመሰንዘር አልቦዘኑም ። ሁለቱ ከድሃ ወገን የተገኙ ታላላቅ ባለሥልጣኖች (ጸሃፌ ትዕዛዝ ወ ልደ ጊዮርጊስና አቶ መኮንን ሀብተወልድ) ቀደም ብሎም “የገጠሩን ሕዝብ ከመንግስት ጋር ለማቀ ራረብ” በሚል፣ አገረ ገገርዎቹን ሳያማክሩ 25 ም ስለኔዎችና 25 ጭቃ ሹሞችን አዲስ አበባ አስመ ጥተው በማሰልጠናቸው ያዘኑት መስፍን ፣ ለአ ቶ መኮንን ሀብተወልድ ተቃውሞአቸውን ሲያሰ ሙ “ሕዝቡ…የፈረንጅ ፊደል የቆጠረ ሁሉ፣ ከየ ሜዳው ተነስቶ ልግዛህ ቢለው አይቀበልም ። አ ንድ ሰው የሕዝብ ገዥ እንዲሆን ከንጉሥ ተመ ርጦ የሚሾመው፣ ከድሃ ወገን የተወለደው ብቻ ነው የሚል ደንብ የለም … በዚያ የመከራው ስ ደት ዘመን፣ እጅግ ሠለጠነ በተባለው በእንግሊዝ አገር እንዳየነው፣ ጌታም በጌትነቱ፣ ድሃም በድህ ነቱ በሰላም ሠርቶ የሚኖር ነው ። መንግስት የ ሚያስበው ለሁሉም ወገን እኩል ዳኝነት እንዲኖ ር ዋስትና መስጠትን እንጂ፣ በትውልዱ ምክንያ ት አንዱን ካንዱ በሥልጣን በማበላለጥ አይደለ ም…በአገራችን ግን እናንተ የምትጠሉት መሳፍን ትና መኳንንት፣ ከዚህ ቀደም ለአገር ነፃነት መስ ዋዕት እየሆነ ብዙ የሚያኮራ ታሪክ የፈፀመና የ አገርን ትልቅነት አስከብሮ የኖረ መሆኑን መርሳ ት አይገባም” ይሉናል ። መስፍናዊ ድምፃቸው ዛ ሬም ያስገመግማል ።

በስደት ሕይወታችን መጠለያና ብሎም እን ደ የጥረታችንና ዕድላችን ትምህርትና ሃብት የ ሰጡን የምዕራብ ሃገራት የሚመሩበት መሠረታ ዊ ፍልስፍና ይኼው የራስ ካሣ ፍልስፍና በመ ሆኑ፣ በመደብ ትግል ስም ያተራመስናትን ሃገራ ችንን ስናስብ ሀዘን ሊሰማን ይገባል እላለሁ። ይ በልጥም ግን ያሳዘነኝ ለውጥ ፈላጊ የነበረው የኔ ው ትውልድ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሥር ከፍተ ኛውን ሥልጣን የያዙት ጸሀፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊ ዮርጊስና አቶ መኮንን ሀብተወልድ የህልሙ ተካ ፋይ መሆናቸውን ሳይረዳ መጨካከን ላይ ልንዳረ ስ መቻላችን ነው። የመጽሃፉ አካልም ባይሆን፣ የመኮንን ሀብተወልድ ዕጣ እንደርሳቸው ለውጥ በሚፈልጉ፣ ነገር ግን ትዕግስቱ ባልነበራቸው ጄ ኔራሎች ጥይት መገደል (በጄኔራል መንግስቱ ነ ዋይ መንግስት ግልበጣ ሙከራ) መሆኑን ስንረ ዳም፣ ይሄ እስከዛሬም ሥልጣን ላይ ያሉ ዜጎቻ ችንን በሃገር ጠላትነት የምናይበት አተያይ፣ ይዞ ን እንጦርጦስ ከመውረዱ በፊት እጅግ ልናስብበ ት የሚገባ ይመስለኛል ። እያንዳንዱ ባለሥልጣ ን መመዘን ያለበት በወሰነው ውሳኔ፣ ይዞ በተከ ራከረው አቋም እንጂ ለኢትዮጵያ መንግስት በ ማገልገሉ እንደ ጠላት መቆጠር የለበትም ባይ ነ ኝ ። ሃገሪቱ ያለመንግስት መኖር ስለማይቻላት ነው ይህን ማለቴ ።

በተቃራኒው ግን ከልዑል ራስ ካሣ መማር እ ☞

ንችላለን ። በሕገ መንግሥት አርቃቂው ኮሚቴ ውስጥ የጦፈ ልዩነት የነበረ ቢሆንም፣ የልዩነት ነጥቦቹ ከጽህፈት ሚኒስቴር በመጡ ቃል ተቀባዮች ሰፍሮ ለንጉሰ ነገስቱ እንዲተላለፍ ሲቀመንበሩ ራስ ካሣ ስብሰባውን ሲያሳርጉ "ሁላችንም ከልባችን የሚቻለንን ማድረጋችንና መድከማችን የሚካድ አይደለም ። በስብሰባችን ላይ ስንነጋገር፣ አለመስማማትና አለመጣጣም ደርሶብናል። ይህ መቼም የአገር ጉዳይ የሆነ ሥራ ሲሠራ የሚያስከትለው ችግር ነው። በዚህም የተነሳ በአንዳንድ ጉዳይ በሐሳብ መከፋፈላችን ለጊዜው በመካከላችን ቅሬታ ያሳደረ መስሎ ቢታይም፣ ወዳጅና ጠላት አድርጎ የሚለያየን መሆን የለበትም። ይህን ሳንስማማ የቀረንበትን ነገር ንጉሠ ነገሥቱ መርምረው ውሳኔ በሚሰጡበት ዕለት፣ ጉዳያችን ይዘጋል" ይሉናል። ለኔ ትውልድ እጅግ ባዕድ በሆነ ሆደ ሰፊነት ያነጋግሩናል። የኔ ትውልድና የቀድሞዎቹ ታላላቆች ሳንተዋወቅ ተጨካክነናል። ሆኖም ባለፉት ሃያ አመታት፣ ዕድሜ ለአምባሳደር ዘውዴ ረታና መሰሎቻቸው፣ ከራሳችን ታላላቆች አንደበት እንድንማር ያደረጉት ድካም ፍሬ እያፈራ ነው። ከአዲሱ ትውልድ ድንቅዬዎች መካከል፣ የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ወጣት ተመስገን ደሳለኝ፣ የ"ነፃነት ለኢትዮጵያ" ሬዲዮ ጋዜጠኛና ባለቅኔ ኢሳይያስ ልሳኑ፣ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁንና፣ በደራሲና ባለቅኔ በዕውቀቱ ሥዩም ጥልቅ ሥራዎች ውስጥ የተስፋ ብርሃን እያጮለቅን ነው ።

ወደመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ስንመለስ፣ በአርቃቂ ኮሚቴው ውስጥ የተፈጠረው የልዩነት ሃሳብ ለጃንሆይ በቀረበላቸው ጊዜ የተናገሩትን ስናዳምጥ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዴሞክራሲን በሚመለከት የነበራቸው አስተሳሰብ እንዲሁ ከዘመኑ የቀደመ ምናልባትም ሥርነቀል ሊባል የሚችል እንደነበር እንገነዘባለን። እንዲህ ይላሉ ፣ "የሠለጠኑት አገሮች የሕገ መንግስታቸውን አመሠራረት የተመለከትን እንደሆነ፣ መንግስትን ለማቆም፣ መንግሥትን ለመሻር የመንግሥትን ሥራ ለመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን ያለው ፓርላማው ሆኖ እናገኘዋለን። እኛ በዚህ ደረጃ ለመድረስ የብዙ ዘመናት ድካም የሚጠይቅን ቢሆንም፣ ቅድም በጅሮንድ ተክለሃዋርያት እንዳስረዳው፣ አጀማመራችን የዴሞክራሲን መንገድ የሚከተል ሆኖ እንዲታይ፣ በመወሰኛና በመምሪያ አማካሪዎቻችን መካከል የመደመጥም ሆነ የወንበር ልዩነት እንዳይደረግ መጠንቀቅ አለብን" ይላሉ። እኔን የተሰማኝ፣ ገና በማለዳ፣ የዛሬ 80 አመት፣ እንዲህ አይነት የዴሞክራሲ ጥብቅና የነበራቸው መሪ፣ ከ43 አመታት በሁዋላ በየካቲት 66ቱ አብዮት ሲዋከቡ፣ "የድካማችን ውጤት ነው" የሚል ውስጣዊ እርካታ ተሰምቷቸው እንደ ሆነስ ብዬ እንድጠራጠር ከንክኖኛል። በኔ ዕምነት መሪዎችን መሪ የሚያደርጋቸው ከተራው ዜጋ የማይጋሩት አንድ ልዩ ባህሪ ስላላቸው ይመስለኛል። አለበለዚያ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለአልጋቸው ተኪ ሳያዘጋጁ ማርጀትን ለምን መረጡ? አንድ ሁላችን የምንስማማበት ፋይዳ ቢኖር፣ በየካቲት 66 ከታች፣ ከሕዝብ የተነሳውን ተቃውሞ በአመጽ ለመደምሰስ ፍፁም ፈቃደኛ ያልነበሩ መሆናቸውን ነው። የካቲትም ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ለአመታት የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ግፊት ያደርግ ለነበረው የተማሪዎች ንቅናቄ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የነበራቸው አባታዊ ስሜትንም፣ "ምናልባት ፊውዳላዊ ቅሪቱን ለማጥፋትና የገባሩን ነፃነት ለማምጣት የሚረዳ አጋዥ ሐይል" አድርገው አይተውት እንደሆንስ? ብዬ ርቄ እንዳስብ ገፋፍቶኛል። ከአንድ ደራሲ ደግሞ እንዲህ የማይገናኙ የሚመስሉ ክስተቶችን አያይዞ እንድናስላስልና እንድናጠይቅ የረዳን ከሆነ ለስራው ትልቅነት ምስክር ይመስለኛል።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከተራማጆቹ ከነበጅሮንድ ተክለሃዋርያት ጋር በመወገን "የፌዎዳልሥርዓት በዓለም ላይ እጅግ የተወገዘና የተፋቀ ስለሆነ፣ለእኛ ለሥልጣኔያችን ጠቃሚያችን የሆነውን ሕገ መንግስት በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመሰርት፣ ይኸው የተጠላው የፌዎዳል አሠራር ካልተጨመረበት ብለን ሳንስማማ ብንቀር ወዳጆችን በሆኑት በዓለም መንግስታት መሪዎች ዘንድ ምን ያህል ትዝብት እንደሚወሰድብንና፣ ጠላቶቻችንንም እንደምናስደስት ማወቅ አለብን" ሲሉም ጉዳዩን መዝጋታቸው የሚያሳየን ነገር ቢኖር፣ በዛሬው ዕለት 120ኛ የልደት በአላቸውን የምናከበርላቸው የሃገር መሪ፣ ምን ያህል ከጊዜው እጅግ የቀደመ ሃገራዊ ርዕይ የነበራቸው ተራማጅ መሪ የነበሩ ቢሆንም፣ ራስ ካሣ "ተው አታስተምር!" ብለዋቸው ነበር በሚባሉ፣ የድሃ ልጆች በሆኑ ዝቅተኛ መኮንኖቻቸው እጅ ታፍነው መገደላቸው የሚሰቀጥጥ ታሪካዊ ፍጻሜ መሆኑን ነው ። በተለይ በወታደሮቻቸው እጅ ለመገደል፣ ምክንያት ሆኖ የቀረበው "ካውሮፓ ወደኒሳ አስቀሩን" የሚለው ክስ መሆኑን ስንረዳ፣ ታሪክ በምጸት የተሞላ መሆኑን ያስገነዝበናል ። ያውም በሳልክው ቢላዋ የመታረድ አይነት መሪር ምጸት ።

ከዚሁ እርስበርስ የመጨካከን ታሪክ ጋር በተዛመደ ሌላው ከአምባሳደር ዘውዴ መፅሃፍ የተማርኩት ጉዳይ፣ እኛ ዘወትር የምዕራቡን ጭራ ለመያዝ የምንቧችር ብንሆንም፣ እነርሱ ለጥረታችን ያላቸው ግምት በአመዛኙ አሉታዊ መሆኑን ነው ። ለምሳሌ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልካም ፈቃድ የቆመውን ሕገ መንግሥት፣ "ለአገሪቱ አመራር አስፈላጊውን ሥልጣን በሙሉ አጠቃልሎ የሰጠው ለንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ስለሆነ፣ ዘመናዊውን የፓርላማ አሠራር ያልተከተለ ነው" በማለት ሲያጣጥሉት ታይተዋል ። ይህ እንግዲህ ከ80 አመታት በፊት ነው ። ምርጫ ያለን አይመስለኝም፣ ወደ ልዑል ራስ ካሣ የተቃውሞ ሃሳብ ነው የሚመልሰን ። ምዕራባውያን ዴሞክራሲን አስመልክቶ በሌሎች ሃገሮች ላይ የሚያደርጉት ትችት፣ ከሃገሩ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተዛምዶ የሚሰጥ ገንቢ ሃሳብ ሳይሆን፣ የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን ማስጠበቂያ የአይዲዮሎጂ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበት መሆኑን ነው የምንገነዘበው። የሚገርመው ግን የምዕራባውያን ሃገራት ታሪክ የሚያስተምረን ነገር ቢኖር፣ ዴሞክራሲ ከላይ ወደታች የተሰጠ ሀብስተ መና ሳይሆን፣ ሕዝቦች አስርተ አመታትን ታግለው በተራዘመ ሠላማዊና ሕጋዊ ትግል የተቀዳጁት መብት መሆኑን ነው። በአሁኑ ሰአት ሃገራችን ኢትዮጵያ ሌላ የሽግግር መድረክ ውስጥ ልትገባ የምትችልበት ንጋት ላይ ስለምትገኝ፣ ይህ ከራሳችንም ከምዕራባውያንም ታሪክ የምንማረው ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ይመስለኛል። ከትርምስ የሚያድነንም ሊሆን ይችላል እላለሁ ።




እኚህ ታላቅ ደራሲ (አምባሳደር ዘውዴ) "ትምህርት የሥልጣኔ መሠረት" ባሰኙት በሶስተኛው ምዕራፍ፣ ተፈሪ መኮንን በአውሮፓ ጉብኝታቸው ወቅት ሰኔ 6 ቀን 1916 ዓ.ም (የዛሬ 88 አመት) ባረፉበት የሆቴል ክፍል ውስጥ ከልዑክ ቡድናቸው አባላት ጋር ስላደረጉት ጠቃሚ ውይይት ያካፍሉናል። ገና በወጣትነታቸው ጀምሮ ከረዳቶቻቸው ጋር እንዴት እንደሚመካከሩና ውሳኔ እንደሚያሳልፉ ያስተምረናል። ባዶ እጃቸውን ከአውሮፓ ጉብኝታቸው ከተመለሱ በሁዋላ በግል ገንዘባቸው የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትን በሚያዚያ 1917 አም ሲያቋቁሙ ከቤተ ክህነትና ከመሳፍንቱ የደረሰባቸው ውግዘትና፣ ካለሙት ለመድረስ ተፈሪ መኮንን ያሳዩት ፅናት የሚደንቅ ነው። ሆኖም በእኔ አመለካከት፣ የመሳፍንቱና የቤተ-ክህነት ተቃውሞ፣ በቂ ተጽዕኖ መፍጠር ችሎ የአውሮፓን ትምህርት በምን መንገድ እንቀበለው በሚለው ላይ ሰፊ ክርክር አድርጎ የሃሳብ ሽግሽግ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ቢያመቻች ኖሮ የት በደረስን ነበር። መጥፎ ዕድል ሆኖ፣ ወደ ሃሜትና አሉባልታ የሚያሽቆለቁለው ባህላችን ተገቢውን ሽግግር እንዳናደርግ ዘግቶ ያሸናፊና ተሸናፊ ክፍፍልን ያስከተለ ሆኖ ተሰምቶኛል ። ምናልባትም ጃፓን በሄደችበት መንገድ ለመዘመን የነበረን ዕድል የተዘጋው ያኔ ይሆናል። ያኔ የጀመረ ሳናጠናና ሳንጨነቅበት ተሯሩጠን አቋም በመያዝ፣ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" በሚል እልህ፣ እንደ ወዳጅ/ጠላት የምንተያይበት አስከፊ የፖለቲካ ባህልም እንደ ክፉ የጥርስ ህመም ይኼው እንደጠዘጠዘን ይኖራል ።

በተፈሪ መኮንን ተማሪነቴ ወቅት ለኔም ሆነ ለሃገሬ ጠቀሜታ ከሌለው ስለ እንግሊዝና ፈረንሳይ የ30 አመታት ጦርነት ታሪክ ከምማር፣ ምነው ትምህርት ቤቱን ለማቋቋም ስለተደረገው አበሳና ትግል በተማርኩ ኖሮ በሚል ቁጭት ነው ምዕራፉን ያጣጣምኩት። ጥቅምት 21 ቀን 1919 አም ለመጀመሪያ ጊዜ ለስኮላርሺፕ ትምህርት ወደ ውጪ የሚላኩት 33 ተማሪዎች አልጋ ወራሹ ተፈሪ መኮንን ፊት ሲቀርቡ ወጣቱ መስፍን ያደረጉላቸው የስንብት ቃል "...እኔ ሰው ነኝ፣ ሟች ነኝ። ለማትሞተው አገራችን ረዳት እንድትሆኗት እግዚአብሔርን እለምንላችኋለሁ..." የሚል ቢሆንም፣ ዛሬ ከ85 አመታት በኋላ፣ እንኳን ለሃገራችን ረዳት ልንሆናት ቀርቶ፣ መሬቷን ለመርገጥ እንኳ ከሕግ ውጪ በቂም በቀልና ክፋት የተከለከልን አያሌ መሆናችንን ላየ፣ የተፈሪ መኮንን ልመና ፈጣሪ የሰማው ለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር አያስችልም ።

ክፍል ሁለት - "ጥቁር ደመና በኢትዮጵያ ፀሐይ" የሚል ሲሆን ምናልባት ብዙዎቻችን የማናውቃቸውን ውሎች፣ ምስጢሮችና ሰነዶች ያካተተ ነው ። ሙሶሊኒ ሥልጣን ላይ ከመጣ በሁዋላ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ጉባኤ አባል እንድትሆን መደገፉን፣ በወረራው ድሮ የአዲስ አበባ ውል መፈራረሙን፣ በመስከረም 1929አም

ወደ ገፅ 26 ዞሯል



# ስለመለስ ውርሶች ጥቂት ነጥቦች

ሙሉነህ አያሌው

የወቅቱ የአገሪቱ አስተዳደር በተደጋጋሚ እያወሳ የሚገኘው ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን ነው፡፡ ጠቅለል አድርገን እንየው ከተባለ ሁሉም የሚሉት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ራዕይ ከግብ ለማድረስ መትጋት አለብን የሚል ነው፡፡ ይህንን ራዕይ ከግብ ለማድረስ የመለስን ራዕይ የፈጠረውን የመለስ ፖለቲካ ፍልስፍና እና በፖለቲካዊ ክስረትና ዴሞክራሲያዊ ድቀት ላይ ተመስርቶ ተገኘ የሚባለውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ስማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ማንም መሪ የቀረፃቸው ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች በአንድም ይሁን በሌላ የመሪውን ብቃትና ማንነት በእጅጉ ቁልጭ አድርገው የማሳየት አቅም አላቸው፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ልማት ስትራቴጂ ፕላን እና እቅድ ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ መለስ የፈጠሯቸው ከመሆናቸው አንፃር አፈፃፀሙንም በተመለከተ በዚህ ፖለቲካ ፍልስፍና የተቃኘ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ መለስ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በጠንካራ አስተዳደራዊ መሰረት ላይ ሰይሟቸዋል ከሚያስብሉ ነገሮች መካከል ሦስቱ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡-

1. መለስ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ካለፉት ሃያ አንድ አመታት ወዲህ (የቀድሞዎቹ መንግሥታት ከሄዱበት አቅጣጫ በተለየ መልኩ) የብሔር እና የቋንቋ ፌዴራሊዝምን መሠረት ባደረገ መልኩ አዋቅረዋል፡፡ ይህንን ስርዓት አወቃቀር ህጋዊ መሆኑንና የትኛውም ተተኪ ባለሥልጣን ኢትዮጵያን ሊታደጋት ከፈለገ በዚህ መስመር መጓዝ እንዳለበት ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ እርሳቸውን የተኩት የመንግሥት ባለሥልጣናት የመለስን ራዕይ ለማሳካት ቀድሞ እርሳቸው እውቅና ሊሰጡትና ፖለቲካዊ ድጋፍ ሽፋን ለጠየቁበት የብሔር ፖለቲካ እውቅና መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለተተኪ ባለስልጣናቱ ግን ምን አልባት የብሔር ፖለቲካዊ አስቸጋሪ ሊሆን ይችልባቸዋል ብዬ የማምንበትን አንዳንድ ነጥቦችን ልጥቀስ፡፡

የመጀመሪያው መከራከሪያ ተተኪዎቹ ባለስልጣናት የብሔር ፖለቲካ ስርዓታዊ ዕውቅና እንዲያገኝ ከመሰረቱ ‹‹ለብሄር ነፃነት መታገል ያስፈልጋል›› በሚል በትጥቅ ትግል ውስጥ ያለፉ አይደሉም፡፡ ይልቅስ ከድህረ-83 ወዲህ የሀገሪቷ መንግሥታዊ ስርዓት በብሔር ከተዋቀረ እና ሕገ-መንግሥታዊ ከለላ ከተሰጠው ወዲህ ወደ ገዢው የፖለቲካ ቡድን የተቀላቀሉ ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ በብሔር ፖለቲካ ትልቁን ቁማር የሚያጫውቱትን ፈጣሪ የተነጠቀው ፓርቲ እርሳቸው እንደያዙት አይነት ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅር (ብሔርን ማዕከል ያደረገ) ተሸክሞ ለማስቀጠል ይቸግረዋል፡፡ መለስ በግለሰባዊ ስብዕና የገነቡት የብሔር ፖለቲካ በተቀሩት ተተኪ ባለስልጣናት በተመሳሳይ ፖለቲካ ስብዕና ላይቀጥል የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ይሆናሉ፡፡ ይሄ አይነት ክፍተት ሌሎች መዘዞችንም ይዞ ብቅ ሊል ይችላል፡፡

ቀዳሚው በኢህአዴግ ነባር አመራርና በተተኪው መካከል የሚፈጠር የውስጥ የሀሳብ ቅራኔ አንዱ ነው፡፡ ነባሩ የግንባሩ አባላት ታግለንለታል የሚሉት የብሔር ፖለቲካ ካርታ ያላቸው ሲሆን አዲሱ አመራር ግን በብሔር ፖለቲካ ትምህርትን ብቻ ቀስሞ የመጣ በመሆኑ የብሔር ፖለቲካውን ወደ ፊት እንዴት ማስቀጠል ይቻላል በሚለው ላይ ቅራኔዎች የመፈጠራቸው ጉዳይ ነው፡፡

ሁለተኛው ችግር ሊፈጠር የሚችለው በቀድሞው ጠ/ሚኒስትር ዘመን እንደታየው ዓይነት የብሔር ግጭት በተባባሰ መልኩ የሚቀጥል ከሆነ የሚዘረጋለት የመፍትሄ አቅጣጫ ምን ሊሆን ይገባል በሚለው ላይ የሚፈጠር አለመግባባት ነው፡፡ አለመግባባቱ አንድም የመፍትሄ አማራጭ ማቅረብ ካለመቻል የሚመጣ ሲሆን በሌላ መልኩም በሚወሰዱ እርምጃዎች ዙሪያ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ናቸው፡፡ እንደ በፊቱ አንድ ወጥ በሆነ አመራር በጠንካራ ወታደራዊ እርምጃ፣ ‹‹የተገደለው ተገድሎ የተረፈው ትምህርቶችን ያግኝ›› እንደሚለው አይነት አፀፋ ተተኪው አመራር ሊወስድ ይችላል? የሚለው አጠያያቂ ነው፡፡

የቀድሞ መለስ ያደጉበት እና ያሳደጉት ግለሰባዊ ስብዕና አሁን ካሉት የግንባሩ ተተኪ አመራሮች ጋር ሲታይ እጅግ የተራራቁ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ቆራጥ አመራር ለመስጠት በሚታየው ክፍተት የተነሳ የብሔር ፖለቲካው እንደሚፈራው አገሪቱን ወዳልተፈለገ ብጥብጥ ይዟት ሊገባ የሚችልባቸው እድሎች ሰፊ ናቸው፡፡

ለዚህም ነው መለስን ለመተካት መለስ በግለሰባዊ ስብዕናቸው የፈጠሯትን ኢትዮጵያ መረዳት የሚያስፈልገው፡፡ አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ በምክር ቤቱ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆነው ሲመረጡ የተናገሩትን ንግግር ማስታወስ በቂ ነው፡፡ አቶ ኃ/ማርያም ከመለስ ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ሲናገሩ ‹‹ከእርሱ ጋር በየቀኑ እንገናኝ ነበር፡፡ በየእለቱ ከስሩ ሆኜ ሁሌም አዳዲስ ነገሮችን እየተማርኩ ነበር፡፡ ለእኔ ከእርሱ ጋር የነበሩኝ ውሎዎች የትምህርት ቤት ያህል ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ያሁሉ ነገር የለም›› ነበር ያሉት፡፡


ይሄ ንግግር ብዙ ነገሮችን አመላካች ቢሆንም በየዋህነት ምን ለማለት ፈልገው ይሆን ብሎ ለሚያጠይቅ ግለሰብ ግን አንዳንድ ቁምነገሮችን ማየት ይቻለዋል፡፡ አንድም አቶ መለስ ተተኪያቸው እርሳቸው በገነቡት፣ መግቢያና መውጫውን በማያውቁት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ቀመር እያስተማሩዋቸው እንደነበርና ይህም ሳያልቅ ህልፈተ ህይወታቸው እንደመጣ የሚጠቁም ሲሆን በሌላ መልኩ ተተኪው መሪ ከቀድሞው የተሻለ ፖሊሲና እስትራቴጂ መቅረፅ ይቅርና አቶ መለስ የደረሱበት ደረጃ እንኳን ለመድረስ ሳይበቁ ጠ/ሚኒስትሩ እንደተለያዩአቸው የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ በቀላል አማርኛ ሲተረጐም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ገብቶ በመማር ላይ የነበረ አንድ ተማሪ ማጠናቀቅ የሚገባውን የትምህርት ሸፋን ሳይጨርስ አቋርጦ የመውጣት ያህል ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በሰለጠነበት ሙያ ብቁ ነው የሚል ማስረጃ ማቅረብ ስለማይቻል በየትኛውም መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የማገልገል እድል አይኖረውም፡፡ ይሄ የሚያሳየው የተማሪውን ውድቀት ብቻ ነው፡፡ ከት/ቤት ማቋረጥና ባልጨረሰበት ሙያ ስራ መያዝ የትህትና ጉዳይ አይደለም፡፡ አለመቻል የሞራል እና የብቃት ጥያቄ ነው፡፡ ‹‹ከመለስ እየተሰጠኝ የነበረውን ትምህርት አልጨረስኩም›› ማለታቸው እርሳቸው በሀላፊነት ይዘውት ለቆዩት ቦታ ብቁ አይደለሁም እንደማለት ነው፡፡ ይሄ የብቃት ጥያቄ ትልቁንና አስፈሪውን የመለስ ውርስ የሆነውን የብሔር ፖለቲካ በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል ስርዓት ለመዘርጋት ይቸገራል፡፡

ሁለተኛው የመለስ ውርስ ሰላምና መረጋጋት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት ለኢትዮጵያውያን ብቻ የሚጠቅም ተደርጐ መወሰድ እንደማይቻል ታሪክ አስተምሮናል፡፡ ለከፍተኛ ቀውስ የተጋለጠ፣ በከፍተኛ ረሃብና ጦርነት በሚታመስ አምባገነን መንግሥታት በተወረሩ አገራት በተከበበ አካባቢ መኖር ፖለቲካውን ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ቀጠና ላይ እራስን ችሎ ለማቆየት አስቀድሞ ውስጣዊ ሰላም አስፈላጊ ነው፡፡ አገራችን ለረጅም አመታት የምትታወቅበት የሰላም መሠረቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንድም አገሪቱን የሚያስተዳድሩ ገዢዎች ህዝቡን በኃይል መቆጣጠር በመቻላቸውና ህዝቡም የብጥብጥን ተሞክሮ ካለማዳበሩ የተነሳ ዝም ለማለት በመገደዱ ምክንያት አገሪቷ ውስጣዊ መረጋጋትን የተላበሰች ያስመስላታል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት መሪዎች በተተካኩ ቁጥር ህዝቡ ለአዳዲሶቹ ገዢዎች በሚሰጠው እውቅና ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች አለመኖራቸው ነው፡፡ የህዝቡ ይሁኝታ ለውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የህዝቡን ይሁኝታ እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ህዝቡን ለማገልገል የደፈረ መሪ ማግኘት ሳይቻለን ቀርቷል፡፡

ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ በተለይ በመለስ የአገዛዝ ዘመን የሰላም ሞዴልና የተረጋጋች መስላ ታይታለች በእርግጥም አንዳንድ አካባቢዎች ግጦሽ መሬት፣ ብሔር እና ሃይማኖት ተኮር ግጭቶች ከመነሳታቸው ውጭ አብዛኛው ህዝብ በሰላም ኑሮውን መግፋቱ የሚታወቅ ነው፡፡ የአቶ መለስ አምባገነን አገዛዝ ለዚህ ሰላም መስፈን ትልቁን ቦታ ይይዛል፡፡

በየአጋጣሚው ለሚነሱ ግጭቶችና የህዝብ ቅራኔዎች እርሳቸው ይሰጡት የነበረው እርምጃ ሌሎቹን መቀጣጫ አድርጐ አገሪቱን የተዳፈነ እሳት አድርጓት ነበር፡፡ የዚህ ውስጣዊ መረጋጋት ሌሎች አገራትን በአመራሩና በህዝቡ ላይ አመኔታ እንዲጣልባቸው አስችሎታል፡፡ በተለይ ነገሩን የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው የሚያደርገው ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ውስጥ ያሉ አገራት ውስጣዊ መረጋጋትን በግድም ይሁን በይሁኝታ ማሳካት አለመቻላቸው ነው፡፡ ስለዚህ የአገራችን ውስጣዊ መረጋጋት በቀጣይም አገሪቷን እና መሪዋን ከራሳችን ላለፈና ሌሎችን ለሚመለከተው የአካባቢያዊ ሰላም ማስከበር ተልዕኮ ኃላፊነት እንድንሸከም ተደርጓል፡፡ ይሄ የአቶ መለስ ሌላኛው ለተተኪው አመራር የተዉት ውርስ ነው፡፡ በእርግጥ ይሄን የተረጋጋ ሀገር መስርተዋል የሚለውን የሚያጠይቁ ሁነቶች አሉ፡፡ ኦጋዴን፣ ኦሮሚያና ጋምቤላ መሰል አካባቢዎችን ስንመለከት የሚለው የተረጋጋ መንግሥታዊ ስርዓት በወታደራዊ ኃይል የቆመ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ ሁነትም ስርዓቱን ሲታይ ጠንካራ የሚመስል ግን ደግሞ ልፍስፍስ (brittle) ተብሎ በአንዳንድ አጥኚዎች እንዲጠራ ያደረገው፡፡ አቶ መለስ ከአገራዊ ፋይዳቸው ይልቅ በአካባቢያዊ፣ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ መድረኮች ላይ የነበራቸው ሚና ከፍተኛ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ተተኪ መሪዎቹ የመለስ ውርስን ለማስቀጠል በቅድሚያ የተተበተበውን የውስጥ ቅራኔ ደረጃ በደረጃ ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚፈቱበትን አካሄድ ማስቀመጥ ይገባቸዋል፡፡ እንደቀድሞው አመራር በጉልበት ለማካሄድ አንድም ጉልበትን ለመጠቀም

ወደ ገፅ 15 ዞሯል



# “ታዲያስ፣ ሰላም ነው!?”

*በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)*

ድሮ ድሮ “ደህና አደራችሁ?”፣ “ደህና ዋላችሁ?” ነበር ሰላምታችን፡፡ አሁን ተቀይሮ ጥያቄው የመዋልና የማደር ጉዳይ ሳይሆን የሰላም ጉዳይ ሆነ፡፡ “ሰላም ነው?” እንባባላለን፡፡ የታወቀ የእርስ በርስም ሆነ ድንበር ዘለል ጦርነት ውስጥ አይደለንም፡፡ ይህ የታወቀ ነው፡፡ ግን “ሰላም ነው ወይ?” ብለን እንጠያየቃለን፡፡ ጥያቄያችን የሰላም ጉዳይ ከጦርነት ጋር ብቻ የተያያዘ አለመሆኑን ይናገራል፡፡

በተለመደው አነጋገር ጦርነት ከሌለ ሰላም ነው፡፡ ሰላም ሁሉ ግን ሰላም አይደለም፡፡ ለዚህ ነው በሰላም ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎች ሰላምን አሉታዊ ሰላም (Negative Peace) እና አዎንታዊ ሰላም (Positive peace) ብለው የሚከፋፍሉት፡፡ አሉታዊ የሚሉት የሰላም ስትራቴጂ ትኩረቱ ጦርነትን መከላከል ላይ ብቻ ነው፡፡ ጦርነትንና ግጭትን በመከላከል ላይ ብቻ ላተኮረው ለዚህ ስትራቴጂ ጥይት ተተኩሶ ህይወት እስካልጠፋ ሰላም ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚገነባው ሰላም መሰረቱ የዜጎች ሁለንተናዊ ተራክቦና የተራክቦው ውጤት አይደለም፡፡ ጥይት እስካልጮኸ የሰብአዊ መብት መከበር አያስጨንቅም፡፡

አሉታዊው ሰላም ትኩረቱን ከጦርነት መኖር ያለመኖር ጋር ማያያዙ በዚህ ፕላኔት ላይ የሚኖሩ ሰዎችን ታሪክ መርምሮ ነው፡፡ የአለም ህዝቦች ታሪክ በጦርነት የተጎሳቆለ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ጦርነትን መከላከል ሰላምን ማምጣት ነው የሚለው ፍልስፍና ሰፊ ተቀባይነት አላጧም፡፡ እዚህ ላይ ታዋቂው የታሪክ ምሁር ዊል ዱራንት፣ በአንድ ወቅት የአለምን ታሪክ በአምስት ደቂቃ መግለጽ ይችል እንደሁ ተጠይቆ ከአምስት ደቂቃም ባነሰ ጊዜ የገለፀበትን መንገድ ብጠቅስ ለጉዳዩ ይረዳኛል፡፡

ዱራንት ሲናገር “የታሪክ መፃህፍት የአለምን ታሪክ ደም የሚጎርፍበት ቀይ ወንዝ አድርገው ይገልጹታል፡፡ ወንዙ በጣም በፍጥነት የሚጎርፍ፣ በወንዶች የተሞላ የደም ጎርፍ ነው፡፡ ንጉሶች፣ መስፍኖች፣ ዲፕሎማቶች እና ፖለቲከኞች ሞልተውታል፡፡ እነሱ አብዮትና ጦርነት ያስነሳሉ፤ መብትንና ድንበርን ይጥሳሉ፡፡ ነገር ግን ትክክለኛው የአለም ታሪክ ያለው በዚህ የደም ወንዝ ውስጥ ሳይሆን በወንዙ ዳርቻ ባለው መሬት ነው፡፡ እዚያ ተራ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች እርስ በርስ ይዋደዳሉ፤ልጆች ወልደው ያሳድጋሉ፤ የተቸገሩትን ይረዳሉ፡፡ በዚህም ሁለንተናዊ መስተጋብር ወደ ወንዙ እንዳይገቡ ይጠነቀቃሉ” ብሏል፡፡

የዱራንት አገላለጽ የአለም ታሪክ ምን ያህል ከጦርነት ጋር ተሳስሮ እንደኖረ ያሳያል፡፡ የኢትዮጵያም ታሪክ ከዚህ አይዘልም፤ የነገስታትን በቀዩ ወንዝ ውስጥ ጉዞ ዘጋቢ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ነው በቀዩ ወንዝ ውስጥ የሚፈሱት ነገስታት፣ ዲፕሎማቶችና ፖለቲከኞች ጦርነትን መከላከል ሰላምን መጠበቅ የሚመስላቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የሰላም ዋናው ጉዳይ ጦርነትን ማስቀረት/መከላከል/ መሆን የለበትም፡፡ ዋናው ጉዳይ ጦርነት-አልባ በሆነው ጊዜ የሚሰራው ስራ ነው፡፡ ጦርነት ቀረ፣ የዜጎች ሁሉ ትኩረት ወደ ኑሮአቸው ተመለሰ፤ ቀጣዩ ምንድነው? እንዴት ነው ህዝቡ የሚተዳደረው? ለሚለው እምብዛም ትኩረት አይሰጥም፡፡ ቢሰጥም መሰረቱ የህዝቡ ጥቅምና መብት አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ጦርነትን በመከላከል ላይ ብቻ ያተኮረውን የሰላም ጥበቃ የመስኩ ምሁራን በመኪና አባራሪ ውሻ (Dog-car problem) የሚመስሉት፡፡ እስቲ ይታያችሁ! አንድ ውሻ ለአመታት በደጁ መኪና ባለፈ ቁጥር እየጮኸ ሲያባርር ከርሞ አንድ ቀን አንዱን መኪና ነክሶ ቢይዘው ምን ያደርግለታል? ምን ያደርግበታል? ጦርነትን የሚከላከሉት ንጉሶች፣ ዲፕሎማቶች ፖለቲከኞች ሰላሙን ሲያገኙት ምን ይሰሩበታል? ጥያቄው ይህ ነው፡፡

ትክክለኛው መንገድ የሚያስተዳድሩትን ህብረተሰብ መሰረት ያደረገ አዎንታዊ ሰላምን ለመገንባት ከተጠቀሙበት ነው፡፡ አዎንታዊ ሰላም መንግስታትና የሚያስተዳድሩት ህብረተሰብ በተወሰኑ መሰረታዊ ደንቦች ላይ ከስምምነት እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ ጦርነትንም ሆነ ሌሎች አነስተኛ መቃቃሮችና ግጭቶችን ይቀንሳል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን አዎንታዊ ሰላም መዋቅራዊ መናጋትን (structural- violence) ይቀንሳል፡፡ እዚህ ላይ መዋቅራዊ መናጋት የሚባሉት መንግስትና አንዳንድ ባህላዊ ማህበራዊ ተቋማት በዜጎች ላይ የሚያደርሱትን በደል ነው፡፡

የመዋቅራዊ መናጋት መሰረቱ የዜጎችን ማህበራዊና ፖለቲካዊ እኩልነትና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ አለመከበር ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ አዎንታዊ ሰላምን መገንባት አይቻልም፡፡


ሰዎች የሚበሉት አጥተው በረሀብ የሚሞቱ ከሆነ፣ በህክምና በሚድኑ ወረርሽኞች ህይወት የሚቀጠፍ ከሆነ ሰላም ተናግቷል፡፡ ሰላም የምንተነፍሰው አየር፣ የምንጠጣው ውሃ፣ የምንበላው ምግብ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ሰላም ስሜታዊ (emotional) እና መንፈሳዊ (Spiritual) ጤናችንም ጭምር ነው፡፡ እነዚህን ለዜጎቹ ማሟላትን መሠረት አድርጎ የተነሳ የሰላም ስትራቴጂ ነው ‹‹ሰላማዊ ሰላም›› የሚያመጣው፡፡ ለዚህ ደግሞ የዜጎች መሰረታዊ መብቶች (ለምሳሌ፣ የመማር፣ ሰርቶ ንብረት የማፍራት፣ በፖለቲካዊ መብት የመጠቀም፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣. . .ወዘተ) ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በተነደፉ የጋራ መግባቢያ ደንቦች መሰረት የጸኑ መሆን ያሻቸዋል፡፡

በተለይ ደግሞ አዎንታዊ ሰላም ከሰብአዊ መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን መገንዘብ አግባብ ነው፡፡ በመሠረቱ ሰብአዊ መብትን መጣስ ሰላምን መጣስ ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ በመሳሪያ የሚደረግ ጦርነት/ ግጭት ባይኖርበትም መሠረታዊው የዜጎች ሰብአዊ መብት እስካልተጠበቀ ድረስ ‹‹ሰላም አለ›› ማለት አይቻልም፡፡ ለጊዜው ስሙን የማላስታውሰው አንድ የሰላም ተመራማሪ የሰብአዊ መብት እጅግ ሰፊ ሀሳብ መሆኑን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡፡ “አንድ ህፃን ገና እንደተወለደ በተመጣጠነ ምግብ እጦት ወይም በንጽህና ጉድለት ህይወቱ ቢቀጠፍ፤ ወይም ቆይቶ ለአቅመ-አዳም ከደረሰ በሁዋላ በፖለቲካ ተቃውሞ ወይም በጦርነት ህይወቱ ቢያልፍ፣ ሁሉም የሚያሳየው የዚያን ሀገር የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ደካማነት ነው”፡፡

ዛሬ ዛሬ እኛም ጦርነት በሌለበት ሀገር “ሰላም ነው?” ስንባባል ጥያቄያችን ኑሮአችንን ነው፡፡ የጠጣነውን ውሃ፣ ያልበላነውን ምንም ወይም የበላነውን እህል፤ ያዳመጥነውን ዜና፤ የፀደቀልንን ወይም የፀደቀብንን አዋጅ ከፍ ሲልም የደረሰብንን በደልና ያገኘነውን ፍትህ፣ የጠየቅነውን በሽተኛና የዋልንበትን ቀብር ጭምር ማለታችን ነው፡፡ የእለት ውሎ አዳራችንን ሳይሆን፣ የአኗኗር ዘይቤያችንን፡፡

አበሻ ተርቦም ለተራበ አንጀቱ ይላወሳል፡፡ ታርዞም የተራቆተ ገመናውን ያለብሳል፡፡ አብዛኛው ወገኔ ገና ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ ረሀብ ሲቦረቡረው ያደረ አንጀቱ ደልቶት እንዳደረ ሁሉ፣ “በሰላም ያሳደርከኝ ፈጣሪ በሰላም አውለኝ” ብሎ፣ ፈጣሪውንና አንጀቱን በጸሎት ደልሎ፣ ለአዋዋሉ ሰላምን ይማጸናል፡፡ ከባዶ መሶብ ታድሞ የጸለየለት ሰላም ግን የበሩን ደፍ አይሻገርም፡፡ መንገድ ሲወጣማ ሰላሙ ይለይላታል፤ አስፋልት ሊሻገር ቆሞ ጎርፍ ይረጭበታል፤ በሀብታም መኪና ተጭኖ፣ ከቀዬው ስንት ምእራፍ ርቆ የቀን ስራ ሲሰራ ውሎ፣ ከስራ በተረፈ ጉልበቱ ኳትኖ ጎጆው ሲመለስ ባለቤቱ በህይወቱ ኖሮት አይደለም አይቶት ስለማያውቀው ሰላም ትጠይቀዋለች፤ “ሰላም ነው?”፣ “ፈጣሪን አይክፋው፤ሰላም ነው?” ይላታል፤ የምታውቀውን ገመና ሽፍንፍን አድርጎ፡፡ ኧረ አይጣል ነን እኛስ! . . . ግን እስቲ እኛን እንተውና፣ እናንተ ግን እንዴት ነው ሰሞኑን “ሰላም ነው?”

**...የጠጣነውን ውሃ፣ ያልበላነውን ምንም ወይም የበላነውን እህል፤ ያዳመጥነውን ዜና፤ የፀደቀልንን ወይም የፀደቀብንን አዋጅ ከፍ ሲልም የደረሰብንን በደልና ያገኘነውን ፍትህ፣ የጠየቅነውን በሽተኛና የዋልንበትን ቀብር ጭምር ማለታችን ነው...**



# ፕ/ር መስፍን ቄሣራውያንና የቀንዱ አገዛዝ አሽከሮቻቸው መናጆን አጠንክረው የሞገቱበት

*ብርሃኑ ደቦጭ (የታሪክ ተመራማሪ)*

## በምክረ አሳባቸው ግን ድክም ያሉበት መጽሐፍ

*ፕ/ር መስፍን ከዚህ በፊት ከጻፏቸው መጻሕፍት ሦስቱ በሙሉም ሆነ በከፊል የአፍሪካ ቀንድ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ እነርሱም፤ ስለሶማሊያ የጻፏቸው ‹‹The Background to The Ethio-Somalian Boundary Dispute›› (እኤአ 1963 ዓ.ም)፣ ‹‹Somalia The Problem Child of Africa›› (እኤአ1978 ዓ.ም) እና ስለአጠቃላዩ የቀንዱ ችግር ያተቱበት ‹‹The Horn: Conflict and Poverty›› (እኤአ በ1999 ዓ.ም) ናቸው፡፡ ሦስቱም በእንግሊዝኛ የተጻፉ ሲሆን፤ በ2004ዓም ያቀረቡልንና ለዚህ አስተያየት መነሻ የሆነኝ ‹‹አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ›› ስለአፍሪካ ቀንድ (ከዚህ በኋላ ‹‹ቀንዱ››) በአማርኛ ያቀረቡት የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው፡፡*

ርዕስ፡- አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ
ጸሐፊ፡- መስፍን ወልደማርያም (ፕ/ር)
የታተመበት ዘመን፡- 2004
ገጽ፡- 237
ዋጋ፡-

### የአፍሪካ ቀንድ የጥናት ስበት

ፕ/ሩ በተለያዩ የጥናትና ምርምር ጉባዔዎች አቅርበው ያሳተሟቸውን ጥናቶች ሳያክል መጽሐፎቻቸውን ብቻ ብንመለከት፤ አምስት የሚደርሱ የአማርኛ መጻሕፍት ‹‹የክህደት ቁልቁለት››፣ ‹‹ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?››፣ ‹‹ኢትዮጵያዊነት ልማት በህብረት››፣ ‹‹አገቱኒ››፣ ‹‹ሥልጣን፣ ባህልና አገዛዝ፣ ፖለቲካና ምርጫ›› አላቸው፡፡ ስለኢትዮጵያ መልክአምድር ለማስተማሪያ የሚያገለግሉት ሁለት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከጻፏቸው ‹‹An Atlas of Ethiopia›› እና ‹‹An Introductory Geography of Ethiopia›› የተሰኙ መጽሐፍት በተጨማሪ ስለችጋር በከፍተኛ ምርምር ላይ ተመስርተው የጻፏቸው ‹‹Rural vulnerability to Famine in Ethiopia›› እና ‹‹Suffering Under God's Environment›› መጽሐፎችም የፕሮፌሰሩ ዓይነተኛ አካዳሚያዊ አስተዋጽኦ ናቸው፡፡ በቀንዱ ዙሪያ ከሠሯቸው ሥራዎች (ከላይ ጠቅሼያቸዋለሁ) ሁለቱ የቀንዱ አካባቢ አገሮችን የግጭት ዳራ የሚተነትኑና ሶማሊያ በቀንዱ/በአፍሪካ ያላትን ችግር የሚያሳዩ ሲሆኑ፤ ሦስተኛው በአጠቃላይ የቀንዱ አካባቢ ግጭትና ድህነት ላይ ያነጣጠረ መጽሐፍ ነው፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት ያቀረቡት አዲሱ መጽሐፍ ደግሞ በቀንዱ አካባቢ ስላንዣበበው አደጋ የቀንዱ አዋሳኝ በሆኑና በአካባቢው ጂኦፖለቲክስ ወሳኝ አካሎች የሆኑትን እንደ አረቡ አለም፣ እስራኤል፣ ቀይ ባህር፣ የሕንድ ውቅያኖስና የምዕራባውያኑን ሚና በመጨመር ሰፋ አድርጎ የሚተነትን ነው፡፡ ስለዚህ በሚዳስሰው ጉዳይና አንድምታው ስፋት ይህ መጽሐፍ የፕ/ሩ ሥራዎች የደርዝ ስፋት ማሳያ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ይህ አስተያየቴ ለ‹‹Suffering Under God's Environment›› ዓይነቱ ጥልቅ ሥራ ያለኝን አስተያየት የሚጣረስብኝ አይደለም፡፡ ጽሑፉ በአማርኛ መሆኑ ደግሞ ጥቅሙን እጅግ ከፍ ያደርገዋል፡፡

ስለቀንዱ አባል አገራት የሚደረጉ ጥናቶች እየተበራከቱ መምጣታቸውን ማስተዋል ይቻላል፡፡ ለዚህም ምክንያት ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው አንዱ በአካባቢው አገሮች መካከል የተካሄዱና/የሚካሄዱ ግጭቶች፣ ጦርነቶችና ድርቆች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያና በኤርትራ አማጺያን፤ እንዲሁም በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል የተካሄዱ ጦርነቶች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዝርዝራቸውን አስመልክቶም ተጠቃሾቹ በቀንዱ አገራት መካከል ስለተካሄዱ ጦርነቶች መንስኤና ዳራ፣ በመካከላቸው የተከናወኑ የሰላም ድርድሮችና በቀንዱ ዙሪያ ባሉ አገሮች የኮንፌዴሬሽን ምሥረታ ያሉ እድሎች፣ ተግዳሮቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ጥቂት ናሙናዎችን ለመውሰድ፤ ተስፋ ፅዮን መድኅኔ በአርታኢነት የሠሩበት ‹‹The Shrinking Deadlock›› (እኤአ 1992 ዓ.ም)፣ በኚሁ ጸሐፊ ‹‹Towards Confederation In The Horn Of Africa: Focus On Ethiopia And Eritrea›› በሚል ርዕስ (እኤአ 2007 ዓ.ም) የተጻፈውን መጽሐፍ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የኦነግ የቀድሞ ሊቀመንበር ሌንጮ ለታ በተከታታይ ያወጧቸው መጽሐፎችም አጠቃላይ ቀንዱን የሚመለከቱት ናቸው፡፡ አዲሱን አግኝቼ ለማንበብ ባልችልም፤ እኤአ በ2004 ዓ.ም ያወጡት ‹‹The Horn Of Africa As A Common Homeland: The State And Self-Determination In The Era Of Heightened Globalization›› የተሰኘው መጽሐፍ ቀንዱን በጠቅላላ የማየት ፍላጎት ሌላ ማሳያ ነው፡፡ ስለቀንዱ የሚጻፉ መጽሐፍት መብዛታቸው አንድም በየአገሩ የሚታየውን ችግር ለብቻ ነጥሎ ማየት በቂ አለመሆኑን የመገንዘብ ውጤት አድርገን ልንወስድ እንችላለን፡፡ ዓላማው መገንጠል ነው የሚባልለትና አሸባሪነት የተፈረጀው ኦነግ የቀድሞ አመራር ሌንጮ ለታ ሳይቀሩ ከላይ በጠቀስሁት መጽሐፋቸው የአካባቢውን ችግር ለመረዳት የቀንዱን አካባቢ በጥቅሉ መፈተሽ እንደሚገባ ያመለክታሉ፡፡ በተመሳሳይ ከድረገጽ እንደተመለከትሁት አዲሱ ‹‹Peace Keeping as State Building; Current Challenges for the Horn of Africa›› የተባለ መጽሐፋቸውም ስለቀንዱ ነው፡፡ ፕ/ር መስፍን ቀንዱ ላይ በስፋት ለመጻፍ ምክንያት የሆናቸውን በግልጽ ይሄ ነው ብለው አያስቀምጡም፡፡ ስለቀንዱ በእንግሊዝኛ በጻፉት መጽሐፋቸው መቅድም ላይ እንዳስቀመጡት የእሳቸው ትውልድ ስለአፍሪካና ቀንዱ አካባቢ የነበራቸው ህልም ተኖ መጥፋቱ ስለሆነ፤ የአካባቢውን ችግር በምልዓት ለመመልከት የመሻት ውጤት አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡

‹‹The Horn: Conflict and Poverty›› በመጀመሪያ ረቂቁ የተጻፈው እኤአ በ1987 ዓ.ም ቢሆንም ሌላኛውን መጽሐፋቸውን የማዘጋጀት ሥራ አዘግይቷቸው ቆይቶ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ የታተመው እኤአ በ1999 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ የዛሬው መጽሐፍ በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ከ13 ዓመታት በኋላ አዳዲስ ለውጦችን አገናዝቦ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ መሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ ርዕስ ‹‹አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ›› መሆኑ ቀንዱ እስካሁን የተጠቃበትን ችግር የዘነጋ እንዳያስመስለው ያሰጋል፡፡ ጸሐፊው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ቀድሞ በጻፉት መጽሐፋቸው እንደጠቀሱት ግጭትና ደህነት የአፍሪካ ቀንድ ባህሪ እስከመምሰል ደርሷል፡፡ አዲሱ መጽሐፍ ግን አደጋውን ገና የሚመጣ (ያንዣበበት ስለሚል) ወይም የሚጠበቅ ያስመስለዋል፡፡ ምናልባት አደጋው መባባሱና መጨረሻው ደረጃ መቼ ደርሶ ቀንዱ ፍጹም ይተራመሳል የሚል ካልሆነ አሁንም ጉዳቱ እየታየ ነው ሊባል ይችላል፡፡

### መጽሐፉ

‹‹አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ›› መደምደሚያውን ጨምሮ 11 ምዕራፎች አሉት፡፡ መፀሀፉ አፍሪካና የአፍሪካ ቀንድ አቀማመጥ በሁለት ምዕራፎች፣ ኢትዮጵያ (ስለውሃ ሀብቷና የቄሣራውያን ፍላጎትና አረቦች፣ እስራኤሎች፣ አፍሪካና አሜሪካ ግንኙነት) በሁለት ምዕራፎች፣ ሶማሊያ (ታሪካዊ ቅኝ ገዢዎቿ፣ አሜሪካ የገጠማትና ከኢትዮጵያ ጋር የገባችበት ጦርነትና የእርስ በእርስ ጦርነታቸው) በሁለት ምዕራፎች፣ የአፍሪካ ቀንድ ግጭት፣ ጦርነትና ችጋር በሁለት ምዕራፎች፣ ስለሽብርተኝነትና የአረብ አብዮት በሁለት ምዕራፎች አቅርቧል፡፡

ለዚህ አስተያየት እንዲመችም የመጽሐፉን ቀልብ ለማግኘት እንዲረዳም የመጽሐፉን ውስጠ ዝርዝር በሦስት ዋና ዋና ፍሬነገሮች አንጻር ማስተንተን ይቻላል፡፡ እነርሱም የአፍሪካ ቀንድ አገራት የውስጥ አስተዳደር፣ የአፍሪካ ቀንድ አገራት የውጭ ግንኙነት(ከቀንዱ አገራት ውጪ ካሉ አገሮች ጋር) እና የአፍሪካ ቀንድ አገራት አካባቢያዊ የእርስ በእርስ ግንኙነት ናቸው፡፡ በእነዚሁ ፍሬነገሮች ዙሪያ ሽብርተኝነት፣ የአረብ አብዮት፣ ግጭትና ችጋር ያላቸውን አንድምታ ስናሰላስል የመጽሐፉን ሙሉ ስዕል ለማግኘት እንችላለን፡፡

### የቀንዱ አባል አገራት ዝርዝር

በቀንዱ ሥር የሚመደቡት አገራት ብዛት ከጸሐፊ ጸሐፊዎች ይለያያሉ፡፡ ስለጉዳዩ ያነሱት ፕ/ር መስፍን ችግሩን ለማቃለልና ሥነ-ልክ ለማበጀት በእንግሊዝኛው መጽሐፋቸው የመከሩትን አሳብ እዚህም ያነሳሉ፡፡ በእርሳቸው አተያይ ከኢትዮጵያ ጋር የሚዋሰኑትን አገሮች የቀንዱ አካል አድርገው ይወስዷቸውና (ጂቡቲ፣ ኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ኬንያና ሱዳን) ከነርሱ መካከል ኬንያና ሱዳን ከቀንዱ ውጪ

ካሉ አገሮች ጋር ስለሚዋሰኑ የቀንዱ አካልነታቸው በከፊል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህ አቀራረብ አመክንዮአዊ መሆኑ በግልጽ ይታያል፡፡ ከላይ ስማቸውን ያነሳኋቸውና ሌሎችም ጸሐፊዎች ስለቀንዱ በጻፏቸው መጻሕፍት ዋና ትኩረት ያደረጉባቸው አገራት አሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የየጸሐፊዎቹ ምዘናና የጽሑፉ ዓላማ ነው፡፡ በቀንዱ ካላት ቦታ አንጻር ኢትዮጵያ የሁሉም ትንተና ማዕከል መሆኗ ይታያል፡፡ ለምሳሌ የቀድሞው ኦነግ ሊቀመንበር የሌንጮ መጽሐፍ (አዲሱን አይደለም) ከቀንዱ አገራት መርጦ በዝርዝር የሚያወራው ስለኢትዮጵያና ስለሱዳን ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ተጠቅሷል፡፡ በፕሮፌሰር መስፍን መጽሐፍ ለዝርዝር ማብራሪያ የተመረጡት ደግሞ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ናቸው፡፡ ጠንካራ መከራከሪያ ባይሆንም ኬንያና ሱዳን ከአፍሪካ ቀንድ ውጪ የሆኑ ጎረቤቶች ስላሏቸው የአፍሪካ ቀንድ አካልነታቸው ከፊል በመሆኑ ተዘለዋል ልንል እንችል ይሆናል (በግማሽ ገጽ ወይም በአንድ አንቀጽ የተነሱበትን አጋጣሚ ሽፋን ነው ካላልን በስተቀር)፡፡ በራሳቸው የቀደመ መጽሐፍ የቀንዱን አገራት ባህሪይ ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል የናይል ወንዝ አንዱ ነው (‹‹The Horn: Conflict and Poverty›› ገጽ 77)፡፡ እንደውም ናይል ለሁሉም ግብፆችና ለከፊል ሱዳን ሕይወት መሆኑን ጠቁመውናል፡፡ ታዲያ ስለቀንዱ በሚተነትነው መጽሐፍ አለማካተታቸው የግብጽን ጉዳይ ለጥንቃቄ ወይም ሌላ ባልተገለጸ ምክንያት ሆን ብለው ዘለውት ካልሆነ ትንተናው ላይ የሚኖረውን ክፍተት ማስፋቱ አይቀርም፡፡ የኤርትራና የሱዳን የውስጥ አስተዳደርና የውጪ ግንኙነት መርህም በቀንዱ ሁነት ላይ ያለው ተጽዕኖ ጉልህ መሆኑም ይታወቃል፡፡ ይህም የመዘለሉ ተገቢነቱ አይታይም፡፡ ሌላው ቀርቶ የኤርትራ ሁነት ከቀንዱ አገራት አንጻር እንዲያው በአለፍ አገደም መልኩ ከተነሳው በቀር በበቂ ሁኔታ አልተሸፈነም፡፡ ይህ ደግሞ መቼም ሕልውናዋን ካለመቀበል ጋር የተያያዘ አይሆንም፡፡

## የቀንዱ አገራት ችግሮችና መንስኤዎቻቸው ጥልፍልፎሽ የኢምፔሪያሊዝም ጣጣ?

መጽሐፉ አጠንክሮ ካነሳቸው የቀንዱ ችግሮች መንስኤ አንዱ አገዛዝ ነው፡፡ ጉዳዩ ራሱን በቻለ ልዩ ምዕራፍ የተብራራ ባይሆንም በየቦታው በተደጋጋሚ በማሠሪያ ሐረጎች የቀረቡት ቁምነገሮች የጉዳዩን አንኳርነት ያመለክታሉ፡፡ እንደ አደገኛ ሥልጣን መቆናጠጫ ሂደት፣ የሕዝቦች ነጻነት ማጣት፣ የጎሣ አስተዳደር፣ የሥልጣን ጥም፣ የሕዝብ ድጋፍ ማጣትና የመሳሰሉት ሁነቶች የውስጣዊ አስተዳደሩ ችግሮች መገለጫ ናቸው፡፡ በውስጣዊ አስተዳደር ከሌሎቹ የተሻለ ስም ያላት ያሏትን ኬንያን ካመሰገኑበት (ገጽ 75) ውጭ ሁሉም ተፈትነው የወደቁ እንደሆኑ ያስረግጣል፡፡

የቀንዱ አገራት የውጭ ግንኙነትም ሌላው መጽሐፉ የሚያተኩርበት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ፕ/ሩ የምዕራባውያን ኃያላን አገሮችን ቄሣራውያን ይሏቸዋል፡፡ ምናልባት የአገራቱን የኢምፔሪያሊስት መንፈስ ለመግለጽ ይመስላል፡፡ በዚህ መሰረት የአፍሪካ ቀንድ አቀማመጥ ቄሣራውያኑን የሳበው ወደመካከለኛው ምሥራቅ ለመፈናጠር አመቺ የሆነው የፖለቲካ ጂኦግራፊው ዕምቅ አቅም፣ የናይል ወንዝ፣ የቀይ ባሕርና ሕንድ ውቅያኖስ አካባቢውን ማዋሰናቸውን መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ጸሐፊውን የሚያስመሰግነው ትንተና እኒህ ቄሣራውያን የሚሏቸውን የዓለም ታላላቅ መንግሥታት ከአፍሪካ ባጠቃላይና ከአፍሪካ ቀንድ አገራት ጋር በተለይ ያላቸው ግንኙነት መግፍኤ አሳብ ፈትል የገመደ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መግፍኤ አሳብ መሰረትነት በቀንዱ አገራትና በቄሣራውያኑ የተሰናሰለው ግንኙነት የቀንዱን አገራት ሁል ጊዜ ክስረት ውስጥ የሚከት እንደሆነ ከገጽ ገጽ መመልከት ይቻላል፡፡ ከቀንዱ አገራት ሽፋን ከተሰጣቸው መካከል የኢትዮጵያን ብንመለከት የናይል ወንዝና የቀይ ባሕር ቄሣራውያንን የጠሩበት ሁነት፤ ኢትዮጵያ በአረቦችና በአፍሪካ፣ በአረቦችና በእሥራኤል፣ በአሜሪካና በእሥራኤል መካከል ያላት ግንኙነት ተብራርቷል፡፡ ግንኙነቱ ግን ሚዛን የሳተ፣ አገሪቱን ለሌሎች ጥቅም ጭዳ የሚያደርግና ጠላትን የሚያበዛ አካሄድ ብቻ ሳይሆን የቀንዱ አገራት ከቄሣራውያኑ ጋር ባላቸው ያልተመጣጠነ ግንኙነት በፈንታው የሚያገኙት ጥቅም ለውስጥ ‹‹ጸጥታ›› መጠበቂያና ሥልጣንን ማጠናከሪያ ከመሆን የዘለለ አይደለም፡፡ በዚህ ዓይነት የሚለኮሰው ግጭት ፍም ግን ቀንዱን የሚያተራምስ ሕዝቡንም ለስቃይ የሚዳርግ ይሆናል፡፡

ፕ/ር መስፍን ሽብርተኝነት፣ የአረብ አብዮት፣ ግጭትና ችጋር ከቀንዱ አገራት የውስጥ አስተዳደር፣ የውጭ ግንኙነትና የእርስ በእርስ ግንኙነት ጋር ያለውን ጥልፍልፎሽም በቅጡ ተመልክተውታል፡፡ የመጽሐፉ አዲስና ወቅታዊ አስተዋፅኦም እነዚህን ጉዳዮች (ስለሽብርተኛነትና የአረብ አብዮት) ማንሳቱ ነው፡፡ የፕሮፌሰሩ ግልጽ መልዕክትም የቀንዱ ችግሮችና መንስኤዎቻቸው የተጠላለፉ ስለመሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ የውስጥ አስተዳደርና የችጋር ግጥምጥሞሹን ለችጋር መንስኤው ከተፈጥሮ መዛባት ይልቅ የጭቆናና የአፈና አገዛዝ ውጤት እንደሆነ ያስረግጣሉ (ገጽ158)፡፡ ስለዚህ የገበሬው ነጻነት ከችጋር ነጻ ለመሆን ወሳኝ(ገጽ160) ነው ይሉናል፡፡ የቀንዱ አገራት ከቄሣራውያኑ ጋር ያላቸው ግንኙነት ለውስጥ አስተዳደሩ መበላሸት ያለውን አስተዋጽኦ ሲያትቱም፤ ቄሣራውያኑ የየአገሮቹን አገዛዞች በነሱ ስር ለማድረግ የሚቀላቸው በአንድ ሰው መዳፍ ስር ሲሆንና ሕዝቡንም ከነጻነት፣ ከዕኩልነትና ከሕጋዊ ሥርዓት ውጭ በጉልበት የሚገዙትን አምባገነኖች በመያዝ (162) እንደሆነ ይሞግታሉ፡፡ ልክ እንዲሁ ሽብርተኝነትም ድንገት ከምንም ነገር ዱብ የሚል ሳይሆን መሰረታዊ መንስኤና ጠባይ እንዳለው ይከራከራሉ፡፡ እንደ ፕ/ር መስፍን ሽብር በአመዛኙ ስሜታዊነት የሚጎላበት፣ ሰለባውም አቅጣጫ የሌለው (85) ሲሆን፤ ዋናው መንስኤውም ጭቆና ይሆናል (ገጽ 80)፡፡ የሽብር ጥንስሱ ደግሞ ምዕራባውያን ቄሣራዊ ኃይሎች ከየአገሩ አምባገነን ጨቋኞች ጋር በማበር ሕዝቡን ለብዝበዛና ለደሀነት፣ ለጭቆናና ለጥቃት መዳረጋቸው ነው(ገጽ82) ማለት ነው፡፡ የአረብ አብዮት በአፍሪካ ቀንድ ላይ ያለውን አንድምታ ‹‹በአረብ አገሮች ውስጥ አዲስ የኩራት መንፈስን የሚያነቃቃ ስሜት›› ስለመፍጠሩ በማተት፤(ገጽ 105) ሁነቱ እሥራኤልንና አሜሪካንን፣ ቱርክን ፍልስጤምን መንካቱ (106) የማይቀር ስለሚሆን አሜሪካ እግሯን ከመካከለኛው ምሥራቅ አንስታ በአፍሪካ ቀንድ የምታሳርፍበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ይሉናል፡፡ የቀደመ አስተያየታቸውን መሰረት አድርገን ስናስብ ይህም ሥልጣን ላይ ላለው አካል አትራፊ ቢመስልም ለቀንዱ አገራት ሕዝቦች የሚበጅ አይሆንም ማለት ነው፡፡





ፕ/ር መስፍን በግልጽ አይበሉት እንጂ የመጽሐፉ አንኳር መልዕክት የቀንዱ አገራት ችግር ቁልፍ ከቄሣራውያኑ ጋር ያላቸው ግንኙነት ነው ወደሚል መደምደሚያ ያደርሳል፡፡ የፕ/ሩ የትንተና አቅጣጫ ሲቀመር የሚሰጠን ውጤት ይሄን ይመስላል፡፡ ልባዊ ቅቡልነት የራቀው የቀንዱ አገራት አገዛዝ ሲደመር የቄሣራውያን አባሪነት እኩል ይሆናል ግጭት፣ ጦርነት፣ ሽብርተኝነትና ችጋር የሰፈነበት የአፍሪካ ቀንድ፡፡ ስለዚህ የትንተናው አቅጣጫ ከወጣላቸው ሶሺያሊስት ተንታኞች ጋር የሚያስመድበው ቢመስልም፤ ቀጥተኛና መደብ ፈላጊ ባለመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡ የኢምፔሪያሊስቶቹን / በፕ/ር አገላለጽ ቄሣራውያኑን/ አገራት የውጭ ግንኙነት ‹‹ሴይጣናዊ›› ባህሪ ግልጥልጥ አድርጎ ያሳያል፡፡ የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ልዩና ዋናው መገለጫው በተለይ ከመስከረሙ ጥቃት በኋላ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ስም የሚደረገው ወረራ/ዘመቻ/ጦርነት ነው፡፡ ፕ/ር መስፍን ካነሷቸው መሰረታዊ ጉዳች አንዱም ይሄው ነው፡፡ በእርግጥም በአገር ውስጥ በኢምፔሪያሊዝም ላይ ከቀረቡ የትችት ስነጽሑፎች የላቀ ያደርገዋል፡፡ ይህም ሆኖ በቀንዱ አገራት ዙሪያ ላንዣበበው አደጋ ከቄሣራውያኑና በቀንዱ አገራት ውስጥ ሥልጣን ላይ ካሉ ገዢዎች አስተዋፅኦ የሕዝቡ ባህልና አኗኗር አደጋውን አይቀሬ ለማድረግ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ተስኖታል፡፡

## የዋህነት የተጫነው የፕ/ር መስፍን ምክረ አሳብ

ፕ/ር መስፍን በመደምደሚያ አሳባቸው ለአፍሪካ ቀንድ አገራት ያቀረቧቸው ምክረ አሳቦች አሉ (ገጽ 169-173) ፡፡ ራሳቸው እንዳሉት ‹‹ከየዋህነት የመነጩ›› ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ችግሩ ግን እርሱ ብቻ አይደለም፡፡ ሲጀመር ፕ/ሩ ስለችግሩ ያቀረቡበትን ጥልቀት የሚመጥን ጥንካሬ ያለው ምክረ አሳብ ለማንሳት አልደፈሩም፡፡ ምክረ አሳቦቻቸውንም እንዲተገብሩ የሚጠበቁት ከላይ የችግሩ ምንጭ የሆኑት የውስጥ አገዛዞች ነው፡፡ ለቀንዱ አገራት ችግር በተለያዩ ምሑራን እንደመፍትሔ ከሚቀርቡ ምክረአሳቦች አንዱ የአፍሪካ ቀንድ አገራት ኮንፌዴሬሽን ነው፡፡ እንደውም ኮንፌዴሬሽኑን ለመመስረት ያሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ዕንቅፋቶችን ሁሉ ይዘረዝራሉ፡፡ አንዳንዶችም ኮንፌዴሬሽኑን እውን ለማድረግ ሊታለፉ የሚገባቸውን ደረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በእርግጥ አሁን በቀንዱ ያሉት መንግሥታት ይህን ለማድረግ ብቃቱም ፍላጎቱም የሌላቸው መሆኑ ከዕንቅፋቶቹ አንዱ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የፕ/ር መስፍን ምክረ አሳብ ይህን ታሳቢ ያላደረገበት ሁነት የአመንጪውን ‹‹የዋህነት›› ያጎላዋል፡፡ ለዚህ ነው የፕ/ር ምክረ አሳብ ድክም ያለ ሆነብኝ ልል የምገደደው፡፡ የቀንዱ አገራት መሪዎች ከሕዝቡ ልባዊ ቅቡልነት እንዲያገኙ፣ የቄሣራውያኑን ተፅዕኖ መቋቋም እንዲችሉ አገዛዞቹ በሕዝብ በተመረጡ መሪዎች መተካት አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ የአካባቢውን ዕውነት የተገነዘበ የራሱ ‹‹የአፍሪካ ቀንድ አብዮት›› ያስፈልግ ይሆን?

መቼም ፕ/ር መስፍን አሳብ ለማመንጨትም ሆነ በይፋ ለማውጣት የሚደክሙ እንዳልሆኑ ባቅሜ ለመመስከር ቅንጣት ጥርጥር ውስጥ አልገባም፡፡ ለዚህ ደግሞ ብዙ ሳይኬድ በዚሁ መጽሐፍ ያካተቱትንና በ29 ዓመታቸው በ1951ዓም ስለኦጋዴን ፖለቲካ ጂኦግራፊ የሰጡትን አሳብ ምስክርነት ማቅረብ ይቻላል፡፡ በአማርኛ በጻፏቸው በ‹‹ሥልጣን፣ ባህልና አገዛዝ ፖለቲካና ምርጫ››ና በ‹‹አገቱኒ›› እንዳደረጉት ከቆዩ ጽሑፎቻቸው ሁለቱን አካተዋል፡

ወደ ገፅ 30 ዞሯል



# ያልተመጣጠኑ ምጣኔዎች በኢትዮጵያ

በአቻምየለህ ታምሩ እውነቱ
(በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ መምህር)

እነሆ ዛሬ ለረጅም ጊዜ በማውቃትና በማደንቃት የፍትህ ጋዜጣ ለብዙ ጊዜ ትኩረት የተነሳውንና ሲያሳስበኝ የነበረን ጉዳይ ለውይይት ያነሳሳል በሚል ለመጀመሪያ ጊዜ ይገሮላችሁ ብቅ ብያለሁ፤ ከፍትህ ከአንባቢነት ወደ ተሳታፊነት መሸጋገሬ መሆኑ ነው። በቅድሚያ ስለ ፍትሆች የሚከተለውን ማለት እፈልጋለሁ። ከምድረ ገፅ እንደ ዳይኖሰር ልትጠፋብን የነበረችውን ፍትህ ጋዜጣ ክንፍ የተቸራቸው አዘጋጆቿ ከላይ ታች ወጥተውና ወርደው ዝንታለም ትነበብ ዘንድ ከመቃብር አፋፍ ታድገው ህይወት በመስጠት የሃገራችንን የዲሞክራሲ ግንባታ አንድ እርምጃ ወደፊት ለማስፈንጠርና የኢትዮጵያውያንን በተለይም የወጣቱን ንቃተ ህሊና ለማጎልበት ጠቃሚና አስተማሪ ፅሑፎችን በማቅረብ ከዜጋ ከሚጠበቅ በላይ እየከፈላችሁት ያለውን መስዋዕትነት በትውልድ ሁሉ ሲታወስ ይኖራል፡ ፡እንድንነጋገርና እንድንማማር በር ከፋች ብቸኛ መንገድም ናችሁ። ሰው በጠፋበት ዘመን ሰው የሆናችሁ። አ! ፍትሆች ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች!!

እኔም ብሆን በፍትህ የተማርሁትን በተለይም በዋና አዘጋጁ በአቶ ተመስገን ደሳለኝ ‹የመለስ አምልኮ› መፅሓፍ የተገፈፈልኝን ጨለማና ያየሁትን ብርሃን ልነግራችሁ ይህችን መጣጥፍ ቢጤ አዘጋጅቼ ብዙወቻችን ኢትዮጵያውያን በምንግባባባት የአማርኛ ቋንቋ ይገሮ ብቅ ብያለሁ። ወደ ተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ልመልሳችሁ፤ፍትሓዊ ያልሆኑ የሃገራችን ምጣኔዎችንና ንፅፅሮች በፍትህ ጋዜጣ ወደ መተንተን። ፅሑፌ ግርድፍ(Preliminary) በመሆኑ ጉዳይ አመላካችና ለውይይት በር ከፋች እንዲሁም ለምርምር ጠቋሚ እንጂ የመጨረሻና ገዥ አይደለም። የፅሑፌ አቀራረብ የተቃና እንዲሆንና ሃሳቤን በቀላሉ ለማስጨበጥ እንዲያመቸኝ ለዚህ ፅሑፍ መከራከሪያ የተጠቀምሁባቸውን ምጣኔዎችና ንፅፅሮች በመዘርዘር እጀምራለሁ።እነዚህ ምጣኔዎች መከራከሪያየን ለማስረዳት የተጠቀምኋቸው ብቻ ናቸው።ሌሎች ምጣኔዎችና ንፅፅሮችን አንስቶ መከራከር ይቻላል። የዚህ ፅሑፍ መከራከሪያ ምጣኔዎችና ንፅፅሮች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የደመወዝ ግብር ምጣኔ፣
2. የተጨማሪ እሴት ግብር(VAT) ምጣኔ፣
3. የባንክ የወለድ ምጣኔ፣
4. ከባለፈው አመት አፈፃፀም አኳያ የሁለት፣የሶስት ወዘተ... እጥፎች ስኬት፣ እመርታ፣ አፈፃፀም፣ ወዘተ... በዘንድሮው የበጀት አመት ተገኝቷል በሚል የሚቀርቡ የእድገት ስሌቶች የአቀራረብ ጉድለቶች በዚህ ፅሁፍ ይተነተናሉ።

ከአንድ እስከ ሶስት የዘረዘርኋቸው ምጣኔዎች በተለያየ ጊዜ በሃገራችን ከተፈጠሩ የኢኮኖሚ ክስተቶችና ሁነቶች (inflation, devaluation, adjustments and reforms) ጋር በተገቢው መጠን እየተሻሻሉ የመጡ አይደሉም።በእኔ ግምት በዚህ ወቅት የሚስተዋለውና የምንሰማው የማህበረሰባችን እሮሮ የዘረዘርኋቸው ምጣኔዎች ከየወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያለመጣጣምና ያለመከለስ ችግር ጭምር ነው ብየ አምናለሁ፡ ፡ በገምዳዬው በየተራ እያንዳንዱን እያነሳሁ ለማስረዳት ልሞክር።

የመጀመርያውን ምጣኔ እንውሰድ።በሃገራችን ያለውን የደመወዝ ግብር ምጣኔ ስናይ ከዛሬ አስርና አስራ አምስት አመት በፊት የተቀመረ ነው፤ እዚህ ግባ ከማይባሉ ሽግሽጎች በስተቀር፡ ፡ከዛሬ አስርና አስራ አምስት አመት በፊት ቀመሩ ሲበጅ ለምሳሌ ከ 5000 ብር በላይ የወር ደመወዝ የሚያገኝ ከፍተኛውን የደመወዝ ግብር ምጣኔ(35%) ይከፍላል ይላል። ሆኖም ከዛሬ አስርና አስራ አምስት አመት በፊት ይቅርና ከ 5 ዓመት በፊት የነበረው የ5000 ብር ዋጋ በዛሬ ገበያ ከ 15000 ብር በላይ ዋጋ ኖሮት እናገኘዋለን፡ ፡ስለዚህ በዛሬው ነባራዊ የሃገራችን ሁኔታ 35% የወር ደመወዝ ግብር ምጣኔ ተግባራዊ መሆን ያለበት ከ 15000 ብር በላይ የወር ደመወዝ በሚያገኙ ሰራተኞች ዘንድ ይሆናል ማለት ነው፡ ፡ነገር ግን መሬት ላይ ያለው እውነታ ይሄ አይደለም፤ እዚያው 5000 ብር የወር ደመወዝ ላይ ነው ተግባራዊ እየሆነ ያለው።ይህ ተገቢ ነው ብየ አላምንም፣ ዜጎችን ያለአግባብና ያለመጠን መበዝበዝ ነውና።ምክንያቱም የዛሬ አስርና አስራ አምስት አመት የ 5000 ብር የመግዛት አቅምና የዛሬው 5000 ብር የመግዛት አቅም የሰማይና የምድር ያህል ተለያይተዋልና። ለዚህም ነው ዛሬ በዋጋ ግሽበት አቅሙ በተዳከመ የወር ደመወዝ ላይ የተጣለው የግብር ምጣኔ ከዚህ በፊት ስንከፍለው ከነበረው አንፃር ሲወዳደር ከአቅማችን በላይ ነው ያልኩት። በተቀሩት የወር ደመወዝ ስኬሎች ላይ የተጣሉት የግብር ምጣኔዎችም ተመሳሳይ ጫናና ችግር የሚያስከትሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። ፍትሓዊነት ያለው የግብር አከፋፈል ለማስፈን ምን መደረግ አለበት? የሚከተሉትን እርምጃዎችን መውሰድ ይቻላል፤

1. የዛሬ 35% ከ 5000 ብር የወር ደመወዝ በላይ የሚያገኙ ሰራተኞች የሚከፍሉት የግብር ምጣኔ ከዛሬ 10 ና 15 ዓመት በፊት የዛሬ 5000 ብር ሊኖረው ከሚችል የመግዛት አቅም ጋር በማመጣጠን፣ ዛሬ ከ5000 ብር በላይ የወር ደመወዝ የሚያገኙ እየከፈሉት ያለው የግብር ምጣኔ ዝቅ እንዲል ማደረግና የተቀሩት የወር ደመወዝ ምጣኔዎችም በተመሳሳይ መንገድ ማስተካከል፤

2. በተመሳሳይ መንገድ ከዛሬ 10 ና 15 አመት በፊት የነበረው 5000 ብርና በላይ የደመወዝ መጠን በዛሬ ገበያ የመገዛት አቅም ተተርጉሞ 35% የደመወዝ ግብር ምጣኔ ስኬሉ በተሻሻለውና በተስተካከለው የደመወዝ መጠን ላይ ተግባራዊ ማድረግና የተቀሩት የወር ደመወዝ ምጣኔዎችም በተመሳሳይ መንገድ ማስተካከል ከእርምጃዎቹ መካከል ናቸው።እነኚህ እርምጃዎች ባጭር አገላለፅ፣ የግብር ምጣኔው ከዛሬ የደመወዝ የመግዛት አቅም ጋር መጣጣም አለበት የሚሉ ይሆናሉ።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርኋቸውን መፍትሔዎች በኢትዮጵያ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ አይከብድም ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፤ ተገቢም ነው፡ ፡ሆኖም ግን ላለፉት 8 ተከታታይ አመታት ሁለት ዲጂት(አሃዝ) እድገት ላስመዘገበ ሃገርና እየተከሰተ ያለውን የኑሮ ውድነት በዕድገት ምክንያት የመጣ ነው እየተባለ በሚነገርበት ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ተግዳሮቱ ያን ያህል አስቸጋሪ አይሆንም የሚል እምነት አለኝ።

ሁለተኛው ትንታኔየ የተጨማሪ እሴት ግብር የሚጣልባቸው ነጋዴዎችን መነሻ አመታዊ የገቢ መጠን የሚመለከት ነው። ምጣኔው ሲጀመር( በ 1997 ዓ.ም አከባቢ) አመታዊ ገቢያቸው ከ 500,000 ብር በላይ የሆኑ ነጋዴዎች ተጨማሪ እሴት ግብር (15%) ከተጠቃሚ በመሰብሰብ ለመንግስት ይከፍላሉ የሚል ነው። ሆኖም ከዛሬ 8 ዓመት በፊት የነበረው የ500,000 ብር ዋጋ በዛሬ ገበያ ከ ሁለት ሚልዮን ብር በላይ ሆኖ እናገኘዋለን፤ በግሽበቱ ምክንያት። ስለዚህ VAT መጣል ያለበት በዛሬ ገበያ አመታዊ ገቢያቸው ከ 2 ሚልዮን ብር በላይ አመታዊ ገቢ በሚያገኙ ነጋዴዎች መሆን አለበት።ዛሬ እየሆነ ያለውን ግን ይሄ አይደለም።እዚያው 500,000 ብር አመታዊ የሽያጭ ገቢ ላይ ነን። በ97 የተሰላው የቫት መነሻ መጠን ከዛሬው የዋጋ ግሽበት ጋር ተመጣጥኖ መነሻው ባለመስተካከሉ የተነሳ ዛሬ በየሰፈሩ የሚገኙ ሻይና ምግብ ቤቶች ሳይቀሩ የቫት ተመዝጋቢዎች ሆነዋል። ለዚህም ይመስለኛል ህዝቡ በቫት የተነሳ እያበደና እሮሮውን እያሰማ ያለው። የቫት መነሻ ምጣኔ ጊዜ ሳይሰጠው መስተካከሉ ለህዝቡ አልማዝ፣ ለመንግስት ደግሞ እንቁ የሆነ የድል አክሊል ለማግኘት መንገድ ከፋች እርምጃ እንደመራመድ ይቆጠራል የሚል እምነት አለኝ ። በተጨማሪም መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች በሙሉ ከቫት ነፃ መሆን ቢችሉ በልቶ ማደር የተሳነውን አብዛኛውን ድሃ አጥግቦ ባያሳድረው እንኳ ባያሌው ኑሮውን ይደጉመዋል።

ሶስተኛው መከራከሪያየ የባንክ ወልድ ምጣኔም ከላይ የቀረበውን ትንታኔ ትይዩ ማስተካከያ ያስፈልገዋል የሚል ነው። የባንክ የወለድ ምጣኔ ከዛሬው የገንዘብ የመግዛት አቅም ጋር መጣጣም አለበት። ባለመጣጣሙ የተነሳ በየጊዜው እያደገ ከመጣው የዋጋ ግሽበት ጋር ተዳምሮ ከባንክ ገንዘብ የተበደረ (ከአመታት በፊት የወሰደውን አይነትና ወለድ ሲመልስ) የመግዛት አቅሙ የተዳከመውን ገንዘብ በመክፈል ያላግባብ ተጠቃሚ ይሆናል። በተጨማሪም የወለድ ምጣኔው ከዋጋ ንረቱ ጋር በተገቢው መጠን ባለመጣጣሙ የተነሳ የገንዘብ ገበያውን(Financial Market)እንዲዛባ ከማድረግ

ወደ ገፅ 30 ዞሯል



## አቶ መለስ ተቋም ወይስ ግለሰብ?

# አብዮታዊ ዲሞክራሲ የልጅ ልጇቿን እየበላች ነው

አናኒያ ሶሪ

ባለፈው ሰሞን የአቶ መለስን በሕይወት መኖር/አለመኖር ተከትሎ የሚንሸራሸረው ፍላጐት-ተኮር ክርክር ከግለሰቡ አልፎ የብዙ ሚሊዮኖችን ህይወት የሚነካ በመሆኑ በዛሬው ጽሑፌ በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ለማተኮር ወደድሁ፡፡ ሰውዬው የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር እና የፓርቲው ቁንጮ ነበሩ፡፡ በዚያ ላይ ፓርቲውም ሆነ አገሪቱ የምትመራበትን መስመር አስማሪ እና ርዕዮተ-ዓለማዊ ጉዳዮችን ቀማሪ ናቸው፡፡ ‹‹አብዮታዊ-ዴሞክራሲም›› ሆነ ‹‹ልማታዊ-መንግሥት››፣ ‹‹ብሔር-መር ፌዴራሊዝም›› ሆነ ‹‹አንቀጽ-39›› አሊያም ‹‹ግብርና-መር የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ›› ወይም ‹‹የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ›› የርሳቸው ወጥ (ጠብቆ የሚነበብ) እና አዲስ ፈጠራ እንኳን ባይሆኑ አሻሽለው የፈበረኳቸው (Modifications) መገልገያዎች ናቸው፡፡ እርሳቸው ካሻሻሉት እና ከቀየሱት ውጥን ውጪ ግን ውልፊት የለም፡፡ እንደውም በአባላቶቹ ዘንድ በኢህአዴግኛ የሚባለው፡- 'አቅጣጫ ከላይ አልወረደም እንዴ?' ነው፡፡ አለበለዚያ ምኑን ከምኑ እንደሚያደርጉት መላው ጥፍት ይልባቸዋል- ዋ! በአንድ ጭንቅላት ማሰብ! አቅጣጫው የሙሴ ትዕዛዝ ይመስል በመለኮት ተነግሮ፣ በሙሴ ተላልፎ፣ በአሮን ተተርጉሞ ሲያበቃ ወደህዝቡ ይወርዳል፡፡ የኢህአዴግ 'ከላይ-ወደ-ታች' አመራር በአንድ ሰው ተቀምሮ፣ በጥቂት ዙሪያ ባሉ ታማኞች ተቆምሮ፣ በታችኛው ካድሬዎች አማካይነት ወደህዝቡ ተንቆርቁሮ በግድ እንድንጋተው ይደረጋል፡፡ ሌላው ሁሉ ('ህዝብ መከረበት'፣ 'ሰላማዊ -ሰልፍ ወጣበት'፣ 'የአቋም መግለጫ አስተላለፈበት' የሚሉት የኢቲቪ ቀረርቶዎች) ነገሩን ዴሞክራሲያዊ እና የህዝብ ተሳትፎ ያለበት ለማስመሰል የሚደረጉ ጉሮ-ወሸባዎች ብቻ ናቸው፡፡ አቤት…ለዚህ የይስሙላ ድራማ ስንት የሕዝብ አንጡራ ሀብት በአበል፣ በድግስ፣ በትርምስ፣ በዘፈን፣ በግርግር ባክኖ ቀረ!

ለማንኛውም እኚሁ የፓርቲውና የአገሪቱ ቁልፍ ሰው አሰላስለው እና ከብዙ መጻሕፍት መርምረው ካገኙት ብሎም ካበጁት ቀኖና ውጪ መሄድ በመናፍቅነት ወይም በአንጃነት አስፈርጆ የቁጣና የመርገምት መዓት ያወርዳል፡፡ በመሆኑም በዴሞክራሲያዊ-ማዕከላዊነት (Democratic-centralism) የኮምዩኒስት ፓርቲዎች መርህ መሠረት ከሰውዬው የፈለቀውን ሀሳብ እንደቁርባን ተቀብለው የድርሻቸውን ከበሉ በኋላ ለቀጣዩ የበታች ተከታይ እያስተላለፉ መላው አገሪቷን በዛው ሃሳብ ማጥለቅለቅ እና ማጥመቅ የስራው አንዱ አካል ነበር፡፡ ለዚህም ነው አቶ መለስ፡- 'ውሃ-ማቆር' ሲሉ 'ውሃ-ማቆር!'፣ 'ውሃ-ማቆር!'፣ 'ውሃ-ማቆር!'… 'ግብርና-መር' ሲሉ 'ግብርና-መር!'፣ 'ግብርና-መር!'፣ 'ግብርና-መር!'… 'ትራንስፎርሜሽን'፣ 'ህዳሴ'፣ 'ሚሊኒየም'፣ 'ኩብልስቶን'… ሲሉን የነበሩት አንድ ይናገራል፤ ብዙዎች ያስተጋባሉ! ለነገሩ በፊትም እንዲሁ ነበር አሉ… ‹ከጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት!› ወደፊት! ወደፊት!… ወደፊት!…

የአቶ መለስ መኖር ወይም አለመኖር ብዙ ጣጣ ይዞብን ሊመጣ ይችላል፡፡ ራሳቸው ኢህአዴጋውያን እንደሚያምኑት፡- በ'ኪራይ-ሰብሳቢው' ኃይል እና በ'ልማታዊው' ሃይል መካከል የሚደረገው 'እህል-አስጨራሽ' (እልህ-አስጨራሽ! ቢሉት ይቀላል) ትንቅንቅ በማን አሸናፊነት እንደሚጠናቀቅ ማወቅ፤ እርሳቸው ከሌሉበት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ እርሳቸው ሁሉን በብልሃት እያቻቻሉ ነበረና 'መንግሥታዊ-ሌባው'ስ ቢሆን በ'መንግሥታዊ-ፖሊሲ' ላይ መነሳቱ ይቀራል እንዴ? ይሰውረን ነው የሚባለው!

የድሮ ስርዓት ናፋቂ 'ነፍጠኞችም' አርፈው አይቀመጡም መቼም! ለለመዱት የትምክህተኝነት እና የበላይነት ፖለቲካ ማሰፍሰፋቸው አይቀርም፡፡ እንዴ… እሳቸው እያስተነፈሱና እያሳበጡ፣ አንዱን ቡድን በሌላው ላይ እያጫወቱ፣ ቀረብ ቀረብ ራቅ ራቅ እያደረጉ ባያቻችሉት ኖሮ አሁን ላይ 80 ምናምን የታጠቀ የአገሬ ብሔር ነፃ-አውጪ ነኝ ባይ ነጋዴዎች አይፈጠሩም ነበር ትላላችሁ? በዚህ የተነሳ 'አንድ አገር ብዙ ሃይማኖት!' ሆነን መኖር እንችል ነበር?! (ከነችግሩ ማለቴ ነው) ሰውዬው፡- መብት፣ ነፃነት እና ስልጣን እየቆነጠሩ በፊት ተበድሎና ተገፍቶ ለነበረው ቡድን በማንኪያ እያደሉ እና ራሱን እያሹ ከሰጡ በኋላ የበፊቱን ጨቋኝ ያሸመደምዱበታል፡፡ ከዚህ በኋላ ወደዚሁ መሳሪያቸው ፊታቸውን ያዞራሉ፡፡ በማንኪያ ያደሉትን በጭልፋ እየተቀበሉ ደም-እንባ ያስለቅሱታል፡፡ ያኔ እግራቸው ስር ወድቆ ጭራውን እንዳልቆላ በጊዜያቶች ልዩነት ዓይንምን-ላፈር እያለ በሩን ዘግቶ ያነባል፡፡አዎ-ጭቆናን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመተካት እንጂ ጨቋኝን እና የጭቁና ሰልትን በማቀያየር እውነተኛ ሰላም፣ ፍትህ፣ መልካም አስተዳደር አይገኝምና ሁሉም ቡድን በጊዜ ሂደት ሰለባ ይሆናል፡፡ 'አብዮት ልጆቿን ትበላለች!' አይደል ከነአባባሉስ! ለወዝ-አደሩና ለሠራተኛው መደብ ቆሜያለሁ! ሲል የነበረው የደርግ 'ስርዓትም' በሰው ከመነገድ አልፎ በባዩ ላይ ሰልጥኖበት ሲበዘብዘው ኖሯል፡፡ ሥርዓቱ (ስርዓት ከተባለ) በመሠረቱ አምባገነን 'እኔ አውቅልሃለው!' ባይ ነበረና በሰው ልጆች ተፈጥሯዊ የነፃነት፣ የመብት፣ የእኩልነት ጉዳዮች ላይ የተንሸዋረረ ግራ-ዘመም ርዕዮተ-ዓለም በመጫን በሰፊው ህዝብ ስም ሰፊ ሀብት እና ስልጣን ሲያግበሰብስ ኖሯል፡፡

አብዮታዊ-ዴሞክራሲም የልጅ ልጆቿን እየበላች ነው፡፡ አዎ-በትግራይ ህዝብ ስም፣ በገጠሩ አርሶ አደር ስም፣ በከተማ ድሃው ስም፣ በሴቶች ስም የማለና የተገዘተው ይህ 'ስርዓት' በብሔር-ብሔረሰቦች መብት ሽፋን የፖለቲካ ልሂቃኑን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጡንቻ እያፈረጠመ ለሎሌዎቹ ፍርፋሪ እየጣለ 'እኔ ያንተ!' እያስባለ ኖሯል፡፡ በዚህም የጡት አባትነት በህዝቡ ውስጥ እየረጩ ባሉት የማይጠቅም እና ጠንቀኛ አስተሳሰብ የተነሳ እስካሁን አደናግረውና አዳክመውን ቆይተዋል የዚህ ሁሉ ቀያሽ መሃንዲስ ደግሞ እኚሁ ሰው ነበሩ፡፡

ወታደራዊ-ሰልፍ ሲያሳምር የኖረው ስርዓት የብሔሮች-ጭፈራ ብቻ በሚያሸሞነሙን አስመሳይ-ስርዓት መተካቱ ለህዝቡ ተጨባጭ ኑሮ ምን ፈቀ አደረገለት? የህዝባችን ዋነኛ ችግርስ ባህላዊ ልብሱን መልበስ/አለመልበሱ ነው ወይስ እዚህም ለማድረግ ነፃ መሆን/አለመሆኑ?

በእስከዛሬው የ21 ዓመታት የገዢው ፓርቲ መንገድስ ሀገር እና ሕዝብ ተገነቡ ወይንስ ፓርቲና ጥቂት ቱባ ባለሥልጣናት? በዛሬዋ የኢህአዴግ ኢትዮጵያስ ተቋማዊ አሰራር ኖሮ እና ስር-ሰዶ ጉዳዮች በሕግና በስርዓት ይከወናሉ ወይንስ በግለሰባዊ የጥቅም ሰንሰለት ትስስሮች? የአብዮታዊ-ዴሞክራሲን ቀመር (Formula) የሚያውቁ አባላት ከአቶ መለስ ውጭስ አሉ? ድርጅቱ ሌሎች ጭንቅላቶች አሉት? በቅርቡ የህወሓት የመንፈስ-አባት የሚባሉት አቦይ ስብሐት ስለልማታዊ-መንግሥት ተጠይቀው ስለፅንሠ-ሀሳቡ ምንም እንደማያውቁ በልበ-ሙሉነት ተናግረዋል፡፡ አቶ ኃ/ማርያምስ?፣ አቶ በረከትስ? ጄኔራል ሳሞራስ? የደህንነት ኃላፊው አቶ ጌታቸውስ? አቶ ስዩምስ? አቶ ግርማ ብሩስ? አቶ ሬድዋንስ? የኛ ክ/ከተማ እና ቀበሌ አመራሮችስ? እነ እንትናስ?…

ግለሰቦች በመለኮት የተቀቡ እስኪመስሉ ድረስ በመላእክትነት በተጠጋ ክብር ሲንሳፈፉ እና ሲሞካሹ ኖረው የተከተለውን አስከፊ ውጤት ከአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘውዳዊ ስርዓት የተማርነው ነው፡፡ በአንፃሩም ሕዝባዊ (Populist) እና አገሪቷን ታዳጊ ተደርገው የተወሰዱት ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም በጀብደኝነት ታውረው ያመሰቃቀሏት አገር እንደ 'መሪ' ሳጠፉት ጥፋት ህያው ምስክር ናት፡፡ በአዋቂ-አንባቢነት የልሂቃን ቁንጮ መስለው የተሳሉት አቶ መለስም ከአንደበታቸው አልፎ በተግባራቸው ርቱዕ ሲሆኑ አልቻሉም፡፡ በመለኮትም ሆነ በጀብደኝነት አሊያም በአዋቂ አንባቢነት ስም ግለሰቦችን አጉነን ሰማይ ላይ ስንሰቅል ብንውል አገር በአንድ ሰው ጫንቃ ላይ አትመሰረትም፡፡ ይህ ከሆነ ግን፡- ባላነበበ ህዝብ ላይ ያነበበ ገገር፣ ነፍጥ ባላነገበ ህዝብ ላይ ነፍጥ ያነገበ ገገር፣ በማይናገር ህዝብ ላይ ነገር-አዋቂ መስሎ ለመኖር የብዙ ሚሊዮኖች ጭንቅላት ታስሮ እና ተለጉሞ መቆየት ነበረበት፡፡

በኛም አገር በዘመናችን የሆነው ይኸው ነው፡፡ መሪ ሲሄድ ሲመጣ የሚሊዮኖች ሕይወት ይታመሳል፡፡ 'ንጉሡ-ነገሥቱም፣ መሪውም፣ ህዝቡም እኛው ነን!' ነበር ያሉት አፄ ኃይለ-ሥላሴ?! ጠ/ሚኒስትሩም፣ ፓርቲውም፣ መንግሥቱም፣ ጭንቅላቱም እኔው ነኝ› በሚመስል ቅኝት ሲሰሩ የነበሩት አቶ መለስም ሲታመሙ ፓርቲውም፣ መንግሥቱም አገሩም ታመመ፡፡ ህልፈታቸው ይዞብን ሊመጣ ከሚችለው ደባ ለማምለጥ ግን ጊዜው አልረፈደም፡፡

ደግ ንጉሥ መጣ ክፉ ንጉስ መጣ
ሁሉም ይሄዳሉ እንዳመጣጣቸው…

ተቋማዊ አሰራር፣ መዋቅር፣ እና ባህል ባልመገንባቱ የተነሳም በብዙ አምባገነን አገራት ትልቅ ቀውስ ወይም አለመረጋጋት ተከስቷል፡፡ የሳዳም ኢራቅ፣ የቤን-አሊ ቱኒዚያ፣ የሙባረክ ግብፅ፣ የጋዳፊ ሊቢያ ለዚህ ጥሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ! እንዲል ብሒሉ ጭንቅላቱን ያጣው ኢህአዴግ ከንግዲህ በኋላ ጡንቻኛ እንጂ ጤነኛ ሆኖ ይኖራል ማለት ዘበት ነው፡፡ የኢህአዴግ ብቸኛ ሶፍትዌር (Software) ጠፍቶ ኮምፒውተሩ ይሰራል ማለትም የማይመስል ነገር ነው፡፡ የአምባገነኖች ችግርም ሁሉን ነገር ጠቅልለው መያዛቸው ብቻ ሳይሆን ሁሉን ነገር ጠቅልለው መሄዳቸውም ጭምር ነው፡፡

**ምስጢሩ**

የአኪለስ የጀግንነት ድምበር
ተረከዙ ነበር፤
የሳምሶን ኀያልነት ምስጢሩ
ጠጉሩ፡፡
ሁለቱም የወደቁት በአንድ አፍታ
ጥንካሬአቸው ሲመታ፡፡
እንግዲህ ታሪክ የሚለው
የሰው ድክመቱ ያለው
ብርታቱ ላይ ነው፡፡
ግንቦት 2002
(ዳዊት ፀጋዬ→ አርነት የወጡ ሐሳቦች)



# አማርኛ ካሳ እንዲከፍል አይገደድም

*ከአሰፋ እንደሻው (ዶ/ር)*
a_endeshaw@yahoo.co.uk

አማርኛ ላይ የባዕድ በተለይ የእንግሊዝኛ ተጽእኖ አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱን በመግለጽ ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ «ኑ በአማርዝኛ እንነጋገር» በሚል በሰኔ 29፣ 2004ዓ.ም የፍትህ እትም ላይ ያሰፈሩትን ተመልክቼ አንዳንድ ሀሳቦችን ለመሰንዘር ፈለግሁ። እያደር የተጽእኖው መዘዝ ጥልቅ እየሆነ፣ የመፍትሄ ማጣፊያውም እየራቀ መምጣቱ ከምን እንደመነጨ እኔም የበኩሌን ልወረውር አቀድሁ። የአማርኛን አወላለድና ዛሬ የሚገኝበትን አጣብቂኝ ካገሪቱ ህዝቦች አሰባጣጠርና ከአክሱም/ኢትዮጵያ አገዛዞ አወቃቀር ታሪክ ጋር አያይዤ ለመመርመር (ውጤቱንም በቅርቡ ለማሳተም) ስለቻልኩ ሁላችንንም የሚያገባን ወይም የሚያሳስበን ሊሆን ቢችልም፤ርእሰ ጉዳዩ እኔን በጣም የሚኮረኩረኝ ነው።

አማርኛ ምን ያህል በውጭ ቃላት፣ አባባሎችና ዘየዎ ስር እየወደቀ ለመሆኑ የሚጠራጠሩ ካሉ ሬዲዮና ቲቪ ከፍተው በመጀመሪያው አንድ ደቂቃ ውስጥ ማስረጃ ያገኛሉ። የችግሩን አይነትና መጠን ግን ለመለካት በቦሌ አካባቢ የተሰቀሉ ማስታወቂያዎችን መልቀም ሳያስፈልግ በየመንግስት መስሪያ ቤቱ፣ በየሻይ (ካፌ!) መሸጫው፣ በተማሪዎ አካባቢ፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ ተነጋጋሪው አጠገብ ካለፉ በእጅጉ መስፋፋቱን ይደርሱበታል። በውጭ ቃላት ያልነው ያለምክንያት አይደለም፡ ፡ ከእንግሊዝኛ ሌላ አረብኛም በተመሳሳይ መልክ አማርኛ ውስጥ እየሰረገ ነው። ዱሮ መጀመሪያ ፖርቱጋልኛ ቀጥሎም ፈረንሳይኛና ጣልያንኛ እየተፈራረቁ በመኳንንቱና ጭፍሮቻቸው መካከል መዝመት ችለው ቅሪቶቻቸው አሁንም በአማርኛ አሉ። የቋንቋዎ ርስበርስ መተሻሸትና መበዳደር የቆየ ጉዳይ ቢሆንም ከጣልያን ወረራ ወዲህ እንግሊዞችና አሜሪካኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ተሰሚነት አግኝተው አጼ ሃይለ ስላሴን በዘውዱ ላይ ካቆናጠጡ ወዲህ የትምህርቱን ስርአት ተረክበው እንደልባቸው የየራሳቸውን አስተሳሰብ፣ ዘየና ባህል በትምህርት ስም በወጣቱ ተማሪ መካከል ለመትከልና ለማስፋፋት ችለው ነበር። ያው ቅያስ እንደቀጠለ ቆይቶ፣ በተማሪው ህብረተሰብ ውስጥ መጀመሪያ በቁንጥ መልክ በኋላም ‹‹የየብሄረሰቡ ቋንቋዎ ስሜትን እንደ እንግሊዝኛ በሙሉ አይገልጹልንም›› በሚል ሰበብ አንደበታቸው በእንግሊዝኛ እየተሸረሸረ ሄደ። ያም ሆኖ ተማርን የሚሉት ባደባባይ ላይ በተለይ እንግሊዝኛ አያውቁም በሚባሉ ሰዎ ዘንድ ሲቀርቡ በአገርኛ ቋንቋዎ መናገሩን አልተውም ነበር። ዋናው ምክንያት ትዝብቱ፣ በፈረንጅ ቋንቋ የመናገር ሀፍረት ነበር። ደርግ ስልጣኑን እስከተቀማ ድረስ በሬዲዮና ቲቪ ሳይቀር በጣም ተባራሪ የሆኑ ቃላትና ዘየዎ ካልሆኑ በስተቀር ሙሉ በሙሉ የአደባባይ መነጋገሪያ ቋንቋዎ ያው የአገርኛዎ‡ ነበሩ። ማለትም አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ ወዘተ.

አዲስ ክስተት ሆኖ ከ20 አመት ወዲህ ብቅ ያለው የጉራማይሌ መረን መለቀቅ የኢህአዴግ/ህወሃት መንግስት አማርኛን ያለአባት፣ ያለተንከባካቢ ሜዳ ላይ አውጥቶ ዘርሮ በመጣሉ ነው። አማርኛ «የጭቆና መሳሪያ» ተደርጎ በመሳሉ፣ «የአማራው ጭቆና» ሲወገድ ልክ ደርግ/ኢሰፓ በአዋጅ እንደተኮነነ አማርኛም በይፋ መወገዝ ብቻ ነበር የቀረው። ሆኖም ግን የጉዱ ጉድ ከውግዘት ተርፎ «የመስሪያ ቋንቋ» ተብሎ ቀስ በቀስ በአጼዎቹ ዘመን የነበረውን ቦታ ተረከበ፣ ምንም እንኳን በወቅቱ አማራጭ ስላልነበር ‹‹ለጊዜው እንገልገልበት›› በሚል መልክ ቢመስልም። ቆየት ብሎ በእጅ ተቀጥቅጦ በደቡብ ህዝቦች ላይ የታውጆ ወዲያው የከሸፈው አዲሱ ቋንቋ እንዳመለከተው ለካስ ገዥዎ‡ ለጨቋኙ አማርኛ ተኪ ነጻ አውጭ ቋንቋ ይፈልጉለት ነበር! ማን ያውቃል ሌላም ቋንቋ ሊያነግሱ አስበው ይሆናል፣ ባደባባይ ባይነገርም።

ለሰሚው ግራ ቢመስልም የአማርኛ ቋንቋ ከመንግስት ጥላ ስር መውጣት ማለትም የገዥ መደብ ልሳን ከመሰኘት መዳኑ ከፍተኛ የምስራች መባል ያለበት ለውጥ ነው። አማርኛ ሲወለድ ከቶ በአፈ ታሪክ እንደሚዘከረውና በዘመናዊ ፈጠራ እንደሚታጀበው ካንድ ጎሳ አብራክ ወይም ከሴማዊ ቋንቋዎ ተወርሶ አይደለም። አማርኛ የዳማትና አክሱም አገዛዞ ከተለያዩ የህዝብ ክምችቶች እየመለመሉ በፈጠሩትና በአራቱም ማእዘን ባሰማሩት ዘማች ሰራዊት ውስጥ መግባቢያ ወይም መነጋገሪያ ሆኖ ያደገ ቅይጥ ቋንቋ ነው። በሰራዊቱ ውስጥ ሆነ አክሱም አካባቢ ብዛት የነበረውን የአገው ህዝብና ቋንቋ መሰረት አድርጎ ከሌሎች የህዝብ ስብስቦችና ቋንቋዎ እያጣቀሰ የተገነባ ቋንቋ ነው። የአገዎ ብቸኛ አገዛዝ (በተለምዶ የዛጉዌ መንግስት የሚባለው) ተቋቁሞ አማርኛ በአጼ ላሊበላ «ልሳነ መንግስት» ተብሎ ከመሰየሙ በፊት ከማናቸውም አገዛዞ ጋር ምንም ቁርኝት አልነበረውም። የአገው ነገስታትም ሆኑ ተተኪዎቹ አክሱማውያን (ሌላ ስማቸው «ሰለሞናዉያን» ነው) የዛሬው ወሎ ላይ ብሎም አንኮበር እና ወጅ (የዛሬው ወንጅ)፣ ከዚያም ቀጥሎ ቋራዎችና ላስቶች (ሁለቱም አገዎች ናቸው) እንዲሁም የየጁ ኦሮሞዎችና የትግራይ መሳፍንት (አጼ ዮሀንስ) መጨረሻም ፊንፊኔ ላይ የተቆናጠጠው የሳህለ ስላሴ ስርወ መንግስት ሁሉም አማርኛን ከመቀባበልና ከማጎልበት ባይመለሱ የአማርኛ ጎሳ ወይም ብሄረሰብ በማየሉ አልነበረም። የዚያ አይነት ጎሳ ወይም ብሄረሰብ በታሪካችን አልተወለደም፣ አልተፈጠረምና! ለምን? ይህ ሊሆን እንደቻለ በቦታ ጥበት ምክንያት ማስፈር ስለማንችል ዋናው ሃሳብ እንዳይዘነጋ ወደሱው እንመለስ። ከላሊበላ ወዲህ በኢትዮጵያ አገዛዝ ላይ የተፈናጠጡ ሁሉ «ዘራቸው» ወይም «ጎሳቸው» ምንም ሆነ ምን አማርኛን ተቀብለውና ባርከው መገልገያ አደረጉ እንጂ የየራሳቸውን የጎጥም ሆነ የብሄረሰብ ቋንቋ በአገዛዙ ላይ ለመጫን አልቻሉም። ፍላጎቱ ቢኖራቸውም ያገዛዙን አጠቃላይ ባህርይ ይዘው ማለትም የተለያዩና የተዘበራረቁ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጋር ስር የሰደደ ትስስር ተገንብቶ በመሰላልነትና ድልድይነት አማርኛ እያገለገለ ስለነበር እሱን ሽሮ ሌላ መተካት የማይሆን ስለመሰላቸው ከሺህ አመት በላይ አማርኛ ያለተፎካካሪ ተንሰራፍቷል።

የደርግ መንግስት (ያለማመንታት) ሆነ ተከታዩ (በዳተኝነት) አማርኛን የስራ ቋንቋ ሲያደርጉትና በህገ መንግስትም ላይ ሲያሰፍሩት ያንኑ ከዘመነ አገው አንስቶ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውን ትውፊት በመከተል ነው። አማራጭስ ምን ነበራቸውና? አማርኛ ከልሳነ መንግስትነቱ በፊት የአክሱም ሰራዊትና በሱ ዙሪያ የተደራጀው አገዛዝ መገናኛ ብቻ ሳይሆን የመገበያያ (የንግድ) ና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መስፋፊያ ቋንቋ በመሆኑ ብሄረሰብ ዘለል አገልግሎቱ አየጎላ ሄዷል። ይሁንና ይህ አድገቱ በነጻነት ተነስቶ (ተወልዶ) ማለትም ከማንም አንድ ጎሳ ወይም ህዝብ ጋር ሳይተሳሰር መሆኑ እየተረሳ ከአክሱም (ኢትዮጵያ) መንግስት መንሰራፋት ጋር እንደተቆራኘና ያለሱም ህልውና እንዳልነበረው እየታየ የመንግስቱን አስከፊ ገጽታዎችም በሱ ላይ ጭምር ለመላከክ አስቻለ።

በመሃሉ ውጥንቅጡ የአክሱም ሰራዊትና በስሜን፣ በአባይ አካባቢ፣ በ«ሸዋ»ና ሌሎች አካባቢዎች የተንሰራፋው አገዛዝ የፈጠራቸው የህዝብ ስብስቦች ከየራሳቸው የትውልድ (የናት) ቋንቋ በተጨማሪ አማርኛ ተናጋሪዎ እየሆኑ በመምጣታቸው ባንድ ህዝብነት እየተፈረጁ በተለይ ከ16ኛው መቶ አመት ወዲህ «አማራ» የመባል እጣ ወጣባቸው። በይበልጥ የአህመድ ኢብራሂም ዘመቻና የኦሮሞ እንቅስቃሴ በአክሱም (ኢትዮጵያ) አገዛዝ ላይ ካስከተሉት መተራመስ ድነው የበላይነት ያገኙት «አክሱማውያን» ራሳቸውን ከአማርኛ ቋንቋ ጋር እያስተሳሰሩ «አማራ» የ«አሸናፊነት» ገናናነትን ተቀዳጁ፡ ፡ ከሁለት ሺህ አመት ተኩል በላይ የቆየው የአክሱም/ኢትዮጵያ አገዛዝ በፈጠረው ምቹ ሁኔታ የተወለደውና የዳበረው መግባቢያ ብሎም መገበያያ ቋንቋ በዙሪያው «አሸናፊ» ህዝብ እንዳጀበው ተደርጎ ከተተበተበ በኋላ ይልቁንም ክርስትናም የአማራነት ተቀጥላ እንደሆነ ከተሳለ ወዲህ የተምታታና የተዘበራረቀ ታሪካዊ ምዕራፍ ውስጥ ተገባ። አማርኛ ከዘርና ከሃይማኖት ውጭ የፈለቀና ያደገ መሆኑ ተድበስብሶ የፖለቲካዊና ስነልቡናዊ ትንቅንቆች መፋለሚያ ሆነ። ተመሳሳይ አወላለድና አስተዳደግ ካላቸው ለምሳሌ ባካባቢያችን ብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን አገር ዘለል ከሆነው ከስዋሂሊ ጋር አስተያይቶ የትንቅንቁን ፋይዳቢስነት ማመልከት የሚችሉ ወገኖችም ጠፉ።

የዳማት ብሎም አክሱም/ኢትዮጵያ ትውፊት ለአገዛዙ አንድ አሸናፊ ቋንቋ ከየህዝብ ስብስቦች (ጎሳዎ ወይም ብሄረሰቦች) መካከል ስላልሰየመለት በአስደናቂ አኳኋን ከየቋንቋው ተወስዶና ተለውሶ ዳዬ ብሎ እየተንፏቀቀ ገናናነትን በመቀዳጀቱ ታሪክን መልሶ ለማጤንና የአማርኛን ይዞታ ለመመርመር ብቃት ያለው የምሁራን ክፍል ባለመኖሩም ይሆናል እስከዛሬ ድረስ አማርኛን መታገል እንደፖለቲካ አላማ ያነገቡ መኖራቸው የቀጠለው። ለማስታወስ ያህል በዱሮው የተማሪ

እንቅስቃሴ ውስጥ ሳይቀር በማናቸውም ስብሰባ ላይ በተሻለ ሁኔታ አቀላጥፈው የሚናገሩትን አማርኛን ትተው በእንግሊዝኛ መንተባተብን መምረጥ የዚህ ተምሳሌት ነበር፡፡

በምሁራን መካከል ከኖረው ደካማነት በተጨማሪ አማርኛ በጉራማይሌ እየተመታ ለመቆየቱ ብሎም ዛሬ እደረሰበት አስፋሪ ደረጃ ለመድረሱ ብዙ ሰበቦች ይጠቀሳሉ፡፡ ዱሮ ዱሮ ‹‹ለውጭ ቋንቋዎ‹ ተመሳሳይ ፍቺ በቋንቋችን የለንም›› በሚል ሰበብ መጀመሪያ ምናልባት ከፖርቱጋልኛ፣ ከፈረንሳይኛ፣ ቀጥሎም ከእንግሊዝኛ፣ ከጣልያንኛና ከአረብኛ እየቀነጨቡ የተማሩ የሚባሉት በንግግራቸው ውስጥ ይሰነቅሩ ነበር፡፡ ያ ሂደት በእጅጉ በተለያዩ መንገዶች ተገድቦ ኖሮ ዛሬ አምሳያ ቃል አይገኝለትም የሚሉት መከራከሪያ በሌለው ሁኔታ፱ የፈረንጅ ቃል መሰንቀር አንደዘየ ሆኖ ይሳቅለታል፣ ይጨበጨብለታል፡፡ ምስጋና ለማቅረብ «ቴንኪው» መባል እየተዘወተረ ነው፡ ፡ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን፣ የሬዲዮና የማስታወቂያ አውታሮች ያለማቅማማትና ያላንዳች ሀፍረት ድብልቅልቅ ያለውን የቋንቋ ስንክሳር ያስተላልፉሉ፡፡ «እሺ»፣ «ውሃ»፣ «አባባ»፣ «እማማ» የሚባሉት ተራ ቃሎች ሳይቀሩ በእንግሊዝኛ እየተተኩ ነው፡፡ አስገራሚው ይህንኑ አነጋገር አማርኛ እያሉ ባብዛኛው እንደሚጠሩት መታየቱ ነው፡፡ እላይ የተጠቀሱት ተንታኝ ሁኔታውን «አማርዝኛ» ማለታቸውም ተስተውሏል፡፡

ለጉራማይሌው መግነን ሌላው አቢይ ምክንያት ሄዶ ሄዶ ማንነትን መናቅና፣ መርገጥ እየተዘወተረ መምጣቱ ነው፡ ፡ በማያውቁትና በማይሰሙት ልሳን ተናግረው ተአምር የወረደላቸው አድርገው እንደሚቆጥሩት አንዳንድ ሰዎ‹፣ አዲሶቹ ተማርን ባዮች የተወለዱበትን ወይ ያደጉበትን ልሳን ከባዕድ ቋንቋ ግርጌ ካላነጠፉት የተናገሩ አይመስላቸውም፡፡ ተራ የዕለት ተዕለት መነጋገሪያ ምልልሶችን ለምሳሌ ምስጋና ለማቅረብ፣ ሰላምታ ለመስጠትና ለመቀበል፣ ስልክ ለመደዋወል፣ የመሄድና የመቀመጥ እንቅስቃሴዎችን ለመግለጽ ከራሳቸው ቋንቋ ይልቅ የባዕድን ያዘወትራሉ፣ ይመርጣሉም፡ ፡ ነገራ ነገሩ እንደመሰልጠን፣ ካገሬው ተወላጅ በተለይ ከገጠሬው በላይ ሆኖ ለመታየት እንደመሞከር ነው፡፡ የራስን ወግ፣ ባህልና ቋንቋ ቀስ በቀስ እየተው ሩቅ እንዳሉት እንደ ምዕራባውያን ወይም በቅርብ ሆነው የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል እንደሚወስውሱት አረብ አገሮች ለመናገር፣ ለመልበስና ባጠቃላይ ለመመሳሰል ነው፡ ፡ አስቂኙ አንድ አረፍተ ነገር በእንግሊዝኛ አሳክቶ መናገር የማይችለው ባለዲግሪ ሁሉ በዚህ ትርኢት መሰለፉ ነው፡፡ ለማንና ለምን አላማ እንደሚናገርም በግዴለሽነት በመዝለል በሬዲዮና በቲቪ ላይ የእንግሊዝኛ ቃላት መደረቱ ለተናጋሪው ብቻ ሳይሆን እንዲናገር መድረክ ለፈጠረለት አስተዛዛቢ ነው፡፡

በመጽሀፍና በጋዜጣ ውስጥ ሳይቀር የውጭ ጽሁፎች የሚጠቀሱት በእንግሊዝኛ ስያሜያቸው መሆኑ ምን ያህል መወናበድ እንዳለ ያሳያል፡፡ የቶልስቶይ መጽሀፍ በመጀመሪያ የታተመበት ቋንቋ ሩሲያኛ በመሆኑ እሱን መጥቀስ አስፈላጊነት (ወይም በቂ ምክንያት) ሲኖረው ያንን ማስፈር ሲገባ የእንግሊዝኛ ትርጓሜ ደርድሮ ያውም በአማርኛ በተዘጋጀ ጽሁፍ መሃል ማቅረብ አላማውም ተግባሩም ምንም ፍቺ የሌለው ነው፡፡ ሰውየው ያቀረቡትን ጽሁፍ ለመጥቀስ ከሆነ ያማርኛ ፍቺውን ይዞ ቢጻፍ አንባቢው ተሳስቶ ባማርኛ የተጻፈ የቶልስቶይ መጽሀፍ ገበያ ላይ እንዳያፈላልግ ተፈርቶ ነው? ካስፈለገ ባማርኛ ስነጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰ የውጭ ጽሁፍ መጀመሪያ በምን ቋንቋ እንደወጣ ማመልከት ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙ ጸሃፊዎ‹ ሳያስተውሉትና ሳያመዛዝኑት ይህን የተሳሳተ አሰራር የሙጥኝ ብለው በአማርኛ ሀተታ መሃል የውጭ ቋንቋ ስሞችና ዝርዝሮችን መደረቱ ተለምዷቸዋል፡፡ የውጭ ደራሲዎችን ስራዎ‹ ሲጠቅሱም የራሳቸውን ትርጓሜዎች በአማርኛ ብቻ ማቅረብ ሲችሉና ሲገባቸው የእንግሊዝኛ ፍቺ ከጎኑ ይደረድራሉ፡ ፡ የተቀዳው በእንግሊዝኛ ከታተመ ጽሁፍ ቢወጣም እንኳን የመጀመሪያው የጽሁፍ ቋንቋ እንግሊዝኛ ላልሆነ ቀርቶ ይህ አሰራር ወይ ተርጓሚው ከመጠን ያለፈ የትርጉሙን ትክክለኛነት፣ የእመኑኝ ልመና የተጠናወተው መሆኑን አሊያም በለሆሳስ የእንግሊዝኛ ችሎ□ውን በማስረጃ ለማጀብና የ‹‹መማሩን›› ፍንጭ አስታ¢ ለማወጅ የመፈለግ አይነት ነው፡፡ ከዚያ ውጭ እንግሊዝኛ ለሚያውቅ ሰው የሚጠቀሰውን መጽሀፍ ባያውቀው እንኳን ፈልጎ ለማግኘት አይሳነውምና ባማርኛው ሰነድ ውስጥ መደንጎሩ ዋጋቢስ ሀተታ ይሆናል፡:

አማርኛ በእንግሊዝኛ ስር መግባቱን ለማቆም መንግስት አዋጅ እንዲያወ× አይጠበቅበትም፡፡ ቋንቋዎ‹ በተለይ እንደአማርኛ ተዳቅሎ የተወለደና ያደገ መገበያያ ሆኖ የተንሰራፋ ቋንቋ አዋጅ አያሻውም፡፡ መንግስት ከህዝብ በሰበሰበው ገንዘብ በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፈውን ዜናና ውይይት ለህዝብ እንዳይደርስ ከመቶ ገና አንድ እንኳን ከማይደርሰው «የተማሪ ትውልድ» ውስጥ በጉራማይሌ ተተብትቦ እንዲቀር ማድረጉ አይበጀውም፡፡ በታቀደው የአምስት አመት የለውጥና መገለባበጥ ትልም ውስጥ የህዝቡ ማንነትና ሰብእ“ ቦታ የለውም;

አማርኛም ሆነ ሌሎች ቋንቋዎችም ለእድገታተ¨< የምሁራን መቆርቆርና እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ በብቃትም በጥራትም ምሁራን ለማፍራት ገና ብዙ የሚቀራት ብትሆንም ማንነትን ለመንከባከብና በጉራማይሌ ወረራ አስተሳሰብንና ባህልን ለመመረዝ ለተከፈተው የጥፋት ምዕራፍ መረባረብ አይሳናቸውም ባይ ነኝ፡፡ በተጨማሪም አማርኛ የዳበረ ስነ ጽሁፍ ይዞ ሳለ ገና ብዙ በሚቀራቸው ያካባቢ ቋንቋዎ‹ በጉራማይሌ ጫና ስር ወድቀው እንዲቀሩ ማድረግ ለየህዝባቸው የእድገት“ ህልውና በራቸውን መዝጋት ነው፡፡ እርግጥ ነው ማንም ህዝብ በሌላው ቋንቋና ስነ ጽሁፍ ላይ ተንጠላጥሎ ነው የራሱን ቋንቋና ስነ ጽሁፍ ለማዳበር የቻለው፡፡ አማርኛ ባንድ በኩል በስህተት በጠላትነት እየተፈረጀ በመምጣቱ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተማረው አካባቢ እንግሊዝኛን የመጠቀም አቅምም ስለተመናመነ የጉራማይሌን ወረራ ለመናድ መፍትሄዎቹ ባስቸኳይ ካልተበጁ ለለውጥ መሳሪያ የሆነውን የዳበረ የአለም ስነ ጽሁፍ ማጣጣም ቀርቶ ያገር ውስጥ ልምዶችና ወጎችን መቅሰም የሚችል ትውልድ ጨርሶ ይጠፋ ይሆናል፡፡

## ስለ መለስ....

(ከገፅ 8 የዞረ)

የራሱ የሆነ ጥበብን በመፈለጉ ሁለትም የሰው ህይወትን ለማጥፋት የሚደፍር ስነ-ልቦና በማስፈለጉ ምክንያት ተተኪዎቹ ሌላኛውን አማራጭ እንዲከተሉ ይገደዳሉ፡፡ አቶ መለስ በጉልበት ያረጓጓትን አገር ተተኪዎቹ በሰላማዊ መንገድ ማስቀጠል አይችሉም ለማለት ግን አይቻልም፡፡

የአቶ መለስን ህልፈት ተከትሎ እርሳቸው በገነቡት የስርዓቱ ሰዎችም ሆነ በምዕራባውያኑ ‹‹ወዳጆቻቸው›› በኩል ተደጋጋሚ የተነሳው የሰውዬው ውርስ ሀገሪቷን በተሻለ የኢኮኖሚ መሰረት ላይ አቁሚታል የሚል ነው፡ ፡ ደጋፊዎቻቸው ይህን ቢሉም ለዘብተኛ የስርዓታቸው ተከታታዮች እና ተቋማት አምጥተውታል የሚባለው የኢኮኖሚ ሽግግር ሌሎች ተፈጥሯዊ እና ህገ-መንግሥታዊ የሆኑትን የዜጎችን መብት በመጨፍለቅ የተከሰተ አድርገው ያቀርቡታል፡፡ ከዚህ በዘለለም ማህበራዊ ምስቅልቅሎሾችን እየፈጠረ የሚሄድ ስለመሆኑ ይናራሉ፡፡ ዘ ኢኮኖሚስት መፅሔት “If Meles goes to…” በሚል ርዕስ ባስነበበው መጣጥፍ የሚንቆለጳጳሰውን የሰውዬውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውርስ ‹‹አምባገነናዊ ልማት›› ሲል ጠርቶታል፡፡ ይህን ፅንሰ ሀሳብ በማፍታታት የሚታወቁት ፕ/ር መሀመድ ሳሊህ ‹‹መንግሥታዊ ጭቆና የአምባገነናዊ ልማት ቀዳሚ ውጤት ነው›› ሲሉ ይናገራሉ፡፡ ፕ/ር መሀመድ እነደሚያወሱት ይህን መንገድ የሚከተሉ መንግሥታት ቀዳሚ አጀንዳቸው አድርገው የሚስዱት ከዜጐቻቸው ይልቅ የሌሎችን (ዓለም አቀፍ የንግድ ተቋማት፣ ሌሎች መንግሥታት ወ.ዘ.ተ) ፍላጎት ማውጣት ሲሆን ይህን ለመከወንም ፖሊሲም ይጠቅማቸዋል ከሚባሉት ነዋሪዎ ፍላጎት ውጪ ዜጎች ከአካባቢያቸው በጉልበት ይፈናቀላሉ፡ ፡ ከላይ ወደ ታች በሚሄደው የዚህ የልማት ፖሊሲ ትግበራ የዜጐች መሰረታዊ መብቶች ይሠፈለቃሉ፤ ፖለቲካዊ አፈናውም ቅጥ ያጣ ይሆናል፡፡ ፕ/ሩ “African democracies and African politics” በሚለው ስራቸው እንደሚከራከሩት፤ የዚህ ፖሊሲ ሀገራዊ መዘዝ ብሄርተኝነትን ማባባሱ ነው፡፡ በልማት ስም የሚፈናቀሉና መብቶቻቸው የሚደፈጠጥባቸው ዜጐች የዘውግ ብሄርተኝነትን አንድ ዋነኛ መሰባሰቢያ ማዕቀፍ በማድረግ የስርዓቱን አፈና ለመግራት ይጠቀሙበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በአቶ መለስ ሞት ማግስት ጥናታዊ ዘገባውን ያወጣው ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ /IEG/ እንደሚያስነብበው ተገኘ የሚባለው ልማት ነዋሪዎችን በማንገላታት የተገኘ ነው፡፡ ተቋሙ “Ethiopia: After Meles” በሚለው ዘገባው፤ ለምግብ፣ አበባ እና ባዮፊዩል ምርቶች ሲባል የኢትዮጵያ መንግሥት ለአለም አቀፎቹ ተቋማት ሰፋፊ መሬቶችን ሲሰጥ በየአካባቢዎቹ የነበሩትን ነዋሪዎች በሃይል በማፈናቀል እና በማያምኑበትና ሀሳቦቻቸውን ባልተጠየቁበት የሰፈራ ፕሮግራም በማስፈር መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ግራሃም ፔብልስ የተባለው ፀሐፊ “Ethiopia’s opportunity bekons a new day.” ብሎ በሰየመው መጣጥፉ በበኩሉ፣ አቶ መለስ ለውጪ ካምፓኒዎቹ መሬት በማቅረብ ዶላር ለመሰብሰብ ሲሉ የሀገሪቱ አርብቶ አደሮች ይጠቀሙበት የነበሩት የግጦሽ መሬቶች ማጣት አልፎም የደን ውድመቶች መከሰታቸውን ይናገራል፡፡ ‹‹ኢትዮጵያን ለሁለት አስርታት በጠንካራ መዳፋቸው ስር ጨፍልቀው ገዝተዋል›› ሲል ሟቹን ‹‹ባለራዕይ›› መሪ የሚከሰው ኢንተር ፕሬስ ሰርቪ /IPS/ የተባለው በተቋም በሌላ ጫፍ በእርሳቸው አመራር ስር የተገኘውን ኢኮኖሚያዊ እድገት በቀዳሚነት የወሰዱት ጥቂቶቹ ከስርዓቱ ጋር ያበሩ ጥቅመኞች መሆናቸውን አልፎም ከኢንዶኔዢያ ቀጥሎ ኢትዮጵያ በዓመት 3 ቢሊዮን ዶላር በማግኘት ሁለተኛው እርዳታ ተቀባይ ሀገር መሆኗ የሚባለው ኢኮኖሚ ሽግግር አለመከወኑን ያወርሳል፡፡ ቴሆር ኻልቮርሰን እና አሌክስ ግላዲስተን የተባሉ አጥኚዎች ይህን የአቶ መለስን ሙከራ የፒንቾቴ-ቻይና ሞዴል ሲሉ ጠርተውታል፡፡ የመናገርና የመፃፍ መብቶች በተነፈጉበት፤ ለተቃውሞ የመሆኑ ዜጐች በአደባባይ በሚገደሉበት አገራዊ አውድ ላይ የሚገኝ የኢኮኖሚ ከፍታ በዚህ ስያሜ ሊበይን እንደሚገባ የጠቀሱት ፀሐፊዎቹ የአቶ መለስ የኢኮኖሚ ውርስም ይኸው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ይመስላል ፀሐፊዎቹ “Ethiopian tyrant should not be lionized” በሚለው መጣጥፋቸው “so, why is this monster being celebrated?” ሲሉ አምርረው መጠየቃቸው፡፡



# አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንዳንድ ከያኒ ስመስለው...

እንዳለ ጌታ

ሕዝባችንን በአንዳንድ ከያኒ ለመመሰል ከማንም ፍቃድ አልተቀበልኩም፤ ወይም ዕውቅና አልጠየቅኩም፤ ሆኖም ግን በተቻለ መጠን አንባቢው ‹እኔ የትኛውን ከያኒ እመስላለሁ ወይም የትኛውን ከያኒ መምሰል አለብኝ› ብሎ እራሱን ቢጠይቅ ከምርጫዎቹ መሀል፣ "መልስ አልተሰጠም" የሚል ላይ እንዳያተኩር ለመጠንቀቅ ሞክሬያለሁ፡፡

አንዳንድ ሰው ገና እንዳየነው ወይም እንደተዋወቅነው ከዚህ በፊት የምናውቀው እንደሚመስለን ሁሉ፤ የአንዳንድ ሰው ባህርይ ደግሞ ‹ቁርጥ እኔን! እኔም አንድ ሰሞን እንዲህ አድርጎኝ ነበር› የሚያስብል ነው፡፡ በተለይ ለሕዝብ ልብ ቅርብ ናቸው የሚባሉ የኪነት ሰዎች፤ ራሳቸውን እንዲገልፁ ጥያቄ በሚቀርብላቸው ጊዜ የሚሰጡዋቸው ምላሾች፤ ብዙዎቻችንን የሚወክሉ ሆነው አግኝቼያቸዋለሁ፡፡

እነዚህ የእኛን የሚመስል ባህርይ ያላቸው ከያንያን በአንድ ዘመን ለሙያቸው ሲሉ "ብዙ ዋጋ" የከፈሉ ለመሆናቸው ይመሰከርላቸዋል፤ ለተወዳጅነታቸውም ጥርጥር የለውም፤ ለስራቸው መሳካት ብለውም ብዙ "ሰማዕትነት" ተቀዳጅተዋል፤ እስከ መጪው ትውልድ የሚሻገር "ሀውልትም" በልባችን አንፀዋል፡፡ አሁን ግን፤ ዋናው ትኩረቴ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ውሎ የት አድሮ በከያኒ እንደተመሰለ ወፍ በረር ቅኝት ማድረግ ነው፡፡

ከያኒዎቹ ብዙ አይደሉም፤ አምስት ናቸው፤ ከአምስት ሶስቱ ድምፃውያን ናቸው፤ ነባር እና አዳዲስ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አየሩንም መንፈሱንም ተቆጣጥረው የገዙ፡፡ ድምፃውያኑም ይርጋ ዱባለ፣ ሰለሞን ተካልኝ እና ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ናቸው፡፡ ከአምስቱ ከያንያን ደግሞ ሁለቱ የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ናቸው፤ ወልደጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ እና ተመስገን ገብሬ፡፡

እነዚህ ሰዎች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያላቸውን ተለያይቶ እና ተገናኝቶ ለማስረዳት እሞክራለሁ- ልክ የአንድ ልቦለድ ገፀባሕርይ ከሌላው ጋር ያለው ቁርኝት ምን ያህል እንደሆነ ለማስረዳት እንደሚፍጨረጨር ተማሪ፡፡

## ሀ. ይርጋ ዱባለዎች

እንደምታውቁት ይርጋ ዱባለ ስመጥር የባህል ዘፈን ተጫዋች ነው፤ "እሱን አይቼና እሱን ሰምቼ ነው፤ ማሲንቆዬን ይዤ ወደ ዘፈን ዓለም የገባሁት" የሚሉ ድምፃውያን ጥቂት አይደሉም፡፡ ስለ ድምጹ አወጣጣቸው እና ግጥምን ከዜማ ጋር ስለማዋሃድ ችሎታቸው አሁን አልናገርም፤ በእኔ እውቀት የሚሰፈር አይደለም፤ እኔ መናገር የምችለው በአንድ ወቅት አንድ ነገር ደርሶባቸው፤ የደረሰባቸውን ነገር ለመቋቋም ሲሉ ስለዘየዱት መላ ነው፤ በመላቸው ውስጥ ራሳችንን ለማየት ይቻለን ዘንድ፡፡

እንደሚታወቀው በ1960ዎቹ አጋማሽ፤ አብዮት ፈንድቶ፤ ‹‹ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም›› የሚል መርህ ደርግ አውጥቶ፣ መርሁን ያወጣው ደርግ ብዙም ሳይቆይ " ያለምንም ደም" የሚሉትን ቃላት ሰርዞ፤ ኢትዮጵያን በደሙ አቀለማት፡፡ የማቅለሙንም ሥራ ሲጀምር፤ በቀደመው ዘመን ‹‹ቦታ›› የነበራቸውን የዘውዱ ሥርዓት ባለስልጣናት "አብዮታዊ እርምጃ" እንዲወሰድባቸው አዘዘ፡፡ በአንድ ቀን ውስጥ ከስልሳ ያላነሱ መኳንንት ‹‹አድሃርያን›› ተብለው የሞትን ፅዋ እንዲጨልጡ ተደረገ፡፡ በመሃከላቸው በአርበኝነት ተጋድሎአቸው የሚታወቁ፣ ለሀገሪቱ የኪነጥበብ ዕድገት የማዕዘን ራስ የሆኑ እና ኤርትራ ከእናት ሀገሯ እንድትዋሃድ ጥረት ያደረጉ ነበሩበት፡፡

በእነዚህ ሰዎች ላይ ሞት ተበይኖ፤ ስማቸው በሬዲዮ ሲነገር በአንድ ባሕላዊ ዘፈን ታጅቦ ነበር፤ "የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ፣ ልቡ ያበጠበት፣ እንዋጋ ብሎ ነብርን ላከበት፡፡ የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች፣ ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች" ይላል ሽለላው፤ ሽለላው ነባር ነው፤ ዘፋኙም የነበሩ ናቸው፤ ይርጋ ዱባለ ይሄ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ስሜት የሚቀሰቅሱ፣ ደምን የሚያሞቁ ዜማዎች አሉዋቸው፡፡

ደርግ፣ የእነዚያን ሰዎች ስም አንድ በአንድ እየጠራ ሽለላቸውን ማጀቢያ ሲያደርገው ምን እንደተሰማቸው "ቁም ነገር መጽሔት" ጠይቋቸው እንዲህ ብለው መልሰዋል፡፡

". . . ይገርምሃል እኮ . . .ጎንደር ፒያሳ አንድ ቡና ቤት ከጓደኞቼ ጋር ቁጭ ብዬ ዜናውን እና ፉከራዬን ተያይዘው ስሰማ ብድግ አልኩ፡፡ ጓደኞቼ ደግሞ "ወንድማችን፤ ተ. . . ው! እንኳን አንተ ሚኒስትሮችም ተገድለዋል፡፡ ስለዚህ አርፈህ ተቀመጥ! እንደውም ከተጠየቅህ ደስ እንዳለህ ንገራቸው! አሉኝ፡፡ እኔ ግን በእጃቸው በልቼ ያሳደጉኝ ባለውለታዎቼ በእኔ ሽለላ አጃቢነት ሞታቸው ሲበሰር እንዴት ዝም ልበል? አላስችል አለኝ፡፡ ግን ተረታሁ፤. ዝምታን በመምረጥ. . ."

አርቲስቱ ምንም እንኳን፣ ሸላሚዎቼ እና አጉራሾቼ ነበሩ የሚሉዋቸው ሰዎች በሽለላቸው ታጅበው ሞታቸው ቢበሰርም፤ በተከታታይ የደርግ አመታት፤ ከአብዮቱ ጎን ተሰልፈው፤ ድምፃቸውን ለፕሮፓጋንዳና ለልማታዊ ተልዕኮ ተጠቅመውበታልና ስለዚህም የሚሉት አላቸው፡፡

". . . . ትክክል! ደግሞም ደግ አደረግሁ! እንጀራዬ ነዋ! አንተ ደግሞ . . . ኢህአፓ ብሎ የፈጀው ምሁር ትላለህ፤ ገበሬ ሲያልቅ ውስጤ እየደማ እሸልል ነበር፡፡ እምቢ ብል የት አባቴ ልገባ! ብቻ . . . አስር ዓመት ያህል አብዮት አብዮት! ወደፊት እያልኩ . . . ሀገሩን ሁሉ አዳርሻለሁ፡፡ እንዲህ እንዲህ ሳደርግ ደርግ የእህቴን ልጆች ሳይቀር ሲፈጅ ተማርሬ፣

የአሳማ ገበሬ የዝንጀሮ ጎልጓይ
የጅብ ዘር አቀባይ፣
ሁሉም አንብላው ባይ የለውም ገላጋይ፣
ብዬ ዘፍኜ ወደ እስራኤል ተሰደድኩ. . ."

አርቲስት ይርጋ ዱባለ ከእስራኤል የተመለሱት፤ ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም ወደ ዙምባብዌ ፈረጠጠ በተባለ ማግስት ነው፡፡ በዚያን ሰሞን አንድ አጋጣሚ ተፈጠረና፤ "የፍየል ወጠጤ . . ." ብለው የሸለሉበት ድምጽ ሌላ ዜማ እንዲያስደምጥ ተጋበዘ፤ እናም እንዲህ ይተርኩታል ትዝታቸውን፡፡

"ዛሬ ጠላታችን የሆኑት የያኔው ኢሳያስ አፈወርቂ፤ የጊዜ ጉዳይ ሆኖ ከክብራቸው ወርደው ወህኒ ሳይገቡ ጠቅላይ ሚኒስትራችን የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔና የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትራችን በተገኙበት በብሔራዊ ቲያትር . . .

አንተ የኢሕአዴግ መንግስት
አንተ የሽግግር መንግስት
ከቶ ለምንድን ነው . . . ግብር የጠራኸኝ
ይበቃኝ የለም ወይ. . . ነፃ ያወጣኸኝ ብዬ ዘፈንኩ" ይላሉ፤ እኚህ አንጋፋ አርቲስት፤ ከዚህ ዘመን በኋላ ቤት እንደገዙ እና በሰላም እየኖሩ መሆናቸውን ለቃለ-መጠየቅ አቅራቢው አጫውተውታል፡፡


ይኸ ሁሉ፣ እሳቸው ያሉትን ለማስታወስ መሞከር፤ ማለት የምፈልገውን ነገር አጉልቶ ለማሳየት ይጠቅመኛል ብዬ ነው፡፡

. . . አንዳንዶቻችን እንዲህ ነን፤ ይርጋ ዱባለዎች፡፡ አንድ መንግስት ወድቆ በሌላ ስርዓት ሲተካ፤ የተቀደሰ ያልነው ሙያችንን ላልተገባ ነገር ተጠቅሞበት ያረክስብናል፤ ሀገርን ለወረረ ጠላት ማስደንበርያ ይሆን ዘንድ የሸለልነውን ዜማ፣ የገዛ ወንድምን ለማጥቃት እንደተዘፈነ በመቁጠር፤ ታሪካችንን አልባሌ ቦታ ላይ ጥሎ ስማችንን ያጎድፈዋል፤ ተባባሪው እንደሆንን እና ሙያችንን ብቻ ሳይሆን ልባችንንም ሰጥተን አብረነው የምንንቀሳቀስ ያስመስልብናል፡፡

ከገዳዩም ሆነ ከጉዳዩ ጋር አንዳችም ሕብረት እንደሌለን ለማሳየት አቅም የለንም፤ ተፍጨርጭረን ‹‹ዘራፍ›› ብንል እንኳን፤ ያለ እኔ ፍቃድ ድምጼ፣ ሙያዬ እና ስሜን አምኜ ላልተቀበልኩት ጉዳይ ተጠቀማችሁበት ብለን ክስ ለማቅረብ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግ ለማሳሰብ ብድግ ብንል እንኳን፤ የገዛ ወገኖቻችን አርፈን እንድንቀመጥ ይገስፁናል፤ ህይወታችንን ለማቆየት፣ ያልተሰማንን እንድንመስክር- ያልበላንን እንድናክክ፡፡

ገዳዮቹ እኛ ከእነዚያ ሰዎች ጋር ስላለን ቅርበት አይመረምሩም፤ ሞታቸው ስላጎደለብን ነገር አይጠይቁንም፡፡ ይህንን ደፍረን ለመናገር ደግሞ አልታደልንም፡፡ ቀና ብለን እንዳንሄድ

ወደ ገፅ 25 ዞሯል



*ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ*

# ይድረስ ለሕወሓት ድርጅት

ከጥቂት ወራት ወዲህ ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጤንነት የተምታቱና እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ዜናዎች የውይይት መድረኮችን አልብሰውት እንደነበረ ታውቃላችሁ። ከተጋጩት ግማሾቹ፥ እንዲያውም ሁሉም፥ ታማኝነት የሌላቸው መስለውኝ ሳለ፥ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለጊዜው በሥራቸው ላይ ሊገኙ አልቻሉም" የሚል መንግሥታዊ መግለጫ ወጥቶ አነበብኩ። ቀጥሎ በሕክምና ላይ እያሉ መሞታቸውን የሚገልፅ ከቤልጂግ የመጣ የራማ ድምፅ ተሰማ፤ እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ይማራቸው።

በዚህ በልጅነት እድሜያቸው መቀጠፋቸው ግን፥ ፈጣሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይመሩት የነበረው ወታደራዊ ድርጅት (ሕወሓት) ስለኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል አዲስ ፈር ለመትለም አርቆ ለማሰብ ሙሉ ነፃነትና ዕድል ሊሰጠው አስቦ ይሆናል። ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ድርጅቱና በውድም በግድም የሚደግፋቸው ሕዝብ በአንድ ወገን፥ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ ወገን፥ ሆነን በቃላት አሎሎ ተደባድበናል። የድርጅቱ ሠራዊት በመሪው ትእዛዝ የሌላውን ወገን መሪዎች አስሯል፤ የረታ ፍትሕ ነፍጓቸዋል፤ ብዙዎችን ለሞት አብቅቷል። በሁለቱ ወገን ያለው ፍጥጫ እስካሁን አንዲት ምናን ያህል አልረገበም። ጋዜጣ ባነበብኩ ቍጥር የማየው እነዚያው የቃላት አሎሎ ሲወናጨፉ ነው። ሕዝቡ ሃያ አንድ ዓመት ሙሉ ውስጣዊ ሰላም ተነፍጎ ነበር ማለት ነው። ከሓዲ ካልሆነ ለዚህ ማስረጃ የሚፈልግ ሰው አይኖርም። ይህን አላስፈላጊ ፍጥጫና ጥላቻ እስከመቸ እንከባክቦ ማኖር ይቻላል? ለምንስ ይጠቅማል? ያለነውኮ በመላው ዓለም ላይ የዲሞክራሲ ጮራ በፈነጠቀበት በሃያ አንደኛው ምእት ዓመት ነው። ጭቆና የሰብአትካት እንጂ የሥልጣኔ መሪዋ የኢትዮጵያ ልጆች ጠባይ ሊሆን አይገባም። ጭቆና ወንጀል ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወረደባቸው የቃላት አሎሎ ስላቈሰላቸው፥ ቂም ይዘው፥ እልሕ ገብተው ስለነበረ፥ ዕርቅ ለማውረድ ባያስቡበት ሊገርመን አይገባም። ያ ዕድል የዛሬ ሃያ አንድ ዓመት አዲስ አበባን የያዙ ዕለት አምልጧል። በዚያ ጊዜ ያልፈራቸውን ሕዝብ ስለፈሩት ፍጥጫ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማዘጋጀታቸው አይረሳም። የሽግግር መንግሥት ቻርተር እንጻፍ ብለው፥ በሕዝቡ ላይ የስድብ ውርጂብኝ የሚያዥጎደጉዱ ቂመኞች ለቀውበት እንደነበረ ታስታውሳላችሁ።

"አገዛዜን ሕዝብ ይደግፈዋል፤ ሕዝቡ እኔንም ይደግፈኛል" ይሉት የነበረው ከእውነት የራቀ መሆኑን እሳቸውም፥ እናንተም፥ እኛም፥ እንዲያውም መላው ዓለም ያውቀዋል፤ አቶ መለስ እንደ ሙሶሊኒ፥ እንደ ሂትለር እና እንደ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተወደዱም የተጠሉም መሪ ነበሩ። ታሪክም የሚያስታውሳቸው እንደዚሁ ከነዚህ ከመሰሎቻቸው ጋር ነው። ታሪካቸውን በዚህ መልክ ያስመዘገቡት ተገድደው ሳይሆን ወደውና ሌሎችን አስገድደው ነው። የሚያነቧቸው መጻሕፍት ሕዝብን እንዴት አፍኖ መግዛት እንደሚቻል የሚያስተምሩ እኩያን የሰፊ ሕዝብ ጠሮዎች የጻፏቸውን ነው። ታዲያ ሕዝብ ምን አይቶባቸው ይደግፋቸዋል? ኢትዮጵያንም ሆነ ሕዝቧን እና ምድሯን እየበደሉ እንዴት ይደግፋቸዋል?

አሁን ግን ህልፈተ ህይወታቸው ተሰምቷል፥ ያለፉት ለዕርቅ ደንቃራ የሆኑትን ቂማቸውንና እልሓቸውን ይዘው ነው። እሳቸው የያዙትን ይዘው ስለሄዱ፥ ብሔራዊ ዕርቅ ለማውረድ ድርጅታቸው ሊታለፍ የማይገባው ዕድል ተሰጥቶታል። የዕርቅ በር ከፍቶ ወደፊት በመገሥገሥ ፈንታ፥ ባለበት ረግቶ፥ ሌላ መለስ ዜናዊ እንዳይሰጠን ድርጅቱን አሳስባለሁ። ሐሳቡን ያቀረበውን ሰው ትታችሁ ሐሳቡን አስቡበት።

አንድ ጨቋኝ ሲያልፍ ግብረ አበሮቹ የተሻለ ዘመን እንደሚያመጡ የብዙ አገሮች ታሪክ አሳይቶናል። በሀገራችን ዕርቅ በፈቃድ የማምጫው ጊዜ አሁን ነው። በኃይል የተገለበጠና በፈቃዱ ዕርቅ ያመጣ ባለሥልጣን ዕድላቸው የተለያየ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይኸንን ለማየት የሕወሓት ሰዎች ሊያቅታችሁ አይገባም። ዕርቅ፥ ዲሞክራሲ እና ነፃነት ጥቅማቸው ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለገዢውም አካል ነው። እስቲ እንሞክራቸውና የሚሆነውን እንይ።

**...ኢትዮጵያ የሚቀርባት እንጂ የሚርቋት ሀገር መሆኗ ይቀራል። ሀገሪቱ ያስተማረቻቸው ልጆቿ በስደት ሌላ ሀገር ከማገልገልና ሀገራቸውን ከመናፈቅ ይድናሉ...**

የሚሆነውን ለመገመት ግን አያስቸግርም፤ ሰብአዊ መብት ከተከበረ፥ ላምና አንበሳ፥ አህያና ጅብ፥ ምጥማጥና ዶሮ፥ አብረው ይውላሉ፤ አብረው ያድራሉ። የጨቆኑና የተጨቆኑ ያለፈውን ረስተው ሳይፈራሩ በሀገር ልጅነት፥ በወንድማማችነት አብረው ያመሻሉ። ባላንጣዎች አብረው ይዘምታሉ። ሊቃውንቱ፥ ምሁራኑ፥ መምህራኑ ችሎታቸውን ለነፃነት ከመታገል ላይ ቀንሰው ድኽነትና ድንቁርና ከሚጠፉበት ላይ ያውላሉ፤ ልዩነቶች ከጉዳት ወደ ጥቅም የሚለወጡበትን ዘዴ ለመፈለግ የተረጋጋ መንፈስ ያገኛሉ። ኢትዮጵያ የሚቀርባት እንጂ የሚርቋት ሀገር መሆኗ ይቀራል። ሀገሪቱ ያስተማረቻቸው ልጆቿ በስደት ሌላ ሀገር ከማገልገልና ሀገራቸውን ከመናፈቅ ይድናሉ። በትምርት አንጻ ያሳደገቻቸው ልጆቿ ሌላ ሀገር እንዴት እንደሚያገለግሉና የተሰደዱበትን ሀገር እንደሚያዳብሩ በሰፊው ተነግሯል። ብዙዎች በምርምር ያገኙት ለእድገት የሚጠቅም ግኝት በስማቸው ተመዝግቦላቸዋል። አሁን በቅርቡ እንኳን የአሜሪካ ላዕላይ ፍርድ ቤት የፕሬዚዴንት ኦባማን የሕዝብ ጤና ጥበቃ እቅድ ደግፎ ሲፈርድ የኢኮኖሚ ጥቅሙን ያሳየው የዶክተር ብርሃኑ ዓለማየሁን ምርምር ጠቅሶ መሆኑ በፍርድቤቱ አፍ ተነግሯል።

በጎሳ፥ በቤት የከፋፈላችሁን የቤቶችን መብት ለማስከበር እንደሆነ ታምናላችሁ። ቤቶቹ ካላመኑበት የናንተ እምነት አዲስ ሃይማኖት እንደማስተማር ይቆጠራል። ጥቂት ጥቅመኞች ለይምሰል ያህል የተቀበሉ ቢመስሉ አትታለሉ። ሕዝቡ ለመቀበሉ ማስረጃ አይሆኑም። እንዲያውም፥ ልብ አላላችሁትም እንጂ፥ ልብ ብትሉት፥ በጎሳ በዘር መከለል ከመጣ፥ ሀገሪቷ ብቻ ሳትሆን፥ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ብዙ ክልሎች ይወጣዋል።

ሕወሓቶች አስቡበት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሄደዋል፤ ሲሄዱ ግን ፥ "ቂሜን፥ እልሔን አደራ" ብለዋችሁም እንደሆነ፥ እሳቸውን በሌሉበት ከመታዘዝ ከአገር ልጆች ጋር በሰላምና በጤና አብሮ መኖር ይብስብናል ብትሉ፥ ዓለም በጀግንነትና በአርቆ አስተዋይነት ይመዘግባችኋል እንጂ፥ ማንም በአደራ በላነት አያማችሁም። ዕድል አምልጧችሁ የሚተገትገን፥ የምንተገትገው ሌላ ተጠልቶ የሚያስጠላችሁ መሪ አታምጡብን። የብዙዎችን ጎባጣ መንገድ ያቀና የወንድሞቻችሁ የእኅቶቻችሁ አምላክ፥ የሰላም ጌታ ቀናውን ይምራችሁ።

*(ከአዘጋጁ፡-*
*ይህ ፅሁ ፍትህ ጋዜጣ በፍርድ ቤት ከታገደች በኋላ ባለው ሳምንታዊ ዕትም የተላከ በመሆኑ፣ ለዚህ የመጽሔት እትም ጥቂት የቃላት ማስተካከያ ተደርገውበታል።)*



# ሀይማኖትና ፖለቲካ

ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

በቀደመው አመት አጋማሽ በፊት በእስልምና ተከታዮች የተነሳው የመጅሊሱ አመራር ይውረድልን ጥያቄ እና ገዢው ፓርቲ ለጥያቄው እየሰጠው ያለው መልስ ሃይማኖትና ፖለቲካ ያላቸውን ተቋማዊ ግንኙነት ለማየት አንድ ገፊ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከተከታታዩቹ የሀገሪቱ የፖለቲካ ስርዓቶች አንፃር የሃይማኖትን ነፃነት በመፍቀድ ኢህአዴግ የተሻለ ቢሆንም፣ ለየሃይማኖቶቹ ተቋማዊ የነፃነት ጥያቄዎች የሰጠው ምላሽና ሰፊ ጣልቃ ገብነቱ ይህን ስርዓቱ ላይ የነበረውን በጎ ዕይታ አጨልሞታል፡፡ ከዚህ ጋር በተዛመደ ለህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ያሳዩት ለዘብተኝነት፤ በሀገሪቱ ውስጥ ስላሉት ዋነኞቹ ሦስት ሃይማኖቶች መስተጋብር ጥቂት ነገሮችን የሚያስብል ተጨባጭ ሁነት ሆኗል፡፡

## "ዘግይተን ብንደርስም"

የድህረ-ደርግ የሃይማኖቶች ነፃነት ፖለቲካዊ እወጃን ተከትሎ አማኞቹን በማስፋፋት ቀዳሚ ሆኖ የወጣው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣውን ቁጥራዊ ዘገባ ተንተርሰው ጆርግ ኸውስቲን እና ተርጄ ኦስቴቦ ‹‹የዚህ ሃይማኖት ብዙው ዕድገት የተገኘው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ዋጋ ነው›› ሲሉ ጠበቅ ያለድምዳሜያቸውን ያስነብባሉ፡፡ ዶ/ር ጆርግ ኸውስቲን "Writing Religious History: The Historiography of Ethiopian Pentecostalism" በሚለው ሌላ ስራቸው እንደሚያወሱት፤ የዚህን ሃይማኖት ዕድገት ያፈጠነውና የሃይማኖቱን ምልከታ በመግራት ተፅዕኖውን ያሰፋው ጴንጤ ኮስታል ተብሎ የሚጠራው መስመር /denomination/ ነው፡፡ ይህ የሃይማኖቱ መስመር በ1950ዎቹ አጋማሽ ወደ አደባባይ ቢመጣም በደርግ ስርዓትም ሆነ በቀደመው የአፄው ዘመን ወደ ጥግ ተገፍቶ ቆይቷል፡፡ ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ ከሌሎቹ የፕሮቴስታንት የእምነት መስመሮች በላቀ ሁኔታ ብዙ የአምልኮ ቦታዎችን በመገንባትና ሌሎቹን የእምነቱን ጫፎች በስነ-መለኮታዊ ትርጓሜው በማቀፍ ራሱን የበለጠ መግለፅ ችሏል፡፡ በደርግ ስርዓት ከደረሰበት ከባድ አፈና የተነሳ በኢህአዴግ ፖለቲካ ውስጥ ባለመሳተፉ ራሱን ለማግለል ቢሞክርም የመካነየሱስ ቤተክርስቲያን በበኩሏ በከፊልም ለዘብተኛ እንዳልነበረች አጥኚዎቹ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የፃፉት ኦይቪንድ ኤዲ "Revolution and religion in Ethiopia: Growth and persecution of the mekeneyesus church" በሚለው መፅሀፋቸው፤ ደርግን አጥብቆ በመውቀስ የሚታወቁትን ቄስ ጉዲና ቱምሳን ተከትለው ቤተክርስቲያኗን ያስተዳደሩት ፍራንሲስ ስቴፋኖስ በድጋሚ እንዳይመረጡ ኢህአዴግ የደርጉ ሽንጎ አባል እንደነበሩ በመጥቀስ መከላከሉን ዘግበዋል፡፡

ሃይማኖት እና መንግሥታዊ ስርዓት የተለያዩ እንደሆኑ መታወጁና የእምነት ነፃነት ከቀደሙት ስርዓቶች በተሻለ መንገድ በመፈቀዱ ለፕሮቴስታኒዝም እምነት መልካም ዘመኖችን ቢፈጥርም አልፎ አልፎ ግጭቶች እንዲስተናገዱም በር ከፍቷል፡፡ ዶ/ር ኸውስቲን ከላይ በተጠቀሰው ስራቸው ቤተክርስቲያኗ በደርግ ስርዓት የተወረሰባት ንብረቶች መመለሳቸውና ለቀብርና ለአምልኮ የሚሆኑ ቦታዎች በተለይም ሃይማኖቱ ከዚህ ቀደም ሊደርስባቸው በማይችልባቸው አካባቢዎች መፈቀድ በሌሎች የሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በበጎ እንዳልታየ ከጥቂት ዓመታት በፊት በባህር ዳር የታየውን ዓይነት ክስተት በመጥቀስ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች የፕሮቴስታንት እምነትን ወደ ህዝባዊ አደባባዮች መምጣት መቀበል እንደተቸገሩ ይናገራሉ፡፡ የተጠቀሱት ፀሐፊዎች እንደሚስማሙት የኢህአዴግ ስርዓት የሃይማኖቱ ተከታዮች ወደ መንግሥታዊ ተቋማት በብዛት እንዲቀላቀሉና ፖለቲካዊ ስልጣን እንዲያገኙ አስችሏል፡፡ ሁኔታዎቹ ይህን ቢመስሉም የገዢው ፓርቲ የብሄር ፖለቲካ በሌሎቹ የሀገሪቱ ሃይማኖቶች ላይ ተፅዕኖውን እንዳሳረፈው ሁሉ በዚህ ሃይማኖትም በተለይም በመካነየሱስ ቤተክርስቲያን ላይ እስከ መከፋፈል ያደረሱ ሁነቶችን ፈጥሯል፡፡ ሚሽኒያዊ ተልዕኮዋን ከምዕራብ ኢትዮጵያ የጀመረችው የመካነኢየሱስ ቤተክርስቲያን ለኦሮሞ ብሄርተኝነት ድጋፍ ስታደርግ ቆይታ ኦነግ ከሽግግር መንግሥቱ ሲወጣ በዝምታ ለመመልከት ብትገደድም የፓርቲውን የልማት ክንፍ ‹‹የኦሮሞ ሰብዓዊ ልማት ማህበር››ን የሚረዳውን ራሱን ‹‹የበርሊን ሚሽን›› ብሎ የሚጠራውን ስብስብ ለመርዳት እንደሞከረች ጆርግ ኸውስተን ይጠቅሳሉ፡፡ ገመቹ ኦላና የተባሉ አጥኚ በበኩላቸው ቤተ ክርስቲያኗ በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ የአምልኮት ቦታዎች በኦሮምኛ ቋንቋ ብቻ እንዲሰበክ ለማስገደድ መሞከሯ ከባድ አደጋ ውስጥ ጥሏት እንደነበር ይናገራሉ፡፡ ገመቹ "A church under challenge: The socio-economic and political involvement of the Ethiopian Evangelical church Mekeneyesus" በሚል ርዕስ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ በሰሩት ጥናት፣ በቀድሞው የቤተ ክርስቲያኗ መሪ ፍራንሲስ ስቲፋኖስ የተመራው፤ ቋንቋውን ለስብከት መጠቀም የለብንም የሚለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ብዙዎቹን የከተማዋን የእምነቱን ስብስቦች ከቤተ ክርስቲያኗ እንዲወጡ ከማድረግ በዘለለ፤ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት እንዲያመራ ቢያስገድድም፤ ተሟጋቾቹ በኢ-ወጋዊ መንገድ ከሁለት ዓመት በፊት ለመስማማት ሞክረዋል፡፡

## ካለኢህአዴግ ፍቃድ

እስልምና እንደ ፕሮቴስታንት እምነት አማኞቹን ይህን ያህል የመጨመር እድል ባያገኝም፣ የድህረ-ሰማኒያሶስቱ የሃይማኖት ነፃነት ፖለቲካዊ ማሻሻያ ከነበረበት መዋቅራዊና ህጋዊ ገደቦች በአንፃራዊነት ነፃ አውጥቶታል፡፡ የእስልምና አስተምህሮቶች ግድ የሚላቸው አለባበሶችና ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች በተሻለ መልኩ የአደባባይ ሁነት መሆናቸው ለዚህ ድምዳሜ እንደማሳያ ተደርገው ይጠቀሳሉ፡፡ በ1984 ዓ..ም በአዲስ አመራሮች የተነቃቃው የሙስሊሞች ጉዳይ የበላይ ተቋሙ (መጅሊስ)፣ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ማህበር እና የዕውቀትና የዳዕዋ ማህበሮች ለሃይማኖቱ መነቃቃት ከፍተኛ ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ፕ/ር ሁሴን አህመድ "Islamic literature and religious revival in Ethiopia (1991-1994)" በሚለው ጥናታዊ ጽሁፍቸው እንደሚናገሩት የመስኪዶች ግንባታ መስፋፋት፣ ከአረብኛ ወደ አማርኛ የተመለሱ የህትመት ውጤቶችን የሚያሳትሙ ተቋማት ቁጥር እየጨመረ መሄድ የ1980ዎቹ መጀመሪያ ተጠቃሽ ክስተቶች ናቸው፡፡ እንደ እነ ተርጄ ኦስቴቦ ሙግት ይህን መሰሉ የሃይማኖቱ መነቃቃት በኦርቶዶክስ አማኒያን በኩል በጥርጣሬ ቢታይም፣ ሼሪያ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ይካተት የሚለው ጥያቄና እሱን ተከትሎ ከወራት በኂላ በአንዋር መስኪድ አካባቢ የተከሰተው የአማኞቹና የስርዓቱ ግጭት ኢህአዴግ ሃይማኖቱን አስመልክቶ ያለውን ሽውራራ ዕይታ ያጋለጠ የመጀመሪያው ማሳያ ሆኗል፡፡ አስቴቦና ኸውስተን "EPRDF's revolutionary democracy and religious plurality: Islam and Christianity in post- Derg Ethiopia" በሚል ርዕስ ከወራት በፊት ባስነበቡት ፅሁፍ፣ ኢህአዴግ እየተነቃቁ የመጡትን የሙስሊም ተቋማት በመዝጋት መጅሊሱን ብቸኛው የሃይማኖቱ ተጠሪ ተቋም ማድረጉን ያነሳሉ፡፡ ይህን ለማድረግም ፓርቲው አክራሪ ፀረ-ሰለፊያ አቋም ያላቸውን አመራሮች የውጪ ጉይ ሚኒስትር ተወካዮች ባሉበት እንዲመረጡ አድርጓል፡፡ እንደ ፀሐፊዎቹ መከራከሪያ መጅሊሱ በዚህ መልኩ የስርዓቱ የሃይማኖት ክንፉ መሆኑ፣ ተቋማዊ ቅርፅ እየያዘ የመጣውን እስልምና እንደገና ወደ ነበረበት ኢ-ወጋዊ አደረጃጀት ገፍቶታል፡፡ በዚህም ስርዓቱ ከሚደግፋቸው ተቋማት ይልቅ መስኪዶች በሃይማኖቱ ጉዳይ ላይ ለሚደረጉ ክርክሮች ዋነኛ መድረኮች ሆነዋል፡፡

ገዢው ፓርቲ ይህ ፀረ-ሰለፊ አቋሙ በሱማሊያ ጣልቃገብነቱ ላይ እንደታየ በማንሳት ሀገራዊው አካሄዱ ከዚሁ ጋር ተያያዥነት እንዳለው ይናገራሉ፡፡ የእስልምና ምክር ቤቱ ሱማሊያን መቆጣጠሩ ያሰጋው ኢህአዴግ ሰራዊቱን በመላክ ‹‹አከርካሪውን ለመስበር›› ሞክሯል፡፡ በዚህ የሱማሊያ ቆይታው የሱፊ እስልምና አስተምህሮት የሚከተለውን ‹‹አሓልአል-ሱና ዋል ጃማኣ›› ተብሎ የሚጠራውን ቡድን በተለያዩ መንገዶች በመደገፍ ሊያጠናክረው ሞክሯል፡፡ ፓርቲው ለዚህ ውሳኔ ያቀረበው መከራከሪያ ‹‹ሱፊ ሀገር በቀልና ሰላማዊ ሲሆን ሰለፊ በበኩሉ በአክራሪ እስልምና የሚበየን መጤ አረዳድ ነው›› የሚል ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የዓለም ዓቀፍ ተቋማት ሪፖርቶች እንደሚያስነብቡት፤ የአሜሪካ መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ በሚያደርገው አሰሳ ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት አላቸው የሚላቸውን ተጠርጣሪዎች ለማሰቃየት ኢህአዴግ በቂ በሚስጥር የተያዙ ማጎሪያ ካምፖችን እንዳዘጋጀ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ

ለ ዘብተኛ ምሁራን በበኩላቸው የስርዓቱን አምባገነንነት በመጥቀስ፣ ለሃይማኖቶች የትኞቹም ጥያቄዎች እየሰጠ ያለው የአፈና መልስ ሁኔታዎችን ወደዚህ ሲገፋቸው እንደሚችል ያስጠነቅቃሉ…

ባለፈም የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ህዝባዊ ቁጥር በመንተራስ ተቋማዊ ጥያቄያቸውን በጽንፈኞች የተነሳ አድርጎ በማቅረብ ለአሜሪካ መንግሥት በተሻለ መልኩ ወዳጅነቱን ለማሳየት እየተጠቀመበት እንደሆነ ይከሰሳል። ከዚሁ ጋር በተገናኘ አንዳንድ ፀሐፊዎች ፓርቲው ለሃይማኖቱ ፈቅዶት የነበረውን ህዝባዊ አደባባይ መንፈግ በመጀመሩ አብዝተው ይወቅሱታል። ማርታ ቶርሲኒ ክሮዛ የተባሉ ፀሐፊ “State and religion in the constitution and politics of Ethiopia” ብለው በሰየሙት ፅሁፍ፤ ፓርቲው በዚህ ንፍገቱ ሕገ-መንግስታዊ ቅርቃር ውስጥ ገብቷል። ሕገ-መንግሥቱ ሃይማኖትን በነፃነት የመከተልን ነፃነት ሲሰጥ በሌላ ጫፍ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከሃይማኖታዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ መሆን አለባቸው የሚሉትን ዕሴቶች አጣሞ በመተርጎም ሂጃብና ኒቃብ በትምህርት ተቋማቱ ውስጥ እንዳይለበሱ አልፎም ሃይማኖታዊ ፀሎቶች እንዳይከወኑ መከላከሉ ኢ-ፍትሐዊ እንደሆነ ክሮዛ ይሟገታሉ። ከዚህ በተጨማሪ ገገሮው ፓርቲ በመጅሊሱ በኩል በሀገሪቱ ውስጥ የሚገነቡ መስኪዶችን የገንዘብ ምንጭና ውስጣዊ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በጥብቀት ለመቆጣጠር ብዙ መንገድ ሄዷል። ኸውስቲን እና ኦቴቦ የመሬት ስርዓቱን አስመልክቶ ያነሱት ነጥብ በብዙ ፀሐፊዎች ሲነሳ አይስተዋልም። በሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት መሰረት መሬት የመንግስት እንደሆነ መቀመጡ እና ሌሎች መሬትን የሚመለከቱ የሀገሪቱ ህጎች የቤተ አምልኮ፣ የመስኪድ አልያም የቀብር ቦታዎችን አስመልክቶ ስለቀደም ተከተላዊ አሰጣጥም ሆነ ተያያዥ ጉዮች በቅጡ አይናገሩም። ይህን መሰል ውሳኔዎም በየክልሉ ላሉ የአካባቢ መንግሥታዊ ተቋማት ተትተዋል። እንደ ፀሐፊዎች ክርክር ይህን ዓይነቱ የህግ ክፍተት በአንድ አካባቢ ያለ ብዙ ተከታዮች ያሉት ሃይማኖት ሌሎች የዕምነት መስመሮች ሊንቀሳቀሱበት የሚችሉበትን አውድ ያጠባል። በውጤቱም የአንድ የተወሰነ አካባቢን የአንድ ሃይማኖት የበላይነትን ያሰፍናል።

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ሲመጣ ነባሩን የሀገሪቱን መንግሥታዊ አመሰራረት በመናድ ብሄር ተኮር በሆኑ እሴቶች እንደገና ለመገንባቱ የሰጠው መከራከሪያ በዘመናዊት ኢትዮጵያ አመሰራረት ተጨቁነዋል ለሚላቸው ማኅበረሰባዊ ቡድኖች ጥያቄ ምላሽ ነው የሚል ከመሆኑ በመነሳት በዋናነት እስልምና ሃይማኖትንም ያየበት ምልከታ ከዚሁ ይነሳል። ፕ/ር ሁሴን አህመድም “Coexistence and/or confrontation; Towards a Reappraisal of Christian- muslim encounter in contemporary Ethiopia” በሚለው ጥናታዊ ስራቸው እንደ ብሄሮቹ ሁሉ ኢትዮጵያውያንን ሙስሊሞች አስመልክቶ ፓርቲው የያዘው አቋም ነፃ ላወጣችሁ መጥቻለሁ የሚል እንደነበር ያወሳሉ። ፓርቲው በዚህና በሌሎች አቋሞቹ የሃይማኖቱ ገበያ በነፃነት እንዲንቀሳቀስ ሲያደርግ፣ ለብዙ ዓመታት ፖለቲካዊ ስልጣኑን በከፍተኛ ሁኔታ ተቆጣጥራ የቆየችው የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ራሷን ወደ መከላከል እንድታዘነብል ተገፍታለች። የኢትዮጵያን ብሄራዊ መለዮና ወጥ ሀገራዊ ማንነት እንደቀረፁ የሚያምኑት የሃይማኖቱ መምህራን፤ ከዚህ በተፃራሪ የመጣውን የፓርቲውን ርዕዮተ-ዓለማዊ መከራከሪያ ለመሞገት ወደቀደሙት የሀገሪቱ ዘመናት ለመመልከት ተገደዋል። የፀሐፊዎቹን ሙግቶች የመረመሩት እነዶ/ር ኸውስተን እንደሚሉት፤ የሃይማኖቱ ሊቃውንት የእስልምናን መስፋፋት የኢትዮጵያን ብሉይ ብያኔ ከመከለስ ጋር ሲያዛምዱት፣ የፕሮቴስታንት እምነትን መጎልበት ከማኅበረሰቡ መፈራረስና የሞራል መውደቅ ጋር አስተሳስረውታል።

## የ‹‹ነጃሺ ትርክት››

የቤተ ክርስቲያኗን የኋላ ዘመን ትንተና የመረመሩ ፀሐፊዎች እንደሚያምኑት የሃይማኖቱ ተሚጋቾች ሙግት በተመረጡ የታሪክ ሁነቶች ላይ ከማተኮር በዘለለ አመክኖያዊ ባልሆኑ መላምቶች መበከሉን ያነሳሉ። የሀገሪቱ የታሪክ አፃፃፍ መንገድም የአንዳንድ የታሪክ መምህራን የኋላ ታሪክ ከሃይማኖቱ ጋር መተሳሰሩ ሚዛን የደፋ ተዋስኦ እንዳይኖር ያደረገ ይመስላል። በዚህ ጭብጥ ላይ የፃፉት ዶ/ር ደረጄ ፋይሳ ዶሪ እንደሚናገሩት በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ሃይማኖቶችን መስተጋብር አስመልክቶ የቤተ-ክርስቲያኗ ሙግት ሆኖ የወጣው ‹‹መቻቻል›› የሚለው አተናተን ሁለት ገፆች አሉት። ይህ መቻቻል በሃይማኖቶቹ ውስጥ ነበር የሚለው መከራከሪያ፤ በአንድ በኩል የሃይማኖቱን ሀገር በቀልነት ሲይዝ፤ በሌላ ገፅ የሌሎችን ሃይማኖቶች መጤነት ለማሳየት እንደሆነ ፀሐፊው ይከራከራሉ። በዘጠነኛው ክ/ዘመን በዮዲት፣ በ16ኛው በአህመድ ግራኝና በ17ኛው በካቶሊካውያኑ ከተሞከሩት ሃይማኖቱን የማለዘብ ሙከራዎች ውጪ፤ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ክብረ-ነገስትን መነሻ በማድረግ እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ የሀገሪቱ ብሄራዊ ሃይማኖት ሆኖ ቆይቷል። በነዚህ ረዥም አመታት ማህበረሰባዊ ህልውናን ያጠፉ ሃይማኖት-ተኮር ግጭቶች አለመካሄዳቸው መቻቻል ነበር ለሚለው መከራከሪያ ማስረገጫ ሆኖ ቀርቧል። በዚህ ጉዳይ ላይ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙ የእስልምና ፀሐፊዎች የሚያነሱት መከራከሪያ፤ የእስልምና ተከታዮች የሌላ ሃይማኖትን አምልኮታዊ ክንውኖች ለመተግበር ስለፈቀዱ/ስለተገደዱ መቻቻል ነበር ብሎ መሟገት አግባብ አይደለም የሚል ነው። አሁን በገበያ ላይ በሌለችው የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት ላይ የተጠቀሰው፣ በእስልምና ጭብጦች ላይ አይጠየቄ ሆኖ የወጣው ኡስታዝ ሐሰን ታጁ፤ የመቻቻል ብያኔ ለሌላው ሃይማኖት እውቅና መስጠትንና መከባበርን መያዝ ሲገባው ‹‹ከዚህ ውጪ ግን ሃይማኖታዊ ማንነትን አቅልጦ በሌላው ሃይማኖት መዋጥና እስልምና የሚከለክላቸውን ተግባራት መፈፀም መቻቻል›› ሊባል እንደማይገባ ይከራከራል።

ዶ/ር ደረጄ “Accommodation, tolerance or forbearance?Thepoliticsofrepresenting Ethiopia’s religious past” በሚለው ስራቸው በሁለቱ ግዙፍ ሃይማኖቶች መሀከል ካሉት አሚጋች የታሪክ አተረጓጎሞች አንዱን ያነሳሉ። ይኸ በተለምዶ የ‹‹ነጃሺ ትርክት›› ተብሎ የሚጠራው ሲሆን፣ ሁነቱን በተመለከተ የሁለቱንም ሃይማኖት ሊቃውንት የሚያስማማ ድምዳሜ የለም። ዶ/ር ደረጀ እንደሚጠቅሱት፣ የቤተ ክርስቲያኗ ፀሐፊዎች የነብዩ መሀመድን ወዳጆች የተቀበለው ንጉስ አርማህ ወደ ሙስሊምነት ስለመቀየሩ አንዳችም የታሪክ ማስረጃ የለም ብለው ሲያምኑ፤ ከዚህ በተፃራሪው እንደ እነ ሐሰን ታጁና አህመዲን ጀበል ያሉ የእስልምና ታሪክ ተራኪዎች፤ ንጉሱ ሲሞት በእስልምና ሃይማኖት መሰረት በርቀት ህይወቱ ላለፈ ሰው የሚደረገው ሃይማኖታዊ ክንውን በነብዩ መሀመድ አማካኝነት ተደርጎለታል ሲሉ ንጉስ ነጃሺ እንጂ አርማህን እንደማያውቁ ይሟገታሉ። ኤፍሬም እሸቴ ‹‹አክራሪ እስልምና በኢትዮጵያ›› ብሎ በሰየመው ስራው በንግሱ አርማህ ሃይማኖት ላይ የሚነሳው ጥያቄ ታሪካዊ አውዶችን ለእስልምና አክራሪነት ከማመቻቸት የዘለለ ፋይዳ እንደሌለው ያነሳል። ኢብራሂም ሙሉሸዋ ‹‹የታሪካችን ተራኪዎች›› በሚለው ፅሁፍ ትንሽ ገፍቶ በመሄድ፤ የነጃሺን ሙስሊምነት ለመቀበል አለመሞከር ብቸኛ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሃይማኖት ሆኖ ለመውጣት ማለምን ታሳቢ እንደሚያደርግ ፅፏል።

ሌላኛው የሃይማኖቱ ተሚጋቾች ጠርዝ ለጠርዝ የሚቆሙበት የታሪክ ጭብጥ ኢብን ኢብራሂም አህመድ አል.ጋዚን አስመልክቶ ያላቸው የአተናተን መስመር ነው። ሁለቱም ምልከታዎች በሰውዬው ቀስቃሽነት የተካሄደውን የአስራ አራት ዓመታት ትንቅንቅ የሃይማኖቶቹ ጦርነት አድርገው ያቀርቡታል። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የኦብነግ ሙከራ ነው። የክልሉን ፖለቲካ ያጠኑ እንደሚናገሩት፤ የኢትዮጵያ የምስራቁ ክፍል ነዋሪዎች ወደ ሀገሪቱ ዘመናዊ መንግሥት ስርዓት ዘግይቶ መቀላቀል ያመጣቸው የማህበር-ኢኮኖሚያዊና የባህላዊ ማንነቶች መገፋት የፖለቲካ ልሂቃኑን በእስልምና ማዕቀፍ ስር ብቻ የሚተረጎም ዘውጋዊ ማንነትን እንዲያራምዱ አስችሏቸዋል። ሜናሊን ሰይድ የተባሉ ፀሐፊ እንደሚጠቅሱትም የኦብነግ አመራሮች ይህን ፖለቲካዊ እስልምና የድጋፍ መሰባሰቢያ ለማድረግ ሞክረዋል። ፀሐፊው “The role of religion in the ofeden conflict” በሚለው ጽሁፋቸው እንደሚያወሱት፤ ፓርቲው የምዕራብ ሀገራትን ድጋፍ ለመሰብሰብ ራሱን ከሃይማኖታዊ ዕሴቶች የነፃ አድርጎ ለማቅረብ ለምክርም፤ ‹‹ግራኝ አልሞተም፣ ፈረሱ አልደከመም፣ ደርቡሾችም አልተሸነፉም›› የሚለውን መዝሙሩን በአደባባይ እስከማሰማት መሄዱን በመጥቀስ በተጠቀሰው ክርክር ውስጥ መሄዱን በመጥቀስ በተጠቀሰው ክርክር ውስጥ የብሄር ፖለቲካም እንዳለ ይናገራሉ። ዶ/ር አህመድ ሐሰን ኡመር፣ ‹‹A preliminary note on religious tolerance in Ethiopia; A Historical Review of Discourse about Islam›› በሚለው ስራቸው ይህ ዓይነቱ የሁለቱም ጫፎች ሙግት ከፀሐፊዎቹ የጎላ ማንነት ጋር እንደሚዛመድ በመጥቀስ፤ በሁለቱም በኩል ከሁለቱም ሃይማኖቶች የመጡ ሰዎች በጦርነቱ እንደተሳተፉ ይናገራሉ። ዶ/ር ውዱ ጣፈጠ በበኩላቸው የጦርነቱ ዋና ምክንያቶች የነበሩት የግዛት መስፋፋት፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ላይ መንግሥት የመመስረትና ንግድን የመቆጣጠር ፍላጎት መሆናቸውን ያነሳሉ። የታሪክ መምህሩ ‹‹የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ›› በሚለው ፅሁፋቸው፤ ‹‹በአህመድ ግራኝ ጐን ብዙ ክርስቲያኖች፣ እንዲያውም ቁልፍ የፖለቲካ አመራር ጨብጠው የነበሩት ታዋቂ የአካባቢ መሪዎች፣ በልብነድንግል ጐን ሙስሊሞች እንደነበሩ የማያውቁ›› ሲሉ ሁለቱንም ተሚጋቾች ይወቅሳሉ።

## አክራሪነት ያሰጋናል?

ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ ፀሐፊዎች እንደየምሁራዊ ዳርቻዎቻቸው የተጣረሱ መልሶችን ያስነብባሉ። ለክርስቲያን መምህራን ኢትዮጵያዊው እስልምና የሀገሪቱን ህልውና ወደሚያጠይቁ አዝማሚያዎች መሄዱ ዓመታትን ያስቆጠረ ሆኗል።በግልባጩ ለእስልምና ሊቃውንት ባለፉት ሃያ ዓመታት ሃይማኖቱ ካገኘው በህዝባዊ መድረኮች የመከወን አንፃራዊ ነፃነት አልፎም የእምነቱ ተከታዮች በተለያዩ የንግድና የትምህርት መስኮች ያዳበሯቸው ልማዶችና እውቀቶች ሀገሪቱ ከመጣችበት መንገድ በተሻለ በመንግሥታዊ ተቋማትም ሆነ ወሳኝ በሆኑ ማዕቀፎች ውስጥ የመወከል ጥያቄ ብቻ እንዳላቸው ይናገራሉ። ለዘብተኛ ምሁራን በበኩላቸው የስርዓቱን አምባገነንነት በመጥቀስ፣ ለሃይማኖቶች የትኞቹም ጥያቄዎች እየሰጠ ያለው የአፈና መልስ ሁኔታዎችን ወደዚህ ሊገፋቸው እንደሚችል ያስጠነቅቃሉ። ከነዚህ ዓይነት አጥኚዎች አንዱ የሆኑት ፕ/ር ጆን አቢቢኒክ ነገሩን ከዘውግ ብሄርተኝነት መክሰር ጋር ያያይዙታል። ‹‹የሙስሊሞች የማንነት ጥያቄ አሁንም ቢሆን አልተመለሰም›› የሚሉት አቢቢኒክ፣ አሁን በአደባባዩ በገዢነትም ሆነ በተቃውሞ በኩል ያሉት የፖለቲካ ልሂቃን ምልከታዎች ከክርስትና የተላቀቁ አይደሉም ሲሉ ይወቀሳሉ። ስለአክራሪነት ዝማሜ የሚፅፉ እንደሚናገሩት አክራሪነት አንድን እውነት ብቸኛ መለኮታዊ መገለጥ ያለው አድርጎ ከመረዳት ይነሳል። ነባራዊውን አውድ በክፉ መንፈሶች የተበከለና ከዚህ ብክለትም መፅዳት እንዳለበት ከማመን ባለፈ፣ ይህን ለማድረግ ማንኛውንም መንገድ መጠቀምን ትክክል አድርጎ ይቀበላል። አቢቢኒክ “An Historical-anthropological approach to Islam in Ethiopia: issues of identity and politics” በሚለው ስራቸው፤ የኢትዮጵያ የማህበረሰባዊ አደረጃጀትም ሆነ ባህላዊ የዕሴት አወቃቀር ለአክራሪነት የተመቹ እንዳልሆኑ ቢያምኑም፤ የብሄር ፖለቲካው በክስረት ከተደመደመ በረዥም ጊዜ ውስጥ ሃይማኖቶች የመሰባሰቢያ ማዕቀፍ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይህም የየትኞቹንም ሃይማኖቶች አክራሪነትን እንደሚያጎለብት አስጠንቅቀዋል።

## ከመለስ....

(ከገፅ 3 የዞረ)

ሆኖ የነበረውን የሀዘን ሰልፍንም እንዲሁ ከእነዚህ እንደ አንዱ ቆጥረን ህይወትንም ፖለቲካውንም ማስቀጠል መቻል አለብን። (ሆኖም ከሰልፉ እና ከሀዘኑ ከመውጣቴ በፊት አንድ ጥያቄ ላንሳ። ይኸውም የሀገር መሪ ሀዘኑን እንዴት ነው የሚገልፀው? መቼም በአደባባይ እንደጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በሁለት እጁ ጭንቅላቱን ይዞ እና እንደህፃን ልጅ ቀልቡን ስቶ ‹‹ኡኡኡ...›› እያለ በማልቀስ አይመስለኝም። ይህ አይነቱ ተለምዶአዊ አለቃቀስ የሚጠበቀው እናቱ ጥላው ከጠፋችበት ህፃን ብቻ ነው። አቶ መለስም ቢሆኑ ማንም ቢሞት እንዲህ አይነት ለቅሶ በቴሌቪዥን ካሜራ ፊት አያለቅሱም። ለማስረጃ ያህልም ከዚህ ቀደም በተገደሉት የደህንነት ሚንስትሩ ክንፈ ገ/መድህን ስርዓተ ቀብር ወቅት ሀዘናቸውን የገለፁት አንድ የሀገር መሪ ፕሮቶኮሉ በሚፈቅድለት መልኩ ተቆጥበው ነበር። ይህ ማለት ግን መለስ በክንፈ ሞት በሚገባ አላዘኑም ማለት አይደለም። በሚገባ አዝነዋልና። በሚገባ አላለቀሱም ማለት አይደለም፤ በሚገባ አልቅሰዋልና። ነገር ግን እንዲህ በአደባባይ አይደለም። የሀገር መሪ ሀዘኑ ምን ያህል የበረታ ቢሆን ከእነእንባው ወደአደባባይ አይወጣም። ምክንያቱም የሚመራው ህዝብ ሙሉ እምነቱን በቁርጠኛ አመራሩ ላይ ከመጣሉ አኳያ ለአንድ የስራ ባልደረባው እንዲህ ምርር ብሎ እየጮኸ በአደባባይ ሲያለቅስ ‹‹ተሸናፊ›› መስሎ ነው የሚታየው። እናም ኃይለማርያም ደሳለኝ ባደባባይ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ማልቀስ አልነበረባቸውም። ልክ አንድ ጄነራል በህዝብ ፊት እንደማያለቅሰው ሁሉ መሪም በአደባባይ አያለቅስም)

> **...መቼም ይህ ሁሉ ህዝብ ያዘነው በአቶ መለስ ማለፍ ለውጥም እንደሚኖር አስልቶ እንጂ እሳቸው በስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ‹‹ሀገሬን አሳድገውልኛል››፣ ‹‹ህይወቴን ቀይረውልኛል››፣ ‹‹መብቴን አክብረውልኛል...›› ብቻ ብሎ እንዳልሆነ እንኳን ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ብልሆቹ የህወሓት እና የብአዴን ሰዎችም በልባቸው ያምናሉ ብዬ አስባለሁ...**

### መግቢያ 2

ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ብዙ ማሻሻያዎችን የመጠበቃችንን ያህል የኢህአዴግ አጥር የማያካልለን ኢትዮጵያውያንም ሀገራዊ ግዴታዎቻችንን ለይተን ማወቅ እና መነጋገር አለብን ብዬ አስባለሁ። ይህ አይነቱ መነጋገር ከመቼውም በላይ አስፈላጊ የሆነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልክ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆንን እና የሀገራችን ፖለቲካ እንደማይመለከተን ሁሉ ከዳር ቆመን ‹‹ስብሃት ነጋ እና በረከት ስምኦን ግብግብ ገጥመዋል››፣ ‹‹ህወሓት በብአዴን እየተሸነፈ ነው››፣ ‹‹ሰራዊቱ እና ደህንነቱ ከህወሓት ጎን መሰለፉ አይቀርም››፣ ‹‹ጄነራል ሳሞራ የኑስ እያንገራገረ ነው››... ጁኒ ቁልቋል በሚሉ የፖለቲካ ዜናዎች ‹‹ቢዚ›› መሆንን የመጨረሻ ግዴታችን እያደረግነው ስለሆነ ነው። ይህ ግን አትራፊ አይደለም። ምክንያቱም የእነዚህ ፓርቲዎችም ሆነ የጉምቱ ባለስልጣናቱ ፉክክር በየትኛውም ወገን ውጤት ቢጠናቀቅ ከኢህአዴግ ውጭ ላለነው ዜጎች የሚፈይደው ነገር የለምና። ለእኛ የሚጠቅመን የፉክክሩ ቀጥተኛ ‹‹ተዋናይ›› መሆን ስንችል ብቻ ነው። አንድ ፓርቲ ብቻውን በሀገር ጉዳይ እና በመንግሥት ፖለቲካ ላይ የሚወስንበት ዘመን ከአቶ መለስ መጨረሻ ጋርም አብሮ መቆም ይኖርበታል። እናም ከኢህአዴግ እኩል በቀጣዩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ የመወሰን መብታችንን የማስከበር ትግል መጀመር እንዳለብንም ነጋሪ መጠበቅ አይኖርብንም።

በእርግጥ ይህንን እድል እነበረከት ስምኦንም ሆኑ እነ ስብሃት ነጋ ከአውሮፓ እና አሜሪካ ጠርተው፣ ወይም ከተጣድንበት የማህበራዊ ድረ-ገፆች አውርደው፤ አሊያም ከየመኝታችን ቀስቅሰው ይሰጡናል ብለን ካሰብን አንድም ኢህአዴግን በሚገባ አላወቅነውም፤ ሁለትም ፖለቲካ እና ተቃውሞን ነጣጥለን አልተረዳንም ማለት ነው።

የሆነ ሆኖ ከኃይለማሪያም መንግስት ቢያንስ በ2005 ዓ.ም በሚደረገው የአዲስ አበባ ምርጫ መሰረታዊ የፖለቲካ ማሻሻያዎች ይደረጋሉ ተብሎ መጠበቁ አይቀርም። ምክንያቱም ኢህአዴግ ከምስረታው ጀምሮ በአንድ ሰው መሪነት ብቻ ይተዳደር ከነበረበት ሁኔታ ተላቋልና። ስለዚህም ቢያንስ የከተማችን ምርጫ ከመደረጉ በፊት አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር አሁን ያለውን የምርጫ ቦርድ ማፍረስና ተአማኒነት ባላቸው ገለልተኛ ባለሙያዎች መልሶ ማዋቀር፣ የመንግስት ሚዲያዎች ለተቃዋሚዎችም ለገዥው ፓርቲም እኩል የሚያገለግሉበትን መመሪያ አዘጋጅቶ መተግበር፣ የሰራዊቱን እና የደህንነት ሀይሉን በመለስ ዘመን እንደነበረው በህልዮት ሳይሆን በገቢር ታዛገርነቱን ለህገ-መንግስቱ ብቻ እንዲሆን ማድረግ፣ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ... ከአዲስ አበባ ምርጫ በፊት ማመቻቸት የግዴታ ውዴታቸው ይመስለኛል።

መቼም ይህ ሁሉ ህዝብ ያዘነው በአቶ መለስ ማለፍ ለውጥም እንደሚኖር አስልቶ እንጂ እሳቸው በስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ‹‹ሀገሬን አሳድገውልኛል››፣ ‹‹ህይወቴን ቀይረውልኛል››፣ ‹‹መብቴን አክብረውልኛል...›› ብቻ ብሎ እንዳልሆነ እንኳን ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ብልሆቹ የህወሓት እና የብአዴን ሰዎችም በልባቸው ያምናሉ ብዬ አስባለሁ። (በነገራችን ላይ ‹‹ነባር ታጋዮች›› (Old Comrades) በትግሉ ወቅት ያልነበሩትን እና ባህላዊውን የሴራ ፖለቲካ ሊረዱ አይችሉም ብለው የሚያስቧቸውን ጓዶቻቸውን ለማታለል ከሚሞክሩበት ነባሩ ጨዋታቸው ስንነሳ በኃይለማርያም ደሳለኝም ላይ የበላይነታቸውን ለማሳየት ከመንቀሳቀሳቸው በተጨማሪ፣ ‹‹መጠቀሚያ›› የማድረግ እቅድ ሊኖራቸው ይችላል ብሎ ማሰቡ አይከፋም። ይህ ከሆነ ደግሞ ከአዲሱ መንግስት ‹‹መሰረታዊ የፖለቲካ ማሻሻያዎች››ን መጠበቅ ላም አለኝ በሰማይ.... አይነት እንደሚሆን ብዙዎች ያምናሉ)

ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው ኃይለማርያም ደሳለኝ ለሰራዊቱ ‹‹ጠቅላይ ወታደራዊ አዛዥ›› (Commander in chief) ለመሆን ያላቸው ብቃት እና ተቀባይነትም እንዲሁ አሳሳቢ ሲሆን ሌላው አደገኛ እንቅፋት የሚሆንባቸው በብሔርና በጥቅመኝነት የተወሳሰበውን የገዢው ልሂቅ ስብስብን ‹‹የፖለቲካ ማሻሻያ መደረግ አለበት›› ብሎ ማሳመኑ ላይ ነው።

መቼም ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ያየነው ፖለቲካ ‹‹የቁማር›› ባህሪ ያለው ነው። ...ብልጣ ብልጡ የሚያሸንፍበት፣ ህግና መርህን ሳይሆን የጨዋታውን ባህሪ እየተከተሉ የሚቆምሩበት፤ ምንአልባትም በጨዋታው በለስ ያልቀናው ጉልበተኛ ‹‹የሚያፍርበት››፣ የጭቦ አምላክ የማይፈርድበት... እናም በዚህ አይነቱ ጨዋታ አቅሙም ፍላጎቱም፣ ችሎታውም ያላችሁ ህወሓት እና ብአዴን ከኃ/ማሪያም ጀርባ ያለውን ወንበር እንደአያት ቅድመ አያት ርስት ‹‹ወራሽ ነኝ›› በሚል በቤተመንግስት እና በኢህአዴግ ጽ/ቤት እያደረጋችሁት ያለውን ትግል ብትረሱት የተሻለ ነው። እናውቃለን ታግላችኋል፤ ነገር ግን በስልጣን የቆያችሁባቸው ሃያ አንድ ዓመታት ከበቂ በላይ ክሷችኋል። እናውቃለን አምባገነኖች ናችሁ፣ ነገር ግን ትውልዱ ከዚህ በላይ አምባገነንነትን ሊሸከም እንደማይችል ሊገባችሁ ይገባል። ‹‹የታላቁ መሪያችን ራዕይ›› በሚል ባልተ ፈለጋቸውን እከንከተላለን ማለታችሁ እሳቸው በተፈጥሮ ሞት ያመለጡትን ‹‹ህዝባዊ እሳተ-ጎመራ›› ቀን ከማቅረብ የዘለለ ፋይዳ የለውም። ...አስገራሚው ነገር ደግሞ ነሀሴ ሃያ ዘጠኝ ቀን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴያችሁ ከመለስ ሞት በኂላ የመጀመሪያውን ስብሰባ አድርጎ ያወጣው መግለጫ ይዘት ነው። ይህ ስብሰባ ከተጠናቀቀ በኂላ በወጣው መግለጫ ላይ ‹‹የሕዝብን ቁጭትና አደራ በህዝቡ በራሱ በተደራጀና ቀጣይነት ባለው ተሳትፎ ወደውጤት በመቀየር....›› የሚል ሀረግ ሰንቅሯል። ምንአልባት አባባሉን ልብ ካላልነው ብዙም አሳሳቢ ላይመስለን ይችላል። ሆኖም ፈታ አድርገን ካየነው ግን መጭው ጊዜ ብሩህ እንደማይሆን በእርግጠኝነት እንደሚጠቁመን እንረዳለን። ምክንያቱም ይህ አይነቱ ሁኔታ የሚያመላክተው አንድም ፓርቲው ‹‹የመለስን አደራ ለማስፈፀም›› በሚል ያለአንዳች የፖለቲካ ማሻሻያ ለመቀጠል የወሰነ መሆኑን ሲሆን፤ ሁለተኛው አደገኛ ነገር ደግሞ ስርዓቱ ወደ "Stationary bandit" (መንግስታዊ ሽፍትነት) የመቀየር አዝማሚያ እንዳለው አመላካች መሆኑ ነው። ይኸውም ‹‹የህዝብን ቁጭትና አደራ በህዝቡ በራሱ... ለመወጣት›› በሚል ፕሮፓጋንዳ በከፍተኛ ደረጃ ግብር መጣልን፣ ለአባይ ግድብ ሁለተኛ ዙር ቦንድ ግዙ ተብሎ እንደተደረገው አይነት ማስገደድና የመሳሰሉት እርምጃዎችን ሊወስድ መቻሉ አይቀሬ ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ የስርዓቱን አምባገነንነት ከማጠናከር አልፎ በኑሮ ውድነቱ ላይ ተጨማሪ ጫና መፈጠሩ አያጠያይቅም።

አሁን ወደዋናው አጀንዳችን እንግባ። ይኸውም የኃይለማርያም ደሳለኝን ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት መምጣት አንዳች ለውጥ የለውም ብሎ በጭፍን መቃወምንም፣ በጭፍን

መደገፍንም የሚመለከት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በግሌ ለውጡ ደካማ ጎን እንዳለው ሁሉ ጠንካራ ጎንም አለው ብዬ ስለማስብ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ የሚሆኑ አንዳንድ ነገሮችን እንይ፡፡

## የለውጡ-ጠንካራ ጎን

የመጀመሪያው ኃይለማርያም ደሳለኝ ወደ ስልጣን በመምጣታቸው ከምንም በላይ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው ሀገሪቱም ሆነች የኢህአዴግ አመራር ከአንድ ሰው ‹‹ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭነት›› (Strong man) ነፃ መውጣቱን አመላካች መሆኑ ነው፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው የአቶ መለስ የሃያ አንድ ዓመት የስልጣን ዘመን ሁለት ባህሪያት ነበረው፡፡ የመጀመሪያው ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. እስከ 1993 ዓ.ም /የህወሓት ክፍፍል/ ድረስ ያለውን ልናካተው እንችላለን፡፡ በእነዚህ ዓመታት መለስ የሀገሪቱን ፖለቲካ ብቻቸውን አይዘውሩም ነበር፡፡ ወሳኝ ሰውም አልነበሩም፡፡ በግልባጩ ዘመኑ ሊወከል የሚችለው በ‹‹ቡድናዊ አመራር›› (Collective leadership) ነበር፡፡ ይህ ግን መላውን የኢህአዴግ የአመራር አባላት አይመለከትም፡፡ ህወሓትን እንጂ፡፡ ምክንያቱም መለስ በጋራ ይወስኑ፣ በጋራ ያቅዱ፣ በጋራ ያስፈፅሙ የነበረው ከህወሓት አመራር ጋር ብቻ ነውና፡፡ (በእርግጥ በዛን ዘመን ክንዳቸውን ከህወሓት አመራር ጋር የሚለኩ እንደ በረከት ስምኦን ዓይነት ባለስልጣን እንደነበሩ መካድ አይቻልም፡፡ በረከት በተወሰነ ደረጃ የህወሓት ‹‹የጋራ አመራር›› የስልጣን ንቅፈ-ክበባቸውን እንዳይደፍር ሲገዳደሩ ይታዩ ነበር)

ሁለተኛው የአቶ መለስ የስልጣን ዘመን ከህወሓት ክፍፍል (ከ1993 ዓ.ም) በኋላ እስከ ህልፈታቸው ድረስ ያለውን የሚያካልል ነው፡፡ በእነዚህ 11 ዓመታትም መለስ የህወሓትም፣ የኢህአዴግም፣ የሀገሪቱም ብቸኛ ‹‹ፈላጭ ቆራጭ›› ገዥ ነበሩ፡፡ ይህንን ሁኔታ በፍትህ ጋዜጣ ላይ ደጋግመን በመፃፍ ኢህአዴግ የእርምት እርምጃ ይወስድ ዘንድ ብናሳስብም የሚሰማን አልነበረም፡፡ ነገር ግን አቶ መለስ ህይወታቸው ካለፈ በኋላ ሁሉም ባለስልጣናት በሚባል መልኩ መለስ ‹‹ብቸኛው ሰው›› እንደነበሩ እየነገሩን ነው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬም ድረስ ‹‹ድርጅታችን ኢህአዴግ ባቀደው፣ በወሰነው… መሰረት›› ከማለት ይልቅ ‹‹መለስ ባስቀመጠልን››፣ ‹‹መለስ ባቀደልን…›› የሚሉ መግለጫዎችን እየሠማን ያለነው፡፡ እናም አሁን በአቶ መለስ ቦታ አቶ ኃይለማርያም መተካታቸው ያንን ‹‹የአንድ ሰው መንፈስ›› ከአራት ኪሎ ስላበረረው ሁሉም ባለስልጣናት ‹‹ራሳቸውን ለማውጣት›› (አቅማቸውን ለማሣየት) የሚጥሩበት ዕድል ተመቻችቷል፡፡ የዚህን አባባል አንድምታ ከተረዳነው አብዛኛው የፖለቲካ አመራር (የስርዓቱ አውራዎች) ‹‹አቻ›› የፖለቲካ ባርኔጣ ማጥለቃቸውን እንገነዘባለን፡፡ ለምሳሌም አፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ኃይለማርያም ደሳለኝን ‹‹ሊያመልኳቸው›› አይችሉም፡፡ ኃይለማርያምም የአባዱላን የስልጣን ድንበር የመዳፈር ዕድላቸው አናሳ ነው፡፡

ይህን ትንተና ለጠጥ ካደረግነው ደግሞ የፓርላማው አባላትም በአንድ አጀንዳ ላይ አንድ አይነት አቋም በመያዝ ‹‹ከፋብሪካ የወጣ ሳሙና›› ሊሆኑ የማይገደዱበት አጋጣሚ እንደተፈጠረ አድርገን እንወስደዋለን፡፡ ምክንያቱም አረብቦባቸው ከነበረው ‹‹የአንድ ሰው አስገዳጅ›› መንፈስ ተላቀዋልና፡፡ ስለዚህም አንድም የፓርቲያቸው ስራ አስፈፃሚ ወስኖ የሚልክላቸውን በአቶ መለስ ዘመን በተለማመዱት ደረጃ ‹‹ሳያላምጡ ሊውጡ›› (ሊያፀድቁ) ላይችሉ ይችላሉ፡፡ ሁለትም የግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ራሱ ከአንድ ሰው ውሳኔ ወደ ሰላሳ ስድስት ሰው ውሳኔ ተሸጋግሯልና የተለያዩ ሃሳቦች የሚንፀባረቁበት ምህዳር ይፈጠራል፡፡ በዚህ አንፃር የሚወሰሱ ውሳኔዎችም በፓርቲ የሚወሰኑ ይሆናሉ፡፡ ይህንም ‹‹ጥሩ›› ሊባል የሚችል ለውጥ ነው፡፡

ይህ ሁኔታ ጉጉት (ambition) እንዳልሆነ የሚያረጋግጡ አንዳንድ ምልክቶችም እየታዩ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ዘመን በፓርቲው ህገ-ደንብ መሰረት ገደብ አልባ እንደነበረ እናስታውሳለን፡፡ በዚህ ምክንያትም አቶ መለስን ያለአንዳች ጭንቀት በአራት የስልጣን ዘመን ልናያቸው ችለናል፡፡ ምንአልባትም ድንገተኛው ህልፈታቸው፣ ድንገት ባይመጣ ኖሮ በ2007ቱም ምርጫ ለአምስተኛ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትር ወንበራቸው ላይ ሲቀጥሉ ብናያቸው ህግ ጠቅሶ መከራከር አለመቻሉ እውነት ነው፡፡ ሌላው እውነት ደግሞ አቶ መለስ ህይወታቸው አልፎ ተተኪያቸው ከመመረጡ በፊት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ዘመን በሁለት የስልጣን የመቆያ ጊዜያቶች የተገደበ እንዲሆን ፓርቲያቸው ኢህአዴግ መወሰኑ ነው፡፡ ይህ በእሳቸው ዘመን ያልነበረ አዲስ ለውጥ ነው፡፡ (የሁኔታው ምፀት የሚገዝፍብን የፓርቲው አመራር በአቶ መለስ ቀብር ወቅት አቶ መለስ የዴሞክራሲ በር ከፋች ነበሩ፣ ዴሞክራት መሪም ናቸው ሲሉ የነበረውን ስናስታውሰው ነው)

የሆነ ሆኖ ኃይለማርያም ደሳለኝ ‹‹ቃለ-መሀላ›› ፈፅመው የተረከቡት ስልጣን ከፊት ለፊቱ በርካታ ተግዳሮቶች እንደሚጠብቁት ግልፅ ነው፡፡ በብዙ የፖለቲካ ተንታኞች እየተነገረ እንዳለው ‹‹አሻንጉሊት›› ሊሆኑ ይችላሉ ከሚለው ጀምሮ የነባር ታጋዮችን ‹‹እምቢተኝነት›› በምን ሁኔታ ሊያስተናግዱት ይችላሉ የሚለውን እንቆቅልሽ ለመፍታት ወራት ወይም ጥቂት አመታት ሊጠይቅ የሚችል ነው፡፡ አንዳንድ የዋሆች የሰውየውን የትምህርት ዝግጅት ብቻ በማየት አሻንጉሊት ሊሆኑ አይችሉም ይላሉ፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፡፡ አሻንጉሊት ለመሆን እና ላለመሆን ወሳኙ ‹‹ዲግሪ›› አይደለም፡፡ የፖለቲካ ስልጣን ነው፡፡ ያ ባይሆን ኖሮማ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በፕሬዝዳንትነት ዘመናቸው የሆኑትን ሁሉ አይሆኑም ነበር፡፡ ምክንያቱም ለምሁራዊ ሰውነትም ሆነ ራስን ችሎ ለመቆም ዶክተሩ የተሻሉ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ እናም ኃይለማሪያም የያዙትን የፖለቲካ ስልጣን የማጠናከር ስልት ቢከተሉ የተሻለ ያዋጣቸዋል፡፡ የግብፅ ፕሬዝዳንት የነበሩትን የአንዋር ሳዳት መንገድ መከተል ይችላሉ፡፡ ሳዳት ገማል አብዱል ናስር ህይወታቸው በማለፉ ነው ወደስልጣን የመጡት፡፡ ሆኖም ሳዳት ተተኪ እንዲሆን በወቅቱ የተመረጡት ‹‹ጭምት እና ትእዛዝ ተቀባይ›› በመሆናቸው ‹‹አሻንጉሊት›› ለማድረግ ባለሙ ጓደኞቻቸው ግፊት ነበር፡፡ የሆነው ግን በግልባጩ ነው፡፡ ምክንያቱም ሳዳት ስልጣን በእጃቸው ገብቶ በዝነኛው የፈርኦኖቹ ቤተ-መንግስት ከተደላደሉ በኋላ በሚገባ ተጠቀሙበት፡፡ እናም ከናስር የበለጠ ጉልቤ ሆኑ፡፡ ይህ ነው የሳዳት መንገድ፤ ሌላ አይደለም፡፡ …አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ስልጣን በመያዛቸው ‹‹በጎ ለውጦች›› ብዬ የጠቀስኳቸው ምልዑ የሚሆኑት ኃይለማርያም በስልጣናቸው ማዘዝ፣ መወሰን እና ተጠያቂ መሆን ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

> *…ኃይለማርያም ሊያነሱት የሚችሉት ጥያቄም ‹‹የ34ቱ ጄኔራሎች ሹመት በማን አቅራቢነት የተካሄደ ነው?›› የሚል ይሆናል፡፡ ሆኖም ጠቅላይ ሚንስትሩ የሚጠበቅባቸው ጥያቄ ማንሳት ብቻ ሳይሆን ለሹመቱ አንድምታ ተነስተው በስራዊቱ ለመጠቀም የሚሞክረው ኃይል ምን ያህል ደፋር እንደሆነ መረዳትም ይኖርባቸዋል…*

## የለውጡ ደካማ ጎን

እንደ ኢትዮጵያ ባለ ‹‹የህግ የበላይነት›› ባልተረጋገጠበት ሀገር እንዲህ አይነት ለውጥ ሲከሰት ‹‹የዕዝ ሠንሰለቱ›› (Hierarchy) መድከሙ አይቀሬ ነው፡፡ በተለይም በፍርሃት ቆፈን ውስጥ የነበሩ አመራሮች ከፍርሃታቸው ድንገት በመላቀቃቸው ኃላፊነታቸውን መወጣት ወይም የስልጣን ተዋረዱን ጠብቀው ለመሥራት ያለመፈለግን አዝማሚያ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ስርዓት አልበኝነትን (Anarchism) ሊያስከትል መቻሉ አይቀሬ ነው፡፡ ለምሳሌም የስኳር ኮርፖሬሽንን በሚንስትር ማዕረግ የሚመሩት አባይ ፀሐዬ የስራቸውን የቀን ተቀን ሂደት ለኃይለማርያም ደሳለኝ ማቀረቡን ‹‹በትግሉ ዘመን ላልነበረ›› ወይም ‹‹ለተገኘው ስልጣን መስዕዋትነትን›› ላልከፈለ ሰው እንደ መታዘዝ አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ፡፡ አይበለውና ይህ አይነቱ አጋጣሚ ቢፈጠር ኃይለማርያም ደሳለኝ ደፍረው ሊጫኗቸው ይችላሉ ተብሎ አይጠበቅም፡፡ የእነዚህ እና መሰል ሁኔታዎች ጥቅል ውጤት ደግሞ መንግሥታዊ ስርዓቱን ያልተረጋጋ ያደርገዋል፡፡ በዚህ መሀልም የተለያዩ ተጣራሽ ፍላጐቶች ያሏቸው ቡድኖች የየራሳቸውን ፍላጐት ለማስጠበቅ ሲሉ የሚወስዱት እርምጃ ሥርዓታዊ መፈራረስን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ቢያንስ ኢህአዴግ የከፉ መንግስታዊ ውሳኔዎችን ጭምር ይወስን በነበረበት ፍጥነት እና ልማታዊ የሚላቸውን ፖሊሲዎቹን በለመዱት ሂደት እንዳይተገብር ሊገታ ይችላል፡፡ እናም ይህ ሁኔታ ‹‹ከፖለቲካው ስንክሳር›› ባሻገር በለውጡ የሚከሰት በጎ ያልሆነ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡

## የኃይለማርያም-የማርያም መንገድ

ኃይለማርያም ደሳለኝ በኢትዮጵያ ኦሪታዊውም ሆነ አዲሱ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሆኑባቸው መሰረታዊ መለያዎች አሏቸው፡፡ በተለይ ከብሔር እና ከሃይማኖት አንፃር፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ተመልሰው በአስተዳደራቸው ላይ ጥቂት የማይባሉ ተግዳሮቶች የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡ በእርግጥም በጠቅላይ ሚንስትሩ ወንበር

ወደ ገፅ 31 ዞሯል

# ሕገ-መንግሥቱን በቆረጣ

የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ በስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሀገሪቱን ሕገ-መንግሥት ማክበርና ማስከበር የመንግሥታቸው ኃላፊነት እንደሆነ አፅንኦት ሰጥተው ይናገሩ ነበር:: በእርግጥ ይህ ተግባር የመንግሥት አይደለም ብሎ ክርክር የሚገጥም ያለ አይመስለኝም:: ይሁንና ከመንግሥት በኩል ሕገ-መንግሥቱን ራሱ ማክበር እንዳለበትም መዘንጋት የለበትም:: እንዲያውም ለዜጎችም ሆነ በቀጣይ ለሚመጡ መንግሥታት የአርአያነት ተግባር ተደርጐ ሊወሰድም ይችላል:: አሁን በስራ ላይ ያለውን የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንዳንድ ድንጋጌዎችን ስንመለከታቸውና ገዢው መንግሥት በተግባር እየፈፀመው ያለውን ስናስተውል፤ እነዚህ ድንጋጌዎች በዚህ ሰነድ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉት ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ በጐ ፍላጐት ነው ብሎ መናገር ይከብዳል:: ይህን የምለው በደፈናው ሳይሆን ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የሀገሪቱን ሕገ-መንግስት በቀጥታም ሆነ በቆረጣ የሚጥስ እንደ መንግሥት ባለመኖሩ ነው:: ትክክለኛና ነፃ በሆነ መንገድ የተቋቋመ የሕገ-መንግስት ጉዳዮችን የሚከታተልና እውነተኛ ውሳኔ የሚሰጥ አካል በሀገሪቷ ቢኖር ኢህአዴግ በሚፈፅማቸው ኢ-ሕገ መንግስታዊ ተግባራት ለብዙ ጊዜ ከስልጣን በተባረረ ነበር:: ሕገ-መንግሥቱ አሁን የያዘውን መልክ እንደያዘ ኢህአዴግ በውስጡ ሊከሰቱ የሚችሉ ቅራኔዎችን በወረቀት ደረጃ ማስታረቅ ነበረበት:: ወደ ስልጣን የመጣው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሳይሆን በጦርነት በመሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ለማግኘትም ሳይወድ በግድ በሕገ-መንግሥት ውስጥ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎችን፤ የመንግሥት ስልጣን በህግ የተገደበ መሆኑን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን ማካተት ይጠበቅበት ነበር:: ሆኖም እነዚህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚያደርጉት ጉዳዮች በሂደት በሀገር ውስጥ ለስልጣኑ ችግር እንደሚሆኑ አልተረዳውም ነበር ማለት አይቻልም:: ሕገ-መንግሥቱ ፀድቆ በስራ ላይ መዋል ከጀመረ በኋላ መንግሥት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን መናድ፣ በሚያወጣቸው አንዳንድ ሕጐች ደግሞ በቆረጣ የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌዎች መሸራረፍ እንደ ስልጣን ማስጠበቂያ ዘዴ ወስዶታል::

በመንግሥት በኩል የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንዘርዝር ቢባል እንኳን በዚህች ትንሽ አምድ ቀርቶ በጥራዝ መልክ በሚዘጋጅ መፅሐፍትም ማጠቃለል አይቻልም:: የቀድሞ ኢሰመጉ የአሁኑ ሰመጉ እስከ ቅርብ ዓመት ድረስ በሀገሪቱ ተከሰቱ የተባሉ የሰብዓዊ መብት ጥስቶችን ያካተተበትን መጽሐፍ ብናይ ለዚህ ጉዳይ አብይ ምስክር መሆን ይችላል:: ከዚህ ሌላ በአለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት ያላቸው የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች ኢትዮጵያን አስመልክተው የሚያወጡት መግለጫ በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ኢህአዴግ መራሹን መንግሥት የሚያወግዙ ናቸው:: ‹‹ሂዩማን ራይትስ ዎች›› በሚያወጣቸው መግለጫዎች ምክንያት በኢትዮጵያ መንግሥት ከሚጠሉ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች አንዱ የሆነው በዚሁ ምክንያት ነው:: መንግሥትን በውዴታም ይሁን በግዴታ በመደገፍ ወደ አደባባይ መውጣት እንጂ ለተቃውሞ በመሰባሰብ ወደ የትኛውም ጉዳናና አደባባይ ብቅ ማለት ጣት ያስቆርጣል፤ ዘብጥያ ያስወርዳል:: ከዚያም አለፍ ሲል ህይወትን እስከማጣት ያደርሳል:: ከአንቀፅ 14 እስከ 28 ድረስ የተቀመጡትን የሰብዓዊ መብቶች ብንመለከት ከአንድ ወይም ሁለት አንቀፆች በስተቀር የተቀሩትን በሙሉ ገዥው መንግሥት በየቀኑ የሚጥሳቸው ድንጋጌዎች ናቸው:: የህይወት መብት፣ የአካል ደህንነት መብት፣ የነፃነት መብት፣ ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ፣ የተያዙ ሰዎች መብት፣ የተከሰሱ ሰዎች መብት፣ የክብርና የመልካም ስም መብት፣ የእኩልነት መብት… የመሳሰሉት መብቶች በሀገሪቱ የበላይ ሕግ የተቀመጡ ሲሆን ህጉን ማክበርና ማስከበር ባለበት መንግሥት በገሀድና በህቡዕ የሚጣሱ ናቸው:: እነዚህን ሁኔታዎች ስናስተውል ኢህአዴግ ወዶና ፈቅዶ ሳይሆን በተለያዩ ግፊቶችና ዓለም አቀፍ እውቅናን ለማግኘት ሲል ያካተታቸው እንደሆኑ እንረዳለን::

ኢህአዴግ በገሀድ ከሚያደርጋቸው ሕገ-መንግሥታዊ ጥሰቶች በተጨማሪ በቆረጣ የሕጉን ድንጋጌዎች የሚሸረሽርበት የራሱ የሆኑ መንገዶችም አሉት:: ከእነዚህ የቆረጣ ስልቶች አንዱ በራሱ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ‹የመግቢያ በር› ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ በሂደት በሚወጡ ህጐች ውስጥ እነዚህን ድንጋጌዎች በመጠቀም መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን ለመጣስ ይጠቀምበታል:: የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2 እንዲህ ይላል ‹‹ማንኛውም ሰው በግል የሚፅፋቸውና የሚፃፃፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌ ኮሚንኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም::›› አንቀጹ በግልፅ እንዳስቀመጠው የግል ህይወትን የመጠበቅ መብት ሊጣስ በማይችል መልኩ በመርህ ደረጃ ተቀምጧል:: ሆኖም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 ውስጥ ‹የመግቢያ በር› ተቀምጧል:: በዚሁ ድንጋጌ መሰረት አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲኖሩ በህግ በሚገለፅ መልኩ እነዚህን መብቶች ማለፍ እንደሚችል ይገልፃል:: ይህን መሰረት አድርገው ከወጡ ድንጋጌዎች አንዱ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ አንቀጽ 14 ነው:: ድንጋጌው ለብሔራዊ የመረጃና የደህንነት አገልግሎት የግንኙነት መስመሮችን የመጥለፍ ስልጣን የሰጠው ሲሆን ይህ ተግባር የሚፈፀመውም የሽብርተኝነት ድርጊትን ለመቆጣጠር እንደሆነ ተገልጿል:: በሀገር ላይ ሊጋረጡ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቆጣጠር የዚህ ዓይነት ሕግ መኖሩ አስፈላጊነቱ የማያከራክር ቢሆንም ብዙውን ጊዜ ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ለሚታወቀው ኢህአዴግና ፍፁም ወገንተኝነት ለሚታይበት ብሔራዊ የመረጃና የደህንነት አገልግሎት ግን ይህን ክፍተት መፍጠር ዜጐችን መብታቸውን ገፎ ለመንግሥት ስልጣን ማስጠበቂያ መንገድ ማመቻቸት በቆረጣም ሕገ-መንግስቱን መሸራረፍ ነው:: ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች በዚሁ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን::

ሌላው ሕገ-መንግሥቱን የመሸራረፊያ መንገድ በውስጡ የተቀመጡ መብቶችን ማጠናከሪያ የሚመስሉ አዋጆችን በማውጣት እና የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌዎች በውስጡ በማካተት ሕገ-መንግሥቱን ያስከበሩ ማስመሰል ነው:: እስቲ ለዚህ ምሳሌ እንዲሆነን ከመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ ከወጣው አዋጅ አንዳንድ አንቀፆችን እንይ:: በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 4(1) ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት በሕገ-መንግሥቱ እውቅና አግኝቷል:: ‹‹ቅድመ ምርመራ በማናቸውም መልኩ የተከለከለ ነው::›› በማለት ተገልጿል ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሚሆኑ ድንጋጌዎች በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት 29(1)(ሀ) ውስጥ ተቀምጧል:: ይሁን እንጂ ከእነዚህ ሁለት አንቀፆች ጋር የሚቃረን ሌላ ድንጋጌ ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት አዋጅ ውስጥ ተካቷል:: አንቀጽ 42 የእገዳ እርምጃዎችን ስለመውሰድ በሚለው ርዕስ ስር ለፌዴራል የክልል ዐቃቤያን ሕግ የቅድመ ምርመራ የእግድ መብት በግልፅ ይሰጣቸዋል:: አንቀጽ 42(2) እንዲህ ይላል ‹‹እንደነገሩ ሁኔታ የፌዴራል ወይም የክልል ዐቃቤ ሕግ በብሔራዊ ደህንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልፅና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በጊዜው የሚወጣ ሕገ-ወጥ ህትመት ወይም መጽሐፍ ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የህትመት ውጤቱ እንዳይሰራጭ ፍርድ ቤት እንዲያዝ ማመልከት ይችላል::›› ዐቃቤ ሕጉ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በፍጥነት ማግኘት ካልቻለ በራሱ ትዕዛዝ ሕትመቱን ማገድ እንደሚችል በቀጣይ የተቀመጠው ንዑስ አንቀፅ ያስረዳል:: በመርህ ደረጃ በደማቁ በሕገ-መንግሥቱ ተፅፎ የተከለከለው የቅድመ ምርመራ መርህ በዚሁ አዋጅ ውስጥም ተጠናክሮ የተቀመጠ ቢሆንም በሌላ ድንጋጌ ለዐቃቤ ሕግ በተሰጠ ለቀቅ ያለ ስልጣን በቀላሉ እንዲሸበብ ተደርጓል:: ዐቃቤ ሕግ ‹‹ማገድ ያስችላል›› ብሎ ባመነበት ወቅት አንድን የሕትመት ውጤት እንዳይሰራጭ የማድረግ መብቱ ትክክል ሆነም አልሆነም ተፈቅዶለታል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሕትመት ሚዲያው ላይ የሚያደርሰውን ኪሳራ ማን ሊከፍለው እንደሚችል በግልፅ አልተብራራም:: የቅድመ ምርመራ ክልከላ የዴሞክራሲ መገለጫ ከሆኑ መብቶች አንዱ ሲሆን በታላላቅ ሀገራት ሕገ-መንግሥቶች የተቀመጠ መርህ ነው:: ብላክስቶንን የመሳሰሉ ስመጥር የሕግ ባለሙያዎችና የቅድመ ምርመራ ተቃዋሚዎች ደግሞ “The liberty of the press… consists in laying no previous restraint upon publication…” (የፕሬስ ነፃነት ምንም አይነት ቅድመ ገደብን ማካተት የለበትም) በማለት ሽንጣቸውን ገትረው ተከራክረውለታል:: በእኛ ሀገር ግን በሕገ-መንግሥቱ በግልፅ ተቀምጦ በቆረጣ ስልት እየተሸራረፈ ይገኛል:: ቸር እንሰንብት::



# “ማጉም ለሰለሰ ሸማኔው ተቆጣ፤ አባ ጎፈን ኃይሌ መጠቅለያው መጣ”

## ለኃይማርያም ማሞ ከተገጠመው የተመዘዘ

ታዴዎስ ታንቱ

በማይጨው ጦርነት ጊዜአዊ ድል መቀዳጀት ዓለምን መቆጣጠር አለመሆኑ ይታወቃል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን በተዛባ ሥነ-ልቦና በዕብሪት ተወጥሯል! በማን አህሎኝነት ሕመም ከሥቃይ ላይ ወድቋል! ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል ከግሥጋሴው ሊገታው እንደማይችል ታይቶታል! ዱሮም ደካማ ብርቱ የሆነ ዕለት መሬት አይበቃውም! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ራሱን አሳምሮ ያውቀዋል! በዘመኑ የኃይል አሰላለፍ ከአውሮጳ ኃያላን በወረደ ረድፍ ተመዝግቧል! ልቡን በልቡ ልቡ አላጣውም! በጀግንነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ይልቃል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በአይሮፕላን መርዝ ጡንቻውን አስመርቋል! ጀግና ይሰለፋል! ድል በሩቅ ርቀት ሊቀር ይችላል! አሁን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንቅፋት ሳይመታው አዲስ አበባ ለመግባት ተስፋ ታጥቋል! መስሎታል! የተደገሰለትን በተግባር ይስተናገዳል! አልሰሜን ግባ በለው! አልሰሜ ግባ! የኢትዮጵያ ጀግና ተዘጋጅቷል! የወራሪው ኃይል መምጫ መንገዱ ታውቋል! የኢትዮጵያ ጀግና በቂ መረጃ ታጥቋል! የቁርጥ ቀን ጀግና በቆረጠ አቋም ፀንቷል! ወራሪው ኃይል በደሴ በኩል አድርጎ መጥቷል! የኢትዮጵያ ጀግና በተጠንቀቅ ቆሟል! ከጫጫ ከተማ ግማሽ ምዕራፍ ያህል ወደ ፊት ተመዝዟል! ማን ማንን ይገዛል? በሰዓታት ውስጥ ጦርነት ይከፈታል! የኢትዮጵያ ጀግና ከወራሪው ኃይል የጦር ሜዳ መነፅር ዕይታ ውጭ ቀርቷል! በቅጠልያ አልባሳት ከብሣናና ዶቅማ ተመሳስሏል! ከእንቅስቃሴ ታቅቧል! በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት አድፍጧል! ወራሪው ኃይል ባሁኑ ሰዓት ከኢትዮጵያ ጀግና በቅርብ ርቀት ይስተዋላል! ባልወየበ ተስፋ ይሳባል! ሐሳብ ልጓም የለውም! እንቅፋት ሳያገኘው አዲስ አበባን ቋምጧል! ተቃርቧል! አንድ ጀግና በመነኩሴ ልብስ እንደ መረጃ መኰንን ተሰማርቷል! የሸማኔ መወርወሪያ ሆኗል! ይሄዳል! ተመልሶ ይመጣል! ይመጣል! ደግሞ ተመልሶ ይሄዳል! በጥንቃቄ ለጥንቃቄ ተግቶ ይሰራል!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አሁን በጣም ተቃርቧል! መንገዱ ሰላም እንዳልሆነ ግን ጠርጥሯል! የኢትዮጵያ ጀግና እንደ ሎጥ ሚስት የጨው ዓምድ ሆኖ ቀርቷል! ንቅናቄ በጦር ሜዳ መነፅር በቀላሉ ያስገኛል! በፀጥታ ማድፈጥ የግድ ይላል! እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ጀግና የራሱን ብቻ ሳይሆን የወገኑንም ህይወት የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት አሳምሮ ያውቃል! አስመሳዩ መነኩሴ አሁን የመረጃ ስራውን አጠናቅቋል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ባንዳን አስቀድሟል! ወፌ ሰማይ ባንዳ ይግተለተላል! ለውሻ ሞት ራሱን ገፀ በረከት አድርጎ አቅርቧል! ማን ይፈራል ታንክ? ማን ይፈራል አይሮፕላን? የኢትዮጵያ ጀግና ቸኩሏል! ጀግናው ኃይለ ማርያም ማሞ ትዕዛዝ አውርዷል! ድም! ም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም! የአርበኝነት የደፈጣ ጦርነት ተከፍቷል! የመድፍ ድምፅ ተስተጋብቷል! የቅድሚያ ተነሳሽነትን የኢትዮጵያ ጀግና ወስዷል! ወራሪ ኃይል አልጠበቀውም ነበር! ከማይጨው ጊዜአዊ ድል አንሥቶ የከፋ ችግር አላጋጠመውም! ደሴንም በሰላም አቋርጧል! አሁን ሰዓቱ ደርሷል! ግፈኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያ አርበኞችን ክንድ ይቀምሳል! ጦርነቱ በሕይወት መስዋዕትነት ሂደቱን ይዟል! እንቅፋት ሳይመታው አዲስ አበባን የተመኘው ከደብረ ብርሃን ከተማ ሳይገባ አሣሩን ይበላ ገባ! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! ድም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም!

ኃይለማርያም ማሞ የጦሩ ገበሬ፤
ፈረሱን እንደ ሰው አስታጠቀው ሱሬ።

ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጅ ኃይለማርያም ማሞ በፍልሚያ ጎራ በግምባር ቀደም መስመር ይስተዋላል! ለሕይወቱ በፍፁም አይሳሳም! ተግባራዊ እንቅስቃሴው በአርአያነቱ ለጀግኖች ሕሊናን ይቆርጻል! መንፈስን ይመግባል! የሰራ አካላትን በወኔ ያግላል! ማን ይፈራል ሞት? ለእናት ሀገር ሲባል! ከኢትዮጵያ አርበኞች በርካታ ጀግኖች ወድቀዋል! ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እስካሁን 80 ነጭና ባንዳ ተነጥፈዋል! በጀግናው ኃይለማርያም ማሞ አመራር ዳግማዊ ማይጨው ተሰምሯል! ሦስት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ካሚዮኖች ከጥቅም ውጭ ሆነዋል! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ኃይለማርያም ማሞ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እርምጃን ገትቷል! ኢትዮጵያ ሆይ! ኩራት! ኩራት! አይልሽም ወይ? ኃይለማርያም ማሞ ያንቺ አይደለም ወይ? ግፋ ወደፊት! ግደል! ተጋደል! በዚህ ጦርነት በጠቅላላው 140 ጣሊያኖችና ባንዳዎች ተገድለዋል! አምስት ካሚዮኖች ከጥቅም ውጭ ሆነዋል! 6 መትረየሶች ተማርከዋል! ጥይቶችን ማን ቆጥሮ ይጨርሳል? በእጅ ታፍሰው በጆኒያዎች ተሞልተዋል! በዓይነት ዓይነቱ የመለየቱ ስራ ቆይቶ ተከናውኗል! አልባሳትና መድኃኒቶችም በብዛት ተማርከዋል! ኢትዮጵያ ሆይ! ኩራት! ኩራት! አይልሽም ወይ? ኃይለማርያም ማሞ ያንቺ አይደለም ወይ?

ቆፍጣናው ጀግና ኃይለማርያም ማሞ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በሰላሌ አውራጃ በ1865 ዓ.ም ተወለደ። በልጅነቱ የዒላማ ጉኩስ ተምሯል! እንዲሁም ውኃ ዋናና ጉግሥ ተለማምዷል። ጀግናው ኃይለማርያም በሡንጠረዥ ጨዋታ ችሎታውም ይደነቃል! ጀግንነት ግን እንዴት ይመጣል? ጀግንነት በሁለት መንገድ ሊመጣ ይችላል። እንደ መልክና ቁመት ከዘር ይወረሳል! ይህ በታሪክ ለአያሌ ጊዜ ተስተውሏል! የጀግና ልጅ ያለጥርጥር በደሙ ውስጥ የጀግንነት ሕዋስ ይኖረዋል! ሕዋሱን ኮትኩቶ ማሳደግ ግን የሱ የተግባር ድርሻ ይሆናል! ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ! እንደ ወላጁ ጀግና ለመሆን የቆረጠ በተግባር ውጤቱን ይመለከተዋል! ያለበለዚያ ተንቀሳቃሽ አስክሬን ሆኖ መቅረት ይጠብቀዋል። ዛሬ በሀገራችን ያለው እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም! የአያሌ ጀግኖች ልጆች በተንቀሳቃሽ አስክሬን እርከን ቀርተዋል! እንኳን ለሀገር መብት ለግል መብታቸው ዘብ ከመቆም ታቅበዋል። ይልቁንም ለሎሌነት ማመልከቻ ማንከርፈፍን ባሕል አድርገዋል። በተንዳኛ የተንዳኛ ሌላው ምስል ደግሞ ይስተዋላል። ሀገርን የሚያህል የቀብብሎሽ ውርስ ለነጋዴ ገገርዎቻችን በመተው ወደ ስደት ማቅናት ተለምዷል። ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን ያልተሰደዱበት ሀገር በምድር ላይ የለም! ስደት ለገገርዎች የወርቅ ጉድጓድ ሲሆን! ለሀገርና ለሕዝብ ግን የሀፍረት ምንጭ ነው! የጀግና ልጆች ተሰድደዋል!

ጀግንነት በሁለት መንገድ እንደሚደራጅ ጠቅሰናል። ቀዳሚው በዘር ሕዋስ ተወርሶ ይኮተኮታል! በዚህ እንስማማ! ማንም ሰው በዕውቀትና በልምድ ራሱን በማዳበር ፍርሃቱን በቁርጠኝነት በመዋጋት ጀግና ሊሆን ይችላል። ይህ ሁለተኛው መንገድ ነው! በእርግጠኝነት ጀግና ይሆናል! ታላቅ ቁም ነገርም ይሰራል! የፈሪ ልጅ ወደር የሌለው ጀግና ሊሆን ይችላል! ቁርጠኝነት ግን የመነሻ ውኃ ልክ ይሆናል! አንርሣ! በልጓም እንኳን የማትበገረው በቅሎ የአህያ ልጅ ናት! ተግባባን?


ያም ሆነ ይህ ኃይለማርያም ማሞ የጀግና ልጅ እንደነበር ታውቋል! አያቱ ኃይሌ አንዳርጋቸው በአድዋ ጦርነት ተአምር ሰርተዋል!

ከፈረሰኞቹ ከምናውቃቸው፤
ባሻህ አቦዬ ኃይሌ አንዳርጋቸው።

ከልጅነቱ አንስቶ ብርቱ የነበረው ኃይለማርያም ማሞ ማይጨው ዘምቷል። ነገር ግን የዘመተው እጁን በሰንሰለት ታስሮ እየተጠበቀ እንደ ነበር ለማወቅ ተችሏል። ቀደም ሲል ሰው ገድሎ ታስሮ ስለነበር በዚህ መልኩ እንዲዘምት ታዝዟል። መጠርጠሩ መጥፎ አልነበረም! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መጥቷል! ሰው ገድሎ የታሰረ ወንጀለኛን ፈትቶ መልቀቅ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ማን ያውቃል? በዚህ አተያይ ተሄዷል! ማይጨው ላይ ግን ሰንሰለቱ ወለቀለት። ጀግና ታስሮ ማን ይዋጋል? ናስ ማሰር ጠብመንጃ ተሰጠው። እሱ ያውቀበታል! በአንድ ጠብመንጃ ብዙ ሰብስቧል። ጀግንነቱን አስመስክሯል! በተግባር አሳይቷል! የስንዴ ዘር እንክርዳድ ሊሆን አይችልም! የኃይሌ አንዳርጋቸው ልጅ ባንዳነትን አይቀበልም! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለጊዜው የበላይነትን ይዟል! የኢትዮጵያ ሰራዊት ከማይጨው ተመልሷል! አሁን ጀግናው ኃይለማርያም ማሞ ሸዋ ውስጥ የራሱን ማይጨው ፈጥሯል!

ድም! ም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም! ይህ የመድፍ ድምፅ ነው። ጥር 11

ወደ ገፅ 30 ዞሯል



# የነፍስ መከዳ የሌሎ መንገድ

ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

ደራሲው በድርሰቱ ላይ ሰፊ ድርሻ ያለውን የደራሲውን ፍፃሜ እብደት አድርጎ ጨረሰው፡፡ የተፈፀመውን አጭር ልብ-ወለድ ሦስት ጊዜ አነበበና ወረቀቱን አሳጥሮ ትልቁ ፖስታ ውስጥ ከቶ አሸገው፡፡

የቤቱን በር ዘግቶ ወደ ታዋቂው ሳምንታዊ ጋዜጣ ዝግጅት ቢሮ ሄደ፡፡ ምናልባት የጥበብ አምድ ላይ ማን እንዳወጣለት የማያውቀውን ስሙን ተጽፎ ለማየት…

ድርሰቱን ጨረሰ፡፡ ልቡ በልቡ ሲደሰትም መድፈር ግን ፈራ፡፡ ‹‹ሕዝብ ምን ይለኛል?›› የሚል ጥያቄ በውስጡ አጫረ…

ገፅ 3

ሌሎ እንደማናቸውም ተራ እብዶች አይደለም፡፡ የራሱ ዓለም ዕብድ ነው፡፡ እብደቱ የጀመረው ከብዙ የትጋት ሌሊቶች መካከል በተከሰተች አንዲት እውነት ነበር፡፡ ክስተት የነበረችው እውነት ‹‹በወረቀትህ ላይ አስበኝ›› አለችው፡፡ እጁ ታዘዘላት፡፡ ጥቁር ቀለም የሚተፋው ብዕሩ ክስተት የነበረችውን እውነት ዘለዓለማዊ ለማድረግ በወረቀቱ ላይ ቀለመ፡፡ መጀመሪያ ሐሳብ ቀጥላ ቀለም የነበረችው የሌሎ ፈጠራ የሕይወቱ መመሪያ ወደ መሆን ተሸጋገረች፡፡ ብዙዎችም ‹‹በደራሲ ሌሎና ድርሰቱ ውስጥ በቀረፀው ገፀ-ባህርይ መካከል አንዳችም ልዩነት የለም፡፡ ወንድማማች ይመስላሉ›› አሉ፡፡ በእውነቱና በምሳሌው መሃል መንታነት ተፈጠረ፡፡ (ወይ እውነቱ (ሌሎ) ምሳሌውን (ገፀ-ባህሪው ግርማን) መስሏል አልያም ገፀ ባህሪው ዋናውን (ሎሌን) ፈጥሯል) አሉ ሐሳቡ በብዙ ወንዶች ሕሊና ጥላቻን ስታተርፍለት በሴቶች ወገን ግን አስመስግናው ነበር፡፡

‹‹የነፍስ መከዳ›› የሚለውን አጭሩን ልብ-ወለድ ያነበቡ ብዙ ሰዎች ደራሲውን ይነቅፉትና ይሰድቡት ጀመር፡፡ ‹‹አጀማመሩና አፈፃፀሙ የማይታወቅ ጋጠ-ወጥ››የማይለው አልነበረም፡፡ የድርሰቱ መግቢያ ላይ ‹‹ለተመረጡት እንጂ ለመንጋ ትውልድ አስቸጋሪ የሆነ ውዝግብ›› የሚል ጽሑፍ አለ፡፡ የመግቢያውን መልእክት የፃፈበት ዋና ምክንያት ከብዙሃን ትችት ለመሸሽ እንደሆነ አንባቢው ልብ ይበል ለማለት ደራሲው የተጠቀመበት ዘዴ መሆኑን የደራሲው ልብ ያምናል፡፡

ተደራሲው ከመግቢያው ጀምሮ ደራሲውን ንቆት ነበር፡፡ ‹‹የመጀመሪያውን ገፅ እንዳነበብኩ ተውኩት›› የማይል ሰው የለም፡፡ በዚህ ምክንያት ከአንድ ጋዜጠኛ ጋር የተመላለሰውን አስታወሰ

ጋዜጠኛ ‹‹መጽሐፉን ያነበቡ በርካታ ወንዶች ይቃወሙሃል ለምን ይመስልሃል?››

ሌሎ ‹‹በርካታ ሴቶች ስለሚወዱኝ ብቻ ነው›› ሲል የመለሰውን አስታውሶ ለብቻው ፈገግ አለ፡፡ የሚያነበውን ወረቀት ወደሚደርስበት ጣለና ፀጉሩን እየፈተለ ከጠረጴዛው ላይ ያለውን የመጀመሪያውን ገጽ በጥቂት ማስተዋል ያነበው ጀመረ፡፡…

ገጽ አንድ

‹‹ይህንን አጭር ልብ-ወለድ ለመፃፍ ስነሳ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ነበር፡፡ ወንዞች በትዕግስት ይጓዛሉ፡፡… በተራሮች አናት የምትንከባለለው ፀሐይ የተናደደች የቀይ ሴት ጉንጭ ትመስል ነበር፡፡›› ለማለት ፈለገ ግን ሌላ ሐሳብ ተቃወመው ‹‹በዚህ ውድቅት ሌሊት ስለአድማስ ውበት መተረክ ቢቀርብህስ?›› አለው፡፡ ‹‹ለሀያሲው ታዘዘ››፣ ወረቀቱን ቀዶ ጣለው፡፡ ተጀምሮ ያላለቀ አዲሱን ድርሰቱን መጨረስ የሚሻለው መስሎ ተሰማው፡፡…

ያላለቀው ድርሰት ከግማሽ በላይ አልሄደም፡፡ ድርሰቱን ለመጨረስ አስቀድሞ የፃፈውን ማንበብ ጀመረ፡፡

‹‹በፍፁም እንደማልጠላሽ እየነገርኩሽ በመጣሁ ቁጥር አንቺን ላለመጥላት የይሉኝታዬ እስረኛ ሆኛለሁ፡፡ መታመን ማለት ከህሊና ተጠያቂነት ነፃ የሚሆኑበት ስርዓት ነው ባልኩሽ ቁጥር አንደበቴ በተናገረው ልክ ሕሊናዬ ተወቃሽ እንዳይሆን ስሜቴ የሁለቱ ምርኮኛ ሆናለች፡፡ አብዝቼ መውደዴን ስነግርሽ ጥቂት የነበረው ጽዋ ሞላ፤ የሞላውን መፍራት ብጀምርም ማፍሰስ ግን አልቻልኩም፡፡ ምክንያቱም ጽዋው ሙሉ ሆኖ እንዲኖር ቀድሜ የማልኩት እኔ ስለሆንኩ ነው››፡፡

የፃፈው ጽሑፍ ግማሽ ሉክ እንዳልሞላ ሲመለከት በፍፁም የደራሲነት ተሰጥዖ እንደሌለው ራሱን ማሳመን ጀመረ፡፡ ግማሽ ላይ የተጀመረው ድርሰት ስለአንድ ወጣት አፍቃሪ የሚተርክ ሆኖ፤ ወጣቱ ፍቅረኛውን ዘወትር ባገኛት ቁጥር በተዋቡ ቃላቶች ፍቅሩን እየገለፀላት በመጣ ቁጥር ሴቲቱን የሚወዳት በርሱ ስለሚነገሩት የተዋቡ ሐሳቦች የተነሳ እየመሰለው ይመጣል፡፡ ይሄ በመምሰል ደረጃ የነበረው የወጣቱ ሃሳብ ለፍቅረኛው ጥያቄ መሆን ይጀምራል? አሁን ከዕለታት በአንዱ ቀን ብሎ ሊጀምር ሲል ድርሰቱ የተረት ትረካ መሰለው፡፡ ድርሰት እየፃፈ ስለድርሰት ጠየቀ፡፡ ‹‹በተረትና በድርሰት መካከል ምን ልዩነት አለ?››

‹‹ምንም›› ብሎ ለራሱ ከመለሰ በኋላ ጥያቄውንም መልሱንም በጥቁሩ ብዕር ሰረዘው፡፡ እንዲህ አይነት ጥያቄና መልስ ማንሳት የሰነፍ ሰዎችን ልብ ከማስደሰት በቀር ምንም ፋይዳ የለውም፡፡ ‹‹ማንበብ የማይወዱ ሰዎች አያስቡም፤ የማያስቡ ሰዎች ደግሞ ለእንስሳት ቅርብ ናቸው›› ልቡን ደስ እያለው መጣ፡፡ በደራሲነቱ እስኪታበይ ድረስ ነጥብ በህሊናው ይመላለስ ጀመር፡፡

‹‹የሰው ልጅ ከእንስሳት የሚለየው በማሰብ ከሆነ›› እጅግ የሚያስቡ ከእንስሳት እጅግ ሩቅ ናቸው፡፡ አብዝቶ ለማሰብ ደግሞ ማንበብ ቁልፍ ነው፡፡ ‹‹ነገሮችን ከመመርመር የራቁ ሰዎች የዘወትር ጭንቀታቸው ሁለት ነገር ብቻ ነው፤ ብርና ሴት፡፡ በብራቸው ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይዳራሉ፣ ይወልዳሉ፣ ይሞታሉ›› በቃ ተፈፀመ፡፡ ‹‹የእንዲህ አይነት ሰዎች ችግር የሚፈታው በገንዘብ ሃይል ስለሆነ ለእንስሳት እጅግ ይቀርባሉ በገንዘባቸው ታላቁ ህልማቸውን ይበሉበታል፣ ይጠጡበታል፣ ይገድሉበታል›› ብሎ ሊቀጥል አሰበና ድፍረትና ዘለፋ የጥበብ አካል መስለው አልታይህ አሉት፡፡ ‹‹አንድ ጽሑፍ ዘለፋና ድፍረት ከሆነ በሌላ ጎን ያለውን ክፍል ለማስደሰት የሚደረግ ጥረት ስለሚመስል ጥሩ ደራሲ ደግሞ በህብረተሰቡ መካከል ጥያቄን ፈጥሮ የሚያልፍ መሆን አለበት›› የሚለው የራሱ መመሪያ ትዝ አለውና ከግማሽ ገፅ ካላለፈች ጽሁፍ ላይ እንዳፈጠጠ መቆየቱን አስቦ እስካሁንም በህሊናው የሚመላለሱትን ሊፅፋቸው እንደሚገባ በማመን ምን ብሎ መጀመር እንዳለበት ያሰላስል ጀመር…

ሐሳብ ሐሳብን እየወለደ አንዲት ውሳኔ በህሊናው ተደመደመች ‹‹አንድ ድርሰት የግዴታ መርዘም አለበት ወይ?›› የህሊናውን ጥያቄ ‹‹የለበትም!›› በሚል መልስ አስሮ የወጣቱን የፍቅር ታሪክ ከግማሽ ገፅ ባነሰ ሁኔታ ሊፈፅመው ከራሱ ጋር ተስማማ፡፡ ሥለደራሲ ታሪክ የሚፅፈው ደራሲ መፃፍ ሰለቸውና ቀና ብሎ ወደ ባዶው እያስተዋለ ያስብ ጀመር (ነው ወይስ እያሰበ ያስተውል ጀመር?)

ከብዙ መተከዝ በኋላ ‹‹ሰዎች ለምን ይጽፋሉ?›› ብሎ አዲስ ወረቀት ላይ አዲስ ርዕስ ፃፈ፡፡ ይህ እንግዲህ ሶስተኛ ጅምሩ መሆኑ ነው፡፡

‹‹የደራሲ ድርሰት ላይ አብዛኛው ክፍል የራሱን ሕይወት የማይገልፅ ከሆነ መጽሐፉ ስኬታማ አይሆንም፡፡ የሰውን ህይወት እኔ ብሎ የሚናገር ደራሲ ለመግለፅ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለመግለፅ የቃላት እጥረት አይኖርበትም፡፡ ድርሰቱም አያሰለችም እንደውም አንዴ ታዋቂው ገጣሚ ሰሎሞን ደሬሳ ወለሎታቱ መግቢያ ላይ ‹‹ለግጥሙ ባዳ የሆነ ገጣሚ›› ብሎ ሊቀጥል ሲል፤ ደግሞ ሰዎች ምናልባት ‹‹ሰሎሞንን የጠቀሰው የወንዙ ልጅ ስለሆነ ነው›› ቢሉኝስ? እያለ አሰበ፡፡ የሚፅፈው ድርሰት ሳይሆን ጥናታዊ ጽሑፍ መሰለው፡፡ ወረቀቱን ቀደደ፡፡ ሲጋራ ለኮሰ፡፡ የተበታተኑ ወረቀቶች ጠረጴዛውን የሲጋራ ጢስ ደግሞ የቤቱን ባዶ ስፍራ አፍነውት ሲመለከት ‹‹ለድርሰቱ መባዕ የሚያቀርብ ደካማ ካህን ይመስል ነበር፡፡››

ወረቀቶቹን ሳይሰበስብ ተነሣ /ነው የሚባል ከተነሳ መጓዝ ያለበት ይመስለኛል/ እሺ ቆመ…

‹ምን ልፃፍ?› ከሚል መጨነቅ ሰላማዊ እንቅልፍ እንደሚሻለው ዐመነ፡፡ በማመን ወደ አልጋው ውስጥ ሳይገባ ከላይ ጋደም አለ፡፡ ዘወትር እንዳስለመደው ከላይ ጋደም ብሎ የቀን ውሎውን ሊያሰላስል በቀን ውሎው ትልቁን ድርሻ ይዞት የነበረውን ፍቅረኛው ከከዳችው ከሰዓሊ ጓደኛው ጋር የተጫወተውን አስታወሰ፡፡ ልቡን አንዳች ደስታ ተሰማው፤ ከአልጋው ላይ ፈጥኖ በመነሳት ያለአንዳች መጨነቅ ይጽፍ ጀመር…

ሙከራ አራት…

**ግማሽ ላይ የተጀመረው ድርሰት ስለአንድ ወጣት አፍቃሪ የሚተርክ ሆኖ፤ ወጣቱ ፍቅረኛውን ዘወትር ባገኛት ቁጥር በተዋቡ ቃላቶች ፍቅሩን እየገለፀላት በመጣ ቁጥር ሴቲቱን የሚወዳት በርሱ ስለሚነገሩት የተዋቡ ሐሳቦች የተነሳ እየመሰለው ይመጣል**

‹‹ሴቶች ለምን ይከዳሉ?››… የሚል ርዕስ አስቀመጠ

‹‹እፀ ከንቱ የምትባል ዕፅ አለች፡፡ ጠዋት ትበቅላለች፣ ረፋድ ላይ ታብባለች፣ ቀትር ታፈራለች፣ አመሻሽ ላይ ትጠወልጋለች፡፡ ከፀሐይ ጥልቀት በኋላ ባለው የምሽት ጊዜ ትረግፋለች፡፡

ሴት ልጅ እንደ ዕፀ ከንቱ ናት፡፡ አንድ ቀን እንደምትታይ፣ በዛው ቀን እንደምትረግፍ አበባ፣ ተፈጥሮዋ ችኩል ነው፡፡ ፀሐይ ልትገባ ስትል እንዳለው ውበት እየሳሳች ታልፋለች፡፡ ሴት ልጅ ሥታፈቅር እርግጠኛ መሆን ትፈልጋለች… የምትፈልገውን እርግጠኝነት ግን አትጠይቅም፡፡ ታፍራለች፡፡ ትፈራለች፡፡ ብዙ ሴቶች አፈቅረዋለሁ ከሚሉት ወንድ ላይ መስማት የሚፈልጉት ነገር ቢኖር ‹‹አገባሻለሁ!!!›› የሚለውን ቃል ብቻ ነው፡፡

ወንዶች በአገባሻለሁ እምብዛም ናቸው፣ ምንም እንኳ እህቶቻቸው ላይ ቢፈልጉትም፣ ምንም እንኳ ሌሎች ሴቶች ላይ ቢቀልዱም ‹‹ለአገባሻለሁ›› ግን ሩቅ ናቸው፡፡

ሴቶች ቀልድ አያውቁም ጊዜያቸውን ይሳሱለታል፡፡ ህይወት ላይ እንዲጣደፉ ተፈጥሮ ሰርታቸዋለች፡፡ በግድ፡፡ ሴት ስለሆኑ፡፡ የምትወዳትን ሴት ‹‹ትዳር… ልጅ.. እናት መሆን›› ትልቁ ፍላጎቷ እንደሆነ ንገራት… መውለድ ያለባትም ካንተ ብቻ እንደሆነ ቀድመህ ንገራት፡፡ ዘወትር መዳፍህ ላይ ናት ወይም እናትህ እንዳሰሩልህ የአንገት ሐብል ስጦታ ‹‹ባለህበት አለች›› ለየትኛዋም ሴት ከዚህ የሚልቅ ህልም የለም፡፡ አዲዮስ!

አንባቢ ሆይ ‹‹ብዙ ሴቶች የጋብቻ ወሬ ለማንሳት የሚጨነቁት ስለሁለት ነገር መሆኑን ልብ በል፡፡ ይኸውም ‹‹ፍቅረኛቸው ትዳርን ሸሽት እንዳይተዋቸው በመስጋትና ሁለት እድሜያቸው ገፍቷል ተብለው እንዳይገመቱ በመፍራት ነው፡፡ እንግዲህ ይህ የሴቶች አስተሳሰብ ምን ያህል ክባድና አስፈላጊያቸው እንደሆነ ከተገነዘብክ አንዲት ወዳጅህ በዚህ ቸልታህ ብትሸሽህና ሌላ ወዳጅ ለማበጀት ብትሞክር /ስታደርገው ብታያት/ ሙግቷ ከፀሐይና ከጨረቃ፣ ከትላንትና ከነገ ጋር እንጂ ከአንተና ከአሁን ጋር አይደለምና በስህተቷ ልክ ናት፡፡››

ደራሲው እያመረረ መጣ፡፡ ለስነ ጽሑፍ ስርዓት ሳይሆን ለአእምሮው ሕግ በመገዛት ድርሳኑን ቀጠለ…

‹‹ሴቶች ወንዶችን ሲከዱ ትክክል ናቸው›› የሚል ጽሑፍ ፅፎ ከስሩ አሰመረበት፡፡ እንዴት? ብሎ ሊቀጥል እንደሚችል ግራ ቢገባውም አያያዥ ቃላትን በመፈለግ ጊዜ ከመፍጀት ይልቅ ‹‹አዎ›› ብሎ ነገሩን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚሻል በማመን የጀመረውን ከጫፍ ለማድረስ ጽሑፉን ቀጠለ…

‹‹አዎ›› ሴቶች ወንዶችን ሲክዱ ረዳት አምላክ የሚሆኑበትን ትልቅ ፀጋ እናትነትን፣ ቤተሰብ የሚባል መንግሥትን፣ ልጆች የሚባሉ ሰራዊቶችን፣ ባል የሚባል ንጉስና ሚስት የምትባል ልዕልትን ማጣት ስለማይፈልጉ ነው፡፡ ወንዶች ሴቶችን ሲለዩ ግን ምንም ምክንያት የላቸውም፡፡ የዕይን አምሮትና ምኞት ብቻ ነው›› ብሎ ከጻፈ በኋላ ከጽሑፉ የሚታይ ጥያቄ ተወለደ እንዲህ የሚል…

‹‹እውነት አንተ ፍቅረኛህ ብትሸሽህ /ብትለይህ/ አሁን በጻፍከው ሐሳብ ላይ ተመስርታ ነው ብለህ ታምናለህ?›› ብሎ አንድ አንባቢ ቢጠይቀኝ ምን ብዬ መመለስ እችላለሁ ብሎ ብዙ ካሰላሰለ በኋላ፣ አንደበትን ሞልተው የሚመልሱት መልስ እንደሌለ ሲረዳ በሴቶች ላይ የተመሰረተውን ድርሰቱን መተው እንደሚሻል በማመን ተወው፡፡

ድርሰቱን ካቆመ ከሦስት ደቂቃ በኋላ ይህን የመሰለ መልካም ሐሳብ ለምን አቋርጠዋለሁ እንደውም..

‹‹ድርሰቱን ያነበቡ ብሶተኛ ወንዶች የደራሲውን ሐሳብ ሙሉ ለሙሉ አጣጣሉት፡፡ ጨካኝና በደለኞች ፍቅር ለሚባለው ነገር ምንም ዓይነት ክብር የሌላቸው ሴቶች መኖራቸውን ያስተጋቡ ጀመር›› ብዬ በወንዶቹ በኩል ሚዛናዊነትን ፈጥሬ ለምን አልፅፈውም በማለት ጽሑፉን ፈፀመ፡፡

የሲጋራውን ቁራጭ ወለሉ ላይ ጥሎ በእግሩ እየረገጠ ስለጻፈው ድርሰት ጭንቀት ይሰማው ጀመር፡፡ ‹‹እንደዚህ ዓይነት ድርሰት ሌላ ሰው ደርሶ ቢሆንስ?›› መቼም ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ይሄን የአፃፃፍ ዘዴ ያላሰበ ይኖራል ማለት በደል ነው፡፡ እሺ. ይሁና ቢኖርስ? ይኑራ ታዲያ…

‹‹እንደዚህ ዓይነት ድርሰት የደረሰ ሰው ካለማ የኔ ብዙ የተጋጋት ሌሊቶች በሐበሻ አንደበት ሊናቁ ነው ማለት ነው? ወይኔ ሌሎ ‹‹ይሄ ትልቁ የደራሲ ህመም መሆን አለበት፡፡ ይፃፍ! ማንስ ቢፅፍስ! እኔም ፃፍኩ ማንም ያው Art / ጥበብ/ እንደሆነ ዋጋ ቢስ ነገር ማለት አይደል? ማን ነው ያ ገጣሚው “All arts are quite useless” ያለው ልበላ ይባላ… ግራ የተጋባ ነገር በልቡ መከረ፡፡

የገዛ ልቡ ተቆጣው ‹‹ጥበብ ዋጋ ቢስ ከሆነ›› እነዚህ ሁሉ ድካሞችህ፣ ይሄ ሁሉ ልፋትህ ለምንድን ነው? ጥበብ ዋጋ ከሌላት በአንተና በገፀ-ባህርይህ መካከል ምን ለውጥ አለ? ዋጋ የሌለው፣ ትርጉም የሌለው ገፀ ባህርይ ለምን? ደግሞ አንድ ፈረንጅ ጠቀሰና መልካም ነው ብለህ ለምን ትፋቱን ሳይቀር ትልሳለህ… አንተ እኔ ሆይ ዞምቢ ነህ? አሣማ? በበላህበት የምትፀዳዳ፣ መከበርያህን ማፈርያ የምታደርግ በቅርፅ ስም (አመክንዮ) ለየት አልኩ ለማለት ፅንቁህን የትም የምትጥል መድረክ ላይ የምትኩስ እኔ ሆይ›› ‹‹ክራሱ ጋር ለስአታት ተጋጨ፣ ራሱን በራሱ ነቀፈ፣ ሌላም ጠየቀ›› ‹‹በተፈጥሮአቸው መፃፍ፣ መቀኘት፣ መሳል የሚችሉ ሰዎች ከፊደልና ከጽሑፍ በቀር በተቋም ደረጃ መማር የለባቸውም፣ ማንበብ የለባቸውም፡፡›› የሚል ሌላ ሐሳብ ልቡን ይሟገተው ጀመር፡፡ በሙግቱ ተሸነፈ፡፡ ላሸነፈችው ሐሳብም ተገዛላት፡፡ ያለማንበብ ጣፆትንም በመጽሐፉ ላይ ተከለ፡፡

‹‹ከላይ ባነበብነው ልክ እናስባለን አሁን ደግሞ የፈጠራ ሰዎች በፍፁም ከሥራዎቻቸው በፊት ማንበብ የለባቸውም ማለት ትክክል ነው ወይ?›› ተብዬ ብጠየቅ አለ፣ ለራሴ አለ፡፡ ለራሱ ከነ መልሱ ተዘጋጀ፡፡ አዎ እንደዛ ተብዬ ብጠየቅ እንዲህ እመልሳለሁ አለና አሰበ…

‹‹ስሙን ጠቅሰህ ግብሩን ገልጠህ በድርሰትህ ብትሰድበው ‹ሰደበኸኝ› ለማይልህ ማህበረሰብ ምን አስጨነቀህ? ‹‹ይሄ ህዝብ እንደሆነ›› አለ ሳይጨርሰው እንደ መንገደኛ ሰዎች ሆኑ፡፡ ይሄ ህዝብ የማይል ሰው በዚህ ሀገር ማንም የለም፡፡ ይሄ ህዝብ! ይሄ ህዝብ! ይሄ ህዝብ! ደሞ ለዚህ ህዝብ!

ይሄ ህዝብ ውስጥ አንቱ አክስቱና ያክስቱ ልጅ መኖራቸው ጠፋው፡፡ ይሄን ህዝብ እንቅልፉን ካመጡት ነገሮች መሃል ይሄ ህዝብ የሚለው የመንገደኞች አዝማች ነው፡፡ ይሄ ህዝብማ ሕዝብ ነበር፡፡ የምን አገባኝ ፅንስ ሀሳብ ሁለት እግሩን ሳይሰባብረው በፊት ህዝብ ነበር፡፡

ድርሰቱን ‹‹ተፈፀመ›› ብሎ ለመጨረስ አሰበና ጥሩ አጨራረስ አልመሰለውም፡፡ ፍፃሜውን ሌላ ጊዜ እንዳስለመደው ካልሆነ ደግሞ ‹‹ድርሰቱ የርሱ አይደለም ቢሉኝስ?›› ብሎ ተጨነቀ፡፡ እርሱ ብዙ ጊዜ ብርሃናማ ፍፃሜ ስለሌለው /እንደ አማናዊ ህይወቱ/ ሐዘንተኛ ፍፃሜ ለድርሰቱ ፈለገ፡፡ ‹‹የ‹ሌሉ› አጨራረስ ‘pessimistic ” ነው አናውቀውም እንዴ?›› እንዳይሉት በህሊና ው ሳይሆን በምን ይሉኛል ጭንቀት ድርሰቱን እንዲህ አድርጎ ጨረሰው፡፡

አሁን በከተማይቱ የጥበብ አራዶች የሚዘወተር አንድ ተረት አለ፡፡ የሆነ ግራ የተጋባ ድርጊት ሲያጋጥም የሚባል ‹‹ሌሎ›› ነገር ሆኗል ሁ፡፡ ይላሉ የፒያሳ ጠቢባን መላ ቅጡ የጠፋ ነገር ውስጥ ሲገቡ፡፡

ግራ የተጋባ ደርሡትም ሌሎ መንገድ ይባላል ለማንም የማይሆን የነፋስ መከዳ፡፡

## አብዛኛውን....

(ከገፅ 16 የዞረ)

ያደረገን ግን እሱ ጨካኝ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን የእኛ ባሕርይ ተለማማጭ ስለሆነም ጭምር ነው፣ እንዲያ አደብ ገዝተን የተቀመጥነው፣ ለመኖር ስንል፡፡ ዝምታችን ገዝግዞ ሊጥለን ሲደርስ ደግሞ፣ የእንጀራ ጉዳይ ይሆንብንና፣ የሆድ ነገር ይፈትነንና ለወላጆቻችን መሞት፣ ለሺሚ ሽላሚያችን መቀጠፍ ምክንያት ለሆነው ሥርዓት ታዛዥ እንሆናለን፣ ወዳዘዘን ለመጓዝ እግሩ ስር እንውተረተራለን፣ ይርጋ ዱባለ እንደሆኑት- “እምቢ ብል የት አባቴ ልገባ?” ብለን፡፡

ሲብስብን ጊዜ፣ የገዳዩ እጅ ረዝሞ፣ የቤታችንን ደጅ ሲያንኳኳ፣ የእህቶቻችንን ልጅ ሳይቀር ሲፈጅ፣ ምርር ይለንና አገር ጥለን እንጠፋለን፡፡ ስደተኛ እንሰኛለን፡ ፡ ‹‹ሰው በላው መንግስት ከአገሬ አፈር ነጠለኝ፣ ከአድባር አወጋሩ አራቀኝ›› ብለን ጥለነው የመጣነውን መንግስት እንኮንነዋለን፡፡ አስር ዓመት አብረነው ሰርተን፣ ለስንቱ መኳንንትና ምሁራን መገደል የኛ ሙያና የኛ ድምጽ ያሳደረውን ተጽዕኖ ዘንግተን፡፡ ሀዘን እቤታችን ስተት ብሎ ሲገባ ነው፣ የሌላው ኢትዮጵያዊ ህመም የሚያምመን፣ ቀንበሩ ትከሻችን ላይ ሲያርፍ ነው ክብደቱ የሚታወቀን፣ አለበለዚያ ግን ዝምተኞች ነን፣ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን ኩብለስቶን እንዲጠርቡ ጥሪ ሲደረግላቸው በደህና ጊዜ ሥራ መያዜ በጀኝ እንላለን እንጂ፣ የዚህ ትውልድ ጉዳይ ይመለከተኛል አንልም፣ ተመራቂ ስንሆን ወይም ተመራቂ ቤተሰብ ሲኖረን ግን አያስችለንም. . .

ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነው ሥርዓት ተገርስሶ፣ አገሪቷ በለውጥ ማዕበል ስትጥለቀለቅ ፣ ከየ አደፈጥንበት ብቅ ብቅ ማለት እንጀምርና ‹‹ባለፈው ሥርዓት ተጠቂ ከሆኑት መሀል አንዱ ነኝ›› እንላለን፣ ‹‹አቤት በእኔ ላይ የደረሰው ፍዳ፣ አቤት ለዴሞክራሲ ለፍትህ እና ለነፃነት የከፈልኩት ዋጋ›› ብለን፣ በአዲሱ መንግስት የከበረ ቦታ ለማግኘት ራሳችንን እናዋድዳለን፣ ‹‹ጭለማ ውስጥ ነበርኩ አሁን ነው የነፃነት ፀሀይ የበራልኝ›› እንላለን፣ አስር ዓመትም ይሁን ሃያ አንድ ዓመት ያ የተሸነፈው መንግስት በዋለበት እየዋልን፣ ስንዘምር፣ ስናሸበሽብ፣ ቅኔ ስናዘንብ፣ መወድስ ስናጎርፍ እንዳልቆየን፣ ‹‹ተገድጄ ነው፣ ለሆዴ ብዬ ነው እምቢ ብል የት አባቴ ልገባ ብዬ ነው፣›› ስንል እንቀይና፣ አዲሱ መንግስት ፊት ስንቀርብ “. . . ምነው ግብር የጠራኸኝ፣ ይበቃኝ የለም ወይ . . . ነፃ ያወጣኸኝ” እንላለን፡፡

. . . አዎን፣ አንዳንዶቻችን እንዲህ እንደ ይርጋ ዱባለ ዓይነት ዕጣ ፈንታ ይከተለናል፣ ሀገሪቷ የተፈጋጋች የሚመስለን እኛ በገጠመን ስኬትና ሀሴት ልክ ነው፣ ከስደት መመለሳችን፣ ቤት መግዛታችን፣ በሰላም መኖራችን በቂ እንደሆነ ይሰማናል፣ ሌሎችን አናይም፣ ሌሎች አገሪቷ በምትከተለው አመራር ሰበብ ዘር ለይተው ጎሳ መርጠው የመወዳጀት አባዜ እንደተጸናወታቸው ልብ አንልም፣ በብሔሩ ምክንያት ከኖረበት ቀዬ ተፈናቅሎ ወደ ዘርማንዘሮቹ እንዲቀላቀል ግዳጅ የተጣለበትን ቤተሰብ አናይም፣ የመከፋፈል፣ የመለያየት እና ለራስ ወገን ብቻ ጥብቅና የመቆም አዲስ የዘረኝነት መንፈስ በዙሪያችን እንዳንገፐበበ አናይም፣ የምናየው ራሳችንን ነው፣ ለዚህም ነው ቶሎ ብለን ትናንት ከነበረው ስርዓት ጋር አነፃፅረን፣ ለአዲሱ መንግስት የምስጋና መባ የምናቀርበው፣ የአዝማሪነትን ሚና የምንጫወተው፡፡

እናም አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰብስቦ፣ በአምስት ወይም በስድስት መስመር እንዲሰለፍ ቢደረግ፣ ‹ለድፍረቱ ይቅርታ ይደረግለትና›፣ ብዘዎቻችን ከይርጋ ዱባለ ኋላ የምንሰለፍ ነን፣ የምንመሳሰልባቸው ነገሮች ይበዛሉ፣ የተሰማንን ጮክ ብለን ለመናገር በፍርሃት የምንዋጥ፣ ለእንጀራ ብለን ላላመንበት ጉዳይ ሙያችንን የምንሸጥ፣ ቁጭት እና ብሶት እጅግ ሲጠነክርብን ስደትን የምንመርጥ፣ አዲስ መንግስት ሲመጣ ደግሞ በሌሎች ላይ ከደረሰው ሺህ ሞት ይልቅ እኛ ዘንድ ለመጣው ሹመት እልልታችንን የምናስደምጥ፣ የወጣቶችን ጭንቀላት ከወረረው የተስፋ መቁረጥ ሽበት ይልቅ ወደኛ እየቀረበ ላለው ሺህ ውበት ደስታችንን የምንገልጽ…

## የቀዳማዊ....


(ከገፅ 7 የዞረ)

የአምስት ሃገራት የጥናት ኮሚቴ ኦጋዴንን ጣ
ሊያን እንዲያለማውና እንግሊዞች የዘይላ ወደብን
ኢትዮጵያ እንድትጠቀምበት እንዲፈቅዱ ቀዳማዊ
ኃይለሥላሴ ሲቀበሉት ሙሶሎኒ እምቢተኛ መሆ
ኑና ንጉሠ ነገሥቱ የጦር ዝግጅት ከማድረግ በ
ዲፕሎማሲ ላይ መተማመናቸውን የመሳሰሉ ቁ
ምነገሮችን ያካተተ ነው። ሌላው ቀልቤን የሳበው
የብሪታኒያው ተወካይ አንቶኒ ኤደንና የካናዳ አቻ
ው፣ የሙሶሎኒ ወረራ በተጀመረ በ15ኛው ቀን፣
የነዳጅ ዘይት፣ ከሰልና ብረታ ብረት እገዳ እንዲ
ደረግበት ለኮሚቴ 18 ሃሳብ ሲያቀርቡ፣ ሙሶሎ
ኒ እጅግ ከመንጸርጸሩ የተነሳ ትግራይንና ኦጋዴ
ንን መውሰዱን ንጉሱ ከተቀበሉ፣ ወረራውን ሊያ
ቆም ሃሳብ ወጥኖ የነበረ መሆኑን፣ ዘውዴ መረ
ጃውን እየፈለፈሉ ያቀርቡልናል። ሆኖም አሜሪ
ካና ጃፓን እኛ እናቀርብልሃለን ሲሉት የድርድር
ሃሳቡን መተውንም ያካፍሉናል ። ከጁላይ 4 በአ
ል ጋር በተያያዘ ኤን.ፒ.አር የሚባል የዲሲ ሬዲ
ዮ ሲዘግብ እንደሰማሁት፣ አሜሪካ ሙሶሎኒን በ
ምታደፋፍርበት ሰሞን፣ የአፍሪካዊ አሜሪካውያ
ን መኖሪያ ቤቶች በእሳት እየጋዩ ነበር ። ምክን
ያት ሆኖ የተገኘውም ጥቁር የቤት አገልጋይ እ
መቤቱ መኝታ ቤት ቢላዋ ይዞ በመገኘቱ ነበር ።
ማን ያውቃል ምናልባት የጥቁሯ ኢትዮጵያ ነፃነ
ት መደምሰስ ለነጭ የበላይነት አስፈላጊ ነው ተ
ብሎ ታምኖበት ሊሆን ይችላል ዋይት ሀውስ ያ
ን ዓይነት አሳፋሪ ዝምድና ከሙሶሎኒ ጋር ለመ
ጀመር የዳዳው ።

ደራሲው ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያላቸው አክ
ብሮትና ፍቅር ጥልቅ በመሆኑ፣ ምናልባት የሚሸ
ፋፍኑት ጉዳይ ይኖራል ብሎ ለተጠራጠረ አንባቢ
እንኳ አይመቹም። ለምሳሌ በልጅ ኢያሱ አሟሟ
ት ላይ "የዚህ መጽሃፍ ደራሲ... ኢያሱ አባ ጤና
ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በህመም ወይም በ
ድንገተኛ አደጋ ሳይሆን በፖለቲካ ውሳኔ መሆኑ
ን ያምንበታል" (ገፅ 226) ይሉናል። ከኔ ትውል
ድ ሰዎች የኢጭአቱን፣ የኢሰፓውን፣ የመኢሶኑ
ን፣ የኢህአፓውን፣ የህውሓቱን አመራር ወንጀሎ
ች በምንደብቅበት ሰአት፣ "የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ
መንግሥት" ደራሲ ግን፣ የሚያከብሯቸውን ንጉ
ሥ ድክመት ለመሸፈን አልዳዳቸውም። ይህ ራሱ
ትልቅ ትምህርት ሆኖ አግኝቼዋለሁ ።

አምባሳደር ዘውዴ፣ ከነፃነት መመለስ በኋላ
በእንግሊዞች አስገዳጅነት ጥር 23 ቀን 1934 አም
ስለተፈረመው ውልና ስለተፈጠረው ሞግዚታዊ
አስተዳደር፣ ከዚህ ጭቆና ለመላቀቅ ቀዳማዊ ኃይ
ለሥላሴ ከመሳፍንቱ፣ ከአርበኞችና፣ ከወጣት ሚ
ኒስትሮቻችው ጋር በመሆን እንዴት በትዕግስት
እንደተወጡት ከዩናይትድ ስቴትስ አርካይቭ እስ
ከ ለንደን ቤተ መዛግብት በመኳተን ተደብቆ የኖ
ረውን ታሪክ ባፍ ባፋችን ያጎርሱናል። ወጣቱ ዲ
ፕሎማት አክሊሉ ሀብተወልድ የማይናቅ አገልግ
ሎታቸውን ሲጀምሩም እናያለን። ልጅ ይልማ ዴ
ሬሳ በወቅቱ ሩዝቬልት ጋ ቀርበው በማስረዳት የ
አሜሪካውን መሪ ከኢትዮጵያ ጎን ለማሰለፍ በመ
ቻላቸው የእንግሊዞችን የቅኝ ግዛት ህልም እንዴ
ት እንዳከሸፉባቸው እንማራለን። በዚህ ክፍል አ
ንድ ቀልቤን የሳበው ጉዳይ፣ ሁለተኛውን የአዲስ
አበባ ውል ለመፈረም ከመጣው የብሪታኒያው ሎ
ርድ ደላዋር ጋር ጃንሆይ ሲነጋገሩ "በእንግሊዞች
ቤት ተቀጥረው የሚያገለግሉትም ሆኑ፣ እንግሊ
ዞች በሚያዘወትሩት ሆቴሎችና ቡና ቤቶች የሚ
ሠሩት ኢትዮጵያውያን የሚደርስባቸው የዘር ልዩ
ነት በደል እጅግ የሚያሳዝን ነው" በማለት ለዘመ
ናችን ገዢዎች በሚጠቅም አርአያነት ሲናገሩ እ
ንሰማለን ። ዛሬ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያ
ዊቶች የመካከለኛው ምሥራቅ የቤት ሠራተኞች
በመሆን ለሚደርስባችው በደል፣ ሬሳ ከመላክ ው
ጪ፣ ኤምባሲዎቻችን የሚያሳዩትን ደንታ ቢስነ
ት ላወዳደረ፣ ታላላቆቻችን ታላቅ፣ ልጆቻቸው ፍ
ሬ ከርስኪ መሆናችንን ነው የሚያስረዳን ።

ዘውዴ የመንግሥቱ የውስጥ አሠራርና የው
ሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ፣ የጽህፈት ሚኒስቴር
መዛግብት ውስጥ ተደፍተው በማጥናት በቀላሉ
የማይገኙ ጉርሻዎች ያቃምሱናል ። ቀዳማዊ ኃ
ይለሥላሴ ሚኒስትሮቻችው መሃል በቡድን አቋ
ም የመያዝ ዝንባሌ ያዩ ሲመስላቸው "...ብዙ ጊ
ዜ እየተደጋገመ እንዳየነው፣ እኛ በም
ናደርገው ስብሰባ ላይ ይልማ ዴሬሳ
ና አክሊሉ ሀብተወልድ እየተደጋገፋ
ችሁ ታላላቆቻችሁ የሚያቀርቡትን
ሓሳብ መቃወምና የራሳችሁን ትል
ቅ አስመስሎ መናገር፣
እንደ መልካም ሥራ
አድርጋችሁ የም
ትቆጥሩት ይመ
ስላል። እርግጥ ነ
ው፣ አንድ ጉዳይ በጉባኤ ቀ
ርቦ ሲጠና፣ እያንዳንዱ ሰው የተ
ለያየ ሓሳብ ሊኖረው ይችላል። ይ
ህም የዘመኑ አሠራር የሚጠይቀ
ው ነው ብለን እንቀበለዋለን። ነገ
ር ግን፣ በየስብሰባው ላይ ሁለት
ና አንዳንድ ጊዜም ሦስት ሰዎች፣
በአንድ ጉዳይ ላይ ሲደግፉም በአን
ድነት፣ ሲቃወሙም በአንድነት እየ
ሆኑ የምናያቸው፣ ወደ ፓርቲ ያዘነ
በለ አሠራር ነው እንጂ፣ የዴሞክራ
ሲን ወግ የተከተለ ነው ማለት አይ
ቻልም" ይሉናል። መኮንን ባር፣ ኪሪያ
ዚስና ጆሊ ባር ተቀምጠን ስናወግዛቸው የነበሩት
ባለሥልጣናት እንዲህ አይነት ውይይት ያደርጉ
ነበር ብለን እንኳ ለመገመት ጠርጥረንም የምና
ውቅ አይመስለኝም።



የኢትዮጵያን የጥንት ባህል አብጠርጥረ
ው የሚያውቁት ልዑል ራስ ካሣ ሀይሉ
በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘንድ ያላቸው ተደማጭነ
ት ከፍተኛ በመሆኑ፣ ሁለት ወሳኝ ወቅቶች ላይ
ሃሳባቸውን ሲያስቀይሯቸው እናያለን። በመጀመ
ሪያው፣ ከማይጨው ሽንፈት በኋላ ለጦሩ የማፈ
ገፈግ ትዕዛዝ እንዲሰጡና ራሳቸውም ወደመናገሻ
ቸው እንዲመለሱ ያስገደደ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣
ስዊዝ ካናል ላይ ቸርችልን አልገናኝም ሲሉ እንዲ
ያነጋግሩት የተገደዱበት ሁኔታ ነው። የዚህ ጠቀ
ሜታው ግልፅ ሆኖ ታየኝና፣ ምን ታሰበኝ መሰላ
ችሁ? መንግሥቱና መለስ ይህ ዕድል ያልገጠማ
ቸው ሆኖ ተሰማኝ። ደግሞም፣ ለፕሬዝዳንትነት
የሚታጨው ሰው፣ ነፃ አሳቢ ሆኖ ጠቅላይ ሚኒ
ስትሩን መገሰፅና ሃይ ማለት የሚችል፣ ለምሳሌ
የፕሮፌሰር መስፍን ዓይነት ዜጋ ቢሆንስ ብዬ ከ
ራሴ ጋር ተነጋገርኩ ።

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መኮንን እንዳልካቸው ይ
በልጥ ተሰሚነት የነበራቸው ለአመታት የንግድና
እርሻ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መኮንን ሀብተወል
ድ ከአድአ ቀሳውስት ቤተሰብ የተወለዱ የድሃ ወ
ገን ቢሆኑም፣ አድራጊ ፈጣሪ ከመሆን እንዳላገዳ
ቸው በክፍል ሰባት ውስጥ ለ140 ገጾች ታሪኩ ይ
ተነተናል። የመኮንንን የለውጥና ጥገና ውጥኖችን
ለተመለከተ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት
ገጾች ውስጥ የራስ አበበ አረጋይን፣ የራስ ካሣንና
ሌሎችንም ታላላቆች ክርክርና አስተያየት ላስተዋ
ለ፣ የሃገራችን ትምህርትና አስተዳደግ ለአመራር
ብቃት ያላቸው ሰዎች ለማፍራት አቅም እንደነበ
ረው እንገነዘባለን ። ለምሳሌ አንድ የገረመኝ የመ
ኮንን ሀብተወልድ ሪፎርም፣ በጣሊያን ጊዜ ሃገሪ
ቱን ያጥለቀለቁትን የየመን ነጋዴዎች በአዋጅ ከ
ማባረር፣ ጉራጌዎች ከሚኖሩባቸው ወረዳዎች ታ
ታሪዎቹ ተመርጠው ከመንግሥት ለዘር የሚሆ
ን ብድር ተሰጥቷቸው የንግድ ሱቆች እንዲከፍቱ
ና በውድድር እንዲያሸንፏቸው በመደረጉ፣ እስቀ
ድሞ "የአረብ ቤት" ይባሉ የነበሩ ሱቆች በእኔ ዕ
ድሜ ወደ "ጉራጌ ሱቅ"ነት ሊቀየሩ ችለዋል ። ለ
መኮንን ሀብተወልድ ሃገር ወዳድነትና አርቆ አስ
ተዋይነት ቀላል ምሳሌ ይመስለኛል ።

መኮንን ሦስቱን ወንድሞቻችውን የአውሮፓ
ትምህርት ለማስተማር፣ ከዛሬ 93 አመት በፊት
ጥር 24 ቀን 1911 አም ከእንጦጦ ራጉኤል የቆ
ሎ ተማሪነት፣ ወደ አዲስ አበባ መኖሪያ ቤታቸ
ው ካመጧቸው በኋላ ይሰጧቸው ስለነበሩት ም
ክር፣ ደራሲው ከሦስቱ የሀብተወልድ ልጆች ጋ
ር በመነጋገር ጨምቀው ያቀረቡልን "ምክር መስ
ጫ" ፕሮግራም፤

1. "...ወደፊት ኢትዮጵያ የፈረንጆቹን ሥል
ጣኔ ለመቀበል የምትችለው፣ ከገባር ጭቆና አስተ
ዳደርና ከመኳንንት ገዢነት ስትላቀቅ ነው

2. ...መኳንንትና የመኳንንት ወገኖች ዘመና
ዊውን ትምህርት አንማርም በማለታቸው፣ ለድ
ሆች ልጆች ጥሩ ዕድል ከፍተዋል

3. ...የድሆች ልጆች ጠንክረው ከተማሩ፣ በ
ዕውቀታቸው የአስተዳደሩን ሥልጣን ወስደው የ
ኢትዮጵያን ሕይወት ማሻሻል ይችላሉ

4. ...ወደፊት የመኳንንት ወገን ሳይማር እን
ደዚሁ ከቀጠለ፣ የአባቱን ሀብት እንጂ፣ አባቱ ይ
ዞት የነበረውን ሥልጣን አይወርስም

5. ... የአልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን አመራር
ብዙ ተስፋ የሚሰጥ ነው ። በዚህ አኳኋን ከቀጠ
ለ፣ ኢትዮጵያ ከጨለማ ወደ ብርሃን ለመሻገር ዕ
ድል አላት..."(ገፅ 551) የሚሉ ነበሩ ።

እነዚህ ነጥቦች የዘመኑን ታላቅ ባለሥልጣን
የመኮንን ሀብተወልድን ሃሳብ ጨምቀው የያዙ ና
ቸው ። በደራሲው ደግነት፣ ጥልቀት፣ ትጋት መ
ደነቅ የግድ ነው ። ከባለሥልጣናቱ የግል ማህደ
ርና የቤተሰብ ጨዋታ ሳይቀር ፍትፍት አድርገ
ው በአፍ ባፋችን ያጎርሱናል ። እጅግ ከባድ ውለ
ታ እንደዋሉልን ነው የሚሰማኝ ።

መጋቢት 18 ቀን 1939 አም በጠቅላይ ሚ
ኒስትሩ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፣ በአቶ
መኮንን ሀብተወልድና በጸሀፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮ
ርጊስ መካከል፣ የምእራቦችን ክስ ለማርገብና ሃገ
ራቱንም ለማዘመን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አንድ ም
ክር ይዘው እንዲመጡ በሰጧቸው መመሪያ መ
ሠረት፣ በሦስቱ መሃል የተደረገው ውይይት፣ የ
ሁለቱን ጓደኛሞች ሃገር የማዘመን ርዕይ ፍንት
ው ያደርጋል። መድረኩ የጭሰኛና ጉልተኛ ግንኙ
ነትን እስከ መወሰን የሚደርሱ ሃሳቦች የቀረቡበ
ት እንደነበር እናጤናለን ፡፡ ሆኖም ጸሀፌ ትዕዛዝ
ደክመው ያቀረቡትን ረቂቅ ቢትወደድ እንዳልካቸ
ው ከወሰዱት በሁዋላ የቀን ብርሃን ሳያይ እንደቀ
ረ ታሪኩን የምንከታተለው በቁጭት ጭምር ነው
፡፡ ለቁጭትም መነሻ የሚሆነው፣ በ1953አ.ም ለ
ተሞከረው መፈንቅለ መንግሥትም ሆነ፣ ኋላ ለ
ተከተለው የየካቲት አብዮት፣ ወጣቱና ምሁሩ በ
ሥርዓቱ ላይ አምርረው እንዲነሱ ትልቁን አስተ
ዋጽዖ ያደረገው ትሁቱና ሩህሩሁ የኢትዮጵያ ገባ
ር የሚገኝበት አስከፊ ሕይወት ነው ፡፡ ገባሩ፣ ታ
ርዞ፣ ተርቦ፣ በቀላል ተላላፊ በሽታዎች አልቆ፣
በወባ ተቆልቶ የሚኖርበት ከባርነት ያልተሻለ ሕ
ይወት የእኔ ትውልድ ሊቀበለው ያልቻለ የሕሊ
ና ቁስል ሆኖበታል ፡፡ የጸሀፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊ
ዮርጊስ የለውጥ ሃሳብ የመሬት ሥሪት መሻሻል
ን አስከትሎ ቢሆን ኖሮ ምናልባት የተማሪው ን
ቅናቄ ሥር ነቀል ባህሪ እንዳይኖረው ይረዳ ነበር
ብዬ አስባለሁ ፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ከዚህ የጸሀፌ ትዕዛዝም
ሆነ ከሳቸው በኋላ ከመጡት የለውጥ ሐዋርያት
ህልም ወደ ቅዠት መቀየር እኔ በግሌ የተማርኩ
ት ነገር ቢኖር፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮ
ጵያ ገባር ጫንቃዬን ከበደኝ፣ መሸከም አልቻልኩ
ም፣ "እኔም በሰብአዊነቴ ከፈጣሪዬ ጋር የምጋራ
ቸው የማይነኩ መብቶች አሉኝ" ብሎ እምቢኝ! አ
ሻፈረኝ! እስካላለ ድረስ፣ ሕልመኞች እርስ በርስ
ይተላለቃሉ፣ ሃገሪቱም በኋላ ማርሽ ቁልቁል ት
ወርዳለች ፡፡ ትልቁ ችግር ሆኖ የተሰማኝ፣ ኢትዮ
ጵያ ዜጎች አልነበሯትም፣ ዛሬም የሏትም፣ ወደፊ
ት ግን ያለዜጋ እንደ ሃገር መቀጠል የማትችልበ
ት መስቀለኛ መንገድ ላይ እየደረሰች ይመስለኛል
፡፡ ወይ ገባሮቿ ተነስተው ዜግነታቸውን ይጠይቃ
ሉ፣ አልያም፣ የሞት/ሽረት ሚዛን ላይ እንዳቃሰ
ተች የወሮበሎች የጦር አውድማ ትሆናለች ፡፡ ወ
ንድሞቼ! እህቶቼ! ገባሮቿ ዜግነታቸውን እንዲጠ
ይቁ የሚረዳቸውን ሁሉ ለማድረግ እንስነፍ ፡፡ እ
ንጻፍ፣ እንግጠም፣ እንቀኝ፣ እንሽልል፣ እንተው
ን፣ እናጥና፣ ከሁሉም በላይ ግን ሁላችንም የአን
ድ ኢትዮጵያ ልጆች በመሆናችን እንከባብር፣ እን
መካከር፣ እንደማመጥ፣ እንተማመን ፡፡

በየኤርትራ ‹‹ጉዳይ›› መጽሃፍ ውስጥ በጥል
ቅ የተዋወቅናቸው ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀ
ብተወልድን በ "ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት"
ገጾች ውስጥ ይበልጥ እንተዋወቃቸዋለን ፡፡ ለምሳ
ሌ፣ መስከረም 6 ቀን 1947 አም ከ24 አመታት
የከንፈር ጓደኛቸው ከማድሚዜል ኮሌት ቫላድ ጋ
ር በወንድማቸው ቤት የጋብቻ ቃል ኪዳን ሲያስ
ሩ፣ እንደ አባት ሆነው ያሳደጓቸው ወንድማቸው
አቶ መኮንን ሀብተወልድ አልተገኙም ፡፡ ወንድማ
ቸው ለምን እንዳልተገኙም ሲጠይቁ ከአቶ አካለ
ወርቅ የተሰጣቸው መልስ "ሁለት ፈረንጆች ሲጋ
ቡ እኛ ምን እናደርጋለን እያለ ሲቀልድ ነበር" የ
ሚል ነው ፡፡ በዚህ ይጣሏቸዋል ቢያንስ ቅር ይሰ
ኛሉ ብዬ ስጠብቅ "በማግስቱ ጠዋት እኔ ቤተመን
ግስት ስገባ፣ አቶ መኮንን ሲወጣ አገኘሁት ፡፡ ከ
ሰላምታ በስተቀር እሱም ጋብቻዬ በመፈፀሙ እን
ኳን ደስ አለህ አላለኝም፣ እኔም ለምን ሳትመጣ
ቀረህ ብዬ አልጠየኩትም" ይሉናል ፡፡ ይህ እንግ
ዲህ ከዛሬ 57 አመታት በፊት ነው ፡፡ እስቲ ከኛ
ው ዘመን የቤተሰብ ግንኙነት ጋር አስተያዩት?
በመከባበርና ነፃነት ላይ የተመሠረተ ወንድማ
ማችነት እንደነበራቸው ነው የምንገነዘበው ፡፡
"ሥራ በዝቶበት ይሆናል፣ ፈረንጅ በማግባቴ
ስላልተደሰተ ይሆናል" ወዘተ ብለው ጸሀፌ ት
ዕዛዝ አክሊሉ ማሰላሰላቸው አይቀርም ፡፡ ሆኖ
ም የወንድማቸውን ውሳኔ ተቀብለው በፍቅር
ቀጥለዋል ፡፡ ድንቅ ነው ፡፡ ልንማርበትም ይገ
ባል ፡፡ እህታችን አንድ ነገር ብታደርግ፣ ያን
ያደረገችበት 10ሺህ ምክንያት ሊኖራት ይችላ
ል ፡፡ እኛ ከገመትነው ውጪ ፡፡ ለዚያ የሚገባ
ውን ክብደት መስጠት እንጀምር ፡፡ ህይወታች
ንንም ከመወሳሰብ ያድነዋል ፡፡ አክሊሉ ሀብተ
ወልድ እንኳ ከአመታት በኋላ "...ወደ ኋላ ተ
መልሼ ሳሰላስል፣ ... የእኔ ጋብቻ ሲፈጸም አ
ቶ መኮንን ያልመጣበት ዋናው ምክንያት፣ ጸ
ሀፊ ትዕዛዝ [ወልደ ጊዮርጊስ] `ምስክሬና ሚዜ
ዬ በመሆናቸው፣ አብሮ ለመገኘት ባለመፈለጉ
መሆን አለበት..."(ገፅ 722) ይሉናል ፡፡

ከአውሮፓ ጉብኝት መልስ፣ ኅዳር 27 ቀ
ን 1947 አም ወልደ ጊዮርጊስ ከንጉሠ ነገሥቱ
ጋር አዲስ አበባ ሲገቡ፣ ከመኮንን ሀብተወልድ
ጋር የሚለያዩበት መድረክ፣ የመጽሀፉ ኤፒክ
ድራማ ሆኖ ታይቶኛል ፡፡ የኢትዮጵያ ተውኔ
ት አባት የነበረውን ፀጋዬን የተካ ባለቅኔ ቢገ
ኝ፣ በመድረክ ላይ የማይጠገብ ድንቅ ሥራ ይ
ወጣዋል ፡፡ በወልደ ጊዮርጊስ እንግዳ መቀበያ
ክፍል ሁለቱ ጓደኛሞች

ሲወያዩ፣ ጸሀፌ ትዕዛዝ እንዲህ አሉ፣ "አ
ንተ እኮ ጃንሆይን እንደ መለኮት እንጂ፣ እን
ደ ሰው አታያቸውም ፡፡ እንደ ሰው ጥሩ የሚ
ሠሩት አለ ፡፡ እንደ ሰው የሚያበላሹትና የሚ
ጎዱት አለ ፡፡ እኛ በቅን ስናገለግላቸውና ስን
ረዳቸው፣ እንዳይሳሳቱ መጠበቅና፣ የሚያደር
ጓቸውንም ስሕተቶች እንዲያርሙ ከመናገርና
ከማስረዳት መቆጠብ የለብንም ፡፡ በዛሬው ሰአ
ት አንተንና እኔን የሚለያየን ትልቁ ነገር፣ በ
ዚህ በጃንሆይ ጉዳይ ነው" ይሏቸዋል ፡፡ መኮን
ንም ሲመልሱላቸው "አንተንና እኔን ያቀራረበ
ንና እንደ ወንድማማች ሆነን ያስተባበረን ጃን
ሆይን ይዘን፣ የጃንሆይን ዕምነትና ድጋፍ አግ
ኝተን፣ ወገናችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመሳፍን
ት አገዛዝ ለማላቀቅ እንችላለን ብለን ነው ፡፡ በዚ
ህ መሠረት ... ሁሉንም ባይሆን ብዙዎቹን አሸ
ንፈናል... ደግሞስ አንተ ለአገራችን መሻሻል ያለ
ህ ሃሳብ ከእሳቸው የፈጠነና ከእሳቸው የተሻለ ሆ
ኖ፣ እሳቸው እንቅፋት ሆነው እንዳትሠራ ያደረ
ጉህ መቼ ነው?...እንደ ኢትዮጵያ በመሰለው አገ
ር በመሪና በአገልጋይ መካከል ሙግት ሲፈጠር፣
ፍጻሜው ጠብ ነው ፡፡ ጠብ ሲደርስ ደግሞ አሸና
ፊው መሪው ነው ፡፡ ተሸናፊው አገልጋይ ደግሞ
መጨረሻው የትም ወድቆ መቅረት ነው ፡፡... ለ
አንተና እኔ ዋስትናችን ጃንሆይ ብቻ ናቸው"4 (ገ
ፅ 727) ብለው ይሞግቱዋቸዋል ፡፡ እንደ ልማዳ
ቸው እራት እንኳ አብረው ሳይበሉ ይለያያሉ ፡፡
ከመኮንን የግል ማህደር ነው ደራሲው ይህን የ
ሚያካፍሉን ፡፡

**የ ሙሶሎኒ ወረራ በተጀመ
ረ በ15ኛው ቀን፣ የነዳ
ጅ ዘይት፣ ከሰልና ብረታ
ብረት እገዳ እንዲደረግበት ለኮ
ሚቴ 18 ሃሳብ ሲያቀርቡ፣ ሙ
ሶሎኒ እጅግ ከመንጸርጸሩ የተነ
ሳ ትግራይንና ኦጋዴንን መውሰ
ዱን ንጉሱ ከተቀበሉ፣ ወረራው
ን ሊያቆም ሃሳብ ወጥኖ የነበረ
መሆኑን፣ ዘውዴ መረጃውን እ
የፈለፈሉ ያቀርቡልናል**

ይህ ቀን እንደሚመጣ አስቀድመው የተነበዩ
ት በወቅቱ በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበ
ሩት አቶ ይልማ ዴሬሣ` ናቸው ፡፡እኤአ መስከረ
ም 1971 አም ደራሲው ለአሥር ቀናት ከጠቅላ
ይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ጋር ፓሪስ ላ
ይ በሰነበቱባቸው ጊዜያቶች ነው የይልማን ትን
ቢት ያጫወቷቸው ፡፡ አክሊሉ እንዲህ ይላሉ "ወ
ዳጄ ይልማዴሬሣ ... ጸሐፌ ትዕዛዝ ከመሻራቸ
ው አንድ አመት በፊት፣ በዋሽንግተን ተገናኝተን
ትእየበላን ስንጨዋወት...ስማ አክሊሉ  ለኝ...እ
ንደምታውቀው እነዚ ን ሁለት ሰዎች በሥልጣ
ን በየደረጃው እያሳደጉ እንዲስማሙና እየተደጋ
ገፉ ጃንሆይን የሚጠቅም አገልግሎት እንዲሰጡ
ያደረጓቸው ራሳቸው ጃንሆይ ናቸው ፡፡ ወደፊት
ም አጣልተው የሚለያዩዋቸው ጃንሆይ ራሳቸው
ናቸው ፡፡ በመጨረሻም፣ ከሁለቱ መካከል የሚያ
ምኑትን አስቀርተው፣ የሚጠረጥሩትን ያባርራሉ
፡፡ ይህንንም ስል፣ ታማኝ አድርገው የሚያስቀሯ
ቸው ያንተን ወንድም ሲሆን፣ ተጠርጣሪውና ተ
ጠቂው ወልደጊዮርጊስ ይሆናሉ ማለቴ ነው" (ገፅ
780) ይሉናል ፡፡ መጽሃፉም ጸሐፌ ትዕዛዝ ወል
ደ ጊዮርጊስ ተሽረው ግንቦት 6 ቀን 1947 አም
ወደ አርሲ መንገድ ሲጀምሩ ይገባደዳል ፡፡ አንባ
ብያን ሁሉ በሐዘን እንሸኛቸዋለን ፡፡ ልብ የሚያ
ንጠለጥል ድራማ ነው።

ለማጠቃለል፣ ይህን "የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ
መንግስት" ታሪክ፣ በዚህ በቀረበበት ስፋትና ጥ
ልቀት እንዲሁም ለዛ፣ ከአምባሳደር ዘውዴ በቀ
ር ማንም ማቅረብ አይቻለውም ነበር ፡፡ ከሃርቫር
ድ ወይም ኦክስፎርድ ዱክትርና በማግኘትም እን
ኳ ሊደረስበት የሚቻል አይመስለኝም ፡፡ ከንግሥ
ተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፀሃፊና ቀዳማዊ ኃይለሥ
ላሴ ላይ ቅሬታ ከነበራቸው አባት መወለዳቸው፣
የቤተመንግስት ዘጋቢ በመሆን በጋዜጠኝነት በመ
ሥራታቸው፣ ለመኮንንና አክሊሉ ሀብተወልድ የ
ነበራቸው ቤተኝነት፣ ከቤተ መንግስቱ ባለሟሎች
ጋር የነበራቸው ቅርበት፣ ከጣሊያንና ፈረንሳይ ከ
ፍተኛ ባለሥልጣናት (ከነአልዲሞሮ) ጋር የነበራ
ቸው ጓደኝነት፣ ከሁሉም በላይ ግን በኢትዮጵያ
ጥናት ውስጥ ሁሌም መንምኖ የሚገኘው ለሥራ
ታታሪ የሆነው ሥነ ምግባራቸው ለዚህ ልዩ ተል
ዕኮ አዘጋጅቷቸዋል ፡፡ በእኔ ዕምነት አምባሳደር ዘ
ውዴ ተልዕኮውን በሚገባ ተወጥተውታል።

በመጨረሻ፣ አምባሳደር ዘውዴ ይህን ሲያዩ
ት የሚከብድ፣ ሲይዙት የማይጠገብ እጅግ አድ
ካሚ የነበረ ታላቅ ሥራ፣ ከዕድሜ፣ ከበሽታ፣ ከ
ብቸኝነት ጋር እየታገሉ የኢትዮጵያችን ሥልጣኔ
ፀሃይ ከመጥለቁ አንድ ሰአት አስቀድመው ደርሰ
ው፣ የታሪክ ማዕዱ ላይ የተራረፈውን እየተቃመ
ስን ቀስ ብለን ማዝገም እንድንችል በመጨነቅ ፣
አይዞን ላሉን ታላቅ ሰው ክፍያችን ምን ይሆን?
ውለታ መላሽ ያድርገን ከማለት በቀር የምጨም
ረው የለኝም። አመሰግናለሁ።

# የኢህአዴግ ፈተና፡-

ዳዊት ታደሰ እና
ሙሉነህ አያሌው

በወቅታዊው የአገራችን ፖለቲካ ትኩሳት ዙሪያ የተለያዩ ወገኖች የተለያየ አስተያየት ሲሰነዝሩ ይሰማል። የትኛው ትንታኔ እና አካሄድ ትክክል ነው የሚለውን ለመበየን ያመች ዘንድ የማህበረሰቡን የፖለቲካ ባህል፣ አመለካከትና ልዩነት በአንድ ወገን ወስደን፤ በስልጣን ላይ ያለውን መንግሥት የሚያስተዳድሩ አካላት የአገዛዙ ‹‹ባህሪ እና ባህል ነው›› እያሉ የሚጠሩትን አስተያየት በሌላ ወገን ወስደን ማየት የተሻለ ይሆናል። በዚህ መሰረት አሁን ካለው ወቅታዊ እና ነባራዊ ሁኔታ ትይዩ የሚሆኑ ጥቂት ነጥቦችን በአስረጂነት በመውሰድ የተለያዩ ወገኖች ለመከራከሪያነር ያነሷቸውን ጭብጦች ውሃ እንደሚቋጥሩና እንደማይቋጥሩ በመገምገም ጉዳዩን ለመረዳት እንሞክር።

በአሁኑ ወቅት በጥቅሉ በአገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ውዝግንብር ዙሪያ አስተያየት እየሰጡ ያሉ ግለሰቦች የመኖራቸውን ያህል በአገሪቷ ውስጥ ምንም ያልተፈጠረ ያህል በዝምታ የተዋጡ መኖራቸውንም መዘንጋት የለብንም። ለእነዚህ ግለሰቦች ዝምታ የመረጃ ክፍተትን እንደ ምክንያት ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም የተቀሩት መረጃው እያላቸው ዝምታን በመረጡ ግለሰቦች ዙሪያ ግን የሚያሳዩትን ቸልተኝነት ለመረዳት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ለአገራዊ ፖለቲካው ያላቸውንም አመለካከት መዳሰስ የግድ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን። በኢትዮጵያ ፖለቲካው መጻኢ እድል ዙሪያ ያሉትንም ይሁን ዝምታን የመረጡ ዜጎችን ካላቸው የፖለቲካ ተሞክሮና ለፖለቲካ ትርጉም ካላቸው ፍልስፍና አንጻር በሶስት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን።

## የቴሎስ መንገድ

ከወቅታዊ አገራዊ የፖለቲካ ትኩሳት አንፃር በመጀመሪያው ረድፍ ላይ የምንመድባቸው ግለሰቦች በኢህአዴግ የአገዛዝ ስርዓት፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ የተሻለ ውጤትን የሚጠብቁት ናቸው። እነዚህ ተከታታዮች አሁን በተፈጠረው የስልጣን ሽግግር ምክንያት የመጣው ለውጥ የተሻለ ወይም ከቀድሞው አመራር የከፋ አስተዳደራዊ ለውጥ ይመጣል ብለው የሚያምኑና ውጤቱንም በሂደት ማየት አስፈላጊ መሆኑን የሚያምኑ ግለሰቦችን የያዘው ክፍል ነው። የእነዚህ ግለሰቦች አመለካከት አርስቶትል ‹‹ፖለቲካ›› በሚለው ድርሳኑ ‹‹ቴሎስ›› ብሎ ከገለፀው ፅንሰ ሀሳብ ጋር የሚዛመድ ርዕዮተ አለም ያላቸው ናቸው።

አርስቶትል ‹‹እያንዳንዱ ፖለቲካዊም ይሁን ማህበራዊ እንቅስቃሴ በስተመጨረሻ አንድ ግብ ሊኖረው ይገባል›› ይላል። ይሄ ፅንሰ-ሀሳብ በጥቅሉ ፖለቲካ የራሱ የሆነ እና ከሌሎች የሚለይበት አካሄድና በስተመጨረሻም ይህንን አካሄድ በአዎንታዊ ጐኑ የሚያስረዳ ግብ ያስፈልገዋል ባይ ነው። ፖለቲካ ምንነቱንና በውስጡ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡ ባመጣው ፋይዳም ጭምር መገምገም እንዳለበት በምሳሌ ያስረዳል። ለምሳሌ ይላል አርስቶትል፤ ቢላዋ ከብረት የተሰራ ስለታማ መሳሪያ ነው ብሎ መናገር ብቻውን የእቃውን ምንነት (ከብረት የመሰራቱን እውነት) በደንብ አይገልፀውም። ከላይ ከተገለጸው ምንነቱ በተጨማሪ ቢላዋው የተሰራበትን አገልግሎት (ለመቁረጥ እንደሚያገለግል) ስንናገር የቁሱን ትርጉም ሙሉ ያደርገዋል የሚል እምነት አለው። ይህንን አስተምህሮ አርስቶትል ‹‹ቴሎስ›› ሲል ይጠራዋል። ስለዚህ የቴሎስ ፅንሰ ኃሳብ ፖለቲካዊ እና ፖለቲካዊ ለውጦች ግብ ያስፈልጋቸዋል የሚል መደምደሚያ ያለው ነው። እነዚህን የፖለቲካ ግቦች ለማሳካት መሪዎች ሞራልና ፍትሃዊነትን ያካተቱ መሆን ይገባቸዋል ማለት ብቻም ሳይሆን እነዚህን የሞራል ማሳያዎች ለማህበረሰቡ በተግባር እያሳዩ እንዲከተሏቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ስለዚህ በአገራችን ባለው የስልጣን ሽግግር ማን መጣ? ወይም ማን ተተካ? የሚለው ሳይሆን የመጣው ግለሰብ አልያም ቡድን ምን የተሻለ ነገር ይዞ ይመጣል?ወይም መምጣት አለበት? ብለው የሚከራከሩትን ዜጎች በአርስቶትል ቴሎስ ፍልስፍና ውስጥ ከተን ልናያቸው እንችላለን።

አዲሱ የአቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ካቢኔም ይሁን ፓርቲዎች በውስጣቸው ያካሄዷቸው ሹመቶች በሙሉ መታየት ያለባቸው በመንግስት ደረጃ የተፈጠረውን የግለሰብ ቦታ ለመተካት ብቻ መሆን እንደሌለባቸው የእነዚህ ግለሰቦች አመለካከት ነው። ማንም ቢሆን የስልጣን እርካቡን ሲቆጣጠር ለማህበረሰቡ በሰጠው ወይም ሊሰጠው ባቀደው ፋይዳ ባለው ፖሊሲና ስትራቴጂ ብቻ መዳኘት እንዳለበት አፅንኦት ሰጥተው የሚሞግቱ ግለሰቦችን ያካትታል።

የመንግሥት ስልጣን የወንበር ብቻም ሳይሆን የተግባር አገልግሎትም ሊኖረው ይገባል። ይህንን ማህበረሰባዊ ፋይዳ ከግብ ለማድረስ አመራሩ የተሻለ እድል ይኖረዋል። ካልተጠቀመበት ደግሞ የባሰ አዘቅት ውስጥ ይዞን ሊገባ የሚችልበትም እድል መኖሩን በሌላኛው ገፅ ማየት ያስችለናል። ጅምሩን ከሁለት መሰረታዊ አገራዊ ፖለቲካ ፋይዳ አንፃር መልካም ይመስላል ለማለት ያስችላል። የመጀመሪያው የቀድሞው ታጋይ አመራር አካላት ወደኋላ ተንሸራተው ለአዲሱ ትውልድ ቅድሚያ እድል የመስጠታቸው እውነት ነው። ይሄ አካሄድ ፋይዳ ይኖረዋል ብሎ መጠበቅ የሚቻለው የግንባሩ አመራር አባላት በአዲሶቹ ተሿሚዎች ስልጣን እና ኃላፊነት ላይ እጃቸውን ማሳረፍ ካልቻሉ ብቻ ነው። አዲሱን አመራር እንደ አሻንጉሊት ከላይ አፈናጦ የመወሰን ሙሉ መብቱን ለብቻቸው ከተቆጣጠሩ ፖለቲካው ከካርቶን ፊልም የዘለለ የመታየት አቅም አይኖረውም።

ሁለተኛው መልካም ጅምር የስልጣን ገደብ የማስቀመጡ አሰራር ነው። እንደሌሎቹ ኃያላን አገራት በተወሰነ ወቅት የተለያዩ ባለስልጣናትን ማየታችን መልካም ነው። መልካም ነው የምለው የጉልቻ መለዋወጡን ሳይሆን በለውጡ ሂደት ከቀድሞው የተሻሉ በእውቀትም ይሁን በግለሰባዊ ስብዕናቸው የተሻሉ ሰዎችን ለማየት እድሉን እናገኛለን ከሚሉ አመለካከቶች የሚመነጭ ነው። ከስር ሆነው ዋናውን ቦታ የያዙ ነባር ታጋዮች አዳዲሶቹን አመራሮች እንደፈለጉ የሚሾሙና የሚሽሩ ብቻ ከሆነ ‹‹ጉልቻ ቢለዋወጥ …›› ከሚለው አገራዊ ብሂል የዘለለ ፋይዳ አይኖራቸውም። የአርስቶትል ቴሎስ ይህንን ማህበረሰባዊ ፋይዳ በአፅንኦት ይመለከተዋል። ቁም ነገሩ የኃ/ማርያም ጠ/ሚኒስትር መሆን ወይም ሌሎች ተተኪ ባለስልጣናት የተለያዩ መስሪያ ቤቶችን በኃላፊነት መቆጣጠራቸው ሳይሆን የተሰጣቸውን የስራ ኃላፊነት ከነሙሉ ስልጣኑ መረከባቸው ነው። የቴሎስ ፅንሰ ሀሳብ ሙሉ የሚሆነው ቢላ ብረት ብቻ ስለሆነ የተሰራበትን ፋይዳ ከግብ ለማድረስ የተሻለ ማድረጉም ጭምር ነው ትርጉም የሚሰጠው። የዚህ ፅንሰ ሀሳብ ተከታታዮች ከሌሎቹ የአገራችን ዜጐች በተሻለ መልኩ የሁኔታዎችን መለዋወጥ ከሚሰጡት አገራዊ ፋይዳ አንፃር የሚመለከቱ ናቸው።

በሁለተኛው ረድፍ ላይ የሚያርፉት የአገራችን ዜጐች ቅዱስ ኦገስቲን “City of God” በሚለው ስራው ካሰፈረው ኃሳብ ጋር የሚዛመድ አመለካከት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው። ኦገስቲን ‹‹የፍትህ የመጨረሻው ግብ ፈጣሪን ማገልገልና በፈጣሪ መንገድ መመራት ብቻ ነው›› የሚል መከራከሪያ ያቀርባል። በምድር ላይ ያሉ መሪዎችን ኦገስቲን ‹‹የፈጣሪ ሚኒስትሮች›› ሲል ይጠራቸዋል። ዜጎች መሪዎቻቸው የሚያወጧቸው ህግጋቶች በራሳቸው ፍላጐትና ችሎታ የሚወጣ ይሆን ‹‹ከእግዚአብሔር የተላኩ ናቸው›› ብለው መቀበል እንዳለባቸው የሚጠቁመው ኦገስቲን፤ ገዢዎቹ ግፈኛም ይሁኑ ሐቀኛ የማክበር እና አገዛዙን በግዴታ መቀበል እንዳለባቸው ይጠቁማል። ማናቸውም ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ፈፅሞ የተወገዙ ናቸው። በአገዛዙ የሚደርስባቸውን ቅጣት በፀጋ መቀበል እንዳለባቸውም ያትታል። የዚህን የኦገስቲን አመለካከት የሚጋሩ ብዙ የማህበረሰብ ክፍሎች ጥንትም ይሁን አሁንም አሉን። አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊያን በእምነት ተቋማቶቻቸው ላይ ካላቸው ጥብቅ ቁርኝት አንፃር በአገራችን የተካሄዱትን/እየተካሄዱ ባሉት ለውጦች ላይ የፈጣሪን መልካም ፍቃድና ጣልቃ ገብነት የሚጠባበቁ ናቸው። ይህ ምልከታ አሁን የተፈጠረውን የስርዓቱን መሪ ድንገተኛ ሞት ተከትሎ ሊፈጠር ይችላል እየተባለ ይነገር በነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ወደፊት በሚሆኑ ነገሮች ዙሪያ ፍፃሜው የፈጣሪ ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ስለሆነ መጨረሻውንም ለእርሱ መተው ይገባል ብሎ ያምናል። ብዙዎችም በየቤተ-እምነቶቻቸው በፀሎት እየተጉ መገኘታቸው የዚህ ውጤት ነው። አብዛኛውን የአገራችን የማህበረሰብ ክፍልም ወቅታዊውን የአገራችንን ፖለቲካ በተመለከተ በእዚህ ረድፍ ውስጥ ልንመድበው እንችላለን።

በአገራችን ለእንደዚህ አይነት አመለካከት ሰፊ ተቀባይነት ማግኘት የተለያዩ ምክንያቶች ማቅረብ ቢቻልም በእኔ አመለካከት ሁለት ጫፎችን ይዘን በጥቅሉ ልናያቸው እንደምንችል አምናለሁ። የመጀመሪያው ነጥብ አብዛኛው የአገራችን ማህበረሰብ የሚገኝበት የአመለካከት እና ማህበራዊ ደረጃ ነው። ከ85% በላይ የሚሆነው የሀገራችን ነዋሪ ዋነኛ የገቢ ምንጭ በባህላዊ መንገድ የሚመረተው እርሻ ብቸኛው የገቢ ምንጭ ነው። እርሻው ዘመናዊነትን ካለመላበሱ የተነሳ ገበሬዎቹ ለምርት የሚያገለግላቸውን ውሃ ከሰማይ አንጋጠው እንዲጠብቁ ግድ ይላቸዋል። ወደ ሰማይ የሚያንጋጥጥ ገበሬ በአመት አንዴ የምትመጣለትን ዝናብ ላለማጣት የግድ ከሰማዩ አምላክ ጋር ታማኝነቱን አጥብቆ እንዲቀጥል ይገደዳል። በእንደዚህ ዓይነት ማህበረሰብ ውስጥ ትልቁ ሰው የእምነት ተቋማትን የሚመራው ግለሰብ ነው። ግለሰቡ ማህበረሰቡ በሚያጋጥመው ማናቸውም አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ውጤቶች በሰማዩ አምላክ ይሁንታ ብቻ ላይ የተመሰረተ

# ከቴሎስ እስከ ቦናፓርቲዝም

መሆኑን እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል፡፡ እንደዚህ አይነት አመለካከት በማናቸውም የህይወት ገጠመኞቻቸው ላይ (ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ጨምሮ) እንዲያንፀባርቁ ይገፋሉ፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ማህበረሰቡ በፖለቲካ በመሳተፉ ምክንያት ከዚህ በፊት የገጠሙትን አሉታዊ ውጤቶች መሰረት አድርገው የሚነሱ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በደርግ ዘመን ፖለቲካው የለበለባቸው ወላጆች እና ይህንን የተመለከቱ ሌሎች ጎረቤቶች በኋለኛውም ዘመን ለፖለቲካ ያላቸው አመለካከት የተለየ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ አንዳንዶቹም ትንሽ ለውጥ አለው በሚል ምክንያት በ97ቱ ምርጫ ወቅት ያደረጉት ተሳትፎ ውጤት ከቀደመው ተሞክሮ የተለየ ባለመሆኑ ምክንያት ፖለቲካውን የጥቂቶች ብቻ ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እነዚህ አሉታዊ ተሞክሮዎች የአገሪቷን እጣ ፈንታ ከገዢዎቹ በላይ ነው ብለው ለሚያምኑት አምላክ መስጠት አማራጭ የሌለው መፍትሄ አድርገው እንዲቀበሉት አስገድዷቸዋል፡፡

በሶስተኛው ረድፍ ላይ የሚያርፉት የአገራችን ዜጎች ቶማስ ሆብስ “Leviathan” በሚለው ስራው ላይ ካሰፈረው ሀሳብ ጋር የሚዛመድ አመለካከት የሚያራምዱ ግለሰቦችን ያቅፋል፡፡ ሆብስ በየትኛውም አይነት የመንግሥት ሥርዓት (አምባ-ገነንም ቢሆን) ዋናው መታየት ያለበት የአገሪቷ ሉዓላዊነት ተጠብቆ ህዝቦቿ በሰላም መኖር መቻላቸው ብቻ ነው ይላል፡፡ እንደ ሆብስ አረዳድ ሰዎች በተፈጥሮ ፀብ ጫሪ፣ ሁከት ፈጣሪ፣ እራስ ወዳድ፣ከሌሎች ጋር የማይግባቡ በመሆናቸው የግድ አስተሳስሮ የሚገዛ ሕግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃርም ፀሐፊው መንግሥትን ለማስወገድ የሚደረጉ ጥረቶች በሙሉ መወገዝ እንደሚገባቸው ይመክራል፡፡ ስለዚህ ሰዎች ተስማምተው ይኖሩ ዘንድ ያለው ብቸኛ አማራጭ (ለማህበረሰቡ ተጠያቂ ያልሆነ መንግሥትም ቢሆን እንኳን) መንግስት እና ህግጋት ናቸው፡፡ ከሁከትና ከብጥብጥ ለመራቅ የተሻለ የሚሆነው በመንግስት መገዛት መሆኑን ይመክራል፡፡

በወቅታዊውም ይሁን በተለያዩ ጊዜያት በአገራችን የፖለቲካ ሥርዓት ላይ በሚከሰቱ ለውጦች ዙሪያ የሆብስን አይነት አቋም የሚያንፀባርቁ ግለሰቦች ሌላኛውን የኢትዮጵያ ፖለቲካ መንገድ ከሚጋሩት መካከል ልንመድባቸው እንችላለን፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በተለይ መንግሥትን በመለወጥ ሂደት ዙሪያ የሚነሱ ማናቸውም አይነት ቅራኔዎች እንዳይኖሩ የሚሹበት የራሳቸው የሆነ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሯቸውም ቢሆንም በዋናነት ግን የሚከተሉትን መከራከሪያዎቻቸውን አንስተን ማየት እንችላለን፡፡

ቀዳሚው ነጥብ የጥቅመኝነቱ መከራከሪያ ነው፡፡ በተለይ ከስርዓቱ ጋር በዝምድናም ይሁን በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች እራሳቸውን ያስተሳሰሩ ግለሰቦች በምንም አይነት መንገድ ስርዓቱ እና የሥርዓቱ መሪዎች ከቦታው እንዲነሱባቸው አይፈልጉም፡፡ የህልውናቸው መሰረት እነርሱ በመሆናቸው ምክንያት በመንበሩ እንዲቆዩ የተቻላቸውን ሁሉ ከማድረግ አይቆጠቡም፡፡ ሁለተኛው የዚህ አይነት አስተሳሰብ ተከራካሪዎች በእድሜያቸው የገፉ ግለሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በመጨረሻው የእድሜያቸው ዘመን ተረጋግተውና ልጆቻቸው በሰላም ወጥተው የሚገቡበትን አካባቢ የሚረብሽ ማናቸውም አይነት እንቅስቃሴዎችን ለማየት የማይሹ ከመሆናቸው በተጨማሪ በወጣቶች ላይ ተፅዕኖ በማሳረፍ በአገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተተኪው ትውልድ የራሱን አሻራ እንዳያሳርፍ አሉታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በጥቅሉ በአገሪቷ ወቅታዊ ፖለቲካ ትኩሳት ላይ እጃቸውን እያሳረፉ እና ሁኔታዎቹን ቀን ተቀን እየተከታተሉ ያሉ ግለሰቦችን ከጠቅላላው የአገሪቷ የህዝብ ቁጥር አንጻር ወስደን ካየነው በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ጥቂት መሆናቸው ደግሞ በለውጡ ግርግር ላይ በስልጣን ላይ ካሉ አመራሮች ጋር ተከራክረው ለውጥን ለማምጣት የሚኖራቸው አዎንታዊ ተጽዕኖ ደካማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በስልጣን ላይ ላለው ፓርቲ ትልቅ ብርታት ይሆነዋል፡፡



## የበረሃው ተሞክሮ

በሕወሓት የትግል ታሪክ የመጀመሪያውና ትልቁ የድርጅቱ ህልውና አደጋ ላይ ወድቆ ነበር የሚባለው በ1969ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ደርሶበት የነበረው ተግዳሮት ነው፡፡ ሕወሓት በጊዜው ከውስጥም ከውጭም የሚገዳደር ኃይል ገጥሞት የነበረው በዚህ ወቅት ነበር፡፡ ይህንን ችግር የቀረፈበት የአፈታት ተሞክሮ እንደ አንድ የድርጅቱ የጥንካሬ ተደርጐ እንዲወስድ አስችሎታል፡፡

በጊዜው ከደርግ ጋር ያደርገው የነበረው ጦርነት በአንድ በኩል ትልቅ ችግር ቢሆንም በተደራቢነት ፓርቲው ባለበት አካባቢ ከተነሳው ሌላ ተገዳዳሪ ቡድን (ኢዲዮ) ጋር እየተዋጋ መክረሙ ድርጅቱን በከፍተኛ ተፅዕኖ ስር እንዲወድቅ አድርጐታል፡፡ ይሄ ውጫዊ ተግዳሮት የድርጅቱን የሰው ኃይል እጅግ ማዳከሙ የማይቀር ሃቅ ቢሆንም በውስጥ አመራሩ ዘንድ የተነሳው መከፋፈልና አለመግባባት በአባላቶቹ ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤ እንዲፈጠር አድርጐታል፡፡ በሕወሓት አመራር መካከል የተከሰተው ውስጣዊ ክፍፍልና አለመግባባት በታሪክ ‹‹ሕንፍሽፍሽ›› በመባል ይታወቃል፡፡

ከትጥቅ ትግሉ አንስቶ ድርጅቱ ከሚታወቅባቸው ልዩ ባህሪያቱ መካከል አንዱ ግልፅነት ያለመኖሩ ጉዳይ ነው፡፡ በጊዜውም የነበረው አመራር በስሩ ላሉ አባላቱ እርስ በርሳቸው የገጠማቸውን አለመግባባቶች በግልፅ መናገር አልደፈረም፡፡ ለዚህም አመራሮቹ በምክንያት የሚያስቀምጡት የመሪዎቹ በሀሳብ መከፋፈል በአባላቱ ዘንድም ይፈጠራል ብለው በመስጋታቸው ነው፡፡ አባላቱ እንዳይከፋፈሉና እንዳይደናገጡ አይነገራቸው እየተባለ በድርጅቱ ላይ አደጋ የሚጭሩ ችግሮችን ሁሉ በድብቅ መያዝ እንደ አንድ አሰራር ይወሰድ ነበር፡፡ ይሄ አይነት አካሄድ እስከአሁን ድረስ ዘልቆ መቆየቱን የአቶ በረከት ስምዖን የቅርቡ ጋዜጣዊ መግለጫ ማሳያ ነው፡፡ አቶ በረከት የጠ/ሚኒስትሩን መታመም ከመንግሥት በኩል መግለጫ ለመስጠት ለምን ዘገየ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፡-

‹‹…ዞሮ ዞሮ የገዢውን ፓርቲ ባህል ማወቅ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ ገዢው ፓርቲ አብዛኛውን ጊዜውን በበረሃ ያሳለፈ ፓርቲ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ከባድ መስዋዕትነት እየከፈለ እነዚህን ተሸክሞ ማለፍ የሚችል ፓርቲ ነው የተገነባው፡፡ ስለዚህ ለገዢው ፓርቲ በባህል ደረጃ እከሌ እንደዚህ ሆነ፣ ይሄ መስዋዕት ከፈለ፣ ያ መስዋዕት ተከፈለ የሚባል ነገር ብዙ ትልቅ ጉዳይ ተደርጐ የሚወሰድ አይደለም፡፡…›› የሚል ነበር፡፡

በእርግጥ የአቶ በረከት ምላሽ ሕወሓት በበረሃ ሳለ በአመራር ዘንድ ተፈጥሮ በነበረው አለመግባባት ለአባላቱ ‹‹እንዲህ ተፈጥሯል›› ብሎ ለማውራት የሚፈጥረውን አደጋ ለመከላከል ሲባል ከወሰደው እርምጃ ጋር ይዛመዳል፡፡ በሰውዬው ህመም ወቅት አብዛኛው የኢህአዴግ ካድሬ ለጠ/ሚኒስትሩ የነበረው ታዛዥነት እንደተጠበቀ እንደነበር ብዙዎቹ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ ስለዚህም የእርሳቸውን የጤንነት ጉዳይ በንቃት ሲከታተሉ የነበሩ አባላቶቻቸውን ለድርጅቱ እየለገሱ ያለውን ድጋፍ ላለመበታተን አልያም ላለመከፋፈል ሲባል እንዲህ አይነት እርምጃዎችን ለመውሰድ ተገደዋል፡፡

ሕወሓት በበረሃ እያለ የነበረው ባህል አሁንም ድረስ እንዴት ሊዘልቅ ይችላል? የሚለውን መከራከሪያም ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ አሁን መቀጠል አልነበረበትም ብሎ ለመከራከር በጥቂቱ ሁለት

ወደ ገፅ 32 ዞሯል

## ለምን.... (ከገፅ 33 የዞረ)

በነፃነትና በእኩልነት እንዲኖሩ በማሰብ ክቡር ዓላማ አንግበው፣ ለዓላማቸው የተሰዉ ታጋዮችን ተረማምደው ወደ ስልጣኑ የደረሱት ግን ሁሉንም ረሱት።

ምናልባትም ‹‹ህወሓት/ኢህአዴግ በባህሪው ዴሞክራሲያዊ አይደለም›› ለሚሉት ስለት ትችቶች ክብር መስጠት ተገቢ ቢሆንም፤ ይሄንን ምሳሌ እየጠቀሱ መከራከር እንደማይገድ ባውቅም፤ የተሰዉ ሰማዕታት ግን ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት የተንገበገቡ እንደነበሩ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

ዛሬ ከሃያ አንድ ዓመት በኋላ በዚሁ በሞቱለት አካል፣ ኢትዮጵያውያን የደህንነት ስሜት አጥተን በየካፌው እንኳ ከጓደኞቻችን ጋር ስለወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳይ ለማውራት ስንገለማመጥ ቢያዩ ሰማዕቱ ምን ይሉ ነበር? ሰላማዊ ሰልፍ መውጣትና መብታችንን መጠየቅ ‹‹አመፅ ለመቀስቀስ›› ተብሎ እንደሚያሳስር ሲያስተውሉ፤ ሀሳብን በነፃነት መግለፅና መሰብሰብ የሚያስከትለውን ጣጣ ቢያዩ ምን ይሰማቸው ይሆን? ‹‹መሬት ላራሹ›› ብለው የጮኹለት የከበረ ጥያቄ ከ50 ዓመት በኋላም ሳይመለስ ‹‹መሬት ለመንግሥት›› እንደተባለ ቢያዩስ? ዛሬ ጋዜጦች በመኖርና ባለመኖር መካከል ተጣብቀው ጋዜጠኞች ጆሮ ጠቢ ተመድቦባቸው ሲሳቀቁና አንዳንዶቹ ከርቸሌ ሲጣሉ ቢመለከቱ ምን ይሰማቸው ነበር? ታግለው የጣሉት ስርዓት ተመልሶ ነፍስ ሲዘራ ማየት፣ ድሎት አይኑን ላልጨፈነውና መስሚያውን ላልደፈነው ከሞት የሚተናነስ አይደለም።

ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ የደህንነት ስሜት አልሰማን ብሏል። ይህንን የፈጠረብን ስርዓቱ ነው። ስርዓቱ እስከምን ድረስ ይቀጥል ይሆን? ይህንን ጥያቄ ለስርዓቱ መሪዎች በክብር አቀርባለሁ። እንደ አንድ ወጣት ከዚህ በኋላ ሀገር ላይ ደም ሲፈስ ማየት አልሻም። በደም መለወጥ ብንችል ኖሮ ለባለፉት 50 ዓመታት የፈሰሰው ደም ያሸረን ነበር። የተረፈን ቁርሾና ዕዳው ነው። ህዝቡ ግን ይችላል። መብትም፣ አቅምም አለው። የሚያስፈልገው ከተበጀልን አጥር ባሻገር ያለውን ሁናቴ መመልከት ነው። መጠየቅ ነው፣ መከራከር ነው፣ እምቢ ማለት ነው። ይሄንን በሰላማዊ መንገድ ማድረግ ይቻላል። ‹‹አይ! ይሄ መብቴ ስለሆነ እንድትነጥቀኝ አልፈልግም›› በማለትና በጨዋ መንገድ። ቴዲ አፍሮ እንዳለው ፍቅር ያሸንፍ የለ?

----------------

## ያልተመጣጠኑ.... (ከገፅ 12 የዞረ)

አልፎ፤ ባንኩ ማግኘት የነበረበትን ተገቢ ገቢ እንዲያጣና በማክሮ ኢኮኖሚው ወይንም በጠቅላላ የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እያደረሰ ይገኛል።የዋጋ ንረቱንም የበለጠ እያባባሰው ይሄዳል። አልፎም በባንኮች ውስጥ መገኘት ያለበትን የገንዘብ ክምችት መጠን የሚያሳሳ ይሆናል። በቀላል ምሳሌ ላስረዳ፡፡ ባንክ ለተበዳሪ ከ 5 ዓመት በፊት 100 ኪሎ ጤፍ የመግዛት አቅም ያለው ገንዘብ ቢያበድር ከአምስት አመት በኋላ (በ 2004 ዓ.ም) ተበዳሪው ለባንኩ የሚመልሰው የገንዘብ መጠን (ከነ ወለዱ) ከ 25-50 ኪሎ ጤፍ ብቻ መግዛት የሚያስችል ጥሬ ገንዘብ ይሆናል ማለት ነው።ባንኩ ለተበዳሪው ስለተበደረለት ከ 50 ኪሎ ጤፍ በላይ መግዛት የሚያስችል ገንዘብ ይከፍለዋል ማለት ነው። የባንክ የወልድ ምጣኔው ከግሽበቱ እኩል መጣጣሙ ከላይ የቀረቡትን ጉዳቶች ባያሌው ይቀርፋል። በመጨረሻ የማነሳው ሃሳብ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያ የሴክተር መስሪያቤቶችን የስራ አፈፃፀም ክንውን በማስመልከት የሚቀርቡ የስኬት አሃዝ ንፅፅሮችን ይመለከታል።ለምሳሌ በቅርቡ በአንድ ሴክተር መስሪያ ቤት የተፈጠረ የስራ ዕድልን በማስመልከት እንዲህ የሚል ሪፖርት ሰምተናል፤ ‹‹ከባለፈው አመት አኳያ ሲነፃፀር በዘንድሮ የበጀት አመት በ 2 እጥፍ የበለጠ የስራ እድል መፍጠር ችለናል›› የሚል ነው።የባለፈው አመት አንድና የዘንድሮው አመት ሁለት እጥፍ ሊወዳደሩ የሚችሉት በመሬት ላይ ያሉ ሁነቶች ካልተለዋወጡ ብቻ ነው (With a common and comparable denominator)። ከዚህ ውጭ ግን የባለፈው አመት ስኬትን በ ሁለት አባዝተን ዘንድሮ ያገኘነውን ሁለት እጥፍ እንደ ሁለት እጥፍ ስኬት ማቅረብ ትርጉም የሚሰጥ ንፅፅር አይሆንም።በምሳሌ ላስረዳ።ባለፈው አመት በሃገራችን የነበረው ስራ ፈላጊ የሰው ሀይል ቁጥር 2 ሚልዮን ነበር እንበል። በዚያው አመት የተፈጠረው የስራ ዕድል አንድ ሚልዮን አድርገን እንውሰድ።በዚህ አመት ደግሞ የነበረው የስራ ፈላጊ የሰው ሀይል ቁጥር 5 ሚልዮን ቢሆንና ሁለት ሚልዮን የስራ እድል በሴክቶሮች ቢፈጠር ከባለፈው አመት አንፃር 2 እጥፍ ያህል የስራ እድል ተፈጠረ ሊባል አይችልም።ምክንያቱም ሁለት እጥፍ የስራ እድል ተፈጠረ ለመባል የዘንድሮው የስራ አጥ ቁጥር ከባለፈው አመት (አንድ ሚልዮን) በዘንድሮው አመት በእጥፍ አድጎ 2 ሚልዮን ከሆነ ብቻ ነው።አለበለዚያ ግን ሁለት እጥፍ የሚለው ንፅፅር ትርጉም አይሰጥም።እንዲህ አይነት ወደ አንድ አቅጣጫ ያጋደለ ንፅፅርም የትም የለም። የተፈጠረውን የስራ እድል(job opportunity) እና የስራ አጥ መጠን(unemployment rate) ያላገናዘበ ንፅፅር ውሃ የሚቋጥር አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ በየመስሪያቤቶች የሚሰበሰበው የገቢ መጠን እድገት ንፅፅር ሪፖርቲትም እንደዚሁ ጉደለት አለበት። ለምሳሌ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በዘንድሮው አመት የሰበሰበውን ገቢ ከአምስት አመት በፊት ከሰበሰበው ጋር በማነፃፀር በ 2፣3፣4 ወዘተ... እጥፍ ጨምሯል ይላል ።ሆኖም ግን በትክክለኛ የመግዛት አቅሙ(In real purchasing power) በ 2፣3፣4 ወዘተ... እጥፍ በለጠ የተባለው ከአምስት አመት በፊት ከተሰበሰበው ጋር ሲወዳድር ዋጋው ያነሰ ነው፤ ምክንያቱም ሁለቱ አሃዞች መወዳድር ያለባቸው በዛሬ ዋጋ(current price) ሳይሆን በቋሚ ዋጋ(constant price) ነውና። ስለዚህ ከላይ በቀረበው መልክ የሚነገር ንፅፅር በተጨባጭ ገቢ እንዳደገ የሚያሳይ አይደለም፤ ይልቁንም በተቃራኒው ሆኖ እናገኘዋለን፤ በተከሰተው የሁለት አሃዝ የዋጋ ግሽበት የተነሳ፤ ዛሬ ያለውን የዋጋ ግሽበት ከግምት በማስገባት በቋሚ ዋጋ(constant price) ሲሰላ ማለቴ ነው። ለዚህም ነው ቋሚ ዋጋን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ስሌቶች ባለመሰላታቸው የተጋነኑና ለማመን የሚቸግሩ የገቢ መጠን ሪፖርቶችን የምናደምጠው። ባጠቃላይ ከአመታት በፊት የተቀመሩት የምጣኔ ልካቶቻችን ከዛሬው የሃገራችን ሁነቶች ጋር አይስማሙም።ስለሆነም የምጣኔዎች(የደመወዝ ግብር ምጣኔ፣ የባንክ ወለድ ምጣኔ፤ የተጨማሪ እሴት ግብር መነሻ ምጣኔ፣ ወዘተ...) እንደየወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ እንዲስማሙ ተደርጎ መመጠን የህብረተሰቡን ኑሮ ከማሻሻልም አልፎ ማህበራዊ ፍትህን የሚያስገኝ ይሆናል።የሚመለከታቸው አካላትም ከላይ በትንተናው ያየናቸውን ተገቢ እውነቶች በማገናዘብ፣ ዙርያ አቀፍ ማሻሻያዎችን ቢያደርጉ መንግስታችን ትቀናለች ማለፊያም ነው ብየ አምናለሁ። የተጣረሱ ምጣኔዎችና አፋኝ ህጎች ያሉት መንግስት ብዙ እድሜ የለውምና።አበቃሁ! ቸር እንሰንብት።

----------------

## ማጉም.... (ከገፅ 23 የዞረ)

ቀን 1929 ዓ.ም! ጀግናው ኃይለማርያም ማሞ የገዛ መኖሪያ ቤቱን በእሳት ለኩሷል! ብዙ ተከታዮች አፍርቷል! በማግስቱ ከጧት አንስቶ ጦርነቱ ተፋፍሟል። ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! አያሌ የኢትዮጵያ ጀግኖች ወድቀዋል! የወራሪው ኃይል ተዋጊዎች ተገድለው ሬሳቸው በየቦታው ተዝረክርኳል! አንድም የኢትዮጵያ ጀግና አስክሬን በወራሪው ኃይል አልተማረከም! ጦርነቱ ቀጥሏል! ጥር 11 ቀን 1929 ዓ.ም.! ድም! ም! ም! ም! ድም! ም! ም! ም! ይህ የመድፍ ድምፅ ነው! ከኢትዮጵያ አርበኞች መድፍ ይተኰሳል! የአፀፋ ተኩስ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ይሰጣል! አሁን ከቀኑ አሥር ሰዓት ይነበባል! የተፋፋመ ውጊያ ቀጥሏል! ጥር 11 ቀን 1929 ዓ.ም.! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በጄኔራል ትራኪያ፤ በጄኔራል ፋጆርና በኮሎኔል ሮሲኒ እንደ ተመራ ታውቋል! በጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ እጅ ምሱን አግኝቷል! አሁን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሲፈረጥጥ ይስተዋላል! በለው! አሳድደህ ድፋው! ይህ የኢትዮጵያ አርበኞች ድምፅ ነው! ጀግናው ኃይለማርያም ማሞ በአንበሳ አምሳል ይጎማለላል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሸሽቷል! 363 ሙታንን ትቶ ፈርጥጧል! ድል የኢትዮጵያ አርበኞች ሆኗል! ጉሮ ወሸባ! ጉሮ ወሸባ! የኢትዮጵያ አርበኛ ድል አድርጎ ሲገባ!

ከአስር ቀናት በኋላ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንደገና ከአርበኞች ሰፈር መጥቶ ጦርነት ከፍቷል! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ በአፀፋ ተኩስ የአስራ አምስት ፋሽስቶችን ሬሳ አስቆጠረ። ከአርበኞች በኩል ሁለት ጀግኖች ተሰውተዋል! በተያያዘ ሂደት ፍቼ ላይ ጦርነት ተካሄዶ አርበኞች የበላይነትን ጨብጠዋል!

ቆራጡ ጀግና ኃይለማርያም ማሞ ሚያዝያ 21 ቀን 1929 ዓ.ም.¸ከአስራ አምስት ሺህ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጋር ጦርነት ገጥሞ እንደነበር ታውቋል! የኢትዮጵያ ጀግኖች ደግሞ በቁጥር አነስተኛ ነበሩ! ጀግናው ኃይለማርያም ማሞ በለበን ጥይት አይሮፕላን መትቶ ጥሏል። በውስጡ የነበሩ በሙሉ አልቀዋል! ጦርነቱ 3 ሰዓት ፈጅቷል! በዚሁ ጦርነት ሁለት የጣሊያን መኮንኖች ተገድለዋል! ከመካከላቸው አንዱ ከፍተኛ መኮንን እንደ ነበር ታውቋል! ኮሎኔል ጓሬኒ የተባለ ፋሽስት ለጥቂት አምልጧል! ጀግናው ኃይለማርያም 23 ጣሊያን ምርኮኞችን መድፍ አሸክሞ እንደ ከብት ነድቷቸዋል!

ጀግናው ኃይለ ማርያም ማሞ ግንቦት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ክፉኛ ቆስሏል! በሐምሌ ወር 1929 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ይህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ በታሪክ ለዘለዓለም ሕያው ሆኗል! ዘሩ ይለምልም! ተወላጆቹ ይባረኩ!

ማጉም ለሰለሰ ሸማኔው ተቆጣ፤
አባ ጎፈን መጠቅለያው መጣ።

----------------

## ፐ/ር መስፍን.... (ከገፅ 11 የዞረ)

፡ የመጀመሪያው ኢትዮጵያውያን የሱማሊዎችን አያያዝ ስህተት በቅጡ ተመልክቶ የማያወላውል መፍትሔ ለመስጠት የሞከሩበት ነው። ጽሑፉ የዚያን ዘመኑ ወጣት የአርቆ ማየት ደረጃና ለወጣቱ የሚሰጠውን ኃላፊነትም ያመለክታል። እንዲህ ዓይነቶቹን ጽሑፎች በአዲስ መጽሐፍ ላይ ማካተት ወጥ ሥራ ላይ እንደመደረብ ስለሚሆን የሚፈጥረው ጫና እንደሚኖር ማሰባችን አይቀርም። በሌላ ጎን ደግሞ 40ና 30 ዓመታት ባስቆጠሩት ጽሑፎች የተነሱት ችግሮችም ዛሬም ያልተፈቱ፤ የቀረቡ ምክረአሳቦችም ዛሬም ያልተተገበሩ መሆናቸው ሲታሰብ የጽሑፎቹንም ዋጋ፣ የፐ/ሩንም ምጸት እንረዳለን።

በመጨረሻ በዚህ መጽሐፍ ብዙ የአርትኦት ስንፈቶችን መጥቀስ ቢቻልም፤ ለጊዜው አስፈላጊ ወደሆነ ሌላ ጉዳይ መግባት ይሻላል። መጽሐፉ ለቀንዱ አገራት የፖለቲካ ሳይንስና የውጭ ግንኙነት ተማሪዎችና ተግባሪዎች የሚያስተምረው ብዙ ነገር እንዳለ አምናለሁ። ምርምርን ከሕዝባዊ አገልግሎት ጋር አጣምረው የያዙት ፐ/ር በዚህ መጽሐፍም ትውልድ በብዙ መልኩ እንዲያስባቸው አድርገዋል ማለት እችላለሁ። ከሰብዓዊ መብት ተከራካሪነት ወደፖለቲካው ከገቡ በኋላ (በተለይ በአንድነት ክፍፍልና ግርግር ውስጥ ያላቸው ሚና) በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን የሞራል ልዕልና የፈተነው ቢሆንም፤ ከዚያ በመለስ መጽሐፉና ያነሱት ጉዳይ ትክክለኛ ቦታቸው እንዲህ ዓይነት ሥራዎችን መሥራት እንደሆነ እንደሚያመለክት በድፍረት መናገር እችላለሁ።

## ከመለስ....

*(ከገፅ 21 የዞረ)*

የተቀመጠውን አዲስ ሰው አዲስ ማንነት ለማጎን ከሞከሩ የሚያስነሳው አቧራን መገመት ከቻልን ኃይለማርያም ወደ ስልጣን እንዲመጡ ያመቻቹት ጓዶቻቸው በራሳቸው በኃይለማርያም ላይ ‹‹ለክፉ ቀን›› የሚሆን ቃጭል ማጥለቃቸውን አሊያም ድብቅ መግፍኤ እንዳላቸው መጠርጠር እንችላለን፡፡ በ1995 ዓ.ም. ኃይለማርያም ደሳለኝ የደቡብ ክልል መስተዳደር ፕሬዝዳንት ሆነው ቢሮአቸውን በአዋሳ ከተማ አድርገው ነበር፡፡ እናስ! በወቅቱ ምን ተፈጠረ? የተፈጠረው የሲዳማ ልሂቃኖች ኃይለማርያም የወላይታ እንጂ የሲዳማ ተወላጅ ባለመሆናቸው የፖለቲካ ጉንተላ ማድረግ ጀመሩ፡፡ አያያዙናም ‹‹የሲዳም ህዝብ ከሶስት ሚሊዮን በላይ በመሆኑ ራሱን ችሎ ክልል ሊሆን ይገባል››፣ ‹‹በቁመታችን ልክ ውክልና አልተሰጠንም›› የሚል ጥያቄ አቀረቡ፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች እና በማዕከላዊ መንግስት ፍላጎት እንዲሁም በወላይታ እና በሲዳማ ተወላጆች መካከል ባለ ቅራኔ ቅርቃር ውስጥ የገቡትን ኃይለማሪያም ‹‹ሊያስተዳድሩን አይገባም›› አሉና ተቃውሞአቸውን አደባባይ በመውጣት ገለፁ፡፡ ያንጊዜም መንግሥት የሀይል እርምጃን ወሰደ፤ በርካታ የሲዳማ ተወላጆችም ህይወታቸው አለፈ፡፡ ሆኖም የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ከመዳከም ይልቅ መስፋት ጀመረ፤ ይህን ጊዜም መንግሥት ደነገጠ፡፡ በድንጋጤም ኃይለማርያም ላይ ‹‹ብቃት ማነስ›› የሚባል ታፔላ ለጠፈና ከቦታቸው እንደተነሱ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ይፋ አስደረገ፡፡ (ምንም እንኳን በሶተኛው ቀን ከኃላፊነታቸው የተነሱበት ምክንያት የብቃት ማነስ እንዳልሆነ ማስተባበያ ቢሰጥም) በኃይለማርያም ቦታም የሲዳማ ተወላጅ የሆኑት ሽፈራው ሽጉጤ ተተኩ፡፡ ይህ እንግዲህ ከዓመታት በኋላ የጠቅላይ ሚንስትሩን ወንበር በመረከባቸው ከጀርባቸው በማድፈጥ ‹‹ሚካኤል ሱሁል››ን (ሚካኤል ስዑል በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ በጎንደር ንጉስ እንጋሽና አውራጅ በመሆን የስልጣን መዘውሩን የያዙ ኃያል ሰው ነበሩ) ለመሆን ለተዘጋጁ ሰዎች ‹‹የመጫወቻ ካርድ›› መሆኑ ነው፡፡ የተዳፈነውን ‹‹የሲዳማ ፖለቲካ› በማናፈስ (የሲዳማ ልሂቃን ክልል ለመሆን ህግ-መንግስታዊ መስፈርቶችን አሟልተናል እያሉ መከራከራቸውን ልብ ይሏል) የሲዳማን ህዝብ ከኃይለማርያም በተቃራኒ በማቆም ከደኢህዴን ሊቀመንበርነት ማንሳት፡፡ ከዚህ ሀላፊነታቸው ከተነሱ ደግሞ በቀጥታ ከኢህአዴግ ሊቀመንበርነታቸው ይነሳሉ፡፡ ከኢህአዴግ ሊቀመንበርነታቸው ከተነሱ ደግሞ…

የሃይማኖት ጉዳይም ቢሆን በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሀገሪቱ ስልጣን ለዘመናት ከ‹‹ኦርቶዶክሳዊ›› መለዮ ብዙ የራቀ አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በኃይማኖት ጉዳይ ‹‹ፀለምተኛ›› የሚባሉት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንኳ ከሶስት አጋጣሚዎች በላይ በአደባባይ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ፓትርያርክ ከነበሩት አቡነ ጳውሎስ እጅ መስቀል መሳለማቸው የራሱ የሆነ ፖለቲካዊ አንድምታ አለው፡፡ ዙሩን ይበልጥ የሚያከረው ደግሞ በኃይለማርያም ለመጠቀም ያስባሉ የሚባሉት ብአዴን እና ህወሓት መሰረታቸውም ሆነ ሊያንቀሳቅሷቸው የሚችሏቸው ቡድኖች (Selectorate) የእምነቱ ተከታዮች ከሚበዙበት አካባቢ መሆኑ ነው፡፡ እናም ኃይለማርያም ቀጠሮ ባልተሰጠበት ሰአት ከእንዲህ አይነት ቦታ የሚነሳ ‹‹ሰው-ሰራሽ›› ማጉረምረምን እንዴት መሻገር እንዳለባቸው የቤት ሥራቸው መሆኑ አይቀርም፡፡

## ወንዙን የሚያሻግር ጥቂት ምክር

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ምንአ ልባት ድፍረቱ ካላቸው ከህወሓት እና ብአዴን ‹‹የስልጣን እገታ›› ወደ አርነት የሚመሩ የፖለቲካ መንገድ ማግኘት ላይቸገሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በዋናነት የአጋኞቹ ጉልበት በሰራዊቱ እና በደህንነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን አጢነው ‹‹የጠቅላይ ሚኒስቴር መንበራቸው››ን ስልታዊ ሆነው መጠቀም ከቻሉ ወንዙን ለመሻገር አይቸገሩም፡፡ በአናቱም አቶ መለስ ደህንነቱን እና ሰራዊቱን ሙሉ በሙሉ በግላቸው ከመቆጣጠራቸው በፊት (ከ1983ዓ.ም. -1993 ዓ.ም.) የ‹‹ጉልበተኛ ጓደኞቻቸውን አቅም›› ያፍረከረኩት መንግሥታዊ ስልጣናቸውን በመጠቀም በመሆኑ ከእሳቸው ስልት (ከመለስ አጠገብ ሆኜ ብዙ ተምሬአለሁ እንደሚሉት) ትምህርት ወስደው ከሆነ ለብልህነታቸው እና ለአርቆ አሳቢነታቸው አድናቆት አለኝ፡፡

እንዲሁም ሕገ-መንግሥቱን በሚገባ ለመተግበር ከቆረጡም በራሱ በህገ- መንግስቱ ጡንቻቸው ከተገዳዳሪዎቻቸው ሊበረታ የሚችልበትን ዕድል አያጡም፡፡ ይኸውም በህገ መንግሥቱ ‹‹የመከላከያ መርሆች›› በሚል በአንቀጽ 87፣ በቁጥር 1 ላይ፡-

**‹‹የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች የብሔረሰቦች እና የህዝቦችን ሚዛናዊ ተፅዕኖ ያካተተ ይሆናል››**

የሚለውን ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ እናም ይህ አንቀጽ ይከበር ዘንድ ሠራዊቱ የብሔር ተዋፅኦን እንዲጠበቅ ‹‹የመዋቅር ማስተካከያ›› ካደረጉ ከሕገ-መንግሥቱ ይልቅ ለፓርቲ ታማኝ በሆነው ሠራዊት ላይ ድንገት ደርሰው የሀይል ሚዛኑን ማመጣጠን አይከብዳቸውም፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የተጠቀሰው የህገ-መንግሥቱ አንቀፅም ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡

በእርግጥ ይህንን ማድረግ ‹‹ራስንም ማደን›› መሆኑ የሚገባን አቶ መለስ ህይወታቸው ካለፈ በኋላ እና ተተኪያቸው ከመመረጡ በፊት በእሽቅድምድም ለ34 ኮሎኔሎች የተሠጠውን የብርጋዴል ጄኔራልነት ማዕረግ ከህጋዊነቱ አንፃር ስናየው ነው፡፡ ምክንያቱም ህገ-መንግሥቱ የጄኔራል ማዕረግ በምን መልኩ ሊሰጥ እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡ ‹‹የፕሬዘዳንቱ ሥልጣንና ተግባር›› በሚለው ክፍል አንቀጽ 71 ቁጥር 6 ላይ እንዲህ ይላል፡-

**‹‹በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህግ በተወሰነው መሠረት ከፍተኛ የውትድርና ማዕረጎችን ይሰጣል››**

ኃይለማርያም ሊያነሱት የሚችሉት ጥያቄም ‹‹የ34ቱ ጄኔራሎች ሹመት በማን አቅራቢነት የተካሄደ ነው?›› የሚል ይሆናል፡፡ ሆኖም ጠቅላይ ሚንስትሩ የሚጠበቅባቸው ጥያቄ ማንሳት ብቻ ሳይሆን ከሹመቱ አንድምታ ተነስተው በሰራዊቱ ለመጠቀም የሚሞክረው ኃይል ምን ያህል ደፋር እንደሆነ መረዳትም ይኖርባቸዋል፡፡ (በነገራችን ላይ ይህን ሹመት በህወሓት እና በብአዴን መካከል ተከሰተ ከተባለው ከስልጣን ፉክክር ጋር የሚያያይዙት የፖለቲካ ተንታኞች አሉ)

ሌላው ኃይለማርያም ስልጣናቸውን ከዕገታ ነፃ ሊያወጡ የሚችሉበት አማራጭ ከፓርቲው ይልቅ (በይበልጥ) መንግሥታዊ ስርዓቱን በመጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት እጅግ ጠንካራ እና ሚሊተራይዝድ ሆኖ የተዋቀረ ነው፡፡ ይህን የሚያውቅ መሪ ደግሞ ከላይ እስከ ቀበሌ ድረስ ማዘዝ የሚቻልበትን ልማድ በሚገባ ይተገብራል፡፡ ይህን ዓይነቱን መንግሥታዊ መዋቅር የወረሱት አቶ መለስም በ1993ቱ ክፍፍል ወቅት ተገዳዳሪዎቻቸው በፓርቲ ህገ-ደንቦች አጥረው ሊያቆሟቸው ሲሞክሩ እርሳቸው ግን ይህን ተሻግረው መንግስታዊ መዋቅሩን በመጠቀም (ለስዬ ፍርድ ቤትን እንደተጠቀሙት) የሃይል ትንቅንቁን ተሻግረዋል፡፡ ኃይለማርያምም ይህን ሊያደርጉ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ እርግጥ ነው ይህን ማድረግ የሚችሉት ጥቂት ዓመታት ሀገሪቷን መምራት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

በእንዲህ አይነት ሁኔታ ወንዙን መሻገር ከቻሉ ደግሞ ገላጣው ሜዳ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ተጨማሪ የመለስን ስልትም ያገኛሉ፡፡ መለስ ከዚህ በፊት የውስጣዊ ኃይል መደላደላቸውን ከፓርቲ ፓርቲ ሲቀያይሩ ሚሊተሪውን እና ደህንነቱንም እንዲሁ እያፈራረቁ የተጠቀሙበትን ማለቴ ነው፡፡

በአናቱም ሊጫኗቸው የሚሞክሩትንም እንዲሁ መለስ እንዳደረጉት ‹‹ግራ-ዘመም ጠባብ ብሄርተኞች ናቸው›› የምትል ካርድ ለምዕራባውያኑ ማሳየት ይችላሉ (ምዕራባውያኑ ኃይለማርያምን Pragmatic፣ ነባሮቹን ደግሞ ማቻቻል የማያውቁ ከሚሉት አንፃር)

እንግዲህ መጪዎቹ ጊዜያቶች ለኃይለማርያምም ሆነ ለነባር ታጋዮቹ ፈታኝ ይሆናሉ ብሎ መገምት አያስቸግርም፡፡ ከምንም በላይ እንዲህ ዘግይቶም ቢሆን ኢህአዴግ የእኛን የዜጎቹን ድምፅ መስማት ቢጀምር እጅግ የተሻለ እንደሆነም ማስታወስ ያሻል፡፡

*…የሃይማኖት ጉዳይም ቢሆን በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሀገሪቱ ስልጣን ለዘመናት ከ‹‹ኦርቶዶክሳዊ›› መለዮ ብዙ የራቀ አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በኃይማኖት ጉዳይ ‹‹ፀለምተኛ›› የሚባሉት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንኳ ከሶስት አጋጣሚዎች በላይ በአደባባይ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ፓትርያርክ ከነበሩት አቡነ ጳውሎስ እጅ መስቀል መሳለማቸው የራሱ የሆነ ፖለቲካዊ አንድምታ አለው…*

## የኢህአዴግ....

(ከገፅ 29 የዞረ)

ምክንያቶችን ማቅረብ እንችላለን። ሕወሓት በረሃ በነበረበት ወቅት የነበረው አቋም የአንድ በትግል ውስጥ ያለ ፓርቲ አቋም እና ባህሪ የነበረ ሲሆን አሁን ግን መንግሥት መሆኑ ፓርቲው ባህሪውን በሌላ አቅጣጫ ማየት ይገባው ነበር የሚለው አንደኛው ነጥብ ነው። የትጥቅ ትግል አራማጅ ፓርቲ ባህሪን ወደ መንግሥት አገዛዝ ባህሪ በቀጥታ መቅዳት የለውጥ እንቅስቃሴውን ዘገምተኛ ያደርገዋል። የፖለቲካ ባህል እንደነባራዊ ሁኔታው መለያየት ይጠበቅብታል።

ሁለተኛው መከራከሪያ ሕወሓት በበረሃ እና ሕወሓት እንደ መንግሥት የተለያየ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ሕወሓት በበረሃ በቆየባቸው ወቅቶች ያዳበራቸው ልዩ ባህሪያቱና የሚያስተላልፋቸው የተለያዩ ውሳኔዎች ከፋም ለማም የሚመለከተው የአንድ ፓርቲ አመራርና የፓርቲው አባላትን ብቻ ነው የሚሆነው። አሁን ግን ሕወሓት ሌላ ነው። አንድም መንግሥት ሆኗል በሌላ በኩልም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ግንባር ፈጥሮ እያስተዳደረ ይገኛል።

የሚወስናቸውም ውሳኔዎች ሁሉንም የአገሪቷን ህዝቦች የሚመለከት ነው። በዚህ ምክንያት እንደቀድሞው የፓርቲው ውሳኔ ብቻ የሚባል ነገር አይኖርም ማለት ነው።

አቶ በረከት **‹‹ከበረሃ ጀምሮ ያዳበርነው ባህል ነው››** ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? የሌሎቹ ግንባር ፓርቲዎች ድምፅና ባህልስ ምን መልክ ነበረው? አለው? የሚለውንም እንዲሁ አስተሳስሮ ማየት ይገባል። አልያም አሁንም የሕወሓት ባህል በመንግሥት ደረጃ ያለውን ቀጥተኛ ጫና እንድናስተውል እንገደዳለን።

በወቅቱ በሕወሓት አመራር መካከል የነበረውን መከፋፈል አባላቱ ሰሙ ጊዜ ፓርቲው ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ለመግባት ተገዷል። በጊዜው በሕወሓት አመራር ዘንድ የነበረው ልዩነት እስከመተናኮልም መድረሱ፤ ልባቸውም፣ አስተሳሰባቸውም፣ አካሄዳቸውም አንድ ነው ብሎ ለሚያምን አባል አዲስ ነገር ነበር። የመደበቅ ባህል በሕወሓት አመራር ዘንድ ቀድሞ የነበረ ሁኔታ መሆኑን ከዚህ መረዳት እንችላለን።

ሕወሓት ቀድሞ የነበረው የግልፅነት ባህል በአንድ ወገን ደካማ መስሎ ቢታይም በወቅቱ ችግሮችን ለማርገብ ይከተሏቸው የነበሩ ባህሎቻቸው ግን ጠንካራ ለመሆናቸው የሚካድ ሃቅ አይደለም። በጊዜው በአመራሩ መካከል ተፈጥሮ ለነበረው ልዩነት የተወሰደው የአመራር መተካካት የወደፊት አዲስ ርዕዮተ-ዓለም መስመር ሲነደፍ፣ ያለፈው አሰራር ችግሮቹ ተነቅዞ ወጥቶ በአዲስ አሰራር ሲቀየር፣ አንዳችም የተተኮሰ ጥይት አልነበረም። ከዚህ ይልቅ በሁለቱ የልዩነት መስመሮች አመራር መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ልዩነት የተፈታበት መስመር ለዚህ አመላካች ነው።

በአቶ ግደይ እና በአቶ መለስ መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ልዩነት ለመፍታት 1000 ሰው በተገኘበትና አቶ አርከበ በመሩት መድረክ አስራስምንት ሰዓታት የፈጀ ክርክር ተካሂዶ ነበር። የክርክሩም ውጤት በድምጽ ብልጫ እንዲወሰን በመደረጉ አቶ መለስ እንዲያሸንፉ አድርጓቸዋል።ጥያቄው በአመራሩ መካከል አሁን ያለውን የስልጣን ክፍተት ተከትሎ ችግሮች እንዳይፈጠሩ የቀድሞውን የሕወሓት ችግር አፈታት ባህል አሁንም ይተገብሩት ይሆን? የሚለው ሲሆን ሁኔታውን ወደፊት የምናየው ይሆናል።

### ማደናገሪያው-ቦናፓርቲዝም

ከ1969 ዓ.ም ተግዳሮት በኋላ ሕወሓት ለሁለተኛ ጊዜ አደጋ ውስጥ የገባው በ1993 ዓ.ም. ነበር። ይህኛው አደጋ ከመጀመሪያው ይልቅ ብዙ ትኩረትን ያገኘና በይዘቱም፣ በአይነቱም፣ በተወሰደውም እርምጃ የተለየ እንደነበር ብዙዎቹ ይስማማሉ። በሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል የተፈጠረው አለመግባባትን ተከትሎ የተወሰደው እርምጃ ከቀድሞ የበረሃ ተሞክሮ የተለየ ለመሆኑ አንዳንድ ማሳያዎችን እንመልከት።

በወቅቱ ሕወሓት ውስጥ የተፈጠረውን አለመግባባት እልባት ለመስጠት በተከታታይ አመራሩ ለአንድ ወር ያህል ዝግ ስብሰባ ለማድረግ ተገዶ ነበር። በዚህ ስብሰባ ወቅት ከኢህአዴግ የፖለቲካ ባህርይና አሰራር የተለየ፣ እርስ በርስ መሸዋወድና መፈራራት የነበረበት እንደነበር ይነገራል። ለዚህ ሶስት ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል።

የመጀመሪያው አካሄድ ችግሮቹን ለመፍታት በቀረቡ ፅሁፎች ዙሪያ እንዴት እንወያይበት የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተወሰደው እርምጃ ነው። በወቅቱ በፅሑፎቹ ላይ ድምፅ እየሰጠን እንለፍ የሚለው ውሳኔ አዲስ ነገር ነበር። ፅሁፎቹ ድምፅ እየተሰጠባቸው፣ ግምገማ እየተካሄደባቸው ሂስና ግለሂስ እየተደረገ ይቀጥል መባሉ ከሕወሓት ነባር ተሞክሮ አንፃር አዲስ አካሄድ ነበር። የከዚህ በፊት ተሞክሮን ስንመለከት የተለያዩ ሐሳቦችን አቅርቦ በመሟገት እና አሳዛኝ ሀሳብ ላይ ድምፅ ሰጥቶ ማለፍ የሚባል አካሄድ ይተገበር ነበር።

ሁለተኛው አዲስ ክስተት ስራ አስፈፃሚው አካል የተሰጠውን ኃላፊነት መሸከም ሲያቅተው ወደ ማዕከላዊ ኮሚቴ ኃላፊነቱን ይወረውር ነበር። ስራ አስፈፃሚው አጀንዳውን መሸከም አቅቶት ወደታች ካድሬው ድረስ ጉዳዩ እንዲወርድ ማድረጉ በድርጅቱ ታሪክ ሌላ ያልተለመደ ድርጊት ነበር።

ሦስተኛውና የመጨረሻ ማሳያ በውይይቱ ወቅት የተከሰተው ጉዳይ ነው።በወቅቱ ውይይቱ የመግባቢያ መሆኑ ቀርቶ የማደናገሪያ ታክቲክ መሆኑን ግልፅ ካደረጉት ጉዳዮች መካከል በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የቀረበው የፓርቲው መሰረታዊ ችግር የ‹‹ቦናፓርቲዝም›› ነው የሚለው መከራከሪያ አጀንዳ ነው። ይህ መጠሪያ በሕወሓት አመራር መካከል ተፈጥሮ የነበረውን መሰረታዊ ልተየነት ለመጠቆም የተሰነቀረ ቃል ነው። ቦናፓርቲዝም የሚለውን ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ካርል ማርክስ “The 18th Brumier” በሚለው ፅሁፉ ሲሆን በአጭሩ ሲተነተን ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት፣ ብልሹ አመራር፣ ሙስና፣ ራስን ወደ ገዥ መደብነት መለወጥ የሚሉ ፍቺዎችን ይዟል። ቃሉን እንዲህ በአጭሩ አፍታተው ከማቅረብ ይልቅ አቶ መለስ ስያሜውን ብቻ በጊዜው መጠቀማቸው ብዙዎቹን የሕወሓት አመራሮች ምንነቱን ለመረዳት ብቻ የአንድ ወር ጊዜን ያለምንም ፍሬ ኃሳብ በመነታረክ እንዲያሳልፉ አስገድዷቸዋል። ጠ/ሚኒስትር መለስ ስያሜውን ሳያቀርቡ ፅሁፋቸውን በቀላሉ አቅርበው መቋጨት ይችሉ እንደነበር በወቅቱ የነበሩ የፓርቲው አባላት በተለያየ ወቅት በሰጡት አስተያየት አስፍረዋል።

እነዚህ አካሄዶች የሕወሓትን ፖለቲካዊ ችግር አፈታት ዘዴ ወደ ሌላ ምዕራፍ ያሸጋገሩ ሁነቶች ሆነዋል። ቀድሞ በበረሃ ይዞት ከነበረው ባህል ፈፅሞ የተለየ እና አብረው የነበሩት ነባር ታጋዮችን ጭምር ከቡድኑ ገምሶ ያገለለ ታሪካዊ ምዕራፍ ለመሆን በቅቷል።

በጊዜው የተተገበረው አካሄድ ሕወሓት ቀድሞ በውይይት ችግሮቹን የመፍታት ባህሉን በበረሃ ትቶት ለመምጣቱ አንድ ማሳያ ነው። ምንም እንኳን ነባር ታጋዮቹን በግምገማ ሰበብ ቢያገላቸውም ሕወሓት በውስጡ የነበረውን ችግር ለመፍታት ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ እንደማይል እንድንረዳ ያስችለናል። እንደዚህ አይነት እርምጃዎች ፓርቲውን ይበልጥ እያጠነከሩት ሲመጡ እንጂ ህልውናውን ሲገዳደሩት አንመለከትም።


### የርዕዮተ-አለም ማስተካከያ

እነዚህን ከባባድ ተግዳሮቶች በድል የተወጣው የአሁኑ አመራር ሌላው ተገዳዳሪ ፈተና የነበረው በ1997 ዓ.ም. የምርጫ ውጤትን ተከትሎ የገጠመው ቀውስ ነው። በጊዜው ኢህአዴግ በተናጠል የወሰዳቸው እርምጃዎች በተለያዩ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት የማጣትና ዘላቂ ያለመሆን ችግር ለመቅረፍ ሲባል የስትራቴጂ ለውጥ ማድረግ እንዳለበት የተገነዘበበት ወቅት ነበር። አዲሱ የኢህአዴግ ችግር አፈታት ዘዴዎች በንድፈ-ኃሳብ የተደገፉና ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ የሚል ነበር። ለዚህም አብዮታዊ ዴሞክራሲን ዳግም እንዲከለስ የማድረግ ቀመር ተጀመረ ይላሉ አቶ ገብሩ አስራት በ2001 ዓ.ም ለውይይት ባቀረቡት ‹‹የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲና ችግሮቹ›› በሚለው ፅሁፋቸው። እንደ አቶ ገብሩ አስራት አገላለፅ ከሆነ ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲን በተመለከተ የተለያዩ ሰነዶችን ያዘጋጀ ቢሆንም በተለይ ‹‹ልማት ዴሞክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ›› (1999 ዓ.ም.)፤ ‹‹የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስትራቴጂ፣ ታክቲኮችና የአመራር ጥያቄ›› (ጥቅምት 1999ዓ.ም)፤ ‹‹የአፍሪካ ልማት ተስፋ ቢሱ ጉዞና አዲስ ጅማሬ፤ አገራዊ ለውጦች ቀጣይ ፈተናዎችና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መፍትሔዎች›› (ሰኔ 2000 ዓ.ም.) የሚሉት ዋነኞቹ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

ህወሓት በውስጡ በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ምክንያት አብቅቶለታል ሲባል ዳግም ያንሰራራል። ዳግም ሲነሳ ቀድሞ ከነበረው ጥንካሬ ይበልጥ በርትቶ እናገኘዋለን። ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታን ብቻ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ስለፓርቲው ቀጣይ እጣ ፈንታ ለመናገር አስቸጋሪ የሚያደርገውና ለትንተና የሚመች ባህሪ እንዳይኖረው የሚያደርገውም ይሄው ተሞክሮው ነው። ፓርቲው ዝግና ለመረጃ ቀዳዳ የሌለው ከመሆኑ አንፃር ከውጭ ያለውን ግርግርና ውዥንብር ብቻ ተመልክቶ የውስጡን እጣ ፈንታ ለመፈረጅ አስቸጋሪ ይሆናል። ይህን የሕወሓት ነባር ተሞክሮ ፓርቲው ወደ ኢህአዴግ ግንባር ሲቀየርም አሻራው በጉልህ መኖሩን ለማየት ችለናል።

ኢህአዴግ በስራ ብዛት የደከመውን እያሳረፈ፤ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አካሄዱ ያልተመቻቸውን አባላቱን እያገለለ፤ ያሉት ነባር ቀሪ አመራሮች እና አዳዲስ ተተኪዎችን በአዲስ መንፈስ ይበልጥ እያጠነከረ ሲዘልቅ የምንመለከተውም ለዚህ ነው። ኢህአዴግ በተለይ ሕወሓት ያካበተው የረጅም አመት የፖለቲካ ተሞክሮ፤ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ የማለፍ ልምድ ግንባሩን በቀላሉ የሚበረግግ እንዳይሆን አድርጐታል። በየጊዜው አዳዲስ የማስቀየሻ ስልቶችን እየቀየሰ መግዛቱን ይቀጥላል እንጂ በቀላሉ እጅ ይሰጣል ተብሎ በብዙዎች አይታመንም።

ኢህአዴግ በህዝቡ ዘንድ የገጠመውን የተሻለ የአስተዳደራዊ ፋይዳና ግብ ጥያቄ (ቴሎስ) እንዲሁም በውስጥ በተደጋጋሚ የተፈተነባቸው ቀውሶችን ያስቀየሰባቸው ስልቶች (ቦናፓርቲዝም) ይዘውት እስከዛሬ መጥቷል። ወደፊትስ?



# ለምን የደህንነት ስሜት አልሰማን አለ?

ዳንኤል ተፈራ

ባለፈው ዓመት ሐምሌ አጋማሽ ላይ ነው፡ ፡ ዕለቱ ደግሞ ዓርብ። አራት ኪሎ የደረስኩት በጠዋቱ ነበር። የሚርከፈከፈው የሐምሌ ዝናብ የማለዳዋን ፀሐይ ሸሽጐ ማለዳ አስመሰለው እንጂ ሰዓቱ ለሦስት ጥቂት ቀረኝ እያለ ነበር። የአራት ኪሎ ድምቀቷ ጋዜጣዎቿ ናቸው። ጋዜጦች እንደመቀነት ይከቧታል። መረጃ ለመስጠትና የአንባቢያንን አምሮት ለማርካት አራት ኪሎ ሰስታ አታውቅም። ጉረቤቷ የሆነውና የፖለቲካ ሹሩባ የሚጐነጐንበት ቤተ-መንግሥት፣ ለዜጎቹ ለመስጠት የሚሰስተውን ዴሞክራሲ ወይም ንፉግነት አራት ኪሎ አልተጋባባትም። ከየአቅጣጫው የሚሰበሰበው አዲስ አበቤ ወደ አራት ኪሎ ጉራ በማለት ካሉት ጥቂት ጋዜጦች ሀገሩ እንደምን እንደሰነበተች ይበረብራል።

ዓርብ ዕለት ግን ገና በጠዋቱ ክው ብላለች። የዓርብ ማለዳ ድምቀቷ፤ አራት ኪሎን ‹‹ፍትሕ›› በሚለው ቀይ ቀለሟ የምታደምቀው ጋዜጣ አልወጣችም። ያው እንደተለመደው ‹‹የማተሚያ ቤት ችግር ይሆናል›› በሚል ግምት እየተፅናናሁ ወደ ጋዜጣ ደንበኛዬ ጉዞዬን ቀጠልኩ። ለወትሮው በፈገግታ የሚቀበለኝ ወጣት ጋዜጣ ሻጭ ላይ የለመድኩትን ፈገግታ በማጣቴ ደንገጥ አልኩኝ። ትካዜው ጤናማ አልነበረም። ቀዝቃዛ ሰላምታ ካቀረበልኝ በኋላ አንዳች አዲስ ነገር ለመስማት ጓጉቶ አይኖቼን እያቁለጨለጨ

‹‹ምን ጉድ ነው?! ያቺኑ አንዷን አይናችንን ሊያጠፏት ነው?›› አለኝ።

‹‹ምንድን ነው የምታወራው?›› አልኩት ጥርጣሬ እየጐነጠኝ።

‹‹ይኸው ፍትሕ ጋዜጣ ታገተች አይደል። ግቢው ቀውጢ ሆኗል እኮ። መንግሥት እንዳትሰራጭ ከልክሏል አሉ።›› በማለት ነገረኝ። ከምር ደነገጥኩኝ። በተስፋ ቢስነትና በሀገር አልባነት ስሜት ታጥሬ በድንዛዜ ቆምኩኝ። ደህንነት አልሰማኝ አለ። ከዚያ በኋላም የበርካታ ጋዜጣ አዟሪ ወጣቶች መተዳደሪያ እንደታገቀችና ሌሎች ብሶቶችን እንዳወራኝ ትዝ ይለኛል። በነፃነትና በዴሞክራሲያዊነት ፈንታ አምባገነንነትና ማን አለብኝነት በአራት ኪሎ ጉዳና እግር አውጥቶ ሲራመድ ታየኝ። ሁል ጊዜ ወደ ኋላ፣ ሁልጊዜ መሳቀቅ፣ ሁልጊዜ ነፃነት ማጣት… ምን አይነት ዕድለ ቢስነት ነው? ብቻዬን እያጉረመረምኩ እንደሆነ የታወቀኝ ቆይቶ ነው።

ሁልጊዜ የሚናፍቀኝ በሀገሬ ጉዳናዎች ላይ በርካታ ጋዜጦች ሲርመሰመሱ ማየት ነው። ነፃ ፕሬስ የሌላት ሀገርና መስታወት የሌላት ልጃገረድ እኩል ናቸው። ሁለቱም ጉድፋቸውን አያዩም፤ ሁለቱም ገፅታቸውን አያዩም። ስለዚህ ነፃ-ፕሬስ ለእድገትም ሆነ ለልማት ዋነኛ ሞተር ነው። ኢህአዴግ ነፃው ፕሬስ ላይ የመረረ ጥላቻ እንዳለው እረዳለሁ። የጥላቻውን ግዝፈት የሚገልፅልኝ ደግሞ ነፃ ጋዜጣ የምንላቸው ጋዜጦች ቁጥራቸው ስንት እንደሆነ ሳስብ ነው፤ ጋዜጠኞች ያለባቸውን መከራና ፍዳ ስመለከት ነው። ጥርስ የሚፋጭባቸው ጋዜጠኞች በሰቆቃ የሚኖሩት በእኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ይመስለኛል። በዚህ ቅልጥ ባለው የመረጃ ዘመን፤ መረጃ ውድ ዋጋ የሚያወጣ ሀብት በሆነበት በዚህ ጊዜ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመረጃ ጥማት ግብግብ እንዲል ለምን ይፈረድበታል?

ይሄ ብቻ አልነበረም። የፍትሕ ጋዜጣ በዕለቱ አለመውጣት አወዛጋቢውን የብርሃንና ሰላም ስታንዳርድ ውል እንዳስታውስ አድርጐኛል። መንግሥት የሆነው ፓርቲ የአንድ እጅ ጣቶቻችንን የማይሞሉ ጋዜጦችን አከርካሪያቸውን ለመስበርና በረጅም ገመድ አስሮ ለመቆጣጠር ባለው ምኞት የተነሳ በረጅም እጁ በማተሚያ ቤት በኩል እንደመጣ ለመገመት ብልጥ መሆን አይጠይቅም። እንጂማ ስለስታንዳርድ ውሉ መከራከር የሚገባቸው አሳታሚዎች ሳይሆኑ የሕገ-መንግሥት ጠባቂ የሆነው ገገርው ፓርቲ ነበር። ‹ነበር› ነው እንግዲህ። በነበር የቀረን ህዝቦች እንድንሆን ተፈርዶብናልና ‹ነበር› ነው የምንለው። የሕግ የበላይነት በሌለበት ሀገር ደግሞ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ወይም አንድ ፈላጭ ቆራጭ ፓርቲ ብድግ ብሎ እየታተመ ያለን ጋዜጣ ሊያግድ ይችላል። የቀረችን እስክርቢቷችን ነበረች እሷንም ሊነጥቁን ከበር ቆመዋል። ዋስትና ማጣት ይሏችኋል ይሄው ነው። መንግሥት የሚቋቋምበት ዋናው ምክንያት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ሕይወታችን ዋስትና ለማግኘት ነው። መንግሥታችሁ ራሱ ዋስትና ሲያሳጣችሁ ግን ምን ይባላል? ምንም እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

የዛሬው ርዕሴም መነሻው ይሄው ነው። ስለምን የደህንነት ስሜት አልሰማን አለ? የሚል። እስቲ አንድ ጊዜ ለአንድ ደቂቃ የምትሰሩትን ነገር አቁሙና ወደ ውስጣችሁ ተመልከቱ። ውስጣችሁ ሰላም ነው? ደህንነት ይሰማችኋል? ወይስ ድንግጥ፣ ድንግጥ፤ ብርግግ፣ ብርግግ፤ ሽብር፣ ሽብር ትላላችሁ? ብዙ ሰው ላይ የደህንነት ስሜት ባለማየቴ ነው ጥያቄ ያበዛሁት።

እኛ ኢትዮጵያ የምትባል ዕድሜ ጠገብ ሀገር ያለችን፤ የማያጠራጥር የኩሩነት ታሪክ ባለቤት የሆንን፤ በነፃነት ቀድመን የምንታወቅ ጨዋ ህዝቦች ደህና የሆንን ይመስለናል እንጂ ደህንነት የለንም፤ የደፈርን ይመስለናል እንጂ በጥልቅ ፍርሃት ውስጥ ተደንጉረናል፤ ተርበን ሳለ የጠገበ ሰው መስለን እንታያለን፤ መጠየቅ እየተገባን አፋችንን ከርክመናል፤ ገገርውን ፓርቲ እየፈራን የምንወደው ለመምሰል እንጣጣራለን፤ ሳንኖር እየኖርን ይመስለናል። በቃ የአሁኑ ሕይወታችን ገፅታ ይሄው ነው። የዘመናችን ሀቅም ብንጨምቀው ብንጨምቀው ከዚህ ፈቀቅ አይልም።

እዚች ላይ ከወራት በፊት በወጣችው ‹‹ዕንቁ›› መጽሔት ላይ ያገኘሁትን የመሐመድ ሰልማንን ፅሁፍ እጠቅሳለሁ። መሐመድ ‹‹ኖርዌይና ኑሮዬ›› በሚለው ማስታወሻው የኛን ኑሮ ከኖርዌያውያን ህይወት ጋር እያነፃፀረ ይተርክልናል። እጠቅሳለሁ፦ ‹‹ልማድ ሆኖብን ‹‹ደህና›› እንላለን እንጂ ‹‹ደህንነት›› አይሰማንም። ድህነት ነው የሚሰማን። ፍርሃት ሸብቦናል። የገዛ መንግሥታችንን እንፈራዋለን። ጉምሩክ የምትሰራ ፀሐፊን እንፈራታለን፤ ቀበሌ የመዝገብ ቤት ሰራተኛዋን እንፈራታለን፣ ‹‹ያምቡሌ›› ዘፈን በልቅጦጫትእየተፋብንየሚያመላልሰንንየሚኒባስ ሾፌር እንፈራዋለን፤ ትርፍ ተሳፋሪ ‹‹እሽኮኮ›› እንድንል የሚያስገድደንን ወያላ እንፈራዋለን፤ ደህንነታችንን ማስጠበቅ ስራው የሆነውን የፌዴራል ፖሊስ ተንቀጥቅጠን እንፈራዋለን፤ ፍትሕ ሊሰጥ ካባ የደረበውን ዳኛ እንፈራዋለን፤ በመጨረሻም በመልካም ፈቃዱ ለዚህ ሁሉ ፍርሃት የዳረገንን ፈጣሪ እንፈራዋለን።›› በማለት የሰፈረብንን፣ የተጣባንንና አብሮን እየኖረ ያለውን ብሔራዊ ፍርሃት ይነግረናል። መሐመድ ሰልማን የማይነግረን ይሄንን ፍርሃት ማን እንደፈጠረው ነው። ኢትዮጵያውያን በፍርሃት እየተጠራጠሩ እንዲኖሩ በጡንቻው በመተማመን የፈረደባቸው ማን እንደሆነ ነው። ቢሆንም መሐመድን አመስግነን እንቀጥል።

ለምን የደህንነት ስሜት አልሰማን አለ? ፈሪ የሚያደርገው የደህንነት ስሜት ማጣት ነው። ደህንነቱን ያጣ ህዝብ ደግሞ ፍርሃት በሚባል ስልቻ ውስጥ ራሱን ከትቶ አጮልቆ ይመለከታል። ‹‹ላለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል›› የሚለውን ተረት አሽቀንጥሮ በመጣል ‹‹ዝም አይነቅዝም›› እና ‹‹ዝምታ ወርቅ ነው›› በሚለው ይተካዋል።

የደህንነት ስሜት የማይሰማን ለዜጐቹ ደህንነትን ማረጋገጥ ስራው የሆነው ገገር ፓርቲ ደህንነታችንን ጠቅልሎ ስለወሰደው ነው። ነፃነታችንን የቀማንና በምትኩ ፍርሃት ያስታጠቀን መንግሥት የምንለው አካል ነው። መንግሥት የምንለውን አካል በዜጐች ላይ ጨካኝ እንዲሆን የሚያደርገው ስልጣን የሚባል አሳሳች ሰይጣን ነው። ስለዚህ መድሃኒቱ ስልጣን የተባለውን ሰይጣን ሕዝብ በተባለው ካህን ላይ መጣል ነው። ስልጣኑ ሕዝብ ላይ ከወደቀ ሰይጣኑ እንጦሮጦስ ይወርዳል። እኛም ሰላም እናገኛለን። ይሄን ማድረግ የሚችለው ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው።

ኢህአዴግ ለባለፉት 21 ዓመታት ስልጣን ላይ ቆይቷል። ለቀጣይ 40 ዓመታትም መቆየት እንደሚፈልግ የታገለለትን ዓላማ በዘነጋ መልኩ ነግሮናል። ህወሓት/ኢህአዴግ የደርግን ስርዓት ለመገርሰስ ሲታገል ያነገበው ዓላማ ስህተት ቢኖረውም ባይኖረውም ሙሉ ለሙሉ የማይጠቅም ነበር ማለት፤ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የታገሉና ሕይወትን የሚያክል ውድ ነገር የሰጡ ኢትዮጵያውያንን መካድ ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያውያን መንግሥታቸውን ባለመፍራት

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

## ቃሊቲን....

(ከገፅ 36 የዞረ)

### ከችሎቱ ውጭ

…ወቅቱ ክረምት ቢሆንም ሰማዩን የሞላችው ፀሐይ የከቸረች በመሆኗ ግለቷ ከክረምት ፀሀይ የከበደ ነው፡፡ ችሎቱ ዋስትና ከልክሎኝ በመጠናቀቁ በጥቂት ፖሊሶች ተከብቤ፣ በበርካታ የፍትህ አንባቢዎች ታጅቤ በፍርድ ቤቱ ግቢ ወደሚገኘው ‹‹አንበሳ ቤት›› አመራሁ፡፡ ይህን ጊዜም ድንገት ከከበቡኝ ሰዎች መሀል የማበረታቻ ድምፅ መሰማት ጀመረ፡፡ ቀስ በቀስም ድምፁ እየበረታ፣ ጭብጨባውም እየበዛ ሄደ፡፡ ባልተጠበቀ ሁኔታ እየተፈጠረ ባለው ነገር የተደናገጡት ፖሊሶች ህዝቡ ‹‹ዝም እንዲል›› እና እንዲመለስ በቁጣ አዘዙ፡፡ ነገር ግን በችሎቱ ‹‹ድራማ›› እልህ የተጋባው ህዝብ የፖሊሶቹን ማስፈራሪያ ችላ ብሎ ጭብጨባውን እና ፉጨቱን ሳያቆም ‹‹አንበሳ ቤት›› ደረስኩ፡፡ በተለምዶ ‹‹አንበሳ ቤት›› የሚባለው በፍርድ ቤቱ ግቢ የሚገኝ፣ ጣሪያው ላሜራ ሆኖ ዙሪያ ገባው በብረት ፍርግርግ የተዋቀረ ነው፡፡ የቤቱ አገልግሎት አብዛኛውን ጊዜ ፍርድ ቤት ቀርበው ዋስትና ለሚከለከሉ እና ሳይታሰሩ ሲከራከሩ ቆይተው የሚፈረድባቸው እስረኞች ቃሊቲ ማረሚያ ቤት እስኪላኩ ለሰአታት የሚቆዩበት ቤት ነው፡፡ ቤቱ አንዳንዴም ከወህኒ ቤት የመጡ እስረኞች ችሎት እስኪቀርቡ ለጥበቃ አመች ነው በሚል እሳቤ ለማቆያነት ያገለግላል፡፡ እናም ይህ ቤት ስያሜውን ያገኘው በአሰራሩ ስድስት ኪሎ አካባቢ ከሚገኘው ‹‹አንበሳ ግቢ›› ጋር ስለሚመሳሰል ይመስለኛል -አንበሳ ቤት፡፡

እኔም ከችሎቱ በቀጥታ ወደ አንበሳ ቤት እንድገባ ከተደረገ በኋላ ከአጀቡኝ ፖሊሶች አንዱ መዝጊያውን ከውጭ በኩል ቀረቀረውና በትልቅ ጓጉንቸር ቆለፈው፡፡ አሁንም ከፖሊሶቹ በላይ የተቆጡት የችሎቱ ታዳሚዎች ከውጭ በኩል የአንበሳ ቤቱን ከበው ማበረታታቸውን ቀጥለዋል፡፡ የፖሊሶቹ ‹‹ዞር በሉ›› ማስፈራሪያም እንዲሁ እንደቀጠለ ነው፡፡ በዚህ መሀል ድንገት በቦታው የነበሩ ጥቂት ጋዜጠኞች እረጅም ጊዜ እስር ቤት ሊቆይ ይችላል ብለው ስለሰጉ ነው መሰለኝ ‹‹የምትናገረው የመጨረሻ ንግግር ካለህ ተናገር›› አሉና መቅረፀ ድምፃቸውን ለስራ አዘጋጁ፡፡ ከህዝቡ መሀልም በርከት ያሉ ወጣቶች ሞባይላቸውን ደቅነው ጋዜጠኞቹን ተቀላቀሉ፡፡ ግራ ገባኝ፡፡ የምናገረውም ጠፋኝ፡፡ ውስጤን እልህ ተናንቆታል፡፡ የአንበሳ ቤቱን የከበቡት ጋዜጠኞች እና የፍትህ አንባቢዎች ደግሞ የምለውን ለመቅዳት እየወተወቱኝ ነው፡፡ ከጥቂት ማመንታት በኋላም እንዲህ አልኩ፡-

‹‹የዛሬው የችሎቱ ድራማ ከአምባገነኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ህልፈት በኋላ የመጀመሪያው ነው፡፡ እናም ድራማው አስቂኝም አሳዛኝም ነው፡፡ ግና! አንድ ነገር እርግጠኛ ሁኑ፤ ይኸውም የስርዓቱ ግብአተ-መሬት እየተቃረበ ለመሆኑ ከምልክቶቹ አንዱ ዛሬ ያያችሁት አይን ያወጣና ያፈጠጠ ዳኝነት መሆኑን፡፡››

…ከዚህ በኋላ ፊቴን አዙሬ በአንበሳ ቤት ውስጥ ከተደረደሩት ወንበሮች በአንዱ ላይ ጀርባዬን ከቤቱ ባሻገር ለተሰባሰቡት ሰዎች ሰጥቼ ተቀመጥኩ፡፡ ይህን ጊዜም እስከአሁን ድረስ ያላስተዋልኩት አንድ እስረኛ ከእኔው ጋር በዛች ቤት መሆኑን ተረዳሁ፡፡ እድሜው በግምት አርባዎቹ መጨረሻ ላይ ይሆናል፡፡ ቁመቱ እንደ ሸንበቆ የተመዘዘ ቢሆንም ኑሮ ደህና አድርጎ እንዳጎሳቆለው ያስታውቃል፡፡ ንትብ ያለ ውሃ ሰማያዊ ጃኬት እና አዳፋም ጥቁር ሱሪ ለብሷል፡፡ ጫማውም ቢሆን ብዙ ቦታ የተጣጠፈ፣ ቀለሙ ታይቶ የማይታወቅ አሮጌ እስኒከር ነው፡፡ ቀና ብዬ አየሁት፡፡ ፈገግ አለና የአንገት ሰላምታ ሰጠኝ፡፡ በርከት ያሉ ሰዎች አብረውኝ በመምጣታቸው ግራ የተጋባ ይመስላል፡፡ ፈጠን ብዬ ሰላምታውን ሞቅ ባለሁኔታ መለስኩለት፡፡ በሰላምታዬ ምላሽ ተበረታቶ ነው መሰለኝ ‹‹እነዚህ ሁሉ ጓደኞችህ ናቸው?›› የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡ ‹‹አዎን›› ስል መለስኩለት፡፡ ‹‹አይዞህ›› አለኝ፡፡ (ይች ‹‹አይዞህ›› ለእስረኛ እንዴት አይነት ስንቅ መሰለችህ?)

የሆነ ሆኖ እኔና የአንበሳ ቤት ጓደኛዬም እንደዋዛ ወደ ጭውውት ገባን፡፡

‹‹ምን አድርገህ ነው የመጣኸው?›› ፊቱን አጨልሞ ባለቤቱ ከስሳው እንደሆነ ነገረኝ፡፡

‹‹ለምን ከሰሰችህ?››

‹‹አንድ ልጅ ወልደን ተለያይተናል፡፡ እናም ልጁን ማሳደጊያ ገንዘብ አይረዳኝም ብላ ነው የከሰሰችኝ››

‹‹አንተ ለምን አትረዳትም?››

‹‹ስራ የለኝም ነበር፡፡ በቅርቡ ነው ስራ ያገኘሁት?››

‹‹ታዲያ ስራ ከጀመርክ ለምን አትረዳትም?››

‹‹ከደሞዜ ላይ ተቆራጭ ላደርግላት ተስማምቼ ነበር፡፡ እነሱ ግን እንድሰጣት የወሰኑብኝ ብር ከአቅሜ በላይ ነው፡፡››

‹‹ችሎት ቀርበህ ነበር እንዴ?››

‹‹አዎን፤ ቅድም ቀርቤ ለከሰዓት ተቀጠሬአለሁ››

‹‹ለምን?››

‹‹ዳኛው የወሰኑት በወር መቶ ብር እንድሰጣት ነው፡፡ እኔ ደግሞ ያንን መስጠት አልቻልኩም፡፡ እናም ፍርድ ቤቱ እንድታሰር ወስኗል፡፡›› (…እግዞ! መቶ ብር ያሌለው ሰው ወደእስር ቤት የሚላክበት ሁኔታ ከእዚህ አገር በቀር የት ይገኝ ይሆን? ኢትዮጵያ እጆቿን የምትዘረጋው ወዴት ይሆን? ወደአሜሪካ ወይስ አረብ ሀገር?)

‹‹እየሰራህ ከሆነ ለምንድነው መቶ ብር መስጠት ያቃተህ?››

‹‹አልገባህም! እኔ ስራ ከጀመርኩ ገና 18 ቀኔ ነው፡፡ እነሱ ደግሞ ዛሬውኑ ገንዘቡን መስጠት እንድጀምር ወጥረው ያዙኝ፡፡ ነገር ግን ደሞዝ እስክቀበል ታገሱኝ ብል ሊሰሙኝ አልቻሉም››

ይህን ጊዜ ትንሹ ወንድሜ በርገር እና የታሸገ ውሃ ይዞ ጠራኝ፡፡ የመጀመሪያውን የእስር ቤት ስንቅ እጄን በፍርግርጉ አሾልኬ ተቀበልኩ፡፡ ከመጀመሪያው እስረኛ ጓደኛዬ ጋርም ተካፍለን መመገብ ጀመርን፡፡ ተመግበን እንደጨረስንም የተለያዩ ወዳጆቼ እና የማላውቃቸው የፍትህ አንባቢዎች በፍርግርጉ በኩል እየመጡ ‹‹ሞራልና የስንብት ቃል›› መስጠታቸውን ስለጀመሩ ከእስረኛው ጓደኛዬ ጋር የጀመርኩትን ወግ መጨረስ አልቻልኩም፡፡

> …አንገቴን በመነቅነቅ አረጋገጥኩለት፡፡ ምን አድርጌ እንደሆነም ጠየቀኝ፡፡ ወዴት እየሄድኩ እንደሆነም ገብቶታል፡፡ ነገርኩት፡፡ ጥቂት እንደመከፋት አለና ጣቱን ወደ ሰማይ ቀስሮ ‹‹አይዞህ እግዚአብሔር አለ›› አለና አበረታታኝ…

በእንዲህ አይነት ሁኔታም በግምት ለሁለት ሰአት ተኩል ያህል ከቆየሁ በኋላ ፖሊሶቹ ጓጉንቸሩን ከፍተው ከአንበሳ ቤቱ እንድወጣ አድርገው ወደዋናው የፍርድ ቤቱ በር አካባቢ ከወሰዱኝ በኋላ ፊቷን ወደመውጫው በር አዙራ የቆመች አንዲት የደከመች የፖሊስ ነጭ ሚኒባስ ውስጥ ከተቱኝ፡፡ ይህን ጊዜም ለአንዴና ለመጨረሻ ስንብት በፍርድ ቤት የተሰበሰቡትን ቤተሰቦቼን፣ ጓደኞቼን፣ ባልደረቦቼን እና የፍትህ አንባቢዎችን በሚኒባሱ መስኮት እጄን አውጥቼ ሰላምታ ሰጠዋቸው፡፡

መኪናዋም መንቀሳቀስ ጀመረች፡፡ በሶስት ፖሊሶች ታጅቤም ከፍተኛውን ፍርድ ቤት ለቀቅን፡፡ ሆኖም ሚኒባሷ ከልደታ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብሎ፣ ከፍርድ ቤቱ ፊት ለፊት በሚገኘው አስፓልት ቁልቁል በመውረድ ሳር ቤት ከደረስን በኋላ በአቋራጭ ቃሊቲ የሚያደርሰንን መንገድ ከመያዝ ይልቅ ወደ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አመራች፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች ጉዞ በኋላ ፖሊስ ጣቢያው በር ላይ ደረስንና ከበር ላይ ቆምን፡፡ ጋቢና የተቀመጠው ልጅ እግር ፖሊስም ከመኪናው ወርዶ ወደ ጣቢያው ገባ፡፡ ይህን ጊዜም በር ላይ የቆሙ የጣቢያው ፖሊሶች ለጥበቃ ካጀቡኝ ፖሊሶች ጋር የወዳጅነት ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ በዚህ መሀል አንዱ ፖሊስ አንገቴ ላይ በጠመጠምኩት ‹‹ስከርፍ›› አማካኝነት ያወቀኝ መሰለ፡፡ ማንነቴን ማወቁንም በፊት ገፅታው እየነገረኝ ወደ ተቀመጥኩበት ወንበር ተጠግቶ ‹‹አውቅሀለሁ! ተመስገን አይደለህ?›› አለኝ፤ ጓደኞቹ እንዳይሰሙት ድምጹን ዝቅ አድርጎ፤ አንገቴን በመነቅነቅ አረጋገጥኩለት፡፡ ምን አድርጌ እንደሆነም ጠየቀኝ፡፡ ወዴት እየሄድኩ እንደሆነም ገብቶታል፡፡ ነገርኩት፡፡ ጥቂት እንደመከፋት አለና ጣቱን ወደ ሰማይ ቀስሮ ‹‹አይዞህ እግዚአብሔር አለ›› አለና አበረታታኝ፡፡ በዚህ መሀል ወደ ውስጥ የገባው ፖሊስ በሌሎች ሶስት ፖሊሶች የታጀቡ በግምት ዕድሜያቸው አስራ ስምንት ዓመት የማይሞላቸውን ሶስት እስረኞችን ከእኔ ጋር ስለቀላቀላቸው የአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ጉዳይ እንደተጠናቀቀ የገባው ጎልማሳው የሚኒባሱ ሾፌር ሞተሩን አስነሳ፡፡ ጉዞ ወደ ቃሊቲ ሆነ፡፡

ከፊት ለፊቴ ለተቀመጠው ፖሊስ ወንድሜ ልብስ ይዞ ክራውን ሆቴል አጠገብ ስለሚጠብቀኝ ስንደርስ እንድቀበለው መኪናውን በማቆም ይተባበሩኝ እንደሆነ ጠየኩት:: የጠየኩት ፖሊስ ከመመለሱ በፊት ጋቢና የተቀመጡት ሁለቱ ፖሊሶችና ሹፌሩ ምንም ችግር እንደሌለውና እንደሚተባበሩኝ ተደራርበው መለሱልኝ:: አመስግኜ ትኩረቴን ከመኪናው ውጪ አደረኩ:: በግምት ከሰላሳ ደቂቃ በኋላም ክራውን ሆቴል ደርሰን መኪናው በሩ ላይ ቆመ:: ወንድሞቼ ከእኛ ቀድመው በመድረስ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስና አንሶላ ይዘው እየጠበቁኝ ስለነበር ጊዜ ሳላጠፋ ተቀብዬአቸው ጉዞአችንን ቀጠልን፡፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላም ከሀገሪቱ በስፋት ተስተካካይ ወደሌለው አስቀያሚ እስር ቤት በር ላይ ደርሰን ሹፌሩ ደጋግሞ ጡሩንባ ያሰማ ጀመር:: የእስር ቤቱ ዋና በርም ከውስጥ ወደ ውጭ ወለል ብሎ ተከፈተና ሚኒባሷ ገባች:: ከፍርድ ቤት አጅበው ያመጡኝ ፖሊሶችም ለቃሊቲ ፖሊሶች አስረክበውኝ ሲያበቁ ርክክቡን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ተቀብለው ሞቅ ባለ ፈገግታ ተሰናበቱኝ::

**ይቀጥላል**

# የእነእስክንድር ነጋ ንብረት ሊወረስ ነው



በአሸባሪነት የተከሰሱት ታዋቂው የፖለቲካ ተንታኝና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የአንድነት ፓርቲ የአመራር አባል አንዱአለም አራጌ እና የአዲስ ድምፅ ራዲዮ ባለቤት አበበ በለው ንብረት በፌደራሌ ዐቃቢ ህግ ጥያቄ መሰረት በፍርድ ቤት ሊታገድ ችሏል።

ፍርድ ቤቱ ያገደው የእስክንድር ነጋን ሁለት መኖሪያ ቤትን እና በባለቤቱ በጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል ስም የተመዘገበ አንድ መኪና ሲሆን፣ የአንዱአለም አራጌ ደግሞ በባለቤቱ በዶ/ር ሰላም እሸቴ ስም የተመዘገበ አንድ መኪና እንደሆነ የእግዱ ደብዳቤ ገልጿል። እንዲሁም ነዋሪነቱን በአሜሪካን ሀገር የሆነው አበበ በላው በባለቤቱ በወ/ሮ ትግስት መኩሪያ ስም የተመዘገበ አንድ መኖሪያ ቤትን ነው።

እግዱን አስመልክቶ ጋዜጠኛ ሰረካለም ከአዲሰ ታየምስ ለቀረበላት ጥያቄ ስትመልሰ ‹‹ ባለቤት የታሰረው በልፈፀመው ወንጀል ነው፤ እኛ ኢትዮጵያውያኖች ብቻ ሳንሆን አለም እስክንድር ንፁህ ሰው እንደሆነ እየመሰከረ ነው፤ እናም ይህ አልበቃ ብሎ መተዳደሪያችን የሆነውን መኖሪያ ቤታችንን በግፍ ለመውሰድ ከፈለጉ አሁኑኑ መውሰድ ይችላሉ›› ስትል ገልፃለች።

ጋዜጠኛ ሰርካለም ንብረታቸው መታገዱን የሰማችው ከፍርድ ቤት ሳይሆን የሚያወቋት ሰዎች ስልክ ደውለው ነግርዋት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤ ‹‹እን እስክንድር ሲፈረድባቸው ንብረታቸውም ይውረስ የሚል የዐቃቢ ህግ ጥያቄ አልቀረበም ነበር፤ እናም ፋይሉ ከተዘጋ ከዚህን ያህል ወር በኋላ በምን አግባብና በየትኛው የሀገሪቱ ህግ መሰረት እንደሆነ በማይታወቅብት ሁኔታ የንብረት እግዱ መፈፀሙ የሀገሪቱን የፍትህ ስርዓት ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ነው›› ያለችው ጋዘጠኛ ሰርካለም ‹‹በቀጣይ ንብረቱን በሚመለከት እስክንድር ፍርድ ቤት ቀርቦ አይከራከርም። እኔም የሚስትነቴን ድርሻ ይሰጠኝ ብዬ አልከራከርም፤ ይህ የጋራ አቋማችን ነው። ምክንያቱም ከሳሾቻችን መጀመሪያ እኔም ሆንኩ እሷ ሀገራችን ላይ ሰርተን እንዳንኖር፣ በሙያችን እንዳንሰማራ ፍቃድ ከለኩን፤ አስከተሉና ደግሞ እሱን አሰሩት፤ አሁን ደግሞ እዛው ቃሊቲ የተወለደውን ላጃችንን የምናሳድግበት አኛም የምንተዳደርበትን ንበረት ለመንጠቅ ቆረጠው ከተነሱ ህጉም ሁሉም የነሱ ነውና የፈቀዱትን ያድርጉ። ወደፊት ታሪክና ህዝብ የራሳቸውን ፍርድ ይስጣሉ። ስለዚም እኛ ፍርድ ቤት እየተመላለስን ህገወጥ ድርጊታቸውን አናጅብም›› ስትል ለአዲስ ታየምስ ገልፃለች።

እስክንድር ከተወረሰበት ቤት አንዱ በቅርቡ በሞት ከተለዩት ወላጅ እናቱ በውርስ ያገኘውና ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ሲሆን በላፍቶ ክፍለ ከተማ የሚገኘው ደግሞ G+2 ቪላ ቤት እራሱ ያሰራውና አሁን አከራይቶት፣ ለራሱና ለቤተሰቡ ኮንድምንየም ቤት ተከራይቶ በተቀረው የኪራይ ገንዘብ ደግሞ እየተተዳደረበት እንደሚገኝ የአዲስ ታየምስ ምንጮች አረጋግጠዋል ።

የእነ እስክንድር ነጋ ንብረት ከመወረሱ ጥቂት ወራት በፊት የአበበ በለው መኖሪያ ቤት ፎቶ ግራፍ ጭምር በ‹‹ሰንደቅ ጋዜጣ›› ላይ ወጥቶ ይወረስ ዘንድ ቅስቀሳ ሲደረግበት እንደነበረ ይታወቃል። ገዥው ፓርቲ ሊፈፅም የሚፈልገውን ህግ-ወጥ ድርጊቶች አስቀድሞ በደጋፊዎቹ በሚዘጋጁ ጋዜጠች ላይ ቅስቀሳ ማድረጉ የተለመደ ስልቱ እንደሆነ ይታወሳል።



ፍርድ ቤቱ ያስተላለፈው የእግድ ውሳኔ ሙሉ ቃል ከዚህ በታች የተገለፀው ነው።

1ኛ ተከሳሽ አንዷለም አራጌ እና 7ኛ ተከሳሽ እስክንድር ነጋ በተከሰሱበት የሽብር ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ስለተቀጡ ከተከሰሱበትና ከተቀጡበት ወንጀል አንጻር በወ/ሕ/አ. 98/1-2 እና ጸረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 27 መሰረት እግድ እንዲሰጥ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በጠየቀው መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤት መስከረም 7 ቀን 2005 ዓ.ም. የንብረት እግዱን አስተላልፏል። ተመሳሳይ ጥያቄ በሌሉበት ጉዳያቸው የታየው 16ኛ ተከሳሽ አበበ በለው ንብረት ላይም ፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዙን አስተላልፏል።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስተላለፈው ትዕዛዝ፡-

- የከሣሽ ጥያቄ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ ከዚህ ፍርድ ቤት ተለዋጭ ትዕዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ የ1ኛ፣ የ7ኛ እና የ16ኛ ተከሳሾች ንብረቶች እንዳይሸጡ፣ እንዳይለወጡ እና በሌላ በማንኛውም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ ፍርድ ቤቱ አዟል።
- በፍርድ ቤቱ የታገዱ ንብረቶች በ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት በዶ/ር ሰላም እሸቴ ልየው ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የሰሌዳ ቁጥር 2-79095 አ.አ፣
- በ7ኛ ተከሳሽ ስም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቁጥር 158 የቤት አዲስ G+1 ቪላ መኖሪያ ሕንፃ በ150 ሜ.ካሬ ላይ ያረፈ በውርስ 7ኛ ተከሳሽ በእናታቸው ያገኙት በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/02 የቤት ቁጥር 1152 የሚገኝ ቤትና Atoz መኪና የሰሌዳ ቁጥር 2-ሕ08911 በ7ኛ ተከሳሽ በባለቤት በወ/ሮ ሰርካለም ፋሲል ስም የተመዘገበ መኪና እንዲታገድ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ አስተላልፏል።
- 16ኛ ተከሳሽ በባለቤታቸው በወ/ሮ ትዕግስት መኩሪያ ስም የተመዘገበ በአ.አ. የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 20/21 G+1 ቪላ B1 No.72 የሚገኝ ቤት ላይ ተመሳሳይ እግድ ተላልፏል።
- ፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዙ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲተላለፍ አዟል።

የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ፍርድ ቤቱ ያስተላለፈውን የንብረት እግድ ትዕዛዝ ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል ለሀገርና ሕዝብ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ ህጉ በሚያዘው መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ገልጸዋል።

ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾች ንብረት ላይ በቂ ጥናት በማድረግ ለፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ እንዳቀረበና የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ እንደሚያስፈጽም ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል።



ተመስገን ደሳለኝ

# “ቃሊቲ”ን በጨረፍታ

## ክፍል-፩

ተወዳጁ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ‹‹የቃሊቲው መንግስት›› በሚል ርዕስ በፃፈው መፅሐፍ እስረኞች በቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሚኖራቸውን የህይወት ገፅታ ጨርፎ አሳይቶናል፡፡ ጋዜጠኛ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን ደግሞ ‹‹የቃሊቲ ሚስጥሮች›› በተሰኘው መጽሐፉ የቅንጅት አመራሮች በቃሊቲ እስር ቤት በታሰሩ ወቅት እርስ በእርስ ‹‹ምን እየተባባሉ›› እንደሚጎናነጡ እንዲሁ ጨርፎልናል፡፡ መቼም የቃሊቲ ‹‹ጉድ›› በእነዚህ ሁለት መጽሐፍ ብቻ የሚገደብ እንዳልሆነ ለደቂቃም ቢሆን ግቢውን የረገጠ ይገባዋል፡፡ እናም በአርኪዮሎጂ ጥበብ ከተገኙ ጥንታዊ ከተሞች አንዱን የመሰለ ገፅታ በተላበሰው እስር ቤት ከየትኛውም ብሄርና የሀገሪቱ ድንበር ያልተወከለ የለም-በእስረኝነት ማለቴ ነው፡፡ አይንህ ኢትዮጵያዊ እስረኛ ማየት ቢደብረው የጃማይካ፣ የስዊዲን፣ የሲዊዘርላንድ፣ የአሜሪካ፣ የናይጄሪያ፣ የታንዛኒያ፣ የኬንያ፣ የሶማሊያ፣ የኤርትራ… ሰዎችን እንደልብህ ታየለህ፡፡ ሌላው በቃሊቲ በመኖርህ የምታገኘው ጥቅም ምን መሰለህ? ዘባተሎ የለበሰ ፈረንጅ እስረኛ ‹‹በብር ከስሙኒ›› ብቻ የሚሸጠውን የግቢውን ሻይ እንድትጋብዘው ይጠይቅሀል፤ ይኸን ጊዜም ኩራትህ ተራራ ያክላል፤ ቃሊቲ ባትታሰር ግን ይህን ዕድል አታገኝም፤ ምንአልባትም ይህንኑ ፈረንጅ አንተው ራስህ ደንበል ህንፃ ጋ ቆመህ ‹‹ሚስተር…›› እያልክ ገንዘብ ልትለምነው ትችል ነበር፡፡ ማን ያውቃል? እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የተለያየ ታሪክና ወንጀል ከቃሊቲ ህይወት ጋር የተጣቡ ናቸው፡፡

እመነኝ የቃሊቲ ታሪክ መቶና ሁለት መቶ መጽሐፍም ቅም የሚለው አይደለም፡፡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የፍትህ፣ የብልጠት፣ የስግብግብነት፣ የጭካኔ፣ የሀሰተኝነት… ምሽግ ነውና፡፡ በአጠቃላይ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ‹‹እግሩ የጣለው›› ወይም ‹‹ወንጀሉ የጣለው›› አሊያም አንደእኔ ‹‹አቃቤ-ሕግ የጣለው›› ፀሐፊ ሁሉ ተርኮ የማይጨርሰው አስገራሚ፣ አስደናቂ፣ አሳዛኝ፣ አማራሪ፣ አሸፋች…. ትርክት ያገኛል፡፡ እነሆም በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ለስድስት ቀን ያህል በዐቃቤ ሕግ በተጣልኩበት ጊዜ ያየሁት እና የሰማሁትን እነግርህ ዘንድ ወደድኩ፡፡

### በቅድሚያ-16ኛ ወንጀል ችሎት

‹‹ፍትህ ጋዜጣ››ን መስርቼ በዋና አዘጋጅነት መምራት ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በጋዜጣዋ ላይ በሚስተናገዱ ዘገባዎች እና ነፃ ሀሳቦች የተነሳ የሀገሬ መንግስት ‹‹ደመኛው›› አድርጎኛል፡፡ (አቤት! በገዛ መንግስት እንደክፉ ባለጋራ መታየት እንዴት ያሳቅቃል?) በዚህም የተነሳ ከጥቃቅን እስከ ግዙፍ ማስፈራሪያዎች (ጥቃቅን ሲባል የመንግስት አነስተኛ የስራ ፈጠራ ዘርፍ ብቻም እንዳይመስልህ፣ ለጋዜጠኞች ተብሎ የሚዘጋጅ ጥቃቅን ሽብሮች አሉና)፣ ወከባዎች፣ የስላይ ጫናዎች፣ ተደራራቢ ክሶች… የዕለት ቀለቤ ሆነዋል፡፡ … ከዕለታት በአንዱ ቀንም (ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ.ም) ከመአት ክሶቼ ሶስቱ ተመዘው በከፍተኛው ፍርድ ቤት 16ኛ ወንጀል ችሎት ለመቅረብ ተገደድኩ፡፡

በዕለቱ ፍርድ ቤት የተገኘሁት ከሁለት ጠበቆቼ ጋር ሶስት ሆነን ሲሆን፤ ከሳሾቼ ዐቃቤያን ህግም በተመሳሳይ ቁጥር ሶስት ሆነው ነው የተገኙት፡፡ ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢም ችሎቱ ተሰየመ፡፡ ዳኛውም ቦታቸውን ያዙ፡፡ አስቀድሞ ዐቃቤ ሕግ ላቀረበው ክስም መልስ እሰጥ ዘንድ ተጠየኩኝ፡፡ አንደኛው ጠበቃዬ ለቀረበው ‹‹ክስ›› መቃወሚያ ያሉትን ሀሳብ አቀረቡ፡፡ ዐቃቤያን ህጉም የጠበቃዬን መቃወሚያ እንደኦርኬስትራ ተቀባብለው አጣጣሉት፡፡ ዳኛውም ተደረቡ-የቀረበውን የክስ መቃወሚያም ውድቅ በማድረግ፡፡ አስከትለውም ዐቃቤያን ሕጉ ክሱን ያብራሩ ዘንድ ጠየቁ፡፡ ‹‹ሳተናዎቹ›› ዐቃቢያን ህግም ለሶስት እየተቀባበሉ ሶስቱን ክሶች ተገን አድርገው የሀሰት ወንጀል ደረደሩ፡፡ ድርዳሬውን ሲያበቁም በዳኛው የእምነት ክህደት ቃሌን ተጠየኩ፡፡ ክሱ ውሸት እንደሆነና ያጠፋሁትም ሆነ የጣስኩት ህግ እንደሌለ አስረዳሁ፡፡ ጠበቃዬም ቀጠሉና ከችሎት በዋስ ተለቅቄ የክስ ሂደቱን እከታተል ዘንድ ጠየቁ፡፡ ይህን ግዜም ዐቃቤያን ሕግ ተቃወሞአቸውን በእሩምታ አሰሙ፡፡ ‹‹የተቀውሞ ምክንያታችን›› ያሉትንም ሲያብራሩ ‹‹ተከሳሹ በዚሁ ጉዳይ ተከሶ ለፖሊስ ቃል ከሰጠ በኋላ አሁንም የአመፅ ቅስቀሳውን አላቋረጠም›› አሉና ሐምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም. ከ‹‹ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ›› ጋር ያደረኩትን ቃለ መጠይቅ እንደ ማስረጃ አቀረቡ፡፡ በጣም ደነገጥኩኝ፤ ምክንያቱም ዐቃቤያን ሕጉ የያዙት የክስ መዝገብ ራሱ ለፖሊስ ቃል የሰጠሁት ሐምሌ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. እንደሆነ በግልፅ ይናገራልና፡፡ ሆኖም ደፋሮቹ ዐቃቤያን ሕግ የሀሰት ክርክራቸውን ቀጠሉ፡፡ ሐምሌ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. ‹‹ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ›› ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም. የታገደውን የፍትህ ጋዜጣ ህትመት ‹‹በሲዲ ስላለኝ እለቀዋለሁ›› ብሎ ዝቷል አሉ፡፡ አሁን ዳኛው ማስረጃ የፈለጉ መሰሉ፡፡ እናም ‹‹ጋዜጣው የታለ?›› ሲሉ ጠየቁ፡፡ አንደኛው ዐቃቤ ሕግ ጋዜጣውን እንዳልያዙ ተናገሩ፡፡ ይህን ግዜም እርግጠኛ ሆንኩ፤ ዳኛው ‹‹ያለ ማስረጃ ውንጀላውን አንቀበልም›› እንደሚሉ፡፡ ግና! ምን ዋጋ አለው፤ ያለማስረጃ ክስ ቢቀርብም ለዳኛው ምንም ማለት አልነበረምና የችሎቱ ታዳሚ እስኪታዘብ ድረስ ዳኛውና ዐቃቢያን ህግ ‹‹ሰምና ወርቅ›› ሆነው መስራታቸውን አደሩት፡፡ በዚህ መሀል አንደኛው ዐቃቤ ሕግ ከስነ-ስርዓት ውጭ በሆነ መልኩ አዲስ ክስ አቀረበ፡፡ ‹‹ይህ ጉዳይ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ፍትህ ጋዜጣ ይታገድልን›› የሚል፡፡ አሁን በችሎቱ ከተገኙት ውስጥ አብዛኛው ትግስታቸው በማለቁ ከመገረም አልፈው ማጉረምረም ጀምሩ፡፡ እናም ዳኛው ‹‹ክስ በዚህ አይነት መልኩ እንደማይቀርብ›› ተናግረው ዐቃቤ ሕጉን ይገስፃሉ ብለው የጠበቁ ነበሩ፡፡ እሳቸው እቴ! ምንተዳቸው! ይልቁንም በመንበራቸው ተመቻቹና ከህገ-ደንብ ውጭ ድንገት የእኔ ጠበቆች መልስ እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ (እዚህ ጋር ከኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጋር በተያያዘ የተነገረ አንድ ቀልድ ትዝ አለኝ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- በድህረ ምርጫ 97 የቅንጅት አመራሮች ተከሰው ፍርድ ቤት ይቀርባሉ፡፡ ከተከሳሾቹም መካከል ከምስራቅ ጎጃም ተይዘው የመጡ ይገኙበታል፡፡ መንግስትም ለእኒህ ተከሳሾች ከዛው ከምስራቅ ጎጃም የሀሰት ምስክር አምጥቶ ስለነበር ምስክሩ መስክረው ሲጨርሱ ድንገት ከተከሳሾቹ መካከል ከመንደራቸው ወደአዲስ አበባ ከመጣ አስር ዓመት ያለፈውን አንድ ጋዜጠኛ ያያሉ፡፡ ጋዜጠኛው የተከሰሰው በሚሰራበት ጋዜጣ ላይ በፃፈው ጽሁፍ መሆኑን ያልተረዱት አርሶ አደሩ የዐቃቢ ህግ ምስክር ችሎቱን እንዲህ ሲሉ በትህትና ጠየቁ ‹‹ጌታው! ያያ ‹እከሌ› ልጅም እዚህ ስላለ መንግስት ሁለት ጊዜ የአበልና የትራንስፖርት ከሚያወጣ እሱም ላይ መስክሬበት ልሂድ?››)

ከመራራው ቀልድ እንፋታና ወደችሎቱ እንመለስ፡፡ ደህና! አዲስ ለቀረበው ክስም ጠበቆቼም መልስ ሰጡ፡፡ በዚህ መሀል እኔው ራሴ መናገር እንደምፈልግ ገልጬ እንዲፈቀድልኝ ጠየኩ፡፡ ለተከሰሰ ሁሉ የሚሰጥ መብት ነውና ተፈቀደልኝ፡፡ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ ቃለ መጠይቅ የሰጠሁት ለፖሊስ ቃል ከመስጠቴ አንድ ቀን በፊት እንደሆነ፣ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይም ዐቃቤ ሕጎች ‹‹ዝቷል›› ያሉት ውሸት እንደሆነና ጋዜጣው መጥቶ እንዲታይ፣ እንዲሁም ‹‹አንድ ጋዜጣ የሚታገደው ለብሔራዊ ደህንነት አስጊ ዘገባ መያዙ በማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ›› የፕሬስ ህጉ በግልፅ የደነገገ መሆኑን ጠቅሼ፤ መታተም ከአቆመ ከአንድ ወር በላይ የሆነ ጋዜጣ፣ ያውም ምን አይነት ዘገባ ይዞ ሊወጣ እንደሚችል ያልታወቀ ጋዜጣን አዘጋጁ ድንገት እዚህ ስለተገኘ ብቻ ይታገድልኝ ማለት ‹‹ህገ-ወጥነት›› እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ አስረዳሁ፡፡ በዚህ መሀል ዳኛው ተጨነቁ፡፡ ትንሽ አንሰላሰሉና ‹‹እየደበራቸው›› እንደሆነ በሚያስታውቅ መልኩ ‹‹የእገዳ ጥያቄውን›› ውድቅ አደረጉ፡፡ ነገር ግን የዋስትና ጥያቄዬን ከህግ ውጭ ‹‹በልዩ ሁኔታ ከልክለናል›› አሉ፡፡ (ያ ልዩ ሁኔታ ምን ይሆን? ምንስ ማለት ነው? …ብቻ በችሎቱ ከተገኙት ውስጥ የገባው አንድም ሰው ያለ አልመሰለኝም) ከዚህ በኋላ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሆኜ እንድከራከር ተወሰነ፡፡ ችሎቱም ለነሐሴ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. ተቀጥሮ ተበተነ፡፡ እነሆም በእንደዚህ ባለ ‹‹ሚስጥራዊ›› ሁኔታ በተካሄደ ችሎት ነበር ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ለስድስት ቀናት ያህል ያሳለፍኩት፡፡

ወደ ገፅ 34 ዞሯል

# ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝና ኢትዮጵያዊነት

ፕሮፌሰር ዳንኤል ክንዴ
በአራተኛው የኢትዮጵያና የኤርትራ ወዳጅነት ጉባኤ የቀረበ

ኢትዮጵያዊነት
ክቡር ሊቀመንበር፣
ክቡራትና ክቡራን፦

እንደምታውቁት ሁሉ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ነፃነትና ዕድገት አስተዋጽኦ ያደረጉ ብዙ የኤርትራ ተወላጆች ነበሩ፣ አሁንም አሉ። ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል ከፍተኛውን ቦታ ይዘው የሚገኙት ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝ ናቸው። ብላቴን ጌታ ማለት የንጉሥ ዋና ጉዳይ ፈጻሚ ማለት ነው።

እኚህ ሰውዬ የት ነበር የተወለዱት? ኤርትራ የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት በነበረችበት ወቅት እንዴት ብለው ነው ከአገራቸው ሊወጡ የቻሉት? በጊዜው ጀኔቫ በነበረው የዓለም መንግሥታት ማኅበር ውስጥ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር እንዴት ሊሆኑ ቻሉ? ከጦርነቱ በኋላስ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዴት ሊሆኑ ቻሉ? ለኢትዮጵያ ብዙ ሥራ ይሠራሉ ተብሎ ይታሰብ በነበረበት ወቅት እኚህ ታላቅ ሰው ገና በወጣትነት ዘመናቸው በተወለዱ በ46ኛው ዓመታቸው ስዊድን ላይ ሞቱ። ስለአሟሟታቸው ብዙ ነገር ይወራል፤ ዕውነቱ ግን የት ላይ ነው?

ላነሣኋቸውና ለሌሎችም ጥያቄዎች መልስ አገኛለሁ በማለት የተገኘውን ጽሑፍ ሁሉ አነበብኩ። ግን አጥጋቢ የሆነ መልስ ለማግኘት አልቻልኩም። ስለዚህ ለእርሳቸው ቀረቤታ የነበራቸውን አንዳንድ ሰዎች አነጋገርኩ። መጀመሪያ ያነጋገርኳቸው ልጃቸውን ወይዘሮ ፣ወይዘሪት ሎሬንዞን ነበር። ቀጥሎ በልጅ ሚካኤል ዕምሩ ዕርዳታ ባለቤታቸውን ወይዘሮ የምሥራች ዕምሩን አነጋገርኩ። ከዚያ በኋላ አሥመራ ሔጄ አብሮ አደግ ጓደኛቸውን ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድኅንን እና ወንድማቸውን አቶ መብራቱ ታዕዛዝን አነጋገርኩ። አሜሪካ አገር ደግሞ ለብዙ ዓመታት የሥራ ባልደረባቸው የነበሩትን የኢትዮጵያ መንግሥት የሕግ አማካሪ ሆነው 40 ዓመት ሙሉ የሠሩትን ጆን ስፔንሰርን (John Spencer) ኒው ሄቨን፣ ኮኔክቲከት ድረስ በቀጠሮ ሔጄ ላቀረብኩላቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢ የሆነ መረጃ ለማግኘት ቻልኩ።

ክቡራትና ክቡራን፦

ሎሬንዞ ታዕዛዝ የተወለዱት (እ.አ.አ) ሐምሌ 1 ቀን 1900 ዓ. ም. በአዲቀይህ ከተማ ነበር ። ፊደል ያስቆጠሯቸው መምህር ደስታ የሚባሉ የየጁ ሰው ነበሩ። በኋላም ከረንና አሥመራ ትምህርታቸውን ቀጥለዋል። በሥራ የተሠማሩት ገና በወጣትነት ዘመናቸው ሲሆን ገዥው የኢጣሊያ አስተዳደር በፖለቲካ ክፍሉ ቀጥሮ ያሠራቸውነበር። ማታ ማታ እየተማርኩ ዕውቀቴን ላሻሽል ብለው ቢጠይቁ፣ አለቆቻቸው ሊፈቅዱላቸው አልፈለጉም ነበር።

ይባስ ብሎ ከእለታት አንድ ቀን የሥራ ባልደረቦቻቸው የነበሩ አንዳንድ ጣሊያኖች ሲኒማ አብረው እንዲያዩ ጋብዘዋቸው ኖሮ ከሲኒማ ቤቱ አዳራሽ ገብተው ገና ከመቀመጣቸው "እንዴት አንድ ጥቁር ከእኛ ጋር አብሮ ሲኒማ ይመለከታል?" በማለት ዘረኞቹ ጣሊያኖች ተቃውሟቸውን በጩኸትና በፉጨት ሲያሰሙ፣ ሎሬንዞ በበኩላቸው እራሳቸውን እንደምንም ብለው ተቆጣጥረው ከሲኒማ ቤቱ እንደወጡ ለአብሮ አደግ ጓደኛቸው ለኤፍሬም ተወልደ መድኅን የደረሰባቸውን ውርደት ካጫወቷቸው በኋላ፣ ከዚህ አገር ካልወጣን ምንም ተስፋ የለንም፣ እንደምንም ብለን ኢትዮጵያ መሔድ ብቻ ነው ያለብን በማለት ተስማሙ።

ከዚህ በኋላ ሎሬንዞ የሥራ ስንብት መጠየቅ ብቻ ሳይሆን አሰብ ለመሔድ እፈልጋለሁ ብለው ተሰናብተው ኤደን ሔደው አንድ የጨው ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥረው መሥራት ጀመሩ። ዓመተ ምሕረቱ 1924 (እ.አ.አ) ነበር። በዚሁ ዓመት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን በሥራ ምክንያት ኤደን መጡ። ሎሬንዞም እርሳቸውን ለማነጋገር ዕድል ስላገኙ አዲስ አበባ እንዲመጡ አልጋ ወራሹ ጋበዟቸው። ኤፍሬም ተወልደ መድኅን ጅቡቲ ሔደው እንዲጠብቋቸው ተነጋገሩና ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሁለቱም ጅቡቲ ተገናኝተው በባቡር አዲስ አበባ ሔዱ። በጊዜው በኤርትራ የኢትዮጵያ ቆንሱል በነበሩት በከንቲባ ነሲቡ ዘዓማኑኤል አማካኝነት ሁለቱም ከራስ ተፈሪ መኮንን ዘንድ ቀረቡና ትምህርት ቤት መግባት ነው የምንፈልገው ስላሏቸው ሁለቱም በመንግሥት ወጭ ትምህራታቸውን እንዲቀጥሉ ተደረገ።

በዚያን ወቅት በልዩ ልዩ ምክንያት ከኤርትራ ወጥተው 100,000 የሚሆኑ ኤርትራውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ ነበር።

ብዙዎች ተማሪዎች ለትምህርት ውጭ ሲላኩ ከእነዚህ መካከል ኤርትራውያንም ነበሩ። ለምሳሌ ያህል ዮሐንስ ረዳእግዚእ፣ ዳዊት ዕቁባእግዚእ (በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ምክትል ሚንስትር የነበሩ)፣ እያሱ መንገሻ (በኋላ ጀኔራል፣የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም)፣ ያዕቆብ ገብረልዑል (በኋላ ጀኔራል፣ የጦር ኀይሎች ምክትል ኢታማዦር ሹም)፣ ብላታ መሥፍን የበጋሸት (በኋላ አምባሳደር የሆኑ)፣ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን እና ሎሬንዞ ታዕዛዝ ይገኙበታል። ገብረመስቀል ሀብተማሪያም (በኋላ አምባሳደር፣ ሚኒስትር የሆኑ)፣ አምባየ ወልደማሪያም (ዶክተር፣ በኋላ ሚኒስትር የሆኑ) ወዘተ።

ኤፍሬም ተወልደ መድኅን ቤይሩት ሲላኩ ሎሬንዞ ደግሞ ፈረንሳይ አገር ሞንትፐሊየር (Montpellier) ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት እንዲማሩ ተላኩ። ሎሬንዞ ኢትዮጵያ ውስጥ ሳሉ ትግረኛን፣ አማረኛን፣ ጣሊያንኛን እና ዓረብኛን አጣርተው ያውቁ ነበር። አውሮፓ ሳሉ ደግሞ ፈረንሳይኛን እና እንግሊዘኛን በሚገባ ተምረው በስድስት ቋንቋዎች ለመሥራት የሚችሉ ሰው ነበሩ።

ከሰባት ዓመታት በኋላ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ፣ የኃላፊነት ሥራ እየተሰጣቸው በብዙ ቦታዎች ሠርተዋል። ለምሳሌ ያህል፣ በግመል እየተጓዙ የኢትዮጵያንና የእንግሊዝ ሶማሊላንድን ድንበር እንዲቀየስ አደረጉ። አንዳንድ ፍርድ ቤቶችን እንዲቋቋሙ አደረጉ። የንጉሡም ረዳትና ልዩ ጸሐፊም ሆነው ሠርተዋል። ኢጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ትፈጽም የነበረውን ከበባና የወንጀል ሥራ በተመለከተ ለዓለም ኅብረተሰብ ጽሑፍ እያዘጋጁ ያስተላልፉ ነበር። ጦርነቱም ሲጀመር ኰረም ድረስ ዘምተው ስለ ታመሙ አዲስ አበባ ተመልሰው ሃኪም ቤት ገብተው ነበር።

ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የምታደርገውን ወረራ፣ ጭፍጨፋና ከፍተኛ የወንጀል ሥራ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አሰማለሁ ብለው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አውሮፓ ሲሔዱ፣ እርሳቸውም አብረዋቸው ሔደው ዓለም በሙሉ ሲያደንቀው የኖረውን ትንቢት ያዘለ ንግግራቸውን የጻፉት ሎሬንዞ ታዕዛዝ ነበሩ። ከንግግራቸው ለመጥቀስ፦

"በኢትዮጵያ የተጫረው እሳት ዓለምን ያቃጥላል"

"ለሕዝቤ ምን ይገኔ ልሂድ"

"እግዚአብሔርና ታሪክ ፍርዳችሁን ሲያስታውሰው ይኖራል"

ቀ. ኃ. ሥ. ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ያደረጉትን ንግግር ከጨረሱ በኋላ ስደተኛ ሆነው እንግሊዝ አገር ነበር የተቀመጡት። የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግሉን ግን ሎሬንዞ ታዕዛዝ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር እንደ መሆናቸው ሁሉ ጀኔቫ ሆነው የሚመሩት እርሳቸው ነበሩ።

ጣልያኖች ከተሞችን ይቆጣጠሩ እንጂ ከከተማዎች ውጭ ያለው ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአርበኞች መሪነት ጣሊያንን ከአገሩ ለማስወጣት በመታገል ላይ ይገኛል ብለው ደጋግመው ያሰሙት የነበረው ንግግር ውጤት ነበረው። ምክንያቱም ለጣሊያን ኮሎኒያሊዝም ዕውቅና ሊሰጡ የፈለጉትን መንግሥታት እንዲቆጠቡ አድርጓቸዋል። ሶብየት ኅብረት፣ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ስዊድን፣ሜክሲኮ፣ ዩጉዝላቪያ፣ግሪክና ሌሎች አገሮች ኢትዮጵያ በኢጣሊያን ቁጥጥር ሥር ወድቃለች ብለው የዲፕሎማቲክ ዕውቅና አልሰጡም።

ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስትወር የተጠቀመችው በ800,000 ወታደሮች፣ 600 የጦር አውሮፕላኖች፣ 595 ታንኮች፣ 30,000 የመጓጓዣ መኪኖችና የመርዝ ጋዝ ጢስ በሕዝብና በአካባቢ ላይ በመነስነስ ነበር። ራሷን ከግፈኛ ፋሽስት ወረራ ለመከላከል ይረዳ ዘንድ ኢትዮጵያ 10,000,000 ፓውንድ ብድር በጊዜው ከነበረው የዓለም መንግሥታት ማኅበር ብትጠይቅ እንግሊዝና ፈረንሳይ ስለተቃወሟት ብድሩ ተነፈጋት። ስድስት አውሮፕላኖች እንኳን ልግዛ ብላ እንግሊዝን ብትጠይቅ ተከለከለች። የኢጣሊያን መንግስት ጦር በስዊዝ ካናል ኢትዮጵያን ለመውረር ሲያነቃንቅ ኢትዮጵያ ግን በካናሉ እንዳትጠቀም ተከለከለች። መሣሪያ እንዳታገኝ ማዕቀብ ተደረገባት። ከአዲስ አበባ-ጅቡቲ ድረስ ባለው የባቡር ሃዲድም እንኳ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ እንዳታስገባ የፈረንሳይ ተጽእኖ ነበረባት።

በ1938 ዓ ም. ቀ.ኃ. ሥ. ብላቴን ጌታ ሎሬንዞን እንግሊዝ አገር ድረስ እንዲመጡ አስጠርተው ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው የሕዝቡን ሁናቴ፣ የአርበኞችን ትግል፣ የጣሊያኖችን ድርጊት ሁሉ አጣርተው እንዲመጡ ብለው አገር ቤት ላኳቸው። ሎሬንዞም ጐንደር፣ ጐጃም፣ በከፊልም ሸዋ ገብተው ከአርበኞች ጋር መነጋገር ብቻ ሳይሆን፣ በመሪዎች በኩል አለመግባባት ባለባቸው ቦታዎች መግባባት እንዲሰፍን፣ የተጣሉትን በማስታረቅና ተስፋ የቆረጡትን ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ነፃ ትወጣለች እያሉ ተስፋ በመስጠትና የወሰዱትን መሣሪያ እያደሉ ትግሉ እንዲፋፋም አደረጉ። ለጣሊያኖች ሰለባ ውድቅ እንዳይሆኑ በመጠንቀቅ፣ አንዳንድ ጊዜ መነኩሴ፣ አንዳንድ ጊዜ ቄስ፣ አንዳንድ ጊዜ ድሃ ገበሬ፣ አንዳንድ ጊዜ የሴት ቀሚስ በመልበስ አገሩን አዳርሰው በሦስት ወር ውስጥ ሥራቸውን አከናውነው አውሮጳ ተመለሱ።

ቀ. ኃ. ሥ. የሎሬንዞን ሪፖርት ካዳመጡና ካነበቡ በኋላ፣ "አገሬ ተመልሼ ጦሩን ልምራ ብለው እንግሊዞችን ቢጠይቋቸው፣ ጊዜው አሁን አይደለም፣ አያመችም ብለው አንድ ዓመት ሙሉ ካስጠበቋቸው በኋላ በመጨረሻ የሕዝብ ድጋፍ ስለሌለዎት እርስዎን የምንረዳበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም ብለው አሰናበቷቸው። እዚህ ላይ ስለ አንዳንድ ሁኔታዎች ማብራራት ያስፈልጋል።

የቀ. ኃ. ሥ. ቀንደኛ ተቃዋሚ የነበሩ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት የሚባሉ ስመጡር አርበኛ ነበሩ። በርሳቸው እምነት "በትውልድና በባላባትነት ላይ የተመሠረተ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ የዘውድ መንግሥት ከኢትዮጵያ ተወግዶ በምትኩ የሕዝባዊ ሪፓብሊክ መንግሥት መቋቋም አለበት" የሚል አቋም የነበራቸው ነበሩ። በነገራችን ላይ በ1958ዓ.ም. እ.አ.አ. እነ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መንግሥት ለመገልበጥ ሙከራ ከማድረጋቸው ሁለት ዓመት ቀደም ሲል፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ፓርቲ በሚል ስም ድርጅት አቋቁመው ነበር። እነ ጄኔራል እያሱ መንገሻ፣ ጄኔራል አማን አንዶም፣ አምባሳደር እምሩ ዘለቀና ሌሎችም የፓርቲው አባል ነበሩ።(ይህን የሰማሁት ከአምባሳደር እምሩ ዘለቀ ነበር።)

በ1938 ዓ.ም. በደጃዝማች ታከለ ወልደሃዋሪያት ሊቀመንበርነት የአርበኞች መሪዎች ጎንደር ላይ ስብሰባ አድርገው "የዘውድን ሥርዓት ውድቅ አድርገን ኢትዮጵያን ሪፓብሊክ ለማድረግ ወስነናል" ብለው ጄኔቫ ለነበረው የዓለም መንግሥታት ማህበር ዋና ጽሕፈት ቤት ውሳኔያቸውን አሰታውቀው ነበር። የእንግሊዝ መንግሥት ይህንን ስለሚያውቅ ንጉሡን የሕዝብ ድጋፍ የለዎትም ያሏቸው በዚህ ምክንያት ነበር።

አሁንም ቀ.ኃ.ሥ. ሎሬንዞ ታእዛዝን አስጠርተው "እንደገና በሱዳን በኩል በስውር ኢትዮጵያ ገብተህ የሕዝብ ድጋፍ እንዳለን የሚያረጋግጥ ሠነድ ይዘህ እንድትመጣ"ብለው አዘዟቸው። እርሳቸውም የንጉሡን ጥያቄ ተቀብለው እንደገና ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። የጣሊያን የስለላ ድርጅትበጣም ይፈልጋቸው ስለነበር፣ ዜግነታቸውን፣ ስማቸውን፣ አለባበሳቸውን፣ ሥራቸውንና ሁኔታቸውን እየለዋወጡ በተወሰኑ ክፍለ ሃገራት እየተዘዋወሩ ከአርበኞች ጋር በመነጋገር የቀ.ኃ.ሥን መሪነት እንቀበላለን የሚል የ10,000 የአርበኞች መሪዎች ፊርማ የሰፈነበትን ሰነድ ይዘው ግብፅ ገብተው ካይሮ ላይ ለነበረው የBritish Middle East High Command አስረክበው እንግሊዝ አገር ተመልሰው ሄዱ። ጥራት ያለው ሥራ መሥራታቸውን በመገንዘብ ቀ.ኃ.ሥ. ብላቴን ጌታ ሎሬንዝን ክልብ አመስገኖአቸው።

ሰኔ 10, 1940 ዓ.ም.(እ.አ.አ.) ጣሊያን በእንግሊዝና ፈረንሣይ ላይ ጦርነት ስላወጀች ቀ.ኃ.ሥ. ነፃ አውጪ ወታደር እንዲያዘጋጁ ብለው እንግሊዞቹ አሌክሳንድሪያ ድረስ ጥር 1941 አምጥተዋቸው ወደ ሱዳን ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ ተደረገ። በዚህ አጋጣሚ ንጉሡ ከሁሉ አስቀድሞ የፈለጓቸው ኬኒያ የሚገኙትን 3,000 የሚሆኑ ኤርትራውያንን ነበር። እነኚህ ወታደሮች ወገኖቻችንን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንወጋም ብለው ከተመደቡበት የጣሊያን ጦር እራሳቸውን አግልለው ከራስ እምሩ ጦር ጋር ተቀላቅለው ጠላትን ይወጉ ነበር። ራስ እምሩ በጣሊያን ጦር ተከበው እጅህን ስጥ ሲባሉ፣ ኤርትራኖቹን ኬኒያ እስክትገቡ ድረስ እጠብቃለሁ ብለው ራስ እምሩ መክረዋቸው ስለነበር የእሳቸውን ምክር ተቀብለው ኬኒያ ገብተው የጦርነቱን ጊዜ ያሳልፉት እዚያነበር። ሎሬንዞ ታእዛዝ ክኒያ ሄደው የቀ.ኃ.ሥን የመልእክት ጥሪ ሲያሰሟቸው ሁሉም ጥሪውን ተቀብለው ሱዳን ሄደው ከነፃ አውጪው ጦር ጋር ተቀላቀሉ። እነአማን አንዶምም የነፃ አውጪው ጦር አባል የሆኑት በዚህ ወቅት ነበር።

ቀ.ኃ.ሥን አሁን ያስቸገራቸው ጦር ማቋቋሙ ሳይሆን ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባው በር መዘጋቱ ነበር። ቀናው መንገድ የካርቱም-ገዳሪፍ-መተማ መንገድ ሲሆን፣ በሪፓብሊክ የሚያምኑት አርበኞችና ለጠላት "አጋልጠውን" ሄዱ የሚሉት አርበኞች በአንድ ላይ ሆነው እንዲህ ያለ መሪ ሥልጣን እንዲይዝ በምንም በኩል አንደግፍም ብለው መንገዱን ዘጉባቸው። ሆኖም ጊዜው የተለወጠ እንድነበር አንዳንዶቹ የተገነዘቡ አይመስልም ። ስለሁኔታው የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረን ማብራራት ያስፈልጋል።

የዓድዋ ጦርነት ባለቀ በዓመቱ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛቶቻቸው አማካኝነት በመክበብ የኢትዮጵያን መግቢያና መውጫ በሮቿን በቁጥጥራቸው ሥር በ

ማድረግ አፈኗት፡፡ ቀጥሎም የዓድዋን ጦርነት ኢትዮጵያ በድ
ል አድራጊነት በተቀዳጀችበት በአሥረኛው ዓመት የተጠቀሱት
የአውሮጳ አገሮች ኢትዮጵያን ተከፋፍለው በቁጥጥራቸው ሥ
ር የሚያደርጉበትን ዕቅድ አውጥተው እንደ አውሮጳ አቆጣጠር
በ1906 ዓ.ም. በምስጢር ተፈራረሙ፡፡ ራስ ተፈሪ መኮንን ስለ
ዚህ የምስጢር ስምምነት ያውቁ ስለነበር እንደምንም ታግለው
በ1923 ዓ.ም. ኢትዮጵያን በነበረው የዓለም መንግሥታት ማኅ
በር አባል እንድትሆን አደረጉ፡፡ በእሳቸው አስተሳሰብ 52 አገሮ
ች አባል የነበሩበት ይህ የዓለም አቀፍ ድርጅት የኢትዮጵያን ነ
ጻነት በማስጠብቅ እረገድ አስተማማኝ የሆነ ድጋፍ ይሰጣል በ
ማለት ነበር ነበር፡፡

ጣሊያን ግን በኢትዮጵያ የደረሰባትን ሽንፈትና ውርደት ለ
መበቀል ወደኋላ አላለችም፡፡ ሙሶሊኒ በ1922 ዓ.ም.ሥልጣን ከ
ያዘበት ዓመት ጀምሮ ለጦርነት ይዘጋጅ ነበር፡፡ በ1935 ዓ.ም. በ
ሰሜንና በምሥራቅ በኩል ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ከፍቶ በመ
ርዝ ጭስና በከባድ መሣሪያ በመጠቀም ወረራውን ቀጠለ፡፡ ኢት
ዮጵያ ግን አባል በነበረችበት ዓለም አቀፍ ድርጅት በመተማመን
ለጦርነት ብዙም ዝግጅት አላደረገችም ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ ማይ
ጨው ላይ በተካሄደው ጦርነት በግልጽ ይታይ ነበር፡፡

በዚህም የተነሳ የወራሪውን ኀይል እንዴት ለመቋቋም እን
ደሚቻል የጦርነቱንም ይዘት በጠቅላላ ለመነጋገር በቀ.ኃ.ሥ. ሊ
ቀመንበርነት ሚኒስትሮች፣ የጦር አበጋዞች፣ ጄኔራሎች፣ የአገር
ሽማግሌዎች...ወዘተ ባሉበት ስብሰባ ተደርጎ ሰፋ ያለ የሃሳብ ል
ውውጥ ከተደረገ በኋላ ውይይቱ ሁለት አቅጣጫ ያዘ፦ (1) የመ
ንግሥቱ ማእከል ወደ ጎሬ ተዛውሮ ወረራውን በልዩ ልዩ መንገ
ድ እየታገሉ መቋቋም፣ (2) ጦሩና ሕዝቡ ውጊያውን ይቀጥል፣
ቀ.ኃ.ሥ. ግን ጄኔቫ ሄደው በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተውን ጦርነ
ት፣ ግፍና በደል፣ ጭፍጨፋና በህግ የተከለከለውን የመርዝ ጭ
ስ በመጠቀም ወራሪው ኀይል በአገር ላይ ያደረሰውን ጉዳት ሁሉ
ለዓለም መንግሥታት ማኅበር እንዲያሰሙ ተወሰነ፡፡

የአብዛኛው ምርጫ በንጉሡ መሄድ ስላተኮረ ቀ.ኃ.ሥ. ሚ
ያዝያ 2, 1936 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ወጥተው ሰኔ 30, 1936 ጄ
ኔቫ ላይ ንግግራቸውን አሰሙ፡፡ ድርጅቱ በወራሪዎች ላይ አቋ
ም ካልወሰደና ካልተቋቋማቸው በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው በደል
በሌሎቹም ላይ በቅርብ ጊዜ ይደርሳል ብለው የተናገሩት ትንቢ
ት ያዘ፡፡ የተቃወሟቸው አርበኞች ግን በዚህም አልረጉ፡፡ በኢት
ዮጵያ ታሪክ ውስጥ አገሩን አጋልጦ የሄደ መሪ አይተንም ሰም
ተንም አናውቅም አሉ፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ሠራዊታቸው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በታ
ጠቀ የእንግሊዝ ጦር ቢጨፈጨፍ እጄን ሰጥቼ ኢትዮጵያን አላ
ዋርድም ብለው ራሳቸውን ሰዉ፡፡ አፄ ዮሓንስ ጦሩን መርተው
ሄደው በጀግንነት ተዋግተው ሱዳኖችን ካሸነፉ በኋላ በአንድ ተባ
ራሪ ጥይት ተመትተው ከወደቁ በኋላ በወቅቱ ሕክምና ባለማግ
ኘታቸው በጦር ሜዳ ላይ ሞቱ፡፡ አፄ ምኒልክም ጣሊያንን ለመ
ቋቋም የዘመቱት ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ነበር፡፡ ስለዚ
ህ ንጉሡ የነበራቸው ምርጫ ወደ ጎጃም ተጉዘው ደብረ ማርቆ
ስ መግባት ሆነ፡፡ ስለሆነም መንገዱን በዘጋባቸው አርበኛ ላይ ቂ
ማቸውን በምንም መንገድ አልረሱም ነበር፡፡

ከኬኒያ ወደሱዳን መጥተው ከነፃ አውጪው ጦር ጋር የ
ተቀላቀሉት 3,000 አርበኞች ግዳጃቸውን ከፈፀሙ በኋላ በብርጌ
ድ በብርጌድ ተደራጅተው በሻለቃ አማን አንዶም አዛዥነት ጉር
ጉራ በኋላ አዘዞ እንዲሰፍሩ ተደረገ፡፡ ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ የው
ጪ ጉዳይ ምኒስትር ሆነው ሲሾሙ ከፍተኛ የሆኑ የአገር ችግ
ሮች ከፊታቸው ተደቅነው ነበር፡፡ እንግሊዞቹ ጣሊያኖችን ተክተ
ው ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት ለማድረግ የነበራቸው ዕቅድ፣ የመን
ግሥት መሥሪያ ቤቶችን ሁሉ በቁጥጥር ሥር ማድረግ፣ በደቡ
ብ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የዱር አራዊት በሂሊኮፕተር እያ
ስፈራሩ ወደ ኬኒያ እንዲገባ ማድረግ፣ ፋብሪካዎችን ነቃቅሎ መ
ውሰድ፤ ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎ ትግራይን ከኤርትራ ጋር ቀላቅ
ሎ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ማዋል፣ ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ገ
ንጥሎ ከሶማሊያ ጋር መቀላቀልና በእንግሊዝ ሥር መተዳደር፣
ይህ ሁሉ አልሠራ ካለ ኤርትራን ለሁለት ከፍሎ ቆላውን ክፍ
ል ከሱዳን ጋር መቀላቀልና በእንግሊዝ ሥር ማስተዳደር፡፡ ሎሬ
ንዞ ይህን ሁሉ የእንግሊዞች ተንኮልና ደባ ሊቋቋሙ የቻሉት እ
ስከተወሰነ ደረጃ ነበር፡፡ በኋላ ግን ቀ.ኃ.ሥ. በ1945 ዓ.ም. ከፕ
ሬዚዳንት ፍራንክሊን ሩዝቬልት ጋር በቀጠሮ አሌክሳንደሪያ ተገ
ናኝተው በእንግሊዞች በኩል ያለባቸውን ችግር አስረድተው ከጥ
ቂት ዓመታት በኋላ እንግሊዞቹን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ችለ
ዋል፡፡ ክቡራንና ክቡራት፤

በመጨረሻ ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር
ነቱን ሥራ ለብላታ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን አስረክበው ሞስ
ኮ ምኒስትር ሆነው ሄዱ፡፡ በ1946 ዓ. ም. ፓሪስ ላይ በተደረገ
ው የዓለም መንግሥታት የሰላም ጉባዔ የኢትዮጵያ መልዕክተ
ኛ በመሆን ከሞስኮ መጥተው በስብሰባው ውስጥ በመካፈል ከ
ፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገው ነበር፡፡ የጣሊያን መንግሥት ጠቅላ
ይ ምኒስትር የነበሩት ጋስፐሪ ወደ ስብሰባው ሲገቡ የኒዘርላንድ
ስ ወኪል በጭብጨባ ሊቀበላቸው ሲሞክር ሎሬንዞ በጣም ስለተ
በሳጩ በቀጥታ ሄደው "ድል የሆነ ጠላት ቅጣቱን ፈጽሞ ምህ
ረት እስኪቀበል ድረስ ሰላምታና ክብር አይገባውም ስለዚህ አር
ፈህ ተቀመጥ" አሉት፡፡

የጣሊያኑ ጠቅላይ ምኒስትር ላደረገውም ንግግር ኢትዮጵ
ያን ወክለው መልስ የሰጡት እርሳቸው ነበሩ፡፡ በጣሊያን ወረራ
ምክንያት በሕዝብ ላይ የተፈጸመውን ግፍና በደል፣ ግድያና ዕል
ቂት፣ ጥቃትናቃጠሎ በዝርዝር አስረድተው የውጭ ዕርዳታ ቢነ
ፈገውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላትን እንዴት አድርጎ ሊቋቋም እ
ንደቻለና ተገቢ የሆነ የጦር ካሣ ኢትዮጵያ ማግኘት አለባት ብለ
ው ስሜት የሚቀሰቅስ ንግግር አድረገው ወደ ምድብ ሥራቸው
ሲመለሱ በጉዞ ላይ እንዳሉ ታመው ስቶክሆልም ሆስፒታል ገብ
ተው በተወለዱ በ46 ዓመታቸው ሞቱ፡፡

ስለአማሟታቸው ብዙ ይባላል፡፡ ጆን ስፔንሰርን አጥብቀ
ጠይቄ ያገኘሁት መልስ ግን የሞቱት በintestinal Adhesion
ማለት የአንጀት መታጠፍ ነው አሉኝ፡፡ እንዴት በሽታው ያዛቸ
ው ብዬ ብጠይቃቸው ያንጊዜ የኢትዮጵያንና ሶማሊላንድን ወ
ሰን ለማካለል ብለው ብዙ ቀን በግመል ሲጓዙ የያዛቸው በሽ
ታ ነበር አሉኝ፡፡

በሥራቸው በኩል ከፍተኛ መሰናክል የሆኑባቸው ጸሐፊ
ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ የሚባሉ በወቅቱ ከፍተ
ኛ ባለሥልጣን የነበሩ፣ የጽሕፈት ምኒስቴርን፣ የአገር ግዛት ም
ኒስቴርንና የፍርድ ምኒስቴርን፣ አጣምረው የሚያዝዙ ሹም ነበ
ሩ፡፡ በሎሬንዞ ታዕዛዝ የትምህርት ደረጃና በተመሠከረላቸው የ
ሥራ ችሎታ በጣም ይቀኑ የነበሩ ቦታየን አንድ ቀን ይወስድብ
ኛል እያሉ የሚሰጉ ሰው ነበሩ፡፡ ሎሬንዞ ከመሞታቸው ከአሥር
ዓመት በፊት ስለ ወልደጊዮርጊስ ለኮሎኔል ዳዊት ገብሩ የሚከ
ተለውን ነግረዋቸው ነበር፡፡"ወልደ ጊዮርጊስ በአንደበቱና በተፈጥ
ሮ ዕውቀቱ ትልቅ ቦታ የሚደርስ ሰው ነው፣ ሆኖም የአዋቂነቱ
ን ያኽል ሰው ሲወድቅ ማየት ደስ ይለዋል፣ ይኸም ለአገር ታ
ላቅ ጉዳት ይፈጥራል ፡፡"

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ምሑራን በጣሊያን ጭፍጨፋ በጠፋ
በት ዘመን ለብዙ ዓመታት ሎሬንዞ ታዕዛዝ የኢትዮጵያ ዐይን፣
ጆሮና አደበት ሆነው አገልግለዋል፡፡ "በተለይ እንግሊዞች ከእርሳ
ቸው በስተቀር ሌላ ሰው አያነጋግሩም ነበር" አሉኝ ስፔንሰር ፡፡
እኝህ ታላቅ ሰው ከሞቱ 66 ዓመት ሆኗል፡፡ ሥራቸው ግን አ
ልሞተም፡፡ ለአዲሱ ትውልድ መመኪያ ናቸው፡፡ ማንም አገር ባ
ፈራችው ታላላቅ ሰዎች

ይቀሰቀሳል፣ ይደሰኩራል፣ ይገጥማል፣ ያዜማል፣ ይመካ
ል፣ ይኮራል፡፡ እኛም አጥብቀን የምንኮራባቸው አገር ወዳድ ጀግ
ና ኢትዮጵያዊ ነበሩ፡፡ እኝህ ታላቅ ሰው ለኢትዮጵያ ሲሉ ለከፈ
ሉት መስዋእትነትና ለአደረጉት ትግል ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚ
ገባቸውን መታሰቢያ አላገኙም፡፡

ስለዚህ ሌላ ቢቀር መንገዶችን፣ የጥናትና የምርምር ማዕከ
ሎችን፣ ትምህርት ቤቶችንና ሃውልቶችን በእርሳቸው ስም እን
ድናቋቁም የታሪክ አደራ እንዳለብን በትህትና አሳስባለሁ፡፡

## ክቡራትናክቡራን፤

ድርጅታችን አዲስ አበባና አስመራ ቢሮዎች መክፈት ይ
ኖርበታል፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን በብዛት
በሚገኙባቸው የአሜሪካ፣ የካናዳ፣ የአውስትራሊያ፣ የአውሮፓ
ና የአፍሪቃ ከተማዎች ተመሳሳይ ቅርንጫፎችን ማቋቋም አለ
ብን፡፡ የሁለቱ

አገሮች ሕዝባዊ ድርጅቶች ለምሳሌ ያህል የወጣቶችና የሴ
ቶች ማኅበራት በሚያደርጓቸው የጋራ ስብሰባዎች ምሁሮቻችን
እየተገኙ ጠቃሚ በሆኑ አርዕስቶች ላይ ትምህርታዊ ገለፃዎችን
እንዲያደርጉልን ያስፈልጋል፡፡ በወገኖቻችን ላይ በየጊዜው በልዩ
ልዩ አገሮች በሚደርሰው በደል ድምፃችንን በጋራ ብናሰማ የብ
ላቴንጌታ ሎሬንዞን የሕይወት ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት ወ
ሰድነው ማለት ነበር፡፡

በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# "ት
# አትና

‹‹በዚያም ወራት ሕዝቅያ
ታመመ፡፡ ነቢዩም የአሞጽ ል
ሱ መጥቶ፦ እግዚአብሔር እ
ታለህ እንጂ በሕይወት አትና
ተካክል አለው፡፡ ፊቱንም ወ
እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሐ
ፊትህ በእውነትና በፍፁም ል
የሚያሰኝህንም እንዳደረግሁ
ሃለሁ፡፡ ሕዝቅያስም እጅግ አ
ይያስም ወደ መካከለኛ ከተማ
የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ
መልሰህ የሕዝቤን አለቃ ሕዝ
ው፦ የአባትህ የዳዊት አምላክ
ዲህ ይላል፦ፀሎትህን ሰምቻለ
ይቻለሁ እነሆ እፈውስሃለሁ
ወደ እግዚአብሔር ቤት ትወ
ላይ አሥራ አምስት ዓመት
መጽሐፈ ነገስት ካልዕ

ሕዝብን ለማገልገል ሙ
ት በእግዚአብሔር ፍቃድ የ
ችን በዘመናቸው ጥፋትን አያ
ይበድሉም፣ ፍትሕን አያዛቡ
ውም፣ ጉዟቸው አልጋ በአ
ሰሉትን ብሎ በጥቅሉ መደም
የትኛውም አገር እንዲህ አይ
ም፣ ተሰምቶም አይታወቅም
ናቸው በሚባሉ የአለማችን አ
በአገዛዙ ላይ ህጸፆች አይጠፉ
ገር አገዛዝ ሥርዓት በሰው ል
ት እና ቁጥጥር እስከተያዘ ድ
ም፡፡ እንኳን ከሰው ልጅ ቀር
እንኳን ተነስቶ የለ እንዴ?፡፡

ሰው በባህሪው እንከን የ
ፍጡር ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገ
ገኘቱ ሳይሆን ከስህተት ለመ
ንገድ ለመታረም፣ ለወደፊት
ት አንጉል አካሄድ ለመታረም
እና ተነሳሽነት ነው፡፡ የሰው
ሚለካው ለመታረም በሚያደ
ው፡፡ ከጥፋቱ የማይመለስ አ
ረት የማያደርግ ሰው ዳግም
በደልን ከቀደመው ጊዜ ይበል
ጨረሻውም ያማረ አይሆንም

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ
ግለሰቦችን ታሪክ ጠቅሰን ማ
ዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና በኋ
ራቀው የቀደመው ደቀመዝሙ
ዳን፡፡ ሁለቱም ጌታ ለቁርጥ
ደቀ መዛሙርት መካከል የነ
የህይወት መንገድና አስተም
የበላውን በልተው የጠጣውን
እያደሩ አለምን ከጥፋት ለማ
ርጥ አገልጋዮች ነበሩ፡፡ በኢጋ
ንዱ ቀን ሁለቱም በተለያየ
መንገድ ወጥተው ሳቱ፡፡ ሁለ